ሐመር

ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ


ሐመር ፲፪ኛ ዓመት ቁጥር ፫ ነሐሴ /መስከረም ፲፱፻፺፯ ዓ.ም.

# እንኳን ለብርሃነ መስቀሉ በሰላም አደረሳችሁ!



የመስቀል ደመራ በዓል አከባበር - በሽቱትጋርት (ጀርመን)

## ቋሚ ደንበኛ ይሁኑ




### ለኦሮምኛ ቋንቋ ተናጋሪዎችና አንባቢያን

በብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ካልዕ የተዘጋጀው ለካህናት፣ ለሰባክያነ ወንጌል፣ ለምእመናንና ለወጣቱ ትውልድ በማስተማሪያነት ሲያገለግል የቆየው ***«የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ»*** የሚለው መጽሐፍ ወደ ኦሮምኛ ቋንቋ ተተርጉሞ በገበያ ላይ ዋለ!

*ተርጓሚ፡- ዲያቆን ድጋፌ ዳኛቸው*

*መጽሐፉን፡-*

- በሁሉም የሐመርና ስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ ማከፋፈያዎች /ማኅበረ ቅዱሳን/
- በቅዱስ ራጉኤል ቤተ ክርስቲያን መጻሕፍት መሸጫ ሱቆች /መርካቶ/
- በአርያም መንፈሳዊ መዝሙር ቤት /አውቶቡስ ተራ/
- በዋሸራ መጻሕፍት መሸጫ መደብር /አዲስ ከተማ ት/ቤት ፊት ለፊት/ ያገኙታል።

ለበለጠ መረጃ ስልክ 09 812242 ወይም 556328 ይደውሉ

ውድ አንባብያን፡ ይህ የመጽሔታችን የ1996 ዓ.ም. የመጨረሻ እትም ለሥርጭት የደረሰው በመስከረም ወር 1997 ዓ.ም. በመሆኑ በሽፋኑ ላይ ነሐሴ/መስከረም 1997 ዓ.ም በሚል መውጣቱን በአክብሮት እንገልጻለን።

**የሐመር መጽሔትና የስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ ደንበኛ ይሁኑ**

| | ስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ | | ሐመር መጽሔት | |
|---|---|---|---|---|
| | የ6 እትም | 12 እትም | የ6 እትም | 12 እትም |
| ለአዲስ አበባ | 12.00 | 24.00 | 25.00 | 50.00 |
| ለክፍለ ሀገር | 12.00 | 24.00 | 25.00 | 50.00 |
| አፍሪካ | 9 ዶላር | 18 ዶላር | 12 ዶላር | 24 ዶላር |
| አውሮፓና መካከለኛው ምሥራቅ ምሥ | 12 ዶላር | 24 ዶላር | 15 ዶላር | 30 ዶላር |
| አሜሪካና ሩቅ ምሥራቅ | 15 ዶላር | 30 ዶላር | 18 ዶላር | 36 ዶላር |

ለባለው ታደለ እና/ወይም መስፍን ጥላሁን የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አራዳ ቅርንጫፍ
**Balew Tadelle** ***and /or*** **Mesfin Tilahun**
የባንክ ሒሳብ ቁጥር 68608 አዲስ አበባ ከፍለው
አድራሻዎንና የከፈሉበትን ደረሰኝ ኮፒ
በመልእክት ሣጥን ቁጥር 80078 ይላኩልን

www.eotcmk.org

ማኅበሩ የሚያስተምራቸው ግቢ ጉባኤያት ቁጥር ጥቂት ከነበረበት ጊዜ አንሥቶ ዛሬ 150 እስኪደርሱ ድረስ ተማሪዎቹን በልዩ ልዩ መንገዶች ሲያስተምር ቆይቷል:: በንዑሳን ማዕከላቱ አማካይነት መምህራንን በመጋበዝና በማስተባበር፣ በዋናው ማዕከል ያሉ መምህራንንና ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያንን በየጊዜው በማሠማራት፣ ትምህርታዊ ጽሑፎችን በማዘጋጀት፣ ግቢ ጉባኤያቱ በተወሰነ ደረጃ ራሳቸውን እንዲችሉ ለማድረግ ከመካከላቸው መርጦ ተተኪ መምህራንን በማሠልጠን፣ ልዩ ልዩ ትምህርታዊ ጽሑፎችን በማድረስ ሲያስተምር ቆይቷል::

## የማኅበሩ መልእክት

እግዚአብሔር ሙሴን ለይቶ÷ ወደ ተራራ አውጥቶ÷ ይኸንን ሁሉ ምሥጢር ያሳየውና የነገረው እንደ ቅዱሳን መላእክት ስሙን ለመቀደስ÷ ክብሩን ለመውረስ የተፈጠረ የሰው ልጅም ፍጹም በሆነ የመላእክት ሥርዓት እንዲያገለግለው ስለ ወደደና ስለ ፈቀደ ነው:: የሰው ልጅ ግን እንደ ቅዱሳን መላእክት ሥርዓት ሕግን ቢቀበልም በሕጉና በሥርዓቱ መሔድ እያቃተው ይቸገር ነበር:: ይህም ችግር ፈጽሞ ካለመቻል የመጣ ሳይሆን ከቸልተኝነትና ከስንፍና የመጣ ነበር::

## ከሰሞኑ በረከት

ይህንን ቆራጥነታቸውን ከአንደ በታቸው የተረዳው ፋሺስትም በሰጡት ቁርጠኛ መልስ ተናዶ እርሳቸውንና አብረዋቸው የተያዙትን ቀኝ አዝማች ይነሡንና ግራ አዝማች ተክለ ሃይማኖት ይባሉ የነበሩ አርበኞችን ለስምንት ቀናት ያህል ሌሊት በውርጭ ቀን በፀሐይ ሲያሰቃያቸው ሰነበተ:: በመጨረሻም ኅዳር 21 ቀን 1929 ዓ.ም. ከተያዙት ሁለት አርበኞች ጋር በጥይት ተደብድበው እንዲሞቱ ፍርድ አስተላለፈ:: ኅዳር 24 ቀን 1929 ዓ.ም. ፍርዱ ተግባራዊ ሆኖ ብፁዕነታቸው በሰማዕትነት ዐረፉ:: ነጻነቷ ተመልሶ ንጉሡ ከስደት የተመለሱ በኋላ በ1934 ዓ.ም መታሰቢያ ይሆናቸው ዘንድ በሰማዕትነት ባለፉበት ጎሬ ከተማ አንድ ት/ቤት እንዲቆም አደረጉላቸው::

## በተ ክርስቲያንህን ዕወቅ

ዋና አዘጋጅ - ዲ.መርሻ አለኸኝ
ም/ዋና አዘጋጅ- አሉላ ጥላሁን
ከፍተኛ ሪፖርተር -መ/ር ኃይለ ማርያም ላቀው
መ/ ሪፖርተር - ዲ.ፋሲል አስረስ
ኮምፒዩተር ዲዛይን - ወይንሸት ወጉ
ኮምፒዩተር ጸሐፊ - ፍቅርተ ኃይሌ
ስልክ 556328
ፖስታ 80078
አዲስ አበባ
E -mail:Hamer@EOTC-Mkidusan.org
Website: – www.EOTC-Mkidusan.org

«ማኅበረ ቅዱሳን»

እግዚአብሔር ያከበራቸው
የነቢያት፣የሐዋርያት፣የጻድቃን፣ የሰማዕታት
በአጠቃላይ የቅዱሳን ገድል፣ትሩፋትና አማላጅነት
የሚዘከርበት በመሆኑ

ሐመር
፲፪ኛ ዓመት ቁጥር ፫
ሐምሌ/ነሐሴ ፲፱፻፺፮ ዓ.ም.

# ይዘት

የማኅበሩ መልእክት
• «የአበው ትንቢት እንዲፈጸም... »..........................፪
ደብዳቤዎች .......................................................፬
ከሰሞኑ በረከት
• ከሥርዓቴ ፈቀቅ ብላችኋል......................................፮
ትምህርተ ሃይማኖት
• ምሥጢረ ሥጋዌ.................................................፲
• ትንሣኤ ሙታን ...................................................፲፪
የጥያቄዎቻችሁ መልስ
• «ቡዳ» ምንድን ነው? ............................................፲፬
እናስተዋውቃችሁ
• ደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤል......................................፲፮
• ቅድስት ማርያም ግብፃዊት ......................................፲፰
ኪነ ጥበብ
• ሰባኪ ሕይወት......................................................፳፩
ዓምደ ወሬዙት
• የአብነት ት/ቤት በግቢ ጉባኤያት...............................፳፪
ክርስትና በማኅበራዊ ኑሮ
• ፈተና የሚመጣው ከየት ነው?......................................፳፮
ቤተ ክርስቲያንህን ዕወቅ
• ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ምንድን ነው?.........................፳፱
• ዝክረ ቴዎፍሎስ ፣ ጴጥሮስ ወሚካኤል.............................፴፪
• «ግእዝ ፈጽሞ አይሞትም»........................................፴፬
ስቡጊዳ - የግእዝ ቋንቋ ትምህርት
• ተውሳከ ግሥ........................................................፴፰
ወቅታዊ ጉዳዮች
የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሰሜ
ንና ደቡብ አሜሪካ .................................................፴፱

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ በማኅበረ ቅዱሳን የኅትመት ዝግጅት ማስተባበርያ ክፍል የሚዘጋጅ ትምህርታዊ መጽሔት::

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዓተ እምነትና ክርስቲያናዊ ትውፊት ጠብቆ የሚወጣ::

ስለዚህም መሠረት በተቀረጸው ሥርዓተ ትምህርት መሠረት በማኅበሩ አማካይነት ተዘጋጅተው የታተሙት 20 የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ግቢ ጉባኤያት መማሪያ መጻሕፍት በቅርቡ ሊቃነ ጳጳሳት፣ በጠቅላይ ቤተ ክህነት የልዩ ልዩ መምሪያ ኃላፊዎችና ሌሎች የቤተ ክርስቲያናችን የበላይ ሐላፊዎች፣ ተጋባዥ እንግዶች እንዲሁም የማኅበሩ አባላት በተገኙበት ተመርቀዋል:: የተዘጋጀው ሥርዓተ ትምህርትም ሆነ መማሪያ መጻሕፍቱ ማኅበሩ ለከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ግቢ ጉባኤያት የሚሰጠውን ትምህርት አንድ ዓይነት የሚያደርጉ፣ ከዚህ በፊት በሚሰጧቸው ትምህርቶች ያልተካተቱ ክፍለ ትምህርቶን /ለምሳሌ የቤተ ክርስቲያን አስተዳደራዊ መዋቅር፣ የከፍተኛ መንፈሳዊ ት/ቤቶችና ኮሌጆች እንዲሁም የካህናት ማሠልጠኛዎች ታሪክና የትምህርት አሰጣጥ ይዘት ወዘተ/ የሚያካትቱ፣ የሚሰጡት ትምህርቶች ተማሪዎቹ ካላቸው ዕውቀትና ጊዜ ጋር የተመጣጠነ እንዲሆን የሚያደርጉ፣ ከጊዜያቸው ጋር ባለመጣጣማቸው. ምክንያት ማግኘት ያለባቸው ዕውቀት እንዳይቀርባቸው የሚያደርጉ፣ አላስፈላጊ ድግግሞሽን የሚያስቀሩ እንደሆኑ ይታመናል::

ማኅበሩ ባቀፋቸው ግቢ ጉባኤያት የሚማሩ ተማሪዎች በተዘጋጀው ሥርዓተ ትምህርት መሠረት በመማሪያ መጻሕፍቱ የቤተ ክርስቲያናቸውን ዕውቀት እንዲያገኙና ራሳቸውን ለአገልግሎት እንዲያዘጋጁ ማድረጉን ይቀጥላል:: ነገር ግን ጥረቱ ውጤታማ ይሆን ዘንድ ማኅበሩ የሁሉንም ርብርብ ይጠይቃል::

በመሆኑም በቀዳሚነት ማኅበሩ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎችን ለማስተማርና ለአገልግሎት ለማሠለፍ የያዘውን ዓላማ ተግባራዊ ከሚያደርጉ አስፈጻሚ አካላት /ንዑሳን ማዕከላት/ ብዙ ይጠበቃል:: ተማሪዎቹ በሥርዓተ ትምህርቱ መሠረት በመማሪያ መጻሕፍቱ ተምረው ነገ ለሚጠበቅባቸው ሰፊ አገልግሎት ራሳቸውን ከወዲሁ ለማዘጋጀት እንዲችሉ እያንዳንዱ ተማሪ መጻሕፍቱን እንዲያገኝ ጥረት ማድረግ ይኖርባቸዋል:: መጻሕፍቱን ካገኙ በኋላም የቀረቡላቸውን ዕውቀቶች የሚያዳብሩባቸውን ተያያዥ መጻሕፍት እንዲያነቡ፣ በአካባቢያቸው ከሚገኙ ለቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ጋር ተገናኝተውም ያገኙትን መጠነኛ ዕውቀት እንዲያስፋፉ በማድረግ፣ የሚያነሷቸውን ጥያቄዎችም በመመለስ ለማኅበሩ ዕቅድ ተግባራዊነት የሥርዓተ ትምህርቱም ሆነ የመጻሕፍቱ ዝግጅት በቃ÷ አለቀለት የሚባል ባለመሆኑ በዝግጅቶቹ ላይ የሚጐድሉ ካሉ ጥናት በማድረግ ለሚመለከተው አካል ማቅረብ፣ ወደ ፊት ማኅበሩ ለሚያከናውናቸው ሌሎች ተመሳሳይ ዝግጅቶች ተሳታፊ ለመሆን ከወዲሁ መዘጋጀት አለባቸው::

ለሥርዓተ ትምህርቱም ሆነ እሱን ተግባራዊ ለማድረግ የተዘጋጁት የመማሪያ መጻሕፍት ፍሬያማ ሆነው ቤተ ክርስቲያን ተጠቃሚ ትሆን ዘንድ የግቢ ጉባኤያት ተማሪዎች ቀላል የማይባል ድርሻ አላቸው:: የተዘጋጁላቸውን መማሪያ መጻሕፍት በሚችሉት መንገድ ሁሉ ተግተው በማግኘት አንብበው ቤተ ክርስቲያናቸውን እያወቁ ማገልገል ይኖርባቸዋል:: ማኅበሩ ከልምድ እንደ ሚያውቀው ያለምንም ረዳት የሚማሩ ተማሪዎች በየግቢው አሉና ዐቅሙ ያላቸው ምእመናን እንደነዚህ ዓይነቶቹን ተማሪዎች መማሪያ መጻሕፍቱን ያገኙ ዘንድ በገንዘብ ሊረዷቸው ያስፈልጋል:: እንደ መማሪያ መጻሕፍትነታቸው ዝግጅቶቹን የሚተነትኑላቸውና የሚተረጉሙላቸው ሰው ሊኖር ያስፈልጋልና ተማሪዎቹ በሚያዙላቸው የትምህርት መርሐ ግብራት ላይ በጥንቃቄ በመገኘት ትምህርቶቹን መከታተል አለባቸው:: ከቤተ ክርስቲያን ሰፊ ትምህርት አንጻር በመማሪያ መጻሕፍቱ የቀረቡላቸው ዕውቀቶችም በቂ ናቸው ስለማይባል ተጨማሪ መጻሕፍትን በማንበብ፣ ሊቃውንትንም በመጠየቅ ዕውቀቶቻቸውን ሊያስፋፉ ይገባል:: የተዘጋጁላቸው የመማሪያ መጻሕፍት በግቢ ቆይታቸው ብቻ እንዲያገለግሏቸው ባለመሆኑ በጥንቃቄ ይዘው በሥራ በሚሰማሩበት ጊዜም ሊጠቀሙባቸው ይገባል::

ማኅበሩ ምንም እንኳን የመማሪያ መጻሕፍቱንና ሥርዓተ ትምህርቱን አዘጋጅቶ ቢያሠራጭም በዝግጅቶቹ አማካይነት የማኅበሩ ዓላማ ወደ ተግባር የሚለወጠው ለግቢ ጉባኤያቱ ቦታ ሰጥተው እንዲማሩ በሚያደርጉ አብያተ ክርስቲያናት፣ በቅርበት ሆነው በሚከታተሉ አህጉረ ስብከት ቀና ትብብርና እገዛ ነው:: በመሆኑም ከጠቅላይ ቤተ ክህነት ጀምሮ እስከ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ድረስ ያሉ የቤተ ክርስቲያ አካላት ለሥርዓተ ትምህርቱና መማሪያ መጻሕፍቱ ተግባራዊነት ሰፊ ድርሻ አላቸው::

ማኅበሩ እስከ አሁን በግቢ ጉባኤያት የሚሰጠውን አገልግሎት የተሳካ እንዲሆን የአብያተ ክርስቲያናት አስተዳዳሪዎች ቀላል የማይባል ሚና ተጫውተዋል:. ወደፊትም ይኸንኑ አጠናክረው ተማሪዎቹ በተረጋጋ ሁኔታ ትምህርታቸውን ይከታተሉ ዘንድ ምቹ ቦታዎችን በመስጠት፣ ሌሎች የሚፈልጓቸውን መሣሪያዎች በማቅረብ፣ እንዳመቺነቱም በጉባኤያቸው በመገኘት ምክሮችን በመለገሥ የሚጠበቅባቸውን አገልግሎቶች ሊፈጽሙ ይገባል:: ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያንም እንደ ከዚህ ቀደሙ ከቤተ ክርስቲያን ትምህርት ስፋነት አንጻር /የመማሪያ መጻሕፍቱ/ ራሳቸውን ችለው በበቂ ሁኔታ የተዘጋጁ ናቸው ማለት ስለማይቻል፥ ተገደፉ የሚሏቸውን፣ እንዲሁም መጨመር አለባቸው ብለው የሚያስቡትን ሁሉ በአቅራቢያቸው ለሚገኙ የማኅበሩ አካላት ቢሰጡ የቤተ ክርስቲያንን ሐዋርያዊ ተልእኮ ለማሳካት ወደ ተግባር በመለወጥ ታላቅ አስተዋጽዕ አድርገዋል ለማለት ይቻላል::

ከጥንት ጀምሮ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን የልጆች ድኻ አይደለችም:: ራሳቸውን ለሞት አሳልፈው እስከሚሰጡ ድረስ እውነተኛና ታዛዥ ልጆች ነበሯት:: ዛሬም በእናትነቷ አዝዛ በፈለገችው መስመር ልታሰልፋቸው የምትችላቸው በርካታ ዝግጁ ልጆች አሏት:: እነዚህን ወጣት ልጆቿን ለመያዝም አንድ ዐቃፊ አካል አዘጋጅታ ሓላፊነቷን በመወጣት ላይ ትገኛለች:: ይኸውም ሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ነው:: በዚህ መምሪያ አስተባባሪነት ከ40ና 50 ዓመታት በፊት የተጀመረው እንቅስቃሴ ዛሬ በሁሉም ቦታ ደርሶ በተለይ በታላላቅና ታናናሽ ከተሞች የሚገኙ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት በሥሮቻቸው ሰንበት ትምህርት ቤቶችን አዋቅረው ወጣቶች በቤተ ክርስቲያናቸው ታዛ ሥር እንዲያድጉና ራሳቸውን ለበለጠ አገልግሎት እንዲያዘጋጁ በማድረግ ላይ ይገኛሉ::

ታድያ ለዚህ መልካምና አኩሪ ሥራ ፍጻሜ ማማር ቤተ ክርስቲያናችን ከወዲሁ ፈጥና ልታስብበት የሚገባ ጉዳይ እንዳለ እናምናለን:: ይኸውም ሰንበት ት/ቤቶቻችን ከመዝሙርና ተመሳሳይ አገልግሎቶች በተጨማሪ የዕውቀት መንፈሳዊ እንዲሁም የጥናትና ምርምር ማዕከላት እንዲሆኑ አሁን በተናጠል አንዳንድ ሰንበት ት/ቤቶች የጀመሩትን እንቅስቃሴ ማዕከላዊ ማድረግና ሁሉም የሚገዛበት ወጥ ሥርዓተ ትምህርት መማሪያ መጻሕፍትንም ማዘጋጀት ያስፈልጋል:: ይህ ጉዳይ ደግሞ ማኅበሩ ያዘጋጃቸው የመማሪያ መጻሕፍት በተመረቁ ጊዜ ከሁሉም አካላት በአጽንዖት የተሰነዘረ አስተያየት ነው::

በዚህ ዓይነት ሁላችንም የድርሻችንን ከተወጣን «ህየንተ አበውኪ ተወልዱ ለኪ ደቂቅ» የሚለው ትንቢት ባለ ማቋረጥ ሲፈጸም ይኖራል::

ወስብሐት ለእግዚአብሔር



www.eotcmk.org

# ደብዳቤዎች

## ይበል ያሰኛል

በመቀሌ ከተማ የሚገኘው የደ/ሰ/ቅ/ ሚካኤል ሰንበት ት/ቤትና የአብነት ተማሪዎች በመቀናጀት በሰንበት ት/ቤቱ መርሐ ግብር ላይ ያሬዳዊ መዝሙር ሲያቀርቡ ተመልክቻለሁ:: በተጨማሪም መርሐ ግብር በመምራትና ትምህርት በማስተማር የአብነት ተማሪዎች እንዲሳተፉ ያደርጋሉ:: ሰንበት ተማሪዎችም ቢሆኑ ያሬዳዊውን ዜማ አጥንተው የሚያቀርቡት መዝሙር ይበል ያሰኛልና በርቱ ሊባሉ ይገባቸዋል::

*ዲ/ን ኃ/ገብርኤል ጽጌ ማርያም*
*ቅዱስ ፍሬምናጦስ አባ ሰላማ*
*ከሳቴ ብርሃን መንፈሳዊ ኮሌጅ*

## ከዐውደ ምሕረቱም ውጭ ምሳሌ ቢሆኑ

አንዳንድ ወጣት ሰባክያን በስብከተ ወንጌሉ በእጅጉ ቢመሰገኑም በሥነ ምግባር ራሳቸውን ምሳሌ የማድረጉ ጉዳይ እምብዛም አይታይባቸውም:: እዚህ ላይ ግን እነሱም ሥጋ ለባሽ መሆናቸውን አልዘነጋሁም:: ሆኖም በዚህ ተኩላና ነጣቂዎች በበዙበት ዘመን በሃይማኖቱ ለመጠንከር በጉዞ ላይ ላለ የተዋሕዶ ልጅ በመጠኑም ቢሆን ፈተና ስለሚበዛበት ሰባክያን ቢያስቡበት እና በምግባር ጐልብተው ከዐውደ ምሕረቱም ውጪ ምሳሌ ቢሆኑ መልካም ነው::

*ሃይማኖት እሸቴ እና ጓደኞቹ*
*አርባ ምንጭ*
*ኢሰይያስ ታዬ ይርጋጨፌ*

## የሚያሳዝን ሥራ ነው

ለክብረ በዓል ወደ አንድ ገዳም ሔጄ ነበር:: ገዳሙ ጥንታዊ አሠራርን የተከተለና ክብ ነው:: ጥንታውያን አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማት ውስጣቸው በቅዱሳት ሥዕላት የተመላና የአባቶች የጥበብ ውጤት የሚንጸባረቅበት ነው:: በዚህ ገዳም የተፈጸመው ድርጊት የሚያሳዝን ሆኖ ስላገኘሁት ልጽፍላችሁ ተገደድኩ:: በቤተ መቅደስ ውስጥ እንዳለን ካህናቱ ሕዝቡን ወደ ውጭ እንዲ ወጣ አደረጉ:: ምን ተፈጠረ? ብለን ስንጠይቅ በቅኔ ማኅሌቱ ተሥለው በመጋረጃ ከተጋረዱት ቅዱሳት ሥዕላት መካከል አንዳንዶቹን በጥቁር ቀለም ለማጥፋት ሙከራ መደረጉን ተረዳን:: ሙሉ ለሙሉ ባይጠፉም ሙከራው አሳሳቢ ነውና ተመሳስለው በመግባት ቅርሶቻችንን ለማጥፋት የሚሞክሩ መናፍቃን አሉና ጠንቀቅ እንበል::

*ገብረ ዑራኤል*
*ሰሜን ጐንደር*

## በጀመራችሁት ግፉበት

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ከበራሪ ጽሑፍ ጀምሮ ትላልቅ መጻሕፍትን በኦሮምኛ ቋንቋ እየተረጐማችሁ ማቅረባችሁና መዝሙራትንም በካሴት እያሳተማችሁ ማሠራጨታችሁ በጐ ነው:: እግዚአብሔር ለሐዋርያት ብዙ ቋንቋ እንደ ገለጠ ለእናንተም ምስጢሩን ይግለጽላችሁ:: የጀመራችሁት በጐ ሥራ ፍሬ እያፈራ ነውና ይበልጥ ግፉበት::

*መ/ር ነገራ ኑርጊ*
*ኮምቦልቻ ቴክኒክ ሞያ ማሠልጠኛ ኮሌጅ*

## ቋንቋውን ባያው ቁትም "NO" /ኖ/ አሉት

በ1996 ዓ.ም የጥምቀት በዓልን በጃንሜዳ ሳከብር የገጠመኝን ነገር ላካፍላችሁ:: ለኢትዮጵያውያን በተለይ በኦርቶዶክሳውያን ዘንድ ልዩ ትርጉም ባለው በጥምቀት በዓል ችግር ካልገጠመው በስተቀር በበዓሉ የማይገኝ ምእመን የለም:: ሀገር አቋርጠው የሚመጡ የውጭ ዜጐችን ማየትም የተለመደ ነው:: እንዲህ በሰው ተሞልቶ ጠጠር መጣያ እንኳ በሌለበት በጃን ሜዳ ካህናት ያሬዳዊውን ዜማ ሲያንቀረቁሩት ወረቡን በተመስጦ የሚመለከቱና በያዙት ካሜራ የሚቀርጹ ብዙ ፈረንጆች ነበሩ:: በተለይ እኔ በቅርብ የምመለከተው ፈረንጅ ወረቡን በጥሞና ይከታተላል:: አባቶች ወረቡን እንደ ጨረሱ ወደ አንድ አረጋዊ አባት ጠጋ ብሎ ፈገግታ እያሳያቸው ዐይኑን ወደያዙት ጸናጽል ወረወረ:: እኒህ አባትም ማየት ፈልጐ ነው ብለው የብሩን ጸናጽል ሰጡት:: /ድርድሮቹን/ እየነካካ ከቆየ በኋላ ከኪሱ ዶላር አውጥቶ ሲሰጣቸው አሳቡ ምን እንደ ሆነ ስለ ገባቸው መሰለኝ ቋንቋውን ባያውቁትም «No» /አይሆንም/ አሉት::

*ዲ/ን ንዋይ*
*ቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ*

## ፖስታ ሳጥኔን የኑፋቄ ወረቀት ሞላው

በተለያዩ ርእሶች ዙሪያ ከተለያዩ ሰዎች ጋር መወያየት እፈልጋለሁ:: ለዚህም «የብዕር ጓደኛ እፈልጋለሁ» በማለት በጋዜጣ በሚገኘው አድራሻ እጻጻፋለሁ:: በጣም የገረመኝ ግን በፖስታ ሣጥኔ የሚመጣው የኑፋቄ ወረቀት መሆኑ ነው::" እንግዲህ በየሳምንቱ በየጋዜጣው ለሚወጡት የብዕር ፈላጊዎች በቀን በቀን የሚያስተላልፉት ኑፋቄአቸውን ሊሆን ይችላልና ጥንቃቄ አድርጉ በሉልኝ::

*ዲ/ን ተክሊት ኃ/ማርያም*
*ሻሸመኔ*

*__ከአዘጋጁ__*

*ከአሁን በፊት ተመሳሳይ አስተያየት ቀርቦልን ያስተናገድን ሲሆን ችግሩ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰ የመጣ መሆኑን ተረድተናል:: የፖስታ ቤት ድርጅትን ብናነጋግርም አጥጋቢ መልስ አላገኘንም:: በመሆኑም ሁሉም በያለበት ከሚመለከታቸው የፖስታ ቤት ሐላፊዎች ጋር በመነጋገር መብቱን ያስጠብቅ እንላለን::*

## እንምሰላቸው

እኔ ባለሁበት አካባቢ የሚኖሩ በግብርና የሚተዳደሩ አባት አሉ:: እኚህ አባት ለቤተ ክርስቲያን ካላቸው ፍቅር የተነሣ ባላቸው ትጋት የሌላ እምነት ተከታዮችን በማስተማር 47 አባ ወራ ከነቤተሰቦቻቸው በማስተማር ወደ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እንዲመለሱ አድርገዋል:: እኛም ብዙ መሥራት ይጠበቅብናልና እንምሰላቸው:: እኒህንም አባት አመስግኑልኝ::

*መ/ር አበበ በለጠ ዶሎ መና ወለሱ*
*አበረስ ቅ/ማርያም*

## ጥንቃቄ አድርጉ

በመጽሔቱ በሚወጡ ጽሑፎች ላይ የተለያዩ የፊደል ግድፈቶች ይገኛሉ:: አንዳንዶቹ የተዛባ መልእክት ስለሚያስተላልፉ ጥንቃቄ አድርጉ::

*በላይ ጥላሁን*
*ዲላ*



www.eotcmk.org

## እኛም እንታሰብ

እንኳን ለ12ኛ ዓመት የልደት በዓላችሁ አደረሳችሁ:: ለወደ ፊትም መልካም የአገልግሎት ዘመን ይሁንላችሁ እላለሁ:: መጽሔቷ ካለሁበት ድረስ እየመጣች ታስተምረኛለች:: እንደ ተለመደውም የ12ኛ ዓመት ቁጥር 1 እትም ደርሳኝ አንብቤያታለሁ:: ይህንን ደብዳቤ እንድጽፍ ያደረገኝም ቀደም ሲል ተጀ ምሮ በዚህች እትም የተጠናቀቀ አንድ ትምህርት ነው:: ይኸውም «የንስሐ አባትና ልጅ ግንኙነት» በሚል ርእስ በዶ/ር መስፍን ተገኝ ቀርቦ በሁለት ተከታ ታይ እትም የቀረበው ጽሑፍ ነው:: በእውነቱ ዶ/ር መስፍን ጉዳዩን በሚ መለከት ዋና ዋናውን ነጥብ ብቻ ነው ያስቀመጡት ማለት ይቻላል:: ጉዳዩ ብዙ ሊባልበት የሚችልና የሚ ገባም ነው:: በተለይ በውጭ ስለሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ምእመናን የንስሐ ሕ ይወትና ከአባቶቻቸው ጋር ሊኖር ስለ ሚገባው ግንኙነት ብዙ ሊባል ይገባል:: የንስሐ ሕይወትን በሚመለከት በውጭ ለምንኖር ኢትዮጵያውያን ጉዳዩ ሊታሰ ብበት ይገባል:: ይኸውም ከንስሐ አባት ጋር ሊኖር ስለሚገባው ጥሩ ግንኙነት ሳይሆን በምእመናኑ መካከል ሊኖር የሚገባው አባት አለ መኖሩ ትልቁ ችግር ነውና:: ስለዚህ በተለይ ርዕስ ነቁ በውጭ ከምንኖር ምእመናን አንጻር መፍትሔ ሊሆን በሚችል መንገድ ተቃኝቶ እንደገና በስፋት ሊ ጻፍ ይገባል እላለሁ:: ረድኤተ እግዚ አብሔር አይለየን::

*ትዕግሥት ደሳለኝ*
*ካይሮ*

## ነፍሴ ከጥማቷ ረካች

ሐመር ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ 12ኛ ዓመት ቁጥር 1 «ከሰሞኑ በረከት» በሚለው ዓምዷ የልብ ዐውቃ ሆና ሁል ጊዜ እንዲጻፍ የምፈለገውን የ «ሰሙነ ሕማማት» ትምህርት ሰንቃ ካለሁበት ከተፍ አለች:: እውነቴን ነው የምላችሁ መጽሔቷ የቀዳም ስዑር ልትደርሰኝ ዓርብ የስቅለት ዕለት ጉዳ ዩን አንሥተን ከጓደኞቼ ጋር ስንወያይ በዚያች እትም የማትጽፉ ከሆነ አስተያየት ልንጽፍ ተስማምተን ነበር:: ነገር ግን ሁል ጊዜም የእኛን የአንባብያንን ፍላጐት በርቀት ሆና ችሁ የምትረዱት አዘጋጆች አስቀ ድማችሁ በሰሙነ ሕማማት ዙሪያ ትምህርት አዘጋጅታችሁ ኖሯል:: እግዚአብሔር ይስጣችሁ:: ወደ ፊትም በዚሁ ቀጥሉ::

*መ/ር አሸናፊ ስለሺ*
*ባሌ ጊንር*

## ትኩረት ስገጠሩ

ይህ ያለንበት ዘመን ቅድ ስት ቤተ ክርስቲያናችንም ሆነች አገልጋዮቿ ለገጠሩ የሀገራችን ክፍል ትኩረት ለያደርጉበት የሚ ገባ ዘመን ነው:: ከቤተ ክርስቲያኗ ነባራዊ ሁኔታ እንደምንመለከተው ከሆነ ዛሬ በሚደርስባቸው መጠነ ሰፊ ችግር የተነሣ እየተፈቱና ወደ መፈታት እየቀረቡ ያሉ አብያተ ክርስቲያናት ያሉት በገጠር ነው:: እነዚህ ጥንታውያት ቅዱሳት መካ ናት የዕለት መቀደሻ አጥተው የሚሰጡት አገልግሎት እየታጐለ በከተማ ያሉት የቀን ገቢ ከሚገ መተው በላይ ነው:: የገጠሩ ሕዝብ የእግዚአብሔርን ቃል በሚገባ አዘ ጋጅቶ የሚያቀብለው እያጣ በከተ ማ ሰባክያን ተበራክተው መድረክ ሲሻሙ እናያለን:: በገጠር «አሐዱ አብ» ብሎ ቀድሶ የሚያቆርብ ካህን ጠፍቶ በከተማ ከካህኑ ብዛት የተነሣ በአንድ ደብር የሚኖር ካህን በወር እንኳን ለመቀደስ የማይደ ርስበት ደረጃ እንደ ደረሰ እንሰ ማለን:: በእውነቱ ይህ የሚያሳዝን ጉዳይ ነው:: የቤተ ክርስቲያኗ አስተዳደርም ሆነ የሚመለከተን ሁሉ ትኩረታችን ወደ ገጠሩ የሀገ ራችን ክፍል ላሉት አብያተ ክርስ ቲያናት ብናደርግ መልካም ነው እላለሁ:: ልቡና ይስጠን::

*ጥዑመ ልሳን ልሣነ ወርቅ*
*ደሴ*

## ዕድለኛው ዶክተር

ሳነበው ሰውነቴ ሲንቀጠቀጥ ይታወቀኛል:: ዕለቱ ዓርብ ሚያዝያ አንድ ቀን የስቅለት በዓል ነው:: ሊቃውንቱ እየተፈራረቁ ስግደቱን ይመሩታል:: ምእመናኑም ከ1996 ዓ.ም በፊት ቀራንዮ ያሉ ይመስላሉ:: ግብረ ሕማማቱ ተተርጉሞ ለመጀመሪያ ጊዜ በአማርኛ እየተነበበ ነው:: ሕዝቡ በተመስጦ ይሰማል:: እኔ ሐመርን ብድግ አድርጌ ሳገላብጣት ሰማዕቱ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ የሚለው ሳበኝና ማንበብ ቀጠልኩ:: ሳላስበው «ሕዝቡስ... ሕዝቡስ... እንዴት አባቱ ተላልፈው ለሞት ሲሰጡ ዝም አለ?» አልኩኝ በልቤ ሲቃ ተናንቆኝ:: ዝቅ ብዬ ሳነብ «የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ አስከሬን ተጥሎ የተገኘው በቁጥር «11» በተመለከተው ጉድጓድ ከተቀበረው ከዶ/ር ኃይሌ ጋር ነበር» የሚል አገኘሁ:: ወዲያውኑ የኤልሳዕ ዐፅም ትዝ አለኝና «አባታችን ልጃቸውን አሳልፈው ለሰይጣን አይሰጡም፤ ምን የታደለ ዶክተር ነው?» አልኩኝ:: እንደ ፈያታዊ ዘየማን የታደለ:: እኛ በቁ ማቸው እያየናቸው እየሸሸን፣ ወደ ኋላ እያልን እርሱ ግን ዐፅማቸውን የሙጥኝ አለ:: ለሁላችንም ቅዱሳን አባቶቻችንን የሙጥኝ የምንልበትን ልቡና ያድለን::

*መ/ር ኃ/ኢየሱስ*
*ድሬዳዋ*

## ማብራሪያው አስደስቶኛል

በሐመር 11ኛ ዓመት ቁጥር 6 ላይ ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ ሥራን በተመለከተ የሰጡት ማብራሪያ በጣም አስደስቶኛል:: ስንፍናቸውን በቤተ ክርስቲያን ላይ ምክንያት ለሚያደርጉ ሰዎች መልስ ስለሆነ በወረቀት ላይ ሁኖ የሚነበብ ብቻ እንዳይሆን ሁሉም እንዲ ያውቀው ይደረግ::

*ወ/ሮ አንግሥዎ ተክላይ /ብላቴ*
*ኢጋአዚ/ከ/ክ/ጦር/*
*አቶ ቡሩክ መኩንን /መቐለ ዩኒቨርሲቲ/*
*መ/ር ወርቅነህ ሽቴ ባቲ /ወሎ/*

## በክብር እናስቀምጣቸው

ወደ ተለያዩ ከተሞች ስዘዋወር በተሽከርካሪዎች መስተዋት ላይ የተቀ ዳደዱ ቅዱሳት ሥዕላት ተለጥፈው እመ ለከታለሁ:: ከጐናቸውም የተለያዩ የሙዚቃ ሰዎች ፎቶ ግራፍ አብሮ አለ:: ይህ አግ ባብነት የሌለውና ክብር መንሳት በመሆኑ በክብር በተገቢው ቦታ አስቀምጠን ብንገለገል መልካም ነው::

*ተስፋዬ መብራቴ*
*/ሰሜን ሸዋ ሀገረ ማርያም፣ከሰም ወረዳ/*



www.eotcmk.org

# «ከሥርዓቴ ፈቀቅ ብላችኋል።»

/ሚል.3÷7/

/ጎርጎርዮስ ደጀኔ /

ይኽንን ቃል በነቢዩ በሚልክያስ በረድኤት አድሮ የተናገረው የፍጥረታት ገዥ እግዚ.አብሔር ነው። እግዚ.አብሔር ፍጥረታትን የፈጠረው በዘፈቀደ ሳይሆን በሥርዓት ነው። የሚያስተዳድራቸውም እንዲሁ በሥርዓት ነው። ከፍጥረታትም መካከል በተለየ መልኩ ስሙን ለመቀደስ ክብሩን ለመውረስ የተፈጠሩት የሰው ልጅና ቅዱሳን መላእክት ናቸው። እነዚህም በሰማይና በምድር የመላ ምሉዕ በኩለሄ የሆነ እግዚ.አብሔርን በሥርዓት ያገለግሉታል። «ቅዱስ÷ቅዱስ÷ቅዱስ የሠራዊት ጌታ እግዚ.አብሔር፤ ምድር ሁሉ ከክብሩ ተሞልታለች።» እያሉ ያመሰግኑታል። ኢሳ.6÷3።

ቅዱሳን መላእክት÷ ሰማያዊ ሥርዓት ተሠርቶላቸው በሰማይ ባለ ቤተ መቅደስ እንደ ሚያገለግሉ በቅዱሳት መጻሕፍት ተጽፏል። «ሰባተኛውንም ማኅተም በፈታ ጊዜ እኩል ሰዓት የሚያህል ዝምታ በሰማይ ሆነ። በእግዚ.አብሔር ፊት የሚቆሙትን ሰባቱን መላእክት ዐየሁ÷ ሰባትም መለከት ተሰጣቸው። ሌላም መልአክ መጣና የወርቅ ጥና ይዞ በመሠዊያው አጠገብ ቆመ፤ በዙፋኑም ፊት ባለው በወርቅ መሠዊያ ላይ በቅዱሳን ሁሉ ጸሎት እንዲጨምረው ብዙ ዕጣን ተሰጠው። የዕጣኑም ጢስ ከቅዱሳን ጸሎት ጋር ከመልአኩ እጅ በእግዚ.አብሔር ፊት ወጣ።» እንዲል። ራእ. 8÷1-4። እዚህ ላይ ሰባተኛው ማኅተም ማለቱ ጸሎተ ቅዱሳንን የማሳረግ፣ በኃጥአን ላይ መቅሠፍትን የማዘዝ፣ የፍጹም ሥልጣንና ጌትነት ሥራን ማመልከቱ ነው። በእግዚ.አብሔር ፊት የሚቆሙት መላእክትና የተሰጣቸው መለከት ሰባት መሆኑ የተወሰነ የቁጥር ሥርዓትን ያመለክታል። በተጨማሪም «በሰማይም ያለው የእግዚ.አብሔር መቅደስ ተከፈተ÷ የኪዳኑም ታቦት በመቅደሱ ታየ፤» የሚል ጽሑፍ አለ። ራእ.11÷19። በዚህም ዕረፍታቸው ምስጋናቸው÷ ምስጋናቸውም ዕረፍታቸው በሆኑ በቅዱሳን መላእክት እግዚ.አብሔር አድሮባቸው ይኖራል።

ለሰው ልጅም ይህ የቅዱሳን መላእክት ሥርዓተ አምልኮ ተሰጥቶታል። ይኸውም ይታወቅ ዘንድ÷ እግዚ.አብሔር ሙሴን፡ - «በመካከላቸውም አድር ዘንድ መቅደስ ይሥሩልኝ፤ እኔ እንደ ማሳይህ ሁሉ÷ እንደ ማደሪያው ምሳሌ ሥሩት።» ብሎታል። ዘጸ.25÷8። ከዚህም አያይዞ ስለ ታቦቱ÷ ስለ ስርየት መክደኛው÷ ስለ ሥዕለ ኪሩብ÷ ስለ ገበታው÷ ስለ መቅረዙ÷ ስለ መጋረጃዎቹ÷ ስለ ሳንቃዎቹ÷ ስለ ምሰሶዎቹ÷ ስለ መሠዊያው÷ ስለ ካህናቱ÷ ስለ አልባሳቱ÷ ስለ መሥዋዕቱ÷ ስለ ቅብዐ ዘይቱ÷ ስለ ዕጣኑና ስለ መሠዊያው÷ ስለ ድንኳኑ አሠራርና ስለ አገልግሎቱ አፈጻጸም ሥርዓት በዝርዝር ነግሮታል። አስቀድሞም ወደ ደብረ ሲና አውጥቶ÷ በደመና ጋርዶ÷ ሰማያትን ከፍቶ ሰማያዊውን ሥርዓት አሳይቶታል። «ሙሴም ወደ ተራራ ወጣ÷ ደመናውም ተራራውን ሸፈነው። የእግዚ.አብሔርም ክብር በሲና ተራራ ላይ ተቀመጠ÷ ደመናውም ስድስት ቀን ሸፈነው፤ በሰባተኛውም ቀን ከደመናው ውስጥ ሙሴን ጠራው። በተራራው ራስ ላይ በእስራኤል ልጆች ፊት የእግዚ.አብሔር ክብር መታየት እንደሚያቃጥል እሳት ነበረ። ሙሴም ወደ ደመናው ውስጥ ገባ÷ ወደ ተራራውም ወጣ÷ ሙሴም በተራራው ላይ አርባ ቀን÷ አርባ ሌሊትም ቆየ።» እንዲል። ዘጸ.24÷15-18። እግዚ.አብሔር የሥርዓተ አምልኮውን ዝርዝር ለሙሴ በሚነግረው ጊዜ፡- «በተራራ ላይ እንዳሳየሁህ ምሳሌ እንድትሠራ ተጠንቀቅ።» እያለ ያሳስበው የነበረው ለዚህ ነበር። ዘጸ.25÷40።

እግዚ.አብሔር ሙሴን ለይቶ÷ ወደ ተራራ አውጥቶ÷ ይኽንን ሁሉ ምሥጢር ያሳየውና የነገረው እንደ ቅዱሳን መላእክት ስሙን ለመቀደስ÷ ክብሩን ለመውረስ የተፈጠረ የሰው ልጅም ፍጹም በሆነ የመላእክት ሥርዓት እንዲያገለግለው ስለ ወደደና ስለ ፈቀደ ነው። የሰው ልጅ ግን እንደ ቅዱሳን መላእክት ሥርዓት ሕግን ቢቀበልም በሕጉና በሥርዓቱ መሔድ እያቃተው ይቸገር ነበር። ይህም ችግር ፈጽሞ ካለ መቻል የመጣ ሳይሆን ከቸልተኝነትና ከስንፍና የመጣ ነበር። ለዚህም ነው እግዚ.አብሔር፡- «ከአባቶቻችሁ ዘመን ጀምሮ ከሥርዓቴ ፈቀቅ ብላችኋል÷ አርስዋንም አልጠበቃችሁም። ወደ እኔ ተመለሱ÷ እኔም ወደ እናንተ እመለሳለሁ÷ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚ.አብሔር። እናንተ ግን፡- የምንመለሰው በምንድር ነው? ብላችኋል። ሰው እግዚ.አብሔርን ይሰርቃልን? እናንተ ግን እኔን ሰርቃችኋል። እናንተም፡ - የሰረቅንህ በምንድር ነው? ብላችኋል። በዓሥራትና በበኩራት ነው። እናንተ÷ ይህ ሕዝብ ሁሉ እኔን ሰርቃችኋልና በእርግማን ርጉሞች ናችሁ።» ያለው። ሚል.3÷7-9። ምክንያቱም በበረከትና በሕይወት ከሚያኖራቸው ሥርዓት ፈጽመው ርቀዋልና ነው።

ሕዝቡ ሥርዓቱን ጠብቀው ቢኖሩ በረከት እንደ ሚትረፈረፍላቸው፡ - «በቤቴ ውስጥ መብል እንዲሆን ዓሥራቱን ሁሉ ወደ ጎተራ አግቡ፤ የሰማይንም መስኮት ባልከፍትላችሁ÷ በረከትንም አትረፍርፌ ባላፈስስላችሁ በዚህ ፈትኑኝ÷ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚ.አብሔር። ስለ እናንተ ነቀዙን እገሥጻለሁ÷ የምድራችሁንም ፍሬ አያጠፋም፤ በእርሻችሁም ያለው ወይን ፍሬውን አያረግፍም÷ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚ.አብሔር። የተድላ ምድር ትሆናላችሁና አሕዛብ ሁሉ ብፁዓን ብለው ይጠሩአችኋል÷ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚ.አብሔር።» ተብሎ ተነግሮአቸዋል። ሚል.3÷10-12። በነቢዩ በሕዝቅኤል ትንቢትም ላይ፡- «ሰው ቢያደርገው ኖሮ በሕይወት የሚኖርበትን ሥርዓቴንም ሰጠኋቸው÷ ፍርዴንም አስታወቅኋቸው። የምቀድሳቸውም እኔ እግዚ.አብሔር እንደ ሆንሁ ያውቁ ዘንድ በእኔና በእነርሱ መካከል ምልክት ይሆኑ ዘንድ ሰጠኋቸው። ነገር ግን የእስራኤል ቤት በምድረ በዳ ዐመፁብኝ÷ ፍርዴን ጣሱ÷ ሰንበታቴንም ፈጽመው አረከሱ።» የሚል ጽሑፍ አለ። ሕዝ.20÷11። ይህም ሥርዓተ ሃይማኖትን በእምነት መጠበቅ በሕይወት እንደ ሚያኖር÷ ሁለንተናን እንደ ሚቀድስ÷ ሰው በእግዚ.አብሔር ለመታመኑም ምልክት እንደ ሆነ ያመለክታል። ከዚህም ጋር ዝናም ለዘር÷ ጠል ለመከር ይሰጣል። በዚህን ጊዜ ምድር የዘሩባትን ታበቅላለች÷ የተከሉባትንም ታጸድቃለች። አንዱ ቅንጣት ሠላሳ÷ ስድሣ÷ መቶ ያማረ ፍሬ ያፈራል።

እግዚ.አብሔር በቀጥታም ይሁን በቅዱሳኑ ላይ አድሮ የሠራውን የቤተ መቅደሱን ሥርዓት ካህናቱም ሆኑ ምእመናኑ ሊጠብቁትና ሊያስጠብቁት



www.eotcmk.org

ይገባቸዋል:: /መጽ.ኢዮብ33÷14/ ካልጠ
በቁትና ካላስጠበቁት ግን በእግዚአብሔ
ር ላይ ማመፅ ስለሆነ እግዚአብሔር
በሁሉም ላይ ይፈርድባቸዋል::

*የእግዚአብሔር ፍርድ*
*ሥርዓቱን በማይጠብቁት ላይ፤*

አዳምና ሔዋን በኤደን ገነት
በተድላ ደስታ እየኖሩ ሊጠብቁት
የሚገባቸውን የአምልኮ ሥርዓት ባለ
መጠበቃቸው በርደተ መቃብር ላይ
ርደተ ገሃነም÷ በሞተ ሥጋ ላይ ሞተ
ነፍስ÷ በመርገመ ሥጋ ላይም መርገመ
ነፍስ ተጨምሮ ተፈርዶባቸዋል:: ዘፍ.
2÷17፤ ዘፍ.3÷1-24:: በዚህ ምክንያት
አዳምና ሔዋን ተጸጸቱ÷ ሕጉን ባለ
መጠበቃቸው እንባቸውን እንደ ጐርፍ
አፈሰሱ:: በመቅድመ ወንጌል እንደ
ተጻፈው አዳም በኃጢአቱ ምክንያት
በመጣበት ብድራት ከማልቀስ በቀር
ሌላ ኀሊና አልነበረውም:: ከዚህ የተ
ነሣ፤ «ከልጅ ልጅህ ተወልጄ አድን
ሃለሁ» የሚለውን የእግዚአብሔር
ድምፅ ሰማ፤ የሚያስፈልገው ስሕተትን
ማስተባበል ሳይሆን ስሕተትን አምኖ
ንስሐ መግባት ነውና::

ቃየን:- የእግዚአብሔርን የመሥ
ዋዕቱን ሥርዓት ጠብቆ ለንጹሐ ባሕ
ርይ ለእግዚአብሔር ንጹሕ መሥዋዕት
ማቅረብ ሲገባው:- በሕገ ልቡና /በት
ውፊት/ ከአባቱ ከአዳም የተቀበለውን
የመሥዋዕት ሥርዓት ንቆና አቃልሎ
ከምርቱ ግርዱን በማቅረቡ እግዚአብሔር
ወደ ቃየንና ወደ መሥዋዕቱ ሳይመ
ለከት ቀረ:: በዚህ ምክንያት ቃየን
እጅግ ተናደደ÷ ፊቱም ጠቆረ:: እግዚ
አብሔርም:- «ለምን ተናደድህ? ለም
ንስ ፊትህ ጠቆረ? መልካም ብታደርግ
ፊትህ የሚበራ አይደለምን? መልካም
ባታደርግ ግን ኃጢአት በደጅ ታደ
ባለች፤ ፈቃድዋም ወደ አንተ ነው÷
አንተ ግን በእርስዋ ንገሥባት::» አለ
ው:: «...መልካም ብታደርግ ኖሮ»
አለ÷ «መልካም» የተባለው ሥርዓተ
መሥዋዕቱ፣ የዋህነቱ፣ ደግነቱ ሲሆን
«መልካም ማድረግ» ደግሞ በየዋህነትና
በደግነት ሥርዓተ መሥዋዕቱን መጠ
በቅ ነው:: ቃየን ግን እግዚአብሔርን
ያህል አምላክ «ሥርዓት አልጠበቅ
ህም÷ ተሳስተሃል» እያለው ንስሐ መግ
ባት አልፈለገም:: ይልቁንም በኃጢ
አት ላይ በደልን ለመጨመር ወንድ
ሙን ገደለው:: በግፍ የፈሰሰ የወ
ንድሙም ደም ከሰሰው:: እግዚአብሔ
ርም ሰምቶ «ወንድምህ ምን አደረገህ?
የወንድምህ የደሙ ድምፅ ከምድር
ወደ እኔ ይጮኻል:: አሁንም የወንድ
ምህን ደም ከእጅህ ለመቀበል አፍዋን
በከፈተች በምድር ላይ አንተ የተረ
ገምህ ነህ:: ምድርንም ባረስህ ጊዜ ኃይ
ልዋን /በረከትዋን/ አትሰጥህም፤ በምድ
ርም ላይ ኰብላይና ተቅበዝባዥ ትሆና
ለህ::» አለው:: ከዚህ በኋላ ቃየን:
- «ኃጢአቴ ልሸከማት የማልችላት
ታላቅ ናት:: እነሆ ዛሬ ከምድር ፊት
አሳደድኸኝ፤ ከፊትህም እሰወራለሁ፤
በምድርም ላይ ኰብላይና ተቅበዝባዥ
እሆናለሁ፤ የሚያገኘኝም ሁሉ ይገድለ
ኛል::» እያለ በእግዚአብሔር ፊት ቢወ
ተውትም የልቡን ክፋት የሚያውቅ
እግዚአብሔር አልሰማውም:: ዘፍ.4÷1
-15:: በመወትወት ብዛት ሰውን ማታ
ለል ይቻላል፤ እግዚአብሔርን ግን ማታ
ለል አይቻልም:: የሥርዓተ አልበኞች ጠ
ባይ ሁል ጊዜ እንዲህ ስለሆነ መጠንቀቅ
ያስፈልጋል:: ዛሬም ሥርዓተ ቤተ ክርስ
ቲያንን የሚጥሱ ሰዎች በዚህ ሳያቆሙ
ወደ ሌላም የከፋ ነገር እንደ ሚሔዱ
አያጠራጥርም:: «ነገር ግን÷ ወንድሞች
ሆይ÷ እናንተ የተማራችሁትን ትምህ
ርት የሚቃወሙትን÷ መለያየትንና ማሰ
ናከያን የሚያደርጉትን ሰዎች እንድ
ትመለከቱ እለምናችኋለሁ÷ ከእነርሱ
ዘንድ ፈቀቅ በሉ፤ እንዲህ ያሉት ለገዛ
ሆዳቸው እንጂ ለጌታችን ለኢየሱስ ክር
ስቶስ አይገዙምና÷ በመልካምና በሚያ
ቈላምጥ ንግግር ተንኰል የሌለባቸውን
ሰዎች /የዋሃን ምእመናንን/ ልብ ያታ
ልላሉ::» እንዲል:: ሮሜ.16÷17-18::

ብእሲተ ሎጥ:- «በዚህ ስፍራ አት
ቁሙ÷ ወደ ኋላችሁ አትመልከቱ÷ እን
ዳትጠፉም ወደ ተራራው ሸሽታችሁ
አምልጡ::» በማለት ቅዱሳን መላእክት
የሠሩላቸውን ሥርዓት ባለመጠበቋ
የጨው ሐውልት ሆና ቀርታለች::
ጻድቁ ሎጥ ግን የእርስዋ ሚስትነት
ሳያሸንፈው ሥርዓቱን ጠብቆ በመጓዙ ሕ
ይወቱን አትርፏል:: ሁለት ልጆችዋም
በሥርዓቱ መጽናት የተሳናትን እናታ
ቸውን ትተው ጸንቶ የተገኘውን አባታ
ቸውን በመከተላቸው ሕይወታቸውን
አትርፈዋል:: ስለሆነም በሥጋ ዝምድና
ወይም በሀገር ልጅነት ወይም በመተዋ
ወቅ እየተታለሉ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲ
ያንን የሚጥሱ ሰዎች ከእነዚህ መማር
ይገባቸዋል:: ይኸንን በተመለከተ ጌታ
ችን በወንጌል «እንዲሁ በሎጥ ዘመን
እንደ ሆነ፤ ይበሉ ይጠጡም ይገዙም
ይሸጡም ነበር፤ ሎጥ ከሰዶም በወጣበት
ቀን ግን ከሰማይ እሳትና ዲን ዘነበ፤
ሁሉንም አጠፋ:: የሰው ልጅ በሚገ
ለጥበት ቀን እንዲሁ ይሆናል:: በዚያም
ቀን በሰገነት ያለ በቤቱ ያለውን ዕቃ ሊ
ወስድ አይውረድ÷ እንዲሁም በእርሻ
ያለ ወደ ኋላው አይመለስ:: የሎጥን
ሚስት አስቡአት::» ብሏል:: ሉቃ.
17÷28-32:: ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎ
ስም ከጸኑት ጋር መጽናት እንደ ሚገባ
ሲያስገነዝብ:- «በነፍሳችሁ ዝላችሁ እንዳ
ትደክሙ÷ ከኃጢአተኞች በደረሰበት
እንዲህ ባለ መቃወም የጸናውን አስቡ::»
ብሏል:: ዕብ.12÷3::

ዔሳው:- «እነሆ÷ እኔ ልሞት ነኝ፤
ይህች ብኵርና ለምኔ ናት?» በማለት
ሥርዓተ ብኵርናን በማቃለሉ የአባቱ
ምርቃት÷ የእግዚአብሔር በረከት ቀርቶ
በታል:: ዔሳው ብኵርናውን ያቃለለውና
የሸጠው ለሆዱ ብሎ ነው:: ከበረሃ
ውሎ አደን ስላልቀናው ድካምና ረሃብ
ነበረበት:: እግዚአብሔር ቢፈቅድ ኖሮ
አደን ቀንቶት የዕለት ጉርሱን ያገኝ
ነበር:: በዚያን ዕለት የእግዚአብሔር
ፈቃድ ዔሳው ጾሙን ውሎ ጾሙን
እንዲያድር ነበር:: እርሱ ግን ከእግዚ
አብሔር ፈቃድ ይልቅ የሥጋውን
ፈቃድ በማስበለጥ÷ ሥርዓተ ብኵርናን
አቃለለ:: በዚህን ጊዜ ነው ወንድሙ
ያዕቆብ የሆዴ ነገር ይቅርብኝ ብሎ
ሥርዓተ ብኵርናን ያከበራት:: ዘፍ
25÷26-34:: እርሷም እንዳከበራት አከ
በረችው:: ከሰው ወይም ከከብት
የእናቲቱን ማኅፀን የሚከፍት /በመጀ
መሪያ የሚወለድ/ በኵር ይባላል:: በእ
ስራኤል የበኵር መብት /ብኵርና/
ትልቅ በመሆኑ አባቱ በሌለበት ለወን
ድሞቹ ኃላፊ ይሆናል፤ ከርስት ሁለት
እጅ ያገኛል፤ በቤተ መንግሥትም
አልጋ ወራሽ ነው:: ይሁንና በኵር ቢ
ያጠፋ ብኵርናው ለሌላው ሊታላለፍ
ይችላል:: ዔሳው ሥርዓተ ብኵርናን
/የታላቅነት መብቱን/ በምስር ወጥ
በመለወጡ አጣት፤ ከዚያ በኋላ በረከቱ
ን ሊወርስ ወዶ በእንባ ጭምር ተግቶ
ቢፈልጋትም አላገኛትም:: /ዕብ.
12÷17/:: ስለዚህም ጊዜው ሲደርስ
ያዕቆብ የአባቱን ፈቃድ ፈጽሞ
በመገኘቱ «የልጄ ሽታ እግዚአብሔር
እንደ ባረከው እርሻ ሽታ ነው፤ እግዚ
አብሔር ከሰማይ ጠል ከምድርም ስብ
የእህልንም የወይንንም ብዛት ይስጥህ÷
አሕዛብ ይገዙልህ÷ ሕዝብም ይስገ
ዱልህ÷ ለወንድሞችህ ጌታ ሁን÷
የእናትህም ልጆች ይስገዱልህ፤ የሚረ
ግምህ እርሱ ርጉም ይሁን÷ የሚባር
ክህም ቡሩክ ይሁን::» ተብሎ ተመ
ረቀ:: ዘፍ.26÷27-29:: እግዚአብሔርም
በስደቱ ጊዜ በፍኖተ ሎዛ ተገልጦ
ባረከው:: «የአባትህ የአብርሃም አም
ላክ የይስሐቅም አምላክ እኔ እግዚ
አብሔር ነኝ፤ ይህችን አንተ የተኛ
ህባትን ምድር ለአንተም ለዘርህም
እሰጣለሁ፤ ዘርህም እንደ ምድር አሸዋ
ይሆናል፤ እስከ ምዕራብና እስከ ምሥራ
ቅ እስከ ሰሜንና እስከ ደቡብ ትስፋ
ፋለህ፤ የምድርም አሕዛብ ሁሉ በአንተ
በዘርህም ይባርካሉ:: እነሆም እኔ ከአ
ንተ ጋር ነኝ÷ በምትሔድባትም መን
ገድ ሁሉ እጠብቅሃለሁ÷ ወደ ዚችም
ምድር እመልስሃለሁ፤ የነገርሁህን ሁሉ
እስካደርግልህ ድረስ አልተውህምና÷»
አለው:: ዘፍ.28÷13-15:: በኋላም
ለሙሴ በደብረ ሲና በተገለጠለት
ዘመን ሥርዓተ ብኵርናን የናቀ ዔሳ
ውን ትቶ ያዕቆብን ግን አክብሮ:
- «እኔ የአባትህ አምላክ÷ የአብርሃም
አምላክ÷ የይስሐቅም አምላክ÷ የያዕ
ቆብ አምላክ ነኝ::» ብሏል:: ዘጸ.3÷6::
ሌላው ቀርቶ በለዓም እንኳ መንፈስ
ቅዱስ አፉን ከፍቶ÷ ፊቱን ጸፍቶ በግ
ድ ቢያናግረው:- «ባላቅ ከአራም



www.eotcmk.org

አመጣኝ÷ የሞዓብ ንጉሥ ከምሥራቅ ተራሮች፤ ና÷ ያዕቆብን ርገምልኝ፤ና÷ እስራኤልን ተጣላልኝ ብሎ:: እግዚአብሔር ያልረገመውን እንዴት እረግማለሁ? እግዚአብሔር ያልተጣላውን እንዴት እጣላለሁ?» ብሏል:: ዘኁ. 23÷7-8:: ቀጥሎም «ዐየዋለሁ÷ አሁን ግን አይደለም፤ እመለከተዋለሁ÷ በቅርብ ግን አይደለም፤ ከያዕቆብ ኮከብ ይወጣል÷» በማለት ከእርሱ ወገን ኮከብ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ሚወለድ ተናግሮለታል:: ዘኁ.24÷17:: «እኔ የዳዊት ሥርና ዘር ነኝ፤ የሚያበራም የንጋት ኮከብ ነኝ፤» እንዲል:: ራእ.22÷16:: ነቢዩ ሚልክያስም የያዕቆብን ክብር ሲናገርለት:-

- «ወድጃችኋለሁ÷ ይላል እግዚአብሔር፤ እናንተ ግን:- በምን ወደድኸን ብላችኋል:: ዔሳው የያዕቆብ ወንድም አልነበረምን? ይላል እግዚአብሔር:: ያዕቆብንም ወደድሁ ዔሳውንም ጠላሁ፤» ብሏል:: ሚል.1÷2:: ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ይኽንን ቃል ጠቅሶ የሮሜን ሰዎች አስተምሮበታል:: ሮሜ. 9÷13:: ያዕቆብ የተወደደው በመልካም ግብሩ÷ ዔሳው የተጠላው በመጥፎ ግብሩ ነው:: ዛሬም በቤተ ክርስቲያን ዔሳውም ያዕቆብም አሉ:: ከምእመናን የሚጠበቀው እግዚአብሔርን ተከትሎ ያዕቆብን መውደድ ነው፤ ይኽውም ሥርዓትን የጠበቀ ያዕቆብን እግዚአብሔር ወዶታልና ነው::

ዳታንና አቤሮን ከነገደ ሮቤል÷ ቆሬ ደግሞ ከነገደ ሌዊ እግዚአብሔር በመረጣቸው በሙሴና በአሮን ላይ በሥጋዊ ቅንዓት በመነሣሣት አድማ መቱ:: ዳታንና አቤሮን የታላቁ የሮቤል ልጆች በመሆናችን የሙሴ ምሥፍና ይገባናል አሉ:: ከዚህም የተነሣ በተጥባበ ሥጋ ለያይቶ ለመምታት የሙሴን ምሥፍና የተቀበሉ መስለው÷ «የአሮን ክህነት ይገባናል» በማለት ከሙሴ ዳኝነት ጠየቁ:: ይኽውም የአሮንን ክህነት በእጃቸው ካስገቡ በኋላ የሙሴን ምሥፍና ለመንጠቅ ነበር:: ሙሴ ግን እነ ቆሬን «እግዚአብሔር የመረጠውን ያስታውቅ፤» ብሎ ከአሮን ጋር ወደ መገናኛው ድንኳን አሰናበታቸው:: ዳታንና አቤሮን ደግሞ ወደ እርሱ እንዲመጡ መልእክተኞችን ቢልክባቸው ከሥርዓት ውጭ «አንመ ጣም» ብለው መለሱለት:: በመጨ ረሻም የእግዚአብሔር ፍርድ በሥርዓተ አልበኞቹ ላይ ተገለጠ:: ሙሴ አስቀ ድሞ በተናገረው መሠረት መሬት ተከፍታ እስከነ ቤተሰቦቻቸው÷ እስከነ ዕቃዎቻቸው ዋጠቻቸው:: ያጥኑ የነበሩትንም ሁለት መቶ ኀምሳ ሰዎች እሳት ከሰማይ ወርዳ አቃጠለቻቸው::

በዚህን ጊዜ ከሕዝቡ የሚጠበቀው እግዚአብሔርን መፍራት÷ ሙሴንና አሮንን ማክበር ነበር:: ነገር ግን የተገላቢጦሽ በሙሴና በአሮን ላይ አጕረመረሙ:: ለዐመፀኞቹ ጥብቅና ቆመው ተጣሏቸው:: ወዲያው የእውነት ዳኛ እግዚአብሔር ክብሩን በደመና ገልጦ ድምፁን በማሰማት ቁጣው በሕዝቡ ላይ እንደ እሳት መንደዱን ለወዳጁ ለሙሴ ነገረው:: ሙሴ ግን እንደ ተጣሉኝ ልጣላቸው አላለም÷ ክፉን በክፉ አልመለሰም:: ወንድሙን አሮንን ጠርቶ:- «ጥናህን ውሰድ÷ ከመሠዊያውም ላይ እሳት አድርግበት÷ዕጣንም ጨምርበት÷ ወደ ማኅበሩም ፈጥነህ ውሰደው÷ አስተስርይላቸውም፤ ከእግዚአብሔር ፊት ቁጣ ወጥቶአልና÷ መቅሠፍት ጀምሮአል፤» አለው:: አሮንም ፈጥኖ ሙሴ እንደ ነገረው አደረገ:: መቅሠፍቱም ቆመ:: እርሱም በሙታንና በሕያዋን መካከል ቆመ:: በቆሬም ምክንያት ከሞቱት ሌላ በመቅሠፍቱ የሞቱት ዐሥራ አራት ሺህ ሰባት መቶ ነበሩ:: ዘኁ.16÷1-50:: የዛሬዎቹም ምእመናን ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን በተመለከተ ከማን ጋር መቆም እንዳለብን ይህ ትልቅ ትምህርት ነው:: ሳናውቀው እንደ እስራኤል ዘሥጋ ለዐመፀኞቹ ጥብቅና እንዳንቆም መጠንቀቅ አለብን::

ከሙሴ በኋላ እስራኤል ዘሥጋን ወደ ምድረ ርስት የመራ ኢያሱ ወልደ ነዌ ነው:: በሙሴ እግር እስኪተካ ድረስ የሙሴ አገልጋይ ነበር:: ከልጅነት ጀምሮ ዝቅ ብሎ በማገልገሉ ከፍ ብሏል:: ለዚህም ነው እግዚአብሔር:- «በሕይወትህ ዕድሜ ሁሉ ማንም አይቋቋምህም፤ ከሙሴ ጋር እንደሆንሁ እንዲሁ ከአንተ ጋር እሆናለሁ፤ አልጥልህም÷ አልተውህም:: ለአባቶቻቸው እሰጣችኋለሁ ብዬ የማልሁላቸውን ምድር ለዚህ ሕዝብ ታወርሳለህና ጽና አይዞህ:: ነገር ግን ጽና÷ እጅግ በርታ፤ ባሪያዬ ሙሴ ያዘዘህን ሕግ ሁሉ ጠብቅ÷ አድርገውም፤ በምትሔድበትም ሁሉ እንዲከናወንልህ ወደ ቀኝም ወደ ግራም አትበል:: የዚህ ሕግ መጽሐፍ ከአፍህ አይለይ÷ ነገር ግን የተጻፈበትን ሁሉ ትጠብቅና ታደርግ ዘንድ በቀንም በሌሊትም አስበው፤ የዚያን ጊዜም መንገድህ ይቀናልሃል፤ ይከናወንልሃልም::» ያለው:: ኢያ.1÷5-8::

እግዚአብሔር ለኢያሱ የነገረው ከሙሴ በተማረውና ባየው እምነትና ሥርዓት እንዲጓዝ ነው:: በመሆኑም ኢያሱ በሁሉ መምህሩን ሙሴን መሰለ:: አስቀድሞም ቢሆን መንፈሳዊ አባቱ ሙሴ:- «አምላክህ እግዚአብሔር ከአንተ መካከል ከወንድሞችህ እንደ እኔ ያለ ነቢይ ያስነሣልሃል፤ እርሱንም ታደምጣለህ::» በማለት በሕዝቡ ፊት ተናግሮለታል:: ይኽም ነገር ከእግዚአብሔር መሆኑን አስረግጦ ሲናገር:

- «እግዚአብሔርም አለኝ:- የተናገሩት መልካም ነው፤ ከወንድሞቻቸው መካከል እንደ አንተ ያለ ነቢይ አስነሣላቸዋለሁ፤ ቃሌንም በአፉ አደርጋለሁ÷ ያዘዝሁትንም ቃል ሁሉ ይነግራቸዋል፤ በስሜም የሚናገረውን ቃልን የማይሰማውን ሰው ሁሉ እበቀለዋለሁ::» ብሏል:: ዘዳ.18÷16-19::

ለምሳሌ ኢያሱ እንዴት ሙሴን እንደ መሰለው ብንመለከት የነገራችንን እርግጠኝነት ፍንትው አድርጎ ያሳይልናል:: የነቢያት አለቃ ሙሴ በደብረ ሲና ራስ እግዚአብሔር በሠራለት ሥርዓት መሠረት በቅድስናው ሥፍራ ጫማውን አውልቆ ለእግዚአብሔር የባሕርይ ስግደት ሰግዷል:: ዘጸ.3÷5:: ኢያሱም ከእግዚአብሔር የተላከ የእግዚአብሔር ሠራዊት አለቃ ቅዱስ ሚካኤል ባስተማረው መሠረት በቅድስናው ስፍራ ጫማውን አውልቆ ለመልአኩ የጸጋ ስግደት ሰግዷል:: ኢያ.5÷13-15:: የነቢያት አለቃ ሙሴ እግዚአብሔር ባዘዘው መሠረት ባሕረ ኤርትራን በበትሩ ከፍሎ ሕዝቡን በደረቅ አሻግሯል:: ዘጸ. 14÷15-31:: ኢያሱም እግዚአብሔር ባዘዘው መሠረት ካህናቱ ባከበሩት የእግዚአብሔር ታቦት ኃይል ዮርዳኖስን ለሁለት ከፍሎ ሕዝቡን በደረቅ አሻግሯቸዋል:: መጽ.ኢያሱ ምዕ.3÷4፤ ይህ ተአምር ከመፈጸሙ በፊት እግዚአብሔር ኢያሱን:- «ከሙሴ ጋር እንደ ሆንሁ እንዲሁ ከአንተ ጋር መሆኔን ያውቁ ዘንድ በዚህ ቀን በእስራኤል ሁሉ ዐይን ከፍ ከፍ አደርግህ ዘንድ እጀምራለሁ:: አንተም የቃል ኪዳኑን ታቦት የሚሸከሙትን ካህናት:- በዮርዳኖስ ውኃ ዳር ስትደርሱ በዮርዳኖስ ውስጥ ቁሙ ብለህ እዘዝ::» ብሎት ነበር:: ኢሳ.3÷7-8:: ከዚህ የምንማረው ከአባቶቻችን ጋር የነበረ እግዚአብሔር ከእኛም ጋር የሚሆነው በአባቶቻችን እምነትና ሥርዓት ስንኖር ብቻ ነው:: እምነት ከዘመን ጋር የሚለዋወጥ አይደለም:: ሥርዓትም ቢሆን የእምነት መገለጫና መጠበቂያ ስለሆነ ወደ ፈቃደ ነፍስ ያዘነበለ እንጂ ልቅ ወደ ሆነ ማቆሚያም ወደ ሌለው የሥጋ ፈቃድ ማዘንበል የለበትም::

እግዚአብሔር ለኢያሱ በእምነት ሊጠብቀው የሚገባውን ሥርዓት በየጊዜው ይሠራለት ነበር:: ለምሳሌ:- የኢያሪኮን ከተማ ከመያዛቸው በፊት:

- «ተመልከት÷ ኢያሪኮንና ንጉሥዋን ጽኑዓን ኃያላንዋንም በእጅህ ሰጥቼአለሁ:: ሰልፈኞቻችሁ ሁሉ ከተማይቱን አንድ ጊዜ ይዞሩአት÷ እንዲሁም ስድስት ቀን አድርጉ:: ሰባትም ካህናት ሰባት ቀንደ መለከት በታቦቱ ፊት ይሸከሙ፤ በሰባተኛውም ቀን ከተማይቱን ሰባት ጊዜ ዙሩ÷ ካህናቱም ቀንደ መለከቱን ይንፉ:: ቀንደ መለከቱም ባለመቋረጥ ሲነፋ÷ የመለከቱንም ድምፅ ስትሰሙ÷ ሕዝቡ ሁሉ ታላቅ ጩኸት ይጩኹ፤ የከተማይቱም ቅጥር /የግንብ አጥር/ ይወድቃል፤» ብሏቸዋል:: ኢያ.6÷2-5:: በዚህ ኃይለ ቃል ውስጥ እግዚአብሔር በቁጥር እየወሰነ ያስተ



www.eotcmk.org

ላለፋቸው ትእዛዛት ሁሉ ለአንድ የድርጊት አፈጻጸም ልክና መጠን ያለው መሆኑን ያሳያል፡፡ ኢያሱም ሆነ ሕዝቡ እግዚአብሔር የሠራላቸውን ሥርዓት ምክንያት ሳያበዙ በጥንቃቄ በመጠበቃቸው የተባለው ሁሉ ተፈጽሞላቸዋል፡፡

ከዚህም ጋር «እናንተ ግን እርም ካደረጋችሁት በኋላ እርም ከሆነው ነገር ራሳችሁን ጠብቁ፤ እርም ከሆነው አንዳች የወሰዳችሁ እንደ ሆነ የእስራኤልን ሰፈር የተረገመ ታደርጉታላችሁ÷ ታስጨንቁትማላችሁ፡፡ ነገር ግን ብርና ወርቅ ሁሉ የናስና የብረትም ዕቃ ለእግዚአብሔር የተቀደሰ ይሁን፤ ወደ እግዚአብሔርም ግምጃ ቤት ይግባ፡፡» ተብለው ነበር፡፡ ይህም እግዚአብሔር የሠራላቸው ሥርዓት ነው፡፡ ነገር ግን ከስንዴ መካከል እንክርዳድ ስለ ማይጠፋ ከይሁዳ ወገን የሆነ አካን ከሥርዓቱ ውጪ እርም ከሆነው ነገር ወሰደ፤ በእርሱም ምክንያት የእግዚአብሔር ቁጣ በእስራኤል ልጆች ላይ ነደደ፡፡ ከዚህ የተነሣ ሕዝቡ በጠላቶቻቸው ፊት መቆም ተሳናቸው፡፡ በዚህን ጊዜ ኢያሱ ከጧት እስከ ማታ ከእስራኤል ሽማግሌዎች ጋር በታቦቱ ፊት እየሰገደ ምክንያቱን ከእግዚአብሔር ቢጠይቅ «እሥራኤል በድሎአል፤ ያዘዝኋቸውንም ቃል ኪዳኔን አፍርሰዋል፤ እርም የሆነውን ነገር ወሰዱ÷ሰረቁም÷ ዋሹም÷ በዕቃቸውም ውስጥ ሸሸጉት፡፡ ስለዚህም የእሥራኤል ልጆች በጠላቶቻቸው ፊት መቆም አይችሉም፡፡ የተረገሙ ስለሆኑ በጠላቶቻቸው ፊት ይሸሻሉ፤ እርም የሆነውንም ነገር ከመካከላችሁ ካላጠፋችሁ ከዚህ በኋላ ከእናንተ ጋር አልሆንም፡፡ ተነሣና ሕዝቡን ቀድስ፤» የሚል መልስ አግኝቷል፡፡ ኢያ.6÷18፤7÷6–12፡፡ አንዳንድ ሰዎች በማወቅም ይሁን ባለማወቅ ዋናው እምነት እንጂ ሥርዓት አያጸድቅም ይላሉ፡፡ ይህም ሰውን በመጀመሪያ ከሥርዓቱ ቀጥሎም ከእምነቱ ለመለየት የታቀደ የሰይጣን ደባ ነው፡፡ አካን እኮ! ሥርዓቱን ተላለፈ እንጂ እምነቱን አልካደም፡፡ ታድያ እግዚአብሔር ለምን ተቆጣ?

የሊቀ ካህናቱ የአሮን ልጆች ናዳብና አብድዩ በክህነት እንዲያገለግሉ ከአባታቸው ጋር ተመርጠው ተቀብተው የተሾሙ ናቸው፡፡ ፃመረጣቸውም እግዚአብሔር ነው፡፡ «አንተም ወንድምህን አሮንን ከእርሱም ጋር ልጆቹን ከእሥራኤል ልጆች መካከል ለይተህ ካህናት ይሆኑልኝ ዘንድ ወደ አንተ አቅርብ፤» እንዲል፡፡ ዘጸ.28÷1 ይኸውም በእምነት የቤተ መቅደሱን ሥርዓት እየጠበቁ እግዚአብሔርን እንዲያገለግሉ ነው፡፡ እነርሱ ግን በየራሳቸው ጥናውን ወስደው እግዚአብሔር ባላዘዘው በሌላ እሳት ዕጣን አጠኑ፡፡ ሥርዓቱን ባለመጠበቃቸውም እግዚአብሔር ተቆጣባቸው፡፡ እሳትም ከእግዚአብሔር ፊት ወጥቶ ስለ በላቸው በእግዚአብሔር ፊት ሞቱ፡፡ ዘሌ.10÷1፡፡ ምክንያቱም ካህንም ይሁን ምእመን ለስንፍናው መሸፈኛ፤ ለሥጋው እንዲመቸው? ሥርዓት ቢተላለፍ ይቀጣልና፡፡

የዔሊ ልጆችም በቤተ መቅደስ እግዚአብሔርን እንዲያገለግሉ ተመርጠው ነበር፡፡ እነርሱም የቤተ መቅደሱን ሥርዓት የማይጠብቁ ዓመፀኞች ሆኑ፡፡ በመገናኛው ድንኳን ደጅ የሚያገለግሉትን ሴቶች እያታለለ በቅድስናው ሥፍራ ከእነርሱ ጋር ያመነዝሩ ነበር፡፡ ከላይ እንደ ገለጥነው ሰው ለእግዚአብሔር ቤት ሥርዓት ግድ የለሽ ከሆነ ለእምነቱም እንደዚያው ነው፡፡ ለዚህም ነው፡– «የዔሊም ልጆች ምናምንቴዎች ነበሩ፤ እግዚአብሔርንም አያውቁም ነበር፡፡» የተባለባቸው፡፡ 1ኛሳሙ.2÷11፤22፡፡ የናዳብን እና የአብድዩን ሥርዓተ አልበኝነት ያጋለጠው ሕዝቡ ነው፡፡ ዛሬም የሚያስፈልገው እንዲህ ዓይነት ሕዝብ ነው፡፡ አባታቸው ዔሊ «ስለ ክፉ ሥራችሁ ከዚህ ሕዝብ ሁሉ ሰምቻለሁና ስለ ምን እንዲህ ያለ ነገር ታደርጋላችሁ? ልጆቼ ሆይ ÷የእግዚአብሔርን ሕዝብ ኃጢአተኛ በማድረጋችሁ ስለ እናንተ የደረሰኝ ወሬ መልካም አይደለምና ይህ አይሆንም፡፡ ሰውስ ሰውን ቢበድል እግዚአብሔር ይፈርድበታል፤ ሰው ግን እግዚአብሔርን ቢበድል /እግዚአብሔርን ቢደፍር/ ስለ እርሱ የሚለምን ማን ነው?» እያለ ቢመክራቸውም ቃሉን አልሰሙትም፡፡ 1ኛሳሙ.2÷23–25፡፡ በዚህ ምክንያት ዔሊ ልጆቹን በእግዚአብሔር ስም አውግዞ ከእግዚአብሔር ቤት ባለመለየት «ከእኔ ይልቅ ልጆችህን ለምን አከበርህ?» ተባለ÷ታላቅ ተግሣጽም ደረሰበት፡፡ 1ኛሳሙ.2÷26–36፡፡ በተግሣጹም መሠረት ልጆቹ አፍኒን እና ፊንሐስ በአንድ ምክንያት በጦርነት ላይ ሞቱ፡፡ እርሱም ከወንበር ወድቆ÷አንገቱ ተቆልምሞ ሞተ፡፡ 1ኛሳሙ.4÷1–22፡፡ በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ ተመክሮ የማይመለሰውን ወይም ለይምሰል ተመልሻለሁ፤ ብሎ በውስጥ የሚያደባውን ሰው ÷ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «እኔ ምንም እንኳ በሥጋ ከእናንተ ጋር ባልሆን÷ በመንፈስ ከእናንተ ጋር ነኝ÷ ከእናንተም ጋር እንዳለሁ ሆኜ ይህን እንዲዚህ በሠራው ላይ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አሁን ፈርጄበታለሁ፤ እናንተና መንፈሴም ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ኃይል ጋር ተሰብስበን÷መንፈሱ በጌታ በኢየሱስ ቀን ትድን ዘንድ እንደዚህ ያለው ለሥጋው ጥፋት ለሰይጣን እንዲሰጥ ፍርዴ ነው፡፡» እንዳለ አውግዞ መለየት ግድ ነው፡፡ 1ኛቆሮ.5÷3–5፡፡

ንጉሡ ዖዝያን የቤተ መንግሥት ሰው ነው፤ የቤተ ክህነት ሰው አይደለም፤ ሥልጣነ ክህነት የለውም፡፡ ወደ ቤተ መቅደስ ገብቶ ያጥን ዘንድ ሥርዓቱ አይፈቅድለትም፡፡ ነገር ግን በድፍረት ለማጠን ገባ፡፡ ካህኑ አዛርያስ ከእርሱም ጋር ጽኑዓን የነበሩ ሰማኒያ የእግዚአብሔር ካህናት ተከትለው ገቡ፡፡ ንጉሡንም ዖዝያንን እየተቃወሙ «ዖዝያን ሆይ÷ ዕጣን ማጠን የተቀደሱት የአሮን ልጆች የካህናት ሹመት ነው እንጂ ለእግዚአብሔር ታጥን ዘንድ አይገባህም፡፡ በድለሃልና ከመቅደሱ ውጣ÷ ከአምላክህም ከእግዚአብሔር ዘንድ ክብር አይሆንልህም» አሉት፡፡ ዖዝያን ተቆጣ፡፡ የሚያጥንበትም በእጁ ነበረ፡፡ ካህናቱንም በተቆጣ ጊዜ በካህናቱ ፊት በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ በዕጣኑ መሠዊያ አጠገብ ሳለ በግንባሩ ላይ ለምፅ ታየ፡፡ ...ፈጥነውም አባረሩት፡፡ እርሱ ደግሞ እግዚአብሔር ቀስፎት ነበርና ይወጣ ዘንድ ቸኰለ፤ የልቡ ትዕቢት ስላለቀቀውም እስኪ ሞት ድረስ ከለምፁ አልነጻም፡፡ 2ኛዜና.26÷16–21፡፡ የቤት ሳሚስ ሰዎችም እንዲሁ እንደ ዖዝያን ባለ ድፍረት ተይዘው ወደ እግዚአብሔር ታቦት ውስጥ በመመልከታቸው በሞት ተቀሥፈዋል፡፡ 1ኛሳሙ 6÷19፡፡ ዖዛም ታቦተ እግዚአብሔርን በመንካቱ የእግዚአብሔር ቁጣ እንደ እሳት ነደደበት÷ተቀሥፎም ሞተ፡፡ የናቡከደነፆር ልጅ ብልጣሶር ደግሞ በቤተ መቅደሱ መገልገያ ንዋያተ ቅድሳት ሥጋዊ መብልን በመብላቱና ሥጋዊ መጠጥን በመጠጣቱ በቤተ መንግሥቱ ግድግዳ ላይ ስትጽፍ በተገለጠች እጅ ከተገሠጸ በኋላ የአንድ ቀን ዕድሜ እንኳን አጥቶ ሌሊቱኑ በሞት ተወስዷል፡፡ ዳን.5÷1–31፡፡ ንጉሡ ሳዖልም ነቢዩ ሳሙኤል የሠራለትን የመሥዋዕት ሥርዓት ባለመጠበቁ «እግዚአብሔር ያዘዘህን ትእዛዝ አልጠበቅህምና መንግሥትህ አይጸናም፡፡» ተባለ፡፡ 1ኛሳሙ. 13÷8፡፡ አማሌቃውያንን አጥፋ በተባለም ጊዜ በተሠራለት ሥርዓት ሳይሆን በራሱ አሳብ ስለ ተጓዘ እግዚአብሔር ናቀው÷ የእግዚአብሔር መንፈስ ተለየው÷ርኩስ መንፈስም ተቆራኝቶት ተሠቃየ፡፡ 1ኛሳሙ.15÷16፡፡

*ይቀጥላል፡፡*



www.eotcmk.org

*ውድ አንባብያን፤ ባለፈው እትም ትምህርት መስጠት በጀመርንበት በዚህ ርዕስ «የውዳሴ ማርያም የትመጣ» በሚል ንዑስ ርዕስ የእመቤታችን የምስጋና መጽሐፍ የሆነውን /ውዳሴ ማርያም/ መጽሐፍ ቅዱስ ኤፍሬም የተባለ የነገረ መለኮት ምሁር በአራተኛው መ.ክ.ዘ መገባደጃ ላይ እንደ ደረሰው፤ ይኸው መጻሐፍ በዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት ከዐረብኛ ወደ ግእዝ እንደ ተተረጐመ፤ በሰባቱ ዕለታት÷በ64 ንዑሳን አናቅጽ ተከፋፍሎ በኢትዮጵያውያን ሊቃውንት እንደ ተደራጀና ዛሬ የእመቤታችን ፍቅር የበዛላቸው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን በጸሎት መጽሐፍነት እንደሚገለገሉበት ዐይተናል:: ከዚያም ከተያዘው ርዕስ አንጻር ምሥጢረ ሥጋዌን የያዘውንና የድርሰቱ የመጀመሪያ የሆነውን ዘር ተንትነን አቁመናል:: በዚህ እትም ደግሞ ካቆምንበት ቀጥለን ያለውን ትምህርት እናቀርባለን:: መልካም ንባብ::*

*|መምህር ኃይለ ማርያም ላቀው/*

እክት አንድ አንዱን እየሰደደ በማኅፀን ሳሉ ዕንሱን ይቆራኘው ነበር:: ዕንሱ የማኅፀን ቆይታውን ፈጽሞ ሲወለድ በዚህ ዓለም ኃጢአት ሲያሠራው ባየት ሲያስ መልከው ይኖርና በመጨረሻ ሲሞት ክፉ መልኩን አሳይቶ ያስደነግጠዋል:: ያን ጊዜ ነፍሱ ከሥጋው ትለያለች:: በዚያን ጊዜ ሥጋን በመቃብር ነፍስን በሲኦል ተቆራኝቶ ይኖር ነበር:: ቃለ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ለዚህ ሁሉ ቁራኝነት አልተመቸውም:: ምክን ያቱም የጌታችን ዕንሰቱ እንበለ ዘርዐ ብእሲ ያለወንድ ዘር በመንፈስ ቅዱስ ነው::

# ምሥጢረ ሥጋዌ በውዳሴ ማርያም

## ክርስቶስ ለምን አዘነ?

ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እከብር አይል ክቡር፣ እጸድቅ አይል ጻድቅ፣ እነግሥ አይል ንጉሥ ነው:: የተገዢ የአዳምን ሥጋ ለብሶ ማዘን መተከዝ ለምን አስፈለገው? በርግጥ እግዚአብሔር በባሕርይው ኀዘን የለበትም:: ያዘኑትን የተከዙትን ከኀዘናቸው የሚያረጋጋ አምላክ ነው:: ታድያ የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ተገልጸው ሲነበቡ ብዙ የሚያሳዝኑ ቃላትን እናነባለን:: ለምሳሌ መንገድ በመሔድ ደከመ፣ ተራበ፣ ተጠማ፣ አዘነ÷ ተከዘ የሚሉ ቃላትን ስንመለከት እሱ አምላክ ሲሆን ለምን አዘነ? ለምንስ ተከዘ? ማለታችን አይቀርም:: ክርስቶስ በዚህ ዓለም የተገዥ የአዳምን ሥጋ ለብሶ ማዘኑ መተከዙ ጥበብ እንጂ በባሕርይው ኀዘን የሚስማማው ሁኖ አይደለም::

### 1. በተዋሕዶ ሰው ስለሆነ

እግዚአብሔር ለቅዱሳን መላእክት ያላደረገውን ለሰው ልጅ አድርጓል:: የእኛን ሥጋ ነሥቶ ሊቃነ መላእክት እንዲሰግዱለት አድርጓልና:: ከዚህ የሚልቅ ክብር የለም:: ቅዱስ ጳውሎስ «የአብርሃምን ዘር ይዟል እንጂ የያዘው የመላእክትን አይደለም» እንዳለ:: ዕብ.2÷16:: ክርስቶስ የተገዥ የአዳምን ባሕርይ ገንዘብ ስላደረገ በዚህ ዓለም ከኃጢአት በስተቀር በልደት፣ በሕማምና በሞት አዳምን መስሏል:: ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በልደቱም ሆነ በዕድገቱ ግዕዘ ሕፃናትን አላፋለሰም:: በለበሰው ሥጋ ዘመን የማይቆጠርለት መለኮት ዘመን ተቆጥሮለታል:: «ሁለት ዓመት» ሲሞላው ከእናቱ ጋር ወደ ቤተ መቅደስ ተጉዟል:: እንደዚሁም በጥበብና በቁመት፣ በሞገስም በእግዚአብሔርና በሰው ፊት ያድግ እንደ ነበር ተነግሯል:: ሉቃ.2÷52:: ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያንም ግዕዘ ሕፃናትን አለማፋለሱን እንዲህ በማለት ይገልጹታል:: «በበህቅ ልሕቀ በሠላሳ ክረምት እም ኀበ ዮሐንስ ተጠምቀ፤ ቀስ በቀስ አደገ፤ ሠላሳ ዘመን ሲሞላው ከዮሐንስ ዘንድ ተጠመቀ::» ቅዳሴ ዲዮስቆሮስ ጌታችን÷ አምላክ ነኝና ዕለቱን ተወልጄ ዕለቱን ልደግ አላለም:: ይህም ከእኛ ጋር ያመሳስለዋል:: የእኛን ሥጋ ለብሶ በዚህ ዓለም ሲመላለስ መንገድ በመሔድ መድከሙ፣ መራቡ፣ መጠማቱ ተጽፏል:: ዮሐ.4÷16፤ ማር.11÷12:: ለደካሞች ኃይላቸው በለበሰው ሥጋ መድከሙ፣ የተራቡት ምግባቸው መራቡ፣ ለተጠሙት መጠጣቸው መጠማቱ፣ ለታመሙት፣ ፈዋሻቸው በሥጋ መታመሙ፣ ለመዋትያን ትንሣኤቸው እርሱ በሥጋ መሞቱ ከእኛ ጋር አመሳስሎታል:: «በነገር ሁሉ ወንድሞቹን ሊመስል ተገባው» ተብሎ እንደ ተጻፈ:: ዕብ.2÷17:: ሊቁ ቅዱስ ኤፍሬምም የሐዋርያውን መልእክት ሲያጠናክር:–«ወረሰየነ ዕሩያነ ምስሌሁ በብዝኃ ኂሩቱ፤ በቸርነቱ ብዛት እንድ ንመስለው አደረገን» ብሏል:: እዚህ ላይ እርሱ እኛን በሕማም በሞት እንደ መሰለን እኛም በግብር ከመሰልነው የክብሩ ተካፋይ እንደ ምንሆን ደግሞ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ሲያስረዳ እንዲህ ይላል:– «እምከመ ዐረይነ ሕማም ንኤሪ ክብረ ምስሌሁ፤ የመከራው ተካፋይ ከሆን የክብሩ ተካፋይ እንሆናለን::» ሮሜ.6÷5:: በመለኮቱ ግን የማይራብ፣ የማይጠማና የማይሞት ኃያል አምላክ መሆኑን ልብ ይሏል:: «በሥጋ ሞተ፣ በመንፈስ ግን ሕያው ሆነ» እንዲል:: 1ኛ ጴጥ. 3÷19::

### የዲያብሎስን ጥበብ በጥበቡ ለመሻር

«ወበከመ ተኀብአ ሰይጣን በጉህሉቱ ውስተ ሥጋ ከይሲ ከማሁ ድኅነትነ ኮነ በተሰውሮተ ቃለ እግዚአብሔር በዘመድነ፤ ሰይጣን በተንኰሉ በሥጋ ከይሲ እንደ ተሰወረ ደኅንነታችን ዘመዳችን በምትሆን /በድንግል ማርያም/ ቃለ እግዚአብሔር በመሰወር ተከናወነ::» ጥንተ ጠላታችን ዲያብሎስ የእባብን ሥጋ ለብሶ የሰውን ዘር ሁሉ ጐድቷል:: ዘፍ. 3÷1–8:: አካላዊ ቃልም የአብርሃም ዘር ከምትሆን ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋን ከነፍሷ ነፍስን በመዋሐድ በትሩፋቱ ሰውን ሁሉ አድኗል:: የሰይጣንን ሥራ ለማፍረስ ሰይጣንን ወደ ራሱ አቅርቦታል::

### ለአቅርቦተ 'ሰይጣን /ሰይጣንን ለማቅረብ/

ቅድመ ሥጋዌ ሴቶች ሲፀነሱ በዘር ምክንያት ዲያብሎስ ከርኩሳን መላ ሉቃ.1÷35:: «አምላኬ÷ አምላኬ÷ ስለምን ተውኸኝ?» /ማቴ.27÷46/ በማለት ያዘነ የተከዘ መስሎ ሰይጣንን ወደ ክቡር መስቀሉ ካቀረበው በኋላ «አባ አመኃፅን ነፍስዬ ውስተ እዴከ፤ አባት ሆይ÷ ነፍሴን በእጅህ እሰጣለሁ» በማለት ነፍሱን ከሥጋው በገዛ ሥልጣኑ ባስረከበ ጊዜ ሰይጣንን የለመደውን መንገድ ለውጦበታል:: ይህም ለአብነት ነው:: እርሱ ነፍስን የሚቀበል አምላክ በመሆኑ ነፍሳችሁን ለታመነ ፈጣሪ አደራ ስጡ ሲል ነው:: ይህን በማድረጉ በሰው ልጆች ዘንድ ለዘመናት ነግሦ የነበረውን መርገመ ሥጋንና መርገመ ነፍስን አስቀርቶልናል:: ሊቁም «ወሰአረ እምኔነ መርገመ፤ ከእኛ መርገምን አጠፋልን::» በማለት በተዋሕዶ የተፈጸመውን የድኅነት ሥራ ግልጽ አድርጐልናል::

ሰይጣንን አቅርቦ እኩይ ሥራውን የማክሸፍ ተግባር በስሙም ሆነ በመልካም ግብሩ የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ የሆነው ነቢየ እግዚአብሔር ኢያሱ የፈጸመው ገድል ተጠቃሽ ነው:: ይኸውም ፈሪ መስሎ የጋይን ንጉሥ ድል ያደረገበት የውጊያ ስልት ክርስቶስ ሰይጣንን አቅርቦ ድል ለማድረጉ ምሳሌ ነው:: ኢያ.8÷1-30:: ነቢየ እግዚአብሔር ኢያሱ ለጋይ ንጉሥ ፈሪ መስሎ ታይቷል:: ዳሩ ግን ፈሪ መስሎ የተገመተው ኢያሱ ጠላቱን ማርኮ በመስቀል ሰቅሎታል:: ክርስቶስም «ነፍሴ አዘነች» በማለት ሞትን የፈራ መስሎ ለዲያብሎስ ቢታየው «ይህማ ፍጡር ነው፤ ሥጋውን በመቃብር ነፍሱን በሲኦል ልቆራኝ» ብሎ ሲመጣ ሁሉን ቻይ የሆነው አምላክ በነፋስ አውታር ወጥሮ በእሳት ዛንጀር አስሮ ይዞ ከእግረ መስቀሉ ቀጥቅጦታል::

### ለአጽድቆተ ትስብእት /ፍጹም ሰው መሆኑን ለማጠየቅ/

«ዳግመኛ ነፍሴ ለሞት እስከ መድረስ ደርሳ አዘነች፤ ዳግመኛ አባቴ ሰውነቴን ከዚች ሰዓት አድናት እላለሁ እንጂ ምን እላለሁ፤ ነገር ግን ስለዚህ ሰው



www.eotcmk.org

ሆንኩ፤ ከዚህችም ሰዓት ደረስኩ» በማለት /ማር.14÷34-36፤ ዮሐ.12÷27/ ወደ ባደረገው ሐዘንም ፍጹም ሰው መሆኑን አስረድቷል። ስለ እኛ በታመመው ሕመም የእኛን ነፍስ የምትመስል ነባቢት ነፍስን እንደ ተዋሐደ ለማጠየቅ «ነፍሴ ከሥጋዬ እስከ መለየት ደርሳ አዘነች» በማለት ተናገረ። ይኸውም የነፍሳችንን ሕመም በእውነት ወዶ መቀበሉን ልብ ይሏል። የነፍስ ሕመም የሚባሉት ሁከት፣ ትካዜ የልብ ኀዘን የመሳሰሉት ናቸው። ሃይማኖተ አበው ዘጎርጎርዮስ 6÷11።

በሌላም በኩል «ነፍሴ ለሞት ደርሳ አዘነች» የሚለው ቃል፣ «ነፍስ አልነሳም» የሚሉ የመናፍቃንን የክህደት ትምህርት ያከሸፈ ቃል ነው። «ነፍስ አልነሳም የሚል እንዲህም የሚክድ ነፍሴ እስከ ሞት ድረስ አዘነች ያለውን የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ቃል ሰምቶ ይፈር።» እንዳለ ቅዱስ አግናጥዮስ። ሃይማኖተ አበው ዘአግናጥዮስ 19÷16። መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከቅድስት ድንግል ማርያም ነፍስን ባይነሳ ኖሮ «ነፍሴ እስከ ሞት ደርሳ አዘነች» ባላለ ነበር። ዳሩ ግን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ያሰማው ድምፅ ነፍስን መዋሐዱን የሚያመለክት ነው።

የነፍስን ሕመም በመታመሙ የሰውን ልጅ ውስጣዊ ሁከት አርቋል። «እርሱ ስለ እናንተ ያስባልና የሚያስጨንቃችሁን ሁሉ በእርሱ ላይ ጣሉ።» 1ኛጴጥ.5÷6። ቅድመ ኀዘነ ክርስቶስ የነበሩ ሰዎች ሞትን በመፍራት ወርቃቸውን ለክብራቸው መግለጫ፣ እህላቸውን ለክፉ ቀን ማለፊያ እና ልብሳቸውን ደግሞ «ስናረጅ እንለብሰዋለን» በማለት በስጋት ይኖሩ ነበር። ዛሬ ግን ክርስቲያኖች እውነተኛ የእግዚአብሔር ቤተሰቦች ጥንት የነበረባቸውን የስጋት ካባ አውልቀው በመጣል «እም ከመ ረከብነ ሲሳየነ ወአራዘነ የአክለነ፤ ሠርከ ኀብስትና የዓመት ልብስ ካገኘን ይበቃናል» ወደ ሚለው ውስጣዊ ደስታ ወደ ሚገኝበት ምዕራፍ ተሸጋግረዋል። 2ኛጢሞ.6÷8።

ሞትንም በመፍራት ዛሬ ብንኖር «ነገ ሟች ነን፤ አፈር ይበላናል። በስብሰን እንቀራለን» ይሉ ነበር። ዛሬ ግን ያ ሁሉ ሰቀቀን ቀርቶ የእግዚአብሔር ወዳጆች የሆኑ ቅዱሳን በልበ ሙሉነት «ልሔድ ከክርስቶስ ጋር ልኖር እናፍቃለሁ፤ ከሁሉ ይልቅ እጅግ የሚሻል ነውና» የምንል ሆነናል። ቅዱስ ጳውሎስ «ልሔድ እናፍቃለሁ» ያለው የቅዱሳን ሞታቸው ዕረፍታቸው ስለሆነ ነው። አስጊና አሳዛኝ የነበረው የሞት ጉዳይ የሚናፈቅ ሆኗልና። ፊልጵ.1÷24። ቅዱስ ዳዊትም «ክቡር ሞቱ ለጻድቅ በቅድመ እግዚአብሔር ፤ የጻድቅ ሞቱ በእግዚአብሔር ዘንድ ክቡር ነው።» ብሏል። መዝ 111÷6።

## ወያግብዖ ኀበ ዘትካት መንበሩ /ወደ ቀደመ ቦታው ይመልሰው ዘንድ ወደደ/

አዳም ትእዛዝ በማፍረሱ ምክንያት ጥንተ ቤቱ ገነትን ትቶ ወጥቷል። አዳም ገነትን ብቻ ሳይሆን ያጣው የእግዚአብሔርንም ልጅነት ጭምር ነበር። አዳም ከሕገ እግዚአብሔር ውጭ ቢሆንም የእግዚአብሔር ጥበቃ አልተለየውም። በመሆኑም እግዚአብሔር ወደ ቀደመ ቦታው ይመልሰው ዘንድ ወዷል። አዳም የወጣባት ገነት በዋዛ አልተመለሰችም። እግዚአብሔር ዔደን ገነትን ሠርቶ አዳምን ካስገባበት ጥበቡ አዳምን ወደ ገነት የመለሰበት ጥበቡ ይልቃል። ይህ ጥበቡ እስከ መስቀል ሞት ድረስ ታዛዥ አድርጐታል። ሊቁም «ወገብረ ሰላመ ማእከሌነ በመስቀሉ÷በመስቀሉ በመካከላችን ሰላምን አደረገ» በማለት ጌታችን በሥጋ ያደረገውን የማስታረቅ ሥራ በውዳሴው አሳይቷል።

ከላይ እንደ ተጠቀሰው አዳም ገነትን ሲያጣ አብሮ በገነት የነበረውን ክብር አጥቷል። በገነት የነበረው ክብር የእግዚአብሔር ልጅነት ነው። ይህን ልጅነትንም አጥቶ ስለ ነበር የልጅነት ሥልጣኑን ይመልስላት ዘንድ ወደደ። ሊቁ በክርስቶስ የተገኘውን የመንፈስ ነጻነት እንዲህ በማለት ይገልጣል፡- «ወወሀብከነ መንፈሰ ልደት፤ ረቂቅ ልደትን ሰጠኸን።» ከረቂቅ ልደት ጋር በይቅርታውና በቸርነቱ አዳምን ወደ ቀደመ ቦታ ይመለሰው ዘንድ መውደዱን ደግሞ ሲገልጽ «ወያግቦእ ኀበ ዘትካት መንበሩ÷ ወደ ቀደመ ቦታው ይመልሰው ዘንድ ወደደ» በማለት መስክሯል።

የአዳም የቀደመ ቦታ ገነት ነበር። እግዚአብሔር ስለ ልዕልናው ሰማይ የሚባል ልዑለ ማኅደር እንዳዘጋጀ ሁሉ ከፍጥረታት ሁሉ አልቆ /ከፍ አድርጐ/ ለፈጠረው ሰው ደግሞ ገነትን አዘጋጀቶለታል። በእርግጥ እግዚአብሔር ስለ ልዕልናው በሰማይ ይኖራል ይባላል እንጂ እግዚአብሔር በቦታ የሚወሰን አይ ደለም። «ምሉዕ በኩለሄ» ነው። ገነትም ስለ ልዕልናዋ ሰማይ ትባላለች። ዳሩ ግን ገነት ከምድር ከፍ ከሰማይ ዝቅ ብላ እንደ ምትገኝ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን እማኝነት ይሰጣሉ።

ገነት በዚህ ዓለም ያለችና ያማሩ፣ ለዓይን ደስ የሚያሰኙ ዕፅዋት ይበቅሉባታል። ቀዳማዊ አዳም ያለምንም ተቀናቃኝ ለሰባት ድፍን ዓመታት ያህል ከግራ ጐኑ ከተፈጠረች ከሔዋን ጋር ኖረውባታል። አዳምና ሔዋን በገነት ቆይታቸው ወቅት ሰዎችን የሚያጐሳቁለው ረኀብና ጥም አላገኛቸውም። ለአካላቸው መሸፈኛም ከለላና ልብስ አልነበራቸ ውም። ልብሳቸው የእግዚአብሔር ጸጋ ነበርና። ምንም ልብስ ሳይለብሱ አይተፋፈሩም ነበር። በገነት መካከል ዕፀ ምግብ፣ ዕፀ በለስና ዕፀ ሕይወት የሚባሉ ሦስት ዓይነት ዕፀዋት ነበሩ። እነዚህም ለአዳምና ሔዋን በምግብነት የተፈቀዱና ያልተፈቀዱ ናቸው። የተፈቀዱትን ያለተቀናቃኝ እንዲመገቡ ያልተፈቀዱትን እንዳይመገቡ ተደንግጐባቸዋል።

ከሺህ ዓመት ቆይታ በኋላ አዳምና ሔዋን እንዲመገቧት የተዘጋጀችው ዕፀ ሕይወት ትሰኛለች። እግዚአብሔር ዕፀ ሕይወትን በተለየ መልክ በገነት ማብቀሉ ለሰው ልጆች ካለው የአባትነት ፍቅሩ የመነጨ ቸርነት ነበር። ዳሩ ግን አዳምና ሔዋን ዕፀ ሕይወትን ተመግበው ለመታደስ የነበራቸውን ዕድል በምክረ ከይሲ አበላሽተዋል።

እግዚአብሔር ሰውን የፈጠረው ለጉስቁልና ሳይሆን ለዘላለም በክብርና በቅድስና እንዲኖር ነበር። አዳም በየሺ ዓመቱ ከዕፀ ሕይወት ተመግቦ ከርጅናው ታድሶ እንዲኖር ነበር። ይሁንና በሰይጣን ምክር አቅራቢነት በሔዋን ሰባኪነት ተደልሎ እግዚአብሔር ወዳሰበለት ክብር ሳይደርስ ቀርቷል።

በሌላ በኩል ግን ዕፀ ሕይወትን ዳግመኛ እንድንበላ እንደ ተፈቀደልን ሊቀ ቅዱስ ኤፍሬም እንዲህ ይላል፤ «ከፈለነ ንብላዕ እምዕፀ ሕይወት ዘውእቱ ሥጋሁ ለክርስቶስ ወደሙ ክቡር በእንተ ፍቅረ ዚአነ መጽአ ወአድኃነነ፤ ዳግመኛ ከዕፀ ሕይወት እንበላ ዘንድ አደለን፤ ይኸውም እኛን ስለ መውደድ ሰው ሆኖ ያዳነን የክርስቶስ ክቡር ሥጋውና ደሙ ነው።» እዚህ ላይ ሊቁ ዕፀ ሕይወትን ሥጋ ወደሙ ብሎ እንደ ተረጐመ ልብ ይሏል።

ገነት ስትመሠረት ለአዳምና ሔዋን ከእርጅና በኋላ መታደሻ፣ የበቀለችው ዕፀ ሕይወት ሰውን ሕያው አድርጋ እንድ ታኖር እንደ ሆነ ከላይ የሰጠነው ትምህርት እማኝነት ይሰጠናል። በጥንተ ተፈጥሮ ዕፀ ሕይወትን ከእርጅና ለመታደስ ያበቀለ እግዚአብሔር በልዩ ጥበቡ ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን ቤዛ ይሆን ዘንድ ወደ ዚህ ዓለም ልኮ በዕፀ ሕይወት ፈንታ ሥጋ ወደሙን አዘጋጅቶልናል። «ሥጋዬን የበላ ደሜንም የጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው» ዮሐ. 6÷56 እንዲል።

አዳምና ሔዋን በፈጸሙት ስሕተት ዕፀ ሕይወትን በልተን ታድሰን እንዳንኖር አድርገውናል ብለን አናማርራቸውም። ቸርነት የባሕርይው የሆነ፣ በልግሥናዉ ንፍገት የሌለበት፣ ያልቅብኛል ብሎ የማይሰስት ቸሩ ፈጣሪ ያችን ዳግመኛ ዕፀ ሕይወት ሥጋ ወደሙን ተመግበን ለዘላለም በማታልፍ መንግሥቱ እንድንኖር ፈቅዶ ልናል።

ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ዕፀ ሕይወትን ከነገረ ሥጋዌ ጋር በማያያዝ ደገኛ ምሥጢር ያመሰጥራሉ። ታላቁ ሊቅ ሳዊሮስ ዕፀ ሕይወትን ትንሣኤ ብሎ ተርጉሞታል። ዕፀ ሕይወት ለአዳም ከእርጅና በኋላ መታደሻ እንደ ሆነች ሁሉ ትንሣኤም የድኅረ ሞት መታደሻ ሆኖ የተሰጠን የእግዚአብሔር ጸጋ በመሆኑ ሊቁ ከላይ የተጠቀሰውን ትርጓሜ ሊሰጠው ችሏል። እንዲሁም ማር ይስሐቅ ዕፀ ሕይወትን ፍቅር በማለት ይተረጉማል። ምክንያቱም ሥጋ ወደሙን በፍቅር ሆነን ካልተቀበልንና ታድሰን ካልተነሣን መንግሥተ ሰማያትን መውረስ ስለማይቻል ከላይ የተጠቀሱት ሊቃውንት ዕፀ ሕይወትን ከሥጋ ወደሙና ፍቅር ጋር አመሳጥረው ተርጉመዋል።

ገነት በሌላ አነጋገር ዓለመ ጻድቃን ትባላለች። ይህም ማለት በዚህ ዓለም ሳሉ ፈቃደ ሥጋቸውን ለፈቃደ ነፍሳቸው አስገዝተው በዚህ ዓለም ተድላ ሥጋን ሳይፈጽሙ በመንፈሳዊ አርበኝነት ፋጫቸውን ያጠናቀቁና የድኅረ ሞት ዘላለማዊ ህልውና ያላቸው የእግዚአብሔር እውነተኛ ቤተሰቦች የሚያርፉባት መካነ ዕረፍት ነች።

እግዚአብሔር ወደ ዚያች ረኀብና እንግልት ወደ ሌለባት መካነ ዕረፍት አዳምን ያስገባው ዘንድ ወዷል። እግዚአብሔር አዳምን ፈጥሮ ወደ ገነት ካስገባበት ፍቅሩ ይልቅ አዳምን ወደ ገነት የመለሰበት ፍቅሩ ይልቃል። ምክንያቱም አዳምን ወደ ገነት ሲያስገባው ሰው ሆኖ ሥጋ ለብሶ ሕማምና ሞት አላገኘውም፤ ወደ ገነት ሲመልሰው ግን አዳምን ለመካሥ የማይሰደደው ተሰዷል፣የማይራበው አምላክ ተርቧል፣የማይደክመው አምላክ ደክሟል። ለአምላክነቱ የማይገባ ሕማምና ሞት ተቀብሎ አዳምን ወደ ቀደመ ቦታውና ወደ ቀደመ ክብሩ መልሶታል።

ይቆየን



www.eotcmk.org

# ትንሣኤ ሙታን

*ውድ አንባብያን፣ ባለፈው እትም ዲያቆን ቃኘው ወልዴ «ተዘከሮተ ሞት» በሚል ርዕስ ሰዎች በዚህ ዓለም ሲመላለሱ እግዚአብሔር ሰፍሮ የሰጣቸው ዕድሜ ሲጠናቀቅ እንደ ሚሞቱ በማሰብ እንዲሆን፣ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን የሚያስተምሩትን በሚገባ አቀናብሮ አቅርቦልናል:: በዚህኛው እትም ደግሞ ሰዎች ሞታቸውን ሲያስቡ በትንሣኤ ተነሥተው እንደ ሥራቸው መጠን ወደ ርስት መንግሥተ ሰማያት ወይም ወደ ገሃነመ እሳት እንደ ሚገቡ አስተምሮናል:: መክሮናልም:: መልካም ንባብ::*

/ዲያቆን ቃኘው ወልዴ/

«ሙታን ይነሣሉና:: ሁሉም በአዳም እንደ ሚሞቱ እንዲሁ ሁሉ በክር ስቶስ ደግሞ ሕያዋን ይሆናሉና::» ፩ቆሮ. ፲፭+፳፪:: ገበሬ የሚዘራው ካልፈረሰ አይበቅልም:: ዮሐ.፲፪+፳፬:: የሚዘራው ዘር ቅንጣት ብቻ እንጂ ኋላ የሚገኘው አገዳው የሚዘራ አይደለም፤ የስንዴም ወይም የገብስ ወይም የማናቸውም ዘር ቢሆን ፩ቆሮ.፲፭+፶፯ በሚፈርስ አካል ይቀበራል፣ በማይፈርስ አካል ይነሣል፣ ጉስቁሎ ይቀበራል:: አብሮ ይነሣል፣ ደክሞ ይቀበራል፣ ኃይል አግኝቶ ይነሣል:: ፩ቆሮ.፲፭+ ፵፪-፵፫:: ከፍርድም በኋላ መልካም የሠሩ ወደ ዘለዓለም ሕይወት ክፉ የሠሩ ወደ ዘላለም እሳት ይሔዳሉ:: ዮሐ.፭+፳፱:: «ለሁሉ እንደ ሥራው ዋጋውን ይሰጠዋል:: ባሕርም በእርሱ ውስጥ ያሉትን ሙታን ሰጠ+ መቃብርና ሞትም ከሳቸው ዘንድ ያሉት ሙታን ሰጡ፣ ምድርም በውስጧ ያሉትን ሙታንን መለሰች» እንደ ተባለ አውሬ የበላው ዘንዶ የዋጠውም ቢሆን ይነሣል:: ራእ. ፳+፲፫፣ ፩ቆሮ. ፲፭:: ቅዱስ ዳዊት፡- "እግዚአብሔር በቃሉ ሁሉ የታመነ ነው፤ በሥራውም ጻድቅ ነው" ብሎ እንደ ሰበከ ሥጋን ከድንግል ለራሱ ያደረገ+ የሰው ሁሉ ፈጣሪ የሆነ+ ብቻውንም ከሙታን የተነሣ+ ሙታንንም ሁሉ ራሱ የሚያስነሣ ነው::" ዲድስ ቅልያ::

እግዚአብሔር ለፍጥረቱ ፍርድ የሚሰጥበትን ጊዜ የወሰነው ቢሆንም በሰው ዘንድ ግን አይታወቅም:: ያቺ ዕለት «ዕለተ መዓት+ ወዕለተ ምንዳቤ ወገዓር+ ዕለተ ፃዕር ውኀሣር፤ የቁጣ+ የመከራ+ የጭንቅ+ የጣዕር ዕለት» ትባላለች:: ቅዱስ ጴጥሮስ "በዚያም ቀን ሰማያት በታላቅ ድምፅ ያልፋሉ+ የሰማይም ፍጥረት በትልቅ ትኩሳት ይቀልጣል+ ምድርም በእርስዋም ላይ የተደረገው ሁሉ ይቃጠላል::» ብሏል:: ፪ጴጥ. ፫+፲:: አስቀድሞ የተፈጠረ ፍጥረት ሁሉ በሥልጣነ እግዚአብሔር ያልፋል+ ጽናቱ ያበቃል+ ምድርና በምድር ያለው ሁሉ በእሳት ይቀልጣል+ ከመሬት በላይ ያሉት ዕፅዋት+ እንስሳት+ አራዊት በሙሉ በእሳት ተቃጥለው የዓመድ ክምር ይሆናሉ:: በኃጢአትና በበደል ረክሳ የኖረች ይህች ምድር በዚያን ጊዜ በእሳት ባሕር ትዋጣለች:: በምድር ላይ ያለ ብዕል+ ተድላና ጌጣጌጥ ሁሉ በትልቅ ትኩሳት ተቃጥሎ እንዳልነበረ ይሆናል:: አሁን የሚታየው ሰማይ ያን ጊዜ ጽናቱ ይፈታል+ እንደ ሚጠቀለል ብራና ይጠቀለላል+ እንዳልነበረም ሆኖ ተቃጥሎ ይቀልጣል::

"ይነፍሁ ቀርነ ወይትነሥኡ ምውታን" እንዲል መለከት ይነፋል+ ሙታን ይነሣሉ+ ነፍስ ከሥጋ ትዋሐዳለች+ ቅዱስ ሚካኤል ሦስት ጊዜ፡- "ቅዱስ እግዚአብሔር+ ቅዱስ ኃያል+ ቅዱስ ሕያው ዘኢይመውት፤ ቅዱስ እግዚአብሔር+ ቅዱስ ኃያል+ ቅዱስ ሕያው የማይሞት» ሲል በገደል የወደቀው+ በባሕር፣ በከርሠ መቃብር፣ በከርሠ አራዊት ያለው+ ጅብ የበላው፣ ዘንዶ የዋጠው፣ አሞራ የበተነው፣ ውኃ የወሰደው፣ የወደቀው፣ የበሰበሰውና የፈረሰው ሁሉ ይሰበሰባል:: ሁለተኛም «ቅዱስ እግዚአብሔር+ ቅዱስ ኃያል+ ቅዱስ ሕያው+ ዘኢይመውት» ብሎ «ንቃህ መዋቲ ዘትነውም፤ የተኛህ ንቃ+ የሞትህ ተነሣ» ባለ ጊዜ መቃብር ከፈቱልኝ መግነዝ ፍቱልኝ ሳይል ደጉም ደግነቱን ይዞ ክፉውም ክፋቱን ይዞ እንደ እሸት ተፈልፍሎ እንደ ዘንግ ተመልምሎ ፈጥኖ ይነሣል:: ከእነርሱም ወንዶች የሠላሳ ዓመት ጐልማሳ ሴቶችም በዐቅመ ሔዋን የአሥራ አምስት ዓመት ቆንጆ ሆነው ይነሣሉ:: /አምስቱ አዕማደ ምሥጢር ምስለ ሥነ ፍጥረት አንድምታ+ 1991 ዓ.ም፤ ቅዳሴ ያዕቆብ ዘሥሩግ ተመልከት/::

"አሜሃ ጻድቃን ይበርሁ ከመ ፀሐይ" እንዲል ጻድቃን በዚያን ጊዜ ከፀሐይ ይልቅ ደምቀውና ተውበው ብርሃን ተጐናጽፈው ይታያሉ:: ማቴ. ፲፭+፵፫:: በአንጻሩ ኃጥአን ከቁራ ይልቅ ጠቁረው+ ከጭራ ይልቅ ቀጥነው የግብር አባታቸውን ዲያብሎስን መስለው ይነሣሉ፤ ነፍስ ሥጋን ለማስደሰት ስትል ከእግዚአብሔር አንድነት በመለየቷ ሥጋዋን ትረግማለች፣ ያን ጊዜ ልቅሶ+ ዋይታ+ ጥርስ ማፋጨት ይሆናል፤ ግን የማይጠቅም ልቅሶ ነው::

ቅዱሳን መላእክት ከየመቃብሩ የተነሣውን ሰው ሁሉ የፍርድ ዐዋጁንና ቅጣቱን ወደ ሚሰማበት ቆላተ ኢዮሳፍጥ /የኢዮሳፍጥ ሸለቆ/ እንዲሰበሰብ ያዝዙታል:: ይህ ሥፍራ በኢየሩሳሌምና በደብረ ዘይት መካከል የቄድሮን ወንዝ የሚፈስበት+ ኢዮሳፍጥ ጠላቶቹን ድል በማድረግ ብዙ ምርኮ ከወሰደ በኋላ ለእግዚአብሔር ምስጋና እንዳቀረበበት ተጽፏል:: ፪ዜና.፳+፳፬-፳፯:: ኢዮሳፍጥ ማለት «እግዚአብሔር ፈርዶአል» ማለት ነው:: ነቢዩ ኢዮኤል ትንሣኤና የመጨረሻ ፍርድ በቆላተ ኢዮሳፍጥ እንደ ሚሆን ገልጿል:: ኢዮ.፫+፪፣፲፪:: ሁሉ ሰው በዚህ ሥፍራ በተሰበሰበ ጊዜ ጻድቃንን ከኃጥአን ይለያቸዋል:: «ጻድቃን በቀኝ ኃጥአን በግራ ይቆማሉ» ማለትም ግብራቸው ይመራቸዋል፤ በኃጥአን ላይ ሥቃይ /ጭንቅ/ ይበዛባቸዋል፤ ሌላውን ሥቃይ እንኳ ሳይቆጠሩ ይህችኛዋ ውርደት (ከእኔ ሒዱ መባላቸው) ለብቻዋ ለቅጣታቸው በበቃች ነበር:: በዚያች ጊዜ ልጅ ከአባቱ፣ ባል ከሚስቱ፣ ጌታ ከሎሌው፣ እናት ከልጇ.... ይለያሉ:: ማቴ.፳፭:: እንግዲህ ሰው ሁሉ «የእኔ መቆሚያ በቀኝ ይሆን በግራ?» ብሎ ሊያስብና ዕለተ ሞቱን ሊያዘክር ይገባዋል:: ወደ ግራ የሚወስደው ጉዳና ሰፊ ውጤቱም ክፉ ስለሆነ ዛሬ ነገ ሳይሉ ሊሸሹትና ሊለቁት ይገባል:: ማቴ.፯+፲፫:: በዕለተ ደብረ ዘይት ነገረ ምጽአትን፣ ዕለተ ሞቱን በማሰብ ይቅርታ ከመጠየቅ ይልቅ በመብላት በመጠጣትና ክፉ ሥራ በመሥራት ልቡናውን ሳጸና ወይ በፍርድ ቀን ምን ይመልስ ይሆን? አውግስጢኖስ "የጌታችን አመጣጡ ለጻድ ቃን ደስታ ለኃጥአን ግን ሽብር ነው" ብሏል::

## ዘለዓለማዊ ሥቃይ

ቅዱስ ዮሐንስ የኢየሩሳሌም ኤጲስ ቆጶስ በሃይማኖተ አበው እንዲህ አለ፡- "ከዓመፀኞች በሲኦል ስለ ነፍሱ ደኅንነት እግዚአብሔርን የሚታመን ማነው? ከዚያ ማንም የለም:: ነገር ግን በዓመፃው እንደ ሆነ ለሚሞት ሁሉ እነሆ የእግዚአብሔር ፍርድ መጥቶበታል:: ሰዎችም ትሉ የማይሞተውን+ እሳቱ የማይጠፋውን የመከራ+ የኀሣር ሥፍራ በልባቸው ይመልከቱ:: ስለዚህም በዚህ ዓለም በሕይወት ሳሉ ንስሐ ይግቡ::

በዚህ ዓለም ያላስታወሰችውን ፈጣሪዋን ባየች ጊዜ የኃጥእ ነፍስ ታላቅ ጭንቅና ፍርሃት ይወድቅባታል:: የጻድቅ ዮሴፍ ወንድሞች «እኔ ለነጋዴ የሸጣችሁኝ ወንድማችሁ ነኝ» ባላቸው ጊዜ ተጨንቀው መናገር ካቃታቸው ይልቅ በፈጣሪው ፊት ሲቆም ኃጥኡ ምን ይመልስ ይሆን? አውግስጢኖስ "በስተላይ እውነተኛው ፈራጅ÷ ከታች አፉን የከፈተ እሳተ ገሃነም+ በቀኙ እርሱን የሚከሱት ክፉ ሥራዎቹ÷ በግራው ደግሞ ገሃነም ሊያወርዱት የተሰለፉ አጋንንት+ በውስጡ የኅሊና ወቀሳ የተከበበ ኃጢአተኛ እንዴት÷ ወዴትስ ማምለጥ ይቻለዋል?» በማለት የኃጥኡን መከራ ጽፏል::

ገሃነም የዲንና የእሳት ባሕር ሲሆን



www.eotcmk.org

ጨለማና እስራት ያለበት፥ ትሉ የማይሞትና የማያንቀላፋ እሳቱ የማይጠፋ፥ ወደዚያ የሚጣሉ ኃጥአንም የሥቃያቸው ጢስ ለዘለዓለም እየወጣ ሌሊትና ቀን የሚሠቃዩበት የመከራና የጭንቀት፥ ጥርስ ማፋጨት ያለበት ሥፍራ ነው፤ የገሃነም ቅጣትም እስከ የሌለው ዘለዓለማዊ ነው:: እንኳን ዘለዓለማዊ ሥቃይ ይቅርና ደስታም እንኳ ለረጅም ሰዓት ያለ ዕረፍት ቢደረግ ይሰለቻል:: ገሃነም ሥቃያት ምንዳቤያትና መሪር ነገር ሁሉ ያለበት መካነ ሕማም (የመከራ ፣ የጭንቅ፣ የረዓድ፣ የድንጋጤ ሥፍራ) ነው ቅጣቱ መዓልት ከሌሊት የማያቋርጥ ለዘለዓለሙ ሁሉ ነው:: ይህንንም መጻሕፍት ተባብረውበታል:: ለምሳሌ፡- ሉቃ.፲፪፥ ፭፤ ማቴ. ፳፪፥ ፲፫፤ ማር. ፱፥፵፪፤ ራእ.፲፬፥፩:: ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅም በተግሣጹ እንዲህ አለ፡- "የወዲያ ችግሮች እነሆ ስማቸው በእኛ ዘንድ የታወቀ ነው፤ ከዚያ እሳትና ጨለማ፥ እስራት፥ የማይተኛ ትል አለ፤ ለእኔም ከዚህች እሳት ይልቅ ያቺ እሳት የምትከፋ ይመስለኛል፤ እሳት እየነደደ ጨለማ እንዴት ይገኛል:: ምንም እንኳ እሳት ብትሆን ብርሃን የለባትምና ከዚህች እሳት ያቺ እሳት እንደምትከፋ ተረዳህን? እንዴት ክፉኛ ታቃጥል! ከዚህች ይልቅ ያቺኛዋ እንደ ምታቃጥል አየህን? አትጠፋምና! ስለዚህም እሳቱ የማይጠፋ ተባለ:: ወንድሞች ሆይ፥ የዚህን ሥቃይ መጠን እንረዳ ዘንድ ይገባናል:: ይኸውም የእሳት ወላፈንና በጨለማ ውስጥ መኖርን ረዳት የሌለበት ያለ ማቋረጥ መጮህንና ጥርስ ማፋጨትን ነው::"

ገሃነም የማሠቃያ ነገሮች ሁሉ መዝገብ ነው:: ባዕለ ጸጋው ሌዊ «ብሔረ ሕማም» (የሕማም ሥፍራ) ብሎታል:: ሉቃ.፲፮፥፳፫-፳፬:: ኃጥአንና አጋንንት ቅጣታቸውን ተቀብለው የሚኖሩበት የሥቃይና የመከራ አዘቅት ነው:: በዚህ ዓለም ከሁሉ የበረታ ቅጣት እሳት ቢሆንም በገሃነመ እሳት አንጻር ሲታይ ይህኛው ብርድ ነው:: ነቢዩ ኢሳይያስ ለቅጣታችን የተፈጠረውን የገሃነም እሳት "የቁጣ ትንፋሽ" በማለት ገልጾታል:: «ኃጥአን ወደ ገሃነም ይጣላሉ» ሲባል ወደ እሳት የሚሔዱ ብቻ ሳይሆን የሚዘቅጡ (ከኑሣር ወደ ጎሣር ሲወርዱ የሚኖሩ) መሆናቸውን ያስተውቋል:: ማለትም በእቶን ውስጥ ተጥለው በሚያቃጥል እሳት ተሸፍነው በውስጡ ይዋጣሉ:: ይኸውም ግድግዳውና ወለሉ ሁለ ንተናው የእሳት ባሕር በመሆኑ ወደዚያ የገባ ከእሳት በቀር የሚያየው ነገር የለም:: ዓሣ በውኃ ውስጥ እንዲኖር እር ሱም በሚቆረጣጥም እሳት ይቃጠላል:: በቀትር ዋዕየ ፀሐይን (የፀሐይን ቃጠሎ) በመፍራት ለመውጣት የምንፈራውን ያህል፥ የጋመ ፍሕም ምድጃ ባለበት ዝግ ቤት መቀመጥና የእሳት ፍንጣሪ ሲያርፍብን መታገሥ የሚሳነንን ያህል ያኛውን እሳት በመፍራት ለመዘጋጀት አንነሣሣም:: ይህን ስንፍና ልናርቅ ይገባናል:: አውሬ ጠቦትን እንዲበላ ለቸርነቱ ምክንያት የሚሆን መልካም ሥራ ሠርተን ባንገኝ በገሃነም እሳት እንዋጣለን:: ይህም እስከ የለውም::

"የዚህ ዓለም መከራዎች ቢበረቱና ቢደመሩ ከዚያኛው ሥቃይ ጋር ሲነጻጸሩ ጥላ ብቻ ናቸው:: ይህን ግን አናስተውለውም:: ዮሐንስ ኤጲስ ቆጶስ ዘኢየሩሳሌም በሃይማኖተ አበው "ከዓመፀኞች በሲኦል ስለ ነፍሱ ደኅንነት እግዚአብሔርን የሚታመን ማነው? ከዚያ ማንም የለም:: ነገር ግን በዓመፃው እንደ ሆነ ለሚሞት ሁሉ እነሆ የእግዚአብሔር ፍርድ መጥቶበታል:: ሰዎችም ትሉ የማይሞተውን እሳቱ የማይጠፋውን የመከራ ሥፍራ በልባቸው ይመልከቱ:: ስለዚህም በዚህ ዓለም በሕይወት ሳሉ ንስሐ ይግቡ" በማለት ኃጢአት የሠራ ሰው ንስሐ ካልገባ ቅጣት እንደ ሚጠብቀው ገልጿል:: ምክንያቱም በዚያን ጊዜ መልካም ይሁን ክፉ ሥራ እንጂ ሹመት ባዕለ ጠግነት ዕውቀትና የመሳሰለው በአምላካዊ ሚዛን አይመዘንም::

በፍርድ ቀን ምላሽ መስጠት ግድ ይሆናል:: ምክንያቱም ዲያብሎስና የሠራነው ኃጢአት ይከሰናል፤ የሰማነው ቃለ እግዚአብሔር ይፈርድብናል፤ ሁሉም በሥራው ልክ ብድራቱን ይቀበላል:: "ጻድቁ ስንኳ በብዙ ጭንቅ የሚድን" መሆኑ በወንጌል ተገልጧል:: አንድ ባሪያ ከራሱ አቅንቶ ያልሆነውን ለንጉሡ በመናገሩ ንጉሡ ተቆጥቶ አሽከሩን አስጠርቶ "ለምን ዋሸኸኝ? እንዴትስ ልታታልለኝ አሰብክ?" ብሎ ቢጠይቀው ከቤቱ ወጥቶ ሔደ:: በሐዘንም ሞተ ይላሉ:: በምድሩ እንዲህ ከሆነ በእግዚአብሔር ፊት ቀርበን በፍርድ ቀን የምንመልሰው ምን ይሆን? ሰውን የፈጸማቸው የራሱ ኃጣውእ ይለጉሙታል::

ኃጥአንን "ሑሩ እምኔየ ርጉማን ውስተ እሳት ዘለዓለም ዘድልው ለሰይጣን ወለመላእክቲሁ" ይላቸዋል:: ማቴ.፳፭፥፵፩-፵፮:: ይህም ማለት እኔ ለእናንተ ብዬ ከሰማየ ሰማያት ወርጄ ከድንግል ማርያም ተወልጄ በዕለተ ዓርብ በመልዕልተ መስቀል ተሰቅዬ ሥጋዬን ብቆርስ ደሜን ባፈስ፤ እናንተ ለእኔ ደግ አላደረጋችሁልኝም፥ በጎ አልሠራችሁልኝምና የወደዳችሁን አለቃችሁን ዲያብሎስን ተከትላችሁ ለርሱ ተብሎ ወደ ተዘጋጀ ገሃነመ እሳት /ዘላለም እሳት/ ከርሱ ጋራ እንደርሱ ሲያቃጥላችሁ /ሲበላችሁ ይኖር ዘንድ/ ሒዱ ይላቸዋል:: አውሳብዮስ "ኃጥአን ይህን ፍርድ ሲሰሙ ከሽብር ብርታት የተነሣ ቢቻላቸው ዳግመኛ በሞቱ ነበር" በማለት የሚሰማቸውን ኀፍረትና ዋይታ ገልጿል:: ዲዮናስዮስም" የዚያ ነጐድጓድ ድምፅ ምንኛ ያሸብር ይሆን?... ወዮ" አለ::

ከዚህ ፍርድ ለማምለጥ መሔጃ የለም:: ጌታ፣ «ፈታሒ በጽድቅ ኩናኔ በርዕት ዘኢያደሉ ለገጽ፤ ገጽ አይቶ የማያዳላ በእውነት የሚፈርድ ነውና» ሎሌ ጌታ፥ ደኻ ባዕለ ጸጋ፣ እመቤት ገረድ ደንገጡር ሳይል ሁሉን እንደ ሥራው ሒድ ብሎ ያሰናብታቸዋል:: መዝ.፲፪፥፲፪:: በመ ሆኑም" አውግስጢኖስ ወንድሜ ሆይ፥ እውን እግዚአብሔር ወደ ገሃነም ሊያወርደኝ ይፈል ጋልን? ብለህ እንዳትናገር ተጠንቀቅ፤ ዕብራውያን ደኅና እየመሰላቸው በእምቢታ አል ቀዋልና እንዲህ ያለውን ንግግር አትናገር" በማለት ይመክራል:: እንኪያስ ያለ ፍርድ ጊዜው ሳይደርስ የወደድነው እንዲፈረድልን መጠየቅ፥ በመፍራት በመንቀ ጥቀጥ መለመን ይሻለናል::

ከቅጣት ሁሉ የበለጠ የኃጥእ ቅጣት እግዚአብሔርን ማጣት ነው:: ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ፣ "እመ ትቤ ዓሠርተ ምእተ ገሃነማተ ኢምንት ውእቶሙ በአንጻሪሁ ለውእቱ ሕማም፤ በዚያ ቅጣት አንጻር ሺሕ ገሃነም ምንም ማለት አይደለም /ከቁጥር የማይገባ ነው/" በማለት ከእግዚአብሔር መለየት የቅ ጣቶች ሁሉ ቁንጮ መሆኑን ተናገረ::

ይህች ቅጣት እንዳትደርስባቸው የሚፈሩና ሥጋቸውን ቀጥተው ዓለምን አሸንፈው ለመኖር የሚጥሩ ቅዱሳን ብቻ ናቸው:: ክቡር ዳዊት ልጁን አቤሴሎምን ፊቴን እንዳያይ ባለ ጊዜ አቤሴሎም «ፊቱን ለማየት የማይፈቅድልኝ ከሆነስ ይግደለኝ» ብሎ ተናግሯል:: ይህ ከሆነ ጌታ ከእኔ ሒዱ ብሎ በሚያሸብር ቃል ቢያሰናብተን የሚሰማን ስሜት ምን ይሆን? የአባቴን ፈቃድ አልፈጸማችሁምና ለእኔ አይደላችሁም፥ ከቶ አላውቃችሁም በማለት መልካም ሥራ ከእምነት አዋሕደን ባንገኝ ከዘላለም ሕይወት እንደሚያባርረን ራሱ ባለቤቱ ተናግሯል:: ማቴ.፯፥፳፩:: ኃጥእ ነፍስ በገሃነም እግዚአብሔርን መውደድ ፈቃዱ ይሁንልኝ ብላ ፍርዱን በትዕግሥት መቀበል ቢቻላት ኖሮ ገሃነም ገሃነም ባልሆነባትም ነበር:: ገሃነም ኃጥአንና አጋንንት የሚቀጡበት ሥፍራ መሆኑ በዚህ ታወቀ::

በገሃነም እሳት የመኖሩን ያህል ዐይን በጨለማ ይሰቃያል:: "ኢይሬኢ ብርሃን እስከ ለዓለም" እንዲል:: በዚያ ብርሃን ፀሐይ ወይም ሌላ መብራት የሌለበትና የማይገባበት ዙሪያውን በጨለማ ተቆልፎ የተዳፈነ አዘቅት ነው:: እሳቱ ብርሃን የለውም:: ይሁዳ በመልእክቱ "ድቅድቅ ጨለማ ለዘላለም የተጠበቀላቸው" ይሁ.1÷13 እንዳለ:: ከገሃነም እሳት የሚወጣ ጭስ የጨለማ ጭፍና ሆኖ በዚያ የተጣሉትን ሲያሰቃያቸው ይኖራል:: የብርሃን ፍንጣቂ ቢያዩም እንኳ ሥቃያቸውን ለማብዛት እንጂ ለጥቅማቸው አይደለም::

አንዳንድ ሰዎች ሲቀልዱ ይደመጣሉ፤ «እኔ ብቻዬን አልወርድም:: ስለዚህ ሌሎች ሰዎች እንደሆኑት እሆናለሁ፣ ደግሞስ በዚያ ያለውን ቅጣት ማን ሒዶ አይቶታል» በማለት የሚናገሩ አሉ:: ይህ አለማስተዋል ነው:: ወደ ገሃነም የሚወርደው ሰው የመብዛቱን ያህል ሥቃዩም ብዙ ነው እንጂ ሰው በመብዛቱ አይቀነስም፤ በጠባብ ጉረኖ እንደ ሚታጎሩ ፍየሎች ነው::

በዚያ በቀቢጸ ተስፋ ዘወትር በሚያለቅሱ ሰዎች ድምፅ መቋረጫ በሌለው የሚያስቅቅ የአጋንንት ጩኸት ጆሮ እንደ ደነቆረ ይኖራል፤ ይህም መሪር ሥቃይ ነው፤ ይህም ብቻ አይደለም፤ በነዌ እንደ ታየው የላመ የጣመ የለመደ አፍ እጅግ በበረታ ረሃብና ጥም ይ መ ታ ል ፤

ወደ ገጽ ፴፮ ዞሯል



www.eotcmk.org

# «ቡዳ» ምንድን ነው? «ቡዳ» እና ባለ እጅ ምን አገናኛቸው ?

*«ቡዳ» ማለት ምንድን ነው? «ቡዳ» ሰው ነውን? በአገራችን «እገሌ በላኝ፤ እገሊት በላችኝ?» ይባላል:: ሰው ሰውን ይበላልን? በመልክአ ሥላሴ በአርአያ ሥላሴ የተፈጠረ ኾኖ ሳለ እንዲህ መባሉስ አግባብ ነውን? በተለይም ይህ ዓይነት መጠሪያ የሚሰጣቸው ሰዎች የጥበበ እድ ባለቤት የኾኑቱ ናቸው:: ቀድሞስ ነገር ቡዳ እና ባለ እጅ ምን ያገናኛቸዋል? እባካችሁ ይህ አስተሳሰብ ለከፋው ድህነታችን አስተዋፅዖ ሳይኖረው አይቀርምና ለጥያቄዎቼ በቂ ማብራሪያ እንድትሰጡኝ እለምናለሁ?*

*ኃይለ መስቀል /ናዝሬት/*
*አረጋሽ አበበ /ደብረ ታቦር/*

<u>*መልስ*</u>

የተወደዳችሁ ጠያቂዎቻችን ጥያቄአችሁ:- መንፈሳዊ ይዘት ያለው፣ የታሪክ፣ የማኅበራዊ ሥነ ልቡና፣ እንዲያም ሲል የአገር ጥበብና ዕድገት ጥያቄ በመኾኑ ትኩረት ልንሰጠው ግድ ይለናል:: ጥያቄውን ለመመለስ ጥረት ያደረግነው የ«ቡዳ»ን እምነት ዓለም አቀፋዊ ገጽታና አስተሳሰብ፤ የተግባረ እድን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ገለጻዎችና ተያያዥ ጭብጦች በማውሳት ጭምር ነው::

«ቡዳ» በኅብረተሰባችን ውስጥ የተለየ ግምት የሚሰጠው ክስተት መሆኑ ግልጽ ነው:: በታወቀው አነጋገር «የሰው ዐይን»፣«የሰብ ዕይን» /በዛይ ቋንቋ/ ፣«ዓሳ አይፌ» /በወላይትኛ/ ይባላል:: «በቡዳ የተበላ» ሰው አእምሮው ተነክቶ የተለያዩ ያልተመለዱ ሁኔታዎችን በማሳየት /ጽኑ የራስ ምታት፣ ድካም፣ መብረክረክ፣ የአንጀት መሸምቀቅ (intestinal cramps)፣ የእጅ ጣቶች መጨባበጥ/ ለስቃይና አፋጣኝ መፍትሔም ካልተገኘ ለሞት እንደሚዳረግ ነው በስፋት የሚታመንበት:: ከዚህ ሁኔታ ራስን ለመከላከል «ቡዳ ናቸው» ተብለው የሚታሙ ሰዎችን ማግለል፣ «የቡዳን ዐይን ወይም ቀልብ ይስባሉ» ተብለው የሚታምንባቸውን ለየት ያለ ተክለ ቁመና ያላቸውን ሰዎች /በተለይም ሕፃናትን፣ሙሽሮችን/፣ከብቶችንና በማሳ ላይ ያለ ሰብልን በልዩ ልዩ የሀገረሰብ ወይም «ፀረ-ቡዳ» ናቸው ተብለው በሚታሰቡ ቅመሞች አማካይነት መጠበቅ... ወዘተ ይገኙባቸዋል::

በርግጥ ይህ ችግር በኢትዮጵያውያን ዘንድ ብቻ የተወሰነ አይደለም:: በዑጋንዳ ውስጥ በተለይም ሉግባራ ተብለው በሚጠሩ ጎሳዎች ዘንድ በዐይናቸው በማየት ብቻ ሰውን መጉዳት የሚችሉ ሰዎች እንዳሉ ተቀባይነት ያገኘ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን በእነዚህ ሰዎች ላለመጐዳት ገጸ በረከት ማቅረብ ሊያስፈልግ ይችላል:: የአትላንቲክ ውቅያኖስን ስንሻገር ደግሞ ላቲን አሜሪካ ውስጥ «ዬካታን» የተባሉ የቀይ ሕንድ ጎሳዎች የ«ቡዳ»ን መኖር ያምናሉ:: እነዚህ ሕዝቦችም ይህ «ልዩ ችሎታ» አላቸው ተብለው የሚታመንባቸው ግለሰቦች ሰለባ ላለመሆን በተለያየ ጥቅማጥቅም ለመደለል ይሞክራሉ:: የተለያዩ የአርኪዮሎጂ እና የጽሑፍ ማስረጃዎች እንደጠቆሙትም በሜዲትራንያን ባሕር አካባቢ ይኖሩ የነበሩ ሕዝቦች ክስተቱን «ክፉ ዐይን» (Evil Eye) ብለው ይጠሩት ነበር:: በ«ቡዳው ሰው ላለመበላትም» እንደ የወይን መጠጥ ያሉ ስጦታዎችን ያበረክቱ ነበር:: በዚህ አካባቢ የነበረውን እምነት ለየት የሚያደርገው ደግሞ የክስተቱ ተጠቂዎች ሰዎች ብቻ ሳይሆኑ የቤት እንስሳትም ሊሆኑ መቻላቸው ነበር:: በዚህ የተነሣም የተለያዩ ቀለማት ያላቸውን ጨርቆች በከብቶቻቸው አንገት ላይ በማሰር በቡዳ እንዳይበሉ ለመከላከል ይሞክሩ ነበር::

እምነቱ በመካከለኛው ምሥራቅ ዐረቦች ዘንድም /በሴማውያን ሕዝቦች ዘንድ/ ተቀባይነት እንደነበረው ተመሳሳይ ማስረጃዎች ጠቁመዋል:: ስለ «ቡዳ» በርከት ያሉ የጽሑፍ ማስረጃዎች ያለበትን የአውሮፓን ሁኔታ ስንመለከት ግን በ16ኛው እና በ17ኛው መ/ክ/ዘ ወቅት «ቡዳ ናቸው» የተባሉ ሰዎች ከፍተኛ የሆነ ግፍና ጭፍጨፋ ደርሶባቸዋል:: በርግጥ በወቅቱ ግለሰቦቹ በዐይናቸው ሌላውን ሰው ለመጉዳታቸው በተጨባጭ የተገኘ ማስረጃ አልነበረም፤ ሆኖም በአጋጣሚ በእነዚህ ግለሰቦች «በክፉ የታየ» ሰው በተለያየ ምክንያት ቢሞትም የሞቱ መንሥኤ እነርሱ ተደርገው ስለሚቆጠሩ ወዲያውኑ ለፍርድ ቀርበው የሞት ቅጣት ይበይንባቸው ነበር:: በዘመኑ የኖሩ አውሮፓውያን «ለቡዳ» ከነበራቸው አስገራሚ ፍራቻ የተነሣ «በቡዳነት» የተከሰሱ ሰዎች ለፍርድ ሲቀርቡ ዳኞችን «እንዳይበሏቸው» ፊታቸውን ወደ ኋላ በማዞር ጀርባቸውን ብቻ ለዳኞች ሰጥተው ነበር ፍርዱ የሚበየንባቸው::

ዘመናዊው ሥልጣኔ የአውሮፓን ምድር ሲያጥለቀልቃት ግን አስተሳሰቡ እየከሰመ መጥቶ ደብዝዞ ከመጥፋት ደረጃ ላይ ደርሶ፤ «ክፉ ዐይን» አላቸው ተብለው የተፈረጁ ግለሰቦችን በግፍ አሰቃይቶ መግደልም አብሮ ጠፋ:: በመሆኑም «ክፉ ዐይን ሰው ይጐዳል» የሚል አስተሳሰብ በአሁኑ ወቅት በአውሮፓ ሀገራት ውስጥ አይገኝም:: /ሜዲካል ጋዜጣ፥ ነሐሴ 19 ቀን 1996 ዓ.ም፥ ገጽ 15/::. Zerihun Doda, (2001) “ Culture, Belief and Mental illness among the Zay” , A.A , pp 40-43

ቡዳ የአንድ ሰው፣ብሔር፣ብሔረሰብ፣ነገድ ወይም ጎሣ አልያም አካባቢ መጠሪያ /መለያ/ አይደለም:: ቡዳ ለሚለው ቃል እንደሚገባ የተሰጠ ትክክለኛ ትርጉም ባይኖረውም በላኤ ሰብእ /ሰው በላ፣ደም መጣጭ ጋኔን/፣ዐይነ ወግ ወይም «ክፉ ዐይን» /A person believed to possess the "evil eye"/ ማለትን ያመለክታል:: ስያሜው የተሰጠው /ሊሰጥም የሚችለው/ ሰው ላይ አድሮ ሰውን ለሚወጋው ርኩስ መንፈስ /Malevolent Spirits or Beings/ እንጂ የሰውነት ባሕርያዊ ተፈጥሮ ላለው አዳማዊ ሰው አይደለም::

በቅዱስ መጽሐፍ እንደ ተገለጸው በታሪክም እንደሚታወቀው እሥራኤላውያን ከልዩ ልዩ ሕዝብ ልዩ ልዩ የተግባረ እድ ጥበብን ቀስመዋል:: /1ኛ ሳሙ. 13÷19–20/:: በመሆኑም በሕዝቡ ዘንድ ብዙ ዓይነት ተግባረ እድ ነበር:: ሆኖም የተለየ ችሎታ ያላቸው በከተሞች ውስጥ ይኖሩ ነበር:: የተለየ ሰፈርም ነበራቸው:: ለምሳሌ ጸሐፊዎች በያቤጽ /1ዜና 2÷55/፤ በኢየሩሳሌም የአጣቢያች /2 ነገሥ. 18÷17/፤ የሸክላ ሠሪዎችም ሰፈሮች ነበሩ /ማቴ.27÷7/::

በቅዱስ መጽሐፍ በተግባረ እድ የተጠቀሱትን ሠራተኞች በሰባት አርእስት ማጠቃለል ይቻላል::

1. ወርቅና ብር ሠሪዎች::
   ሀ/ አንጥረኞች /ዘኁል.31÷21–23/÷
   ለ/ ቀራጺዎች /ኢሳ.40÷19/::
2. የዕንቍ ድንጋይን የሚቀርጹ /ዘጸ. 31÷5/::
3. ብረታ ብረት ቀጥቃጮች:: ሀ/ ናስን ÷ መዳብን÷ቆርቆሮን÷ ብረትን÷ እርሳስን የሚያነጥሩ /ዘኁል.31÷22–23/፤ ሕዝ. 22÷18–20/÷ ለ/ የሚቀርጹ /ኢሳ.44÷12/::
4. ድንጋይ ወቃሪዎችና ግንበኞች:: /2ነገሥ. 12÷13/÷የሚቀርጹ /ዘጸአ.28÷10–11/
5. ቤትና የቤት ዕቃ ሠሪዎች::
   ሀ/ አናጢዎችና ጸራቢዎች /2ሳሙ.5÷11/÷
   ለ/ ቀለም ቀቢዎች /ት.ኤር 22÷14/::
6. ልብስ ሠሪዎች:: ሀ/ፈታዮች/ዘጸ.35÷25–26/÷
   ለ/ ሸማኔዎች ዘጸ.35÷35/::
   ሐ/ አጣቢዎች /2ነገሥ. 18÷27/÷
   መ/ ቀለም አግቢዎች /2ዜና.2÷7/
   ሠ/ ጠላፊዎች /ዘጸ.35÷35/::
7. ልዩ ልዩ ባለሞያዎች:: ሸክላ ሠሪ ዎች /ኤር.18÷3/÷ቀማሚ /ዘጸአ.30÷22–38/ ÷ቁርበት ፋቂ /ግብ.ሐዋ.9÷43/ ÷ ቀንድ አንጣጪ /መኃ.7÷23/:: / የእመቤታችን ጠባቂ አረጋዊው ዮሴፍ የጸራቢነት ሞያ ነበረው:: ማቴ.13÷55፤ ማር.6÷3:: ይኸውም ለቤት ሕንፃ፣ ለግብርናና ለሌላም ሥራ ሁሉ የሚውለውን ዕቃ ከደንጊያና ከእንጨት የሚሠራ ባለሞያ ነው:: 1ነገሥ.7÷9፤ 2ዜና. 34÷11፤ አሞ.5÷11:: /መጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ÷1972 ዓ.ም.÷ ገጽ 111–112 እና 254/:: በአገራችንም በዐፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት ከቤተ እሥራኤላውያን ወገን የነበሩት ባለ እጆች በየክፍለ አገሩ በአንድ ሰፈር እንዲሰበሰቡ ተደርገው ነበር:: ከእኒህም መካከል በአዲስ አበባ «ሠራተኛ ሰፈር» የነበሩትና በኋላ ላይ በፋሽስት ኢጣልያ ወረራ ወቅት ወደ አዲስ ከተማ /መርካቶ አካባቢ/ የተዛወሩት ባለ እጆች ይገኙበታል::

በቀድሞ ጊዜ የእጅ ሥራ ለሚሠሩት ሰዎች የሚሰጧቸው ስሞች ልዩ ልዩና ከባ



www.eotcmk.org

ባድም ነበሩ:: ሸክላ ሠሪውን «ካይላ» ፣ ብረት ሠሪውን «ጠይብ ወይም ቀጥቃጭ»፣ ብርና ወርቅ ሠሪውን «አንጥረኛ»፣ልብስ ሠሪውን «ሸማኔ»፣ቆዳ ሠሪውን «ፋቂ»፣ዋንጫ ሠሪውን «አንጣጭ» ይሏቸዋል:: የሁሉም ጠቅላላ ስማቸው «ባለ እጅ» ነው:: ባለ እጅ:- የእጅ ሥራ /ጥበበ እድ/ ባለሞያ ማለት ሲኾን በግእዙ ተግባረ እድ የምንለው ነው:: በአገራችን «ቡዳ» /ሰወ በላ– invisibly sucking one's own blood/ የሚለው ስያሜ ባለ እጆች የሚሰደቡበት ስም ነው::

በአንዳንድ አገባባዊ ፍቺው «ቡዳ» ማለት ብልህ መሆኑን እንረዳለን፤ «ከባለቤቱ ያወቀ ቡዳ ነው» እንዲሉ:: እንዲህም ስለሆነ «ቡዳ» የሚለው ቃል «ጠይብ፣ጥበበኛ፣ባለ እጅ፣ አጥንተ ሰባራ፣የባለ እጆች ዘር» የሚለውን አገላለጽ በውስጡ እንደ ያዘ እንመለከታለን:: አለቃ ደስታ ተክለ ወልድ «ገበታ ሐዋርያ» በተባለ መጽሐፋቸው «በዐረብኛ ጠይብ ማለት 'ማለፊያ÷ደግ' ማለት ነው:: 'ቡድሃ' የጃፓንንና የቻይናን ሃይማኖት ያወጣ የሕንድ ንጉሥ ልጅ ነው:: 'ቡድሃ' እጅግ ብልህ ስለ ነበር 'ከባለቤቱ ያወቀ ቡዳ ነው::' ይባላል:: ብልህ ፈላስፋ ማለት ነው:: ይመሰል አይመሰል የጠይብ እጁ ከከሰል እንዲል:: ፕሮፌሰር ዶናልድ ናታን ሌቪን የተባሉ የሥነ ልሳን ሊቅ «ሰምና ወርቅ» በተባለ መጽሐፋቸው ጠይብ /ጠቢብ/ የሚለው ስያሜ በመሠረታዊ ፍቺው የተግባረ እድ ባለሞያን የሚያመለክት እንደ ነበርና በኋላ ጊዜ ግን «ዐይነ ወግ» የሚል ተጨማሪ ትርጉም እንዳሰማ ያስረዳሉ:: «ዐይነ ወግ» የሚለውም ሐረግ «ቡዳ» የሚለው ስያሜ ጥንተ ትርጉም መሆኑንም ይገልጻሉ:: /Prof.Donald N. Levine, Wax and Gold;. *tradition and innovation in Ethiopian Culture*, 1965,P.70 ]

ከባለ እጆች መካከል ከቀርከሃና ከሸንበቆ የሚሠሩ ዕቃዎችን የሚያበጀው አናጢው፣ሸማ ሠሪውና ፋቂው /አሸን ክታብ፣ አንቀልባ፣ ትራስ የሚሠራ አረብ አራቢው/ «ሰው ይበላል» ተብሎ ብዙ ክብደት አይሰጠውም፤ ስድቡ ግን አይቀርለትም:: «ቡዳ» የሚለው ስም ይበልጥ ተወስኖ የሚገኘው ጠይብ ወይም የሕዝቡን ማረሻ፣ወገል፣ማጭድና ልዩ ልዩ ጌጣጌጦችን /አንባር፣መስቀል/ በሚሠሩት ብር አፍሳሾች፣ብረት ሠራተኞችና ሸክላ ሠሪዎች ላይ ነው:: እኒህም «ባለ እጅ ቡዳ ነው፤ ውቃቢ /ረቂቅ መንፈስ/ ÷ ዕፀ መድኃኒት አለው፤ ሰውን በዐይኑ ተመልክቶ ወግቶ ይገድለዋል፤ የሞተ ሰው ያስነሣል፤ ወደ ዕቃ ለውጦ እንስራና ጋን ያደርገዋል» እየተባለ የማይታመን ሐሰትና ሐሜት ተወርቶባቸዋል፤ ልዩ ልዩ ስም ተሰጥቷቸዋል:: /ፍሥሐ ይሁን ÷ መጽሐፈ ቡዳ÷1990 ዓ.ም÷ ገጽ 11-15::

ከባለ እጆች ብዙዎች የሚያርሱት ርስት ስላልነበራቸው አፈር እየማሱ፣ሸክላ እየሠሩ÷ መዓድናትን አውጥተው እያቀለጡና እየቀጠቀጡ ከመገልገያ መሣሪያዎች አንሥቶ የተለያዩ ጌጣጌጦችን አምርተው በመሸጥ ይተዳደሩ÷ሕዝቡን ያገለግሉ ነበር:: የተግባረ እድ ባለሞያዎች እነዚህን የመገልገያ ዕቃዎች ባይሠሩ ኑሮ ችግሩ ቀላል አልነበረም::

ዳሩ ግን ጥቂት የማይባሉ ወገኖች ይህን አላወቁላቸውምና በመመስገንና በመወደድ ፈንታ ተሰደቡ:: ሞያቸውን ማድነቅ ሲቻል÷ ሥራቸውን መማርና መደገፍ ሲገባ ተናቁ÷ ተጠሉ:: የደረሰባቸው ስድብና ውር ደት በቀላሉ የሚገመት አይደለም:: ቢማሩ፣ቢጽፉ፣ቢደጉሱ ኮቸሮ ለቃሚ፣ጠንቋይ፣አስማተኛ፤ብርና ወርቅ ቢሠሩ አንጥረኛ፤ ብረት ቢሠሩ ቀጥቃጭ፣ቡዳ፣ ሞረቴ፣ ደበላንሳ /ጠይብ/፤ እንጨት ቢሠሩ አናጢ፣ እንጨት ቆርቋሪ ፤ቆዳ ቢፍቁ ጥንብ በላ፣ ፋቂ፤ ቢቆፍሩ÷ቢመነጥሩ ካንቻ መቺ፣ እንጨት ቆራጭ፤በበሬ ቢያርሱ አፈር ገፊ፣ ድኮ ታጣቂ፤ ግንበኛ ቢሆኑ ደንጊያ ቆርቋሪ ፣ ጭቃ ለዋሽ፣ ፉጋ እየተባሉ ለሥራቸው ሁሉ ስም እየተሰጠ ይሰድቡ ነበር::

ባለ እጅ ሰው በመሥራቱ ሲሰደብ የማይሠራው ሰነፍ ሰው ግን ቁጭ ብሎ እየዋለ፣ ጨርቁን ከአፍንጫው ላይ አድርጎ÷ እጁን አለስልሶ ሥራን እንደ ጠላት እየቆጠረ ጌታዬ ተብሎ ተወዶ፣ ተከብሮ በአጥንቱ በዘሩ እየኮራ ትልቅ ሰው ተብሎ ነበር የሚኖረው:: እነርሱ ወይም ልጆቻቸው ቢታመሙ የተግባረ እድ ባለሞያዎችን /ባለ እጆችን/ «ቡዶች ናችሁ፤ ልጆቻችንን በላችሁብን» እያሉ በፈጠራና በሐሰት ወሬ ቀሪውን ሕዝብ አሳምነውት ጥበበኛውንና ሠራተኛውን ባለ እጅ አሰደቡት:: በዚህ ምክንያት ጥበበኛው፣ሠራተኛው ሁሉ የሚያውቀውን ሥራ ለመሥራት ፍርሃትና ስጋት አደረበት:: የተካነበትን የተግባረ እድ ሞያውን ትቶ በቦዘኔነት መኖርን የመረጠ ባለእጅ ብዙ ነው:: በዚህም ሳቢያ የአገራችን የእጅ ሥራ ተዳክሟል ቢባል ከእውነት የራቀ አይሆንም:: ለአንድ አገር ዕድገትና ብልጽግና ደግሞ የተለያየ ሞያ ያላቸው ሰዎች ያስፈልጋሉ:: ሁሉም በየሞያው ጠንክሮ ሲሠራ ነው አገር የምታድገው ልማት የሚኖረው:: ሸማ ስለሚሠራው እንዲህ ተገጥሟል:-

*ጥበበኛውን ሰው ሸማኔን አንናቅ፣*
*ጥሩ አድርጎ የሚሠራ የሚያለብስ ጨርቅ፣*
*ስንቱን አካል ገላ ጉድ የሚደብቅ::*
*ሸማኔ ባይሠራ ገላ መሸፈኛ፣*
*ቅጠል ነበር ሰው ለብሶ የሚተኛ::*
*ሸክላ ሠሪ ሠርቶ ዕቃ ባያመጣ፣*
*ተጎንብሰን ነበር ወንዝ ውኃ የምንጠጣ፤*
*ዱቄትም ቢኖረን ሊጡን ብናቦካው*
*ምጣዱ ከሌለን ሊጡን አንጠጣው::*

እንደ ገለጽነው «ጨዋ» የተባለው ወገን ባለ እጆችን «ቡዳ» ይላቸዋል:: ሕፃናቱን፣ ከብቱን ...«በዐይናቸው አይተው ይበላሉ» ይሏቸዋል፤ ዐይነ ወግ እንዲሉ:: በዚህም ምክንያት ˚ በልጆቻቸው፣በከብቶቻቸው... አንገት ላይ «የቡዳ መድኃኒት» ይታሰርላቸዋል:: በማሳ ላይ የኾነ እንደሆነ ልዩ ልዩ መልክና ቅርጽ ያላቸውን ነገሮች በዘንግ አድርገው ያቆማሉ:: «ክፉ ዐይን ሰብሉን፣ ሕፃናቱን፣ከብቶቹን ሲያያቸው ዐይኑ ከገመዱና ከቆመው ነገር ላይ ያርፋል» ይባላል:: ልጆችም እንግዳ ሰው ፊት ከመቅረብና ከመታየት የሚከለከሉበት ምክንያቱ ይህ እንደሆነ ይነገራል:: /Wax and Gold, P.232/.

ከጊዜ በኋላ በጥንቆላ ፣ በአስማት ተግባር ላይ የተሰማሩ ሰዎች ለጥቅማቸው ሲሉ ይህንኑ ማኅበረ –ሥነ ልቡናዊ ሁኔታ /Social Psychology/ በመንተራስ ርኩስ መንፈስ /ጋኔን/ ያደረበትን ሰው «ቡዳ ነው የበላው፤ እኛ እናድነዋለን» በማለት ሥራ ሥሩን በማጠንና በማሸተት « የቡዳ መድኃኒት» እያሉ እየሸጡ ሲያስተዳድሩበት ኖረዋል:: ጥቂት የማይባሉ ሰዎችም ሲያማቸው ከማኅ በረሰቡ ሥነ ልቡናና የኑሮ ልምድ እንደ ተማሩት ወደ ጠንቋይና ባለዛር /ዐዋቂ ቤት/ ይሔዳሉ:: ባለዛሩም «ቡዳ ነው የበላህ» ይላቸዋል:: በዚህ ሁሉ ምክንያት «ቡዳ» ማለት ÷ «ቡዳ» መባል ልምድ ሆኖ እንደቀረ ይነገራል::

ቅዱሳን /የብርሃን/ መላእክት እንዳሉ ሁሉ ርኵሳን መላእክት /የጨለማ አበጋዞችና መናፍስት/ አሉ:: ርኩሳን መላእክት /አጋንንት/ በልዩ ልዩ መንገድ ይገለጻሉ:: «ሰይጣን ራሱ የብርሃንን መልአክ እንዲመስል ራሱን ይለውጣልና» እንዳለ ጭፍሮቹና አገልጋዮቹ ሥራቸውን የጽድቅ አገልግሎት ራሳቸውን የጽድቅ አገልጋዮች ለማስመሰል ራሳቸውን በተለያየ መንገድ ይለውጣሉ፤ ተአምራትን ያደርጋሉ:: ዘጸአ.7÷10–13፣22፤ ማቴ.24÷24፤ 2ቆሮ.11÷14–15፤ 2ተሰ.2÷9:: ይህም ብቻ ሳይሆን በሥነ ፍጥረት ሁሉ ተመስለው እንደ ሚያሳስቱ ቅዱሳት መጻሕፍት በሚሰጡ ት ምስክርነት ይተባበራሉ::

ዲያብሎስና ጭፍሮቹ አጋንንት ቅዱሳን መላእክትን፣ከወላጆቻችን ጀምሮ የምናውቃቸውን፣ የምናከብራቸውንና የለመድናቸውን ሰዎችን በመምሰል፤ የእነርሱ ፈጻምያነ ፈቃድ የኾኑ ሰዎችን ማኅደር አድርጎ አስማተኛ ፣ጠንቋይ፣መተተኛ፣ባለዛር በመኾን ብዙዎችን ያስታሉ:: *አስማተኛ፤* የሚባለው ምስጢሩ ኃይለ ቃሉና ፍቹ ያልተቃና ያልተገለጠ ስምን እየጠራ «መድኃኒት» የሚያደርግ ሰው ነው:: ዘዳግ.18÷10፤ 2ነገሥ. 17÷17፤ የሐዋ.19÷19፤ ራእ.22÷15:: ***ጠንቋይ*** የሚባለው መናፍስትን በመጥራት÷በድግምት [የተወሰኑ ቃላትን በመድገም አንድ ነገር እንዲሆን ወይም እንዳይሆን አደርጋለሁ ማለት]÷ በአስማት÷ በመተት በሌላም የሰውን ሁኔታ ወይም ነገርን ለመለወጥ÷የሚመጣውን ለመግለጥ እሠራለሁ የሚል ሰው ነው:: /ዘዳግ.18÷11፤ 1ሳሙ.28÷3፣የሐዋ.8÷9–24፤13÷6–12:: *መተተኛ* በሚባለው በርኵስ መንፈስ ኃይል ልዩ ልዩ ድንቅ ነገርን እሠራለሁ ባይ ነው:: <ዛር> ደግሞ ልዩ ልዩ ወረርሽኞችን፣የአካልና የአእምሮ ሕመሞችን ያመጣል የሚባል ክፉ መንፈስ ነው:: ዘጸአ.7÷11፤22÷18:: [*Zar* spirits are of many kinds; they may be male or female, <Christian> or Muslim, educated or unschooled, mischievous or somber. ***Zar*** are depicted as resembling the handsome, light-complexioned Abyssinians ... But they are great carriers of physical and mental illness. / Prof.Donald N.Levine, **Wax and Gold;** ***tradition and innovation in Ethiopian Culture***, 1965,pp 69-70 .]

እንግዲህ ሰይጣን «ፈረሴ» በሚላቸው እንዲህ ባሉ ሰዎች /ባለዛሮች/ ላይ አድሮ በማስጎራት፣በማስጮኸ፣ በመውጣትና በመግባት፤ በመሔድና በመምጣት፣ዐውደ ነገሥት በመዘርጋት፣ጋኔን በመሳብ፣ የጥንቆላ ሥራ በማሠራት ሰውን ከሰው ለማለያየት፣ ለማጋደል፣አንዱ ከአንዱ እንዳይገናኝ /እንዲገለል/ ያደርጋል:: ይህም ሁሉ ለትምህርትና





www.eotcmk.org

ለተግሣጽ በተጻፉልን የቅዱሳን ተጋድሎ ታሪክና የቅዱሳን መላእክት የተራድዖ ዜና ውስጥ የምናገኘው ነው::

አጋንንት ፈቃዳቸውን በሚፈጽሙ ፈጻሚዎቻቸው እያደሩ፣በሰዎች ኅጢ አስተሳሰቦችና ልምዶች እየተገቡ ማኅበራዊ ጥላቻንና መገለልን ከሚፈጥሩባቸው መንገዶች አንዱ የቡድነት ባሕል /ቡዳ መባል÷ቡዳ መሆን/ ነው፤ ይኸውም በአንዱ አድሮ «ሰውን የሚበላ» በሌላው አድሮ «እገሌ በላኝ» በማሰኘት ነው::

አለቃ ደስታ ተክለ ወልድ ቡዳ፣ጠይብ ወይም ባለ እጅን በተመለከተ «ገበታ ሐዋርያ» በተባለ መጽሐፋቸው ያሰፈሩትና ከዚህ በታች የምንመለከተው ታሪክ ሰይጣን ለፈቃዱ በዋሉለት ሰዎች እያደረ፣ ቀደም ሲል እንደ ተገለጸውም የሰዎች ኅጢ ልማዶችን እየተጠቀመ እንዴት እንደ ሚያታልለን የሚያስረዳ ነው::

«አንድ ይሁዳዊ የተግባረ እድ ባለሞያ /ፈላሲ/ ወደ አገራችን መጥቶ ከንጉሡ ጋር ባለሟል ኾነ:: ምክንያቱም አንጥረኛ ስለሆነ ወርቅና ብር እያፈሰሰ አልቦና ድኮት፣አንባርና ቀለበት፣ድሪና ማርዳ፣ሙጣና ጣፋ፣ጫማ በየዓይነቱ ጌጥና ሽልማት ዘውድም ከመሥራቱም የተነሣ ነው:: ያም ንጉሥ ቀጥቃጮቹንና አንጥረኞቹን ጠይብ የተባሉትንም ሁሉ እጅግ ወደዳቸው፤ ከአለቃቸውም ጋር ሁል ጊዜ ቆይታ ያደርግ ነበር::

ቀድሞ በቤተ መንግሥቱ የነበሩትን ጠቢባን /ብልሃተኞች/ ግን በዐይኑ ለማየት ጠላ:: የንጉሡ ጠቢባንም በተግባረ እድ ባለሞያዎቹ እጅግ ቀኑባቸው:: እነርሱንም ለማጥፋት ተማከሩ፤ ከእነርሱም አንዱ ወደ ወንዝ ሔዶ ጋኔን ኀተተ:: ጋኔኑም «ለምን ጠራኸኝ?» ቢለው እነዚህን ጠይቦች ከቤተ መንግሥት የሚያስወጣ፣እኛን የሚያስገባ፤ እነርሱን የሚያስጠላ እኛን የሚያስወድድ ብልሃት አድርግልኝ አለው:: መቼም ለሰይጣን ተንኮል ቅርቡ ነው፤ ሔጄ የንጉሡን ልጅ አሳብዳታለሁ:: ምን ሆንሽ ያላትም እንደ ኾነ የጠይቦቹ አለቃ በላኝ እያለች ትለፈልፋለች:: መድኀኒትህስ ምንድን ነው? ቢኋት ያንተን ስም ጠርታ «መድኀኒቴንና ምሴን ጠቢቡ እገሌ ያውቀዋል» ትላለች:: አንተን በዚያን ጊዜ ይጠሩሃል:: ማንኛውንም እንጨትና ሥር ትቀጠቅጥና ይዘህ መጥተህ ታጥናታለህ:: ያን ጊዜ እንደ ጅብ «አዉዉ» አሰኝቼ አተላ አስጠጥቼ እለቃታለሁ? ከዚህም በኋላ ጠይቦቹ ሁሉ ለብቻቸው በዋሻ ይኖራሉ እንጂ ቤተ መንግሥት አይደርሱም፤ በከተማው አይቀመጡም÷ አይኖሩም:: እናንተ ግን ከነገሥታቱ ጋር ባለሟሎች ትሆናላችሁ» ብሎ ነገረው፤ መከረው:: እንደ ነገረውም ኾነ:: ከዚያ ወዲህ «ጠይቦቹ ሰው ይበላሉ» ይባላል:: ጋኔኑም የማታለል ሥራውን ሲሠራ ይኖራል:: ደስታ ተክለ ወልድ÷ ገበታ ሐዋርያ÷ ገጽ 32::

እንግዲህ አብዛኛው የኅብረተሰብ ክፍል ባለማወቅ የተግባረ እድ ባለሞያዎችን «ቡዳ» ይበላቸው እንጂ «ቡዳ» የተባለው /ሊባል የሚችለውና የሚገባው/ ርኩስ መንፈስ /ጋኔን/ ነው:: ይኸውም ርኩስ መንፈስ /ጋኔኑ/ ፈቃዱን የሚፈጽሙትን በዚህም የሚያምኑትን ሰዎች ማኅደር አድርጎ ሌሎች ሰዎችን የሚወጋ ስለሆነ ኀዳሪው በማኅ ደሩ ይጠራል:: «ከሰው ዐይን ያውጣህ፤ ዐይነ ወግ» /Eye contact, Evil eye/ እንዲሉ:: አንዳንዱም ሰው በፍርሃት ስሜት ሕመም ሲያጋጥመው «ቡዳ በላኝ» ይላል:: ይኸውም ቀደም ብሎ በአእምሮው ያሰበውን ሲናገር ነው:: ሰይጣንም የሚጠቀምበት ይኸንኑ የሰውዬውን «የቡድነት ባሕል» እምነት /mentality/ ነው:: «ከቡድነት» ጋር በተገናኘ ስለ «ምስ» የሚነገረውና የሚታመነው ከዚሁ ጋር በጥብቅ የተያያዘ ነው::

በሌላ በኩል ቀደም ሲል እንደ ተገለጸው የ«ቡዳ» እምነት በድሮ ዘመን በበርካታ የዓለማችን ሕዝቦች ዘንድ ነበር፤ በአንዳንድ ሥፍራዎችም እስከ ዛሬ ድረስ አለ:: ሆኖም ሥልጣኔ በሚታይባቸው ቦታዎች የአስተሳሰቡ መጥፋት እና በአንጻራዊ መልኩ በዕድገት ወደ ኋላ በቀሩ ሥፍራዎች ብቻ ተወስኖ መቅረቱ የሚያሳየው ነገር ቢኖር «ቡዳ» የሚባለው አስተሳሰብ በብዙዎች ዘንድ እንደሚነገረው ዐይንና የብርሃን ጨረር ተባብረው የፈጠሩት ክፉ ክስተት ሳይሆን ኋላ ቀርነት /ዐላዋቂነት/ የወለደው ፍርሃትና ጭንቀት መሆኑን ነው:: በነገሮች ላይ ዐርፎ የተንጸባረቀው የብርሃን ጨረር ወደ ዐይናችን ገብቶ አንድን ቁስ ለማየት÷ ለመመልከት ያስችለናል እንጂ ከዐይናችን ወጥቶ ሰዎችን ለጉዳት አይሰጥም:: በርግጥ ፍርሃትና ጭንቀት የአእምሮ መታወክን ሊያመጣ ይችላል:: እንዲህ ዓይነት የአእምሮ መታወክ በሽታ (Psychiatric Problem) በአእምሮ ሐኪሞች ዘንድ «በባሕል ተጽዕኖ ሳቢያ የሚፈጠር የአእምሮ መታወክ» (Culture Bound Syndromes) ተብለው ነው የሚጠሩት:: ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ በዚህ መደምደሚያ ላይ ስምምነት ቢኖርም ችግሩ «ሥነ አእምሯዊ» አይደለም የሚል የባለሞያዎች አስተያየት /ጽንሰ አሳብ/ ይሰማል:: ይህንንም ለማለት ያስቻላቸው እንደሌሎቹ የአእምሮ ሕመሞች በአብዛኛው የዓለም ክፍል አለመገኘቱና ሕሙማኑም በየትኛውም ዓይነት የአእምሮ ሕሙማን መድኀኒት /Anti-psychiatric drugs/ ሊሻላቸው የማይችል በመሆኑ ነው:: «አማራጭ ሕክምና» /Alternate Medicine/ በሚባለው የሳይንስ ዘርፍ ደግሞ በሰዎች ላይ ለሚደርሱ ሕመሞች ከ/Elector magentic wave/ ሥርጭት ጋር በተገናኘ ትንታኔ ይሰጣል:: በዚህ መሠረት ማንኛውም ሰው የራሱ መለያ የሆነ የ/Electro magentic wave/ ሥርጭት ሲኖረው ሕመም በሰዎች ላይ የሚከሰተው ይህ ሥርጭት ሲረበሽ /disturbance/ መሆኑን ያብራራል:: በዚህ ሳይንሳዊ ትንታኔ መሠረት ስለ ቡዳ /Evil eye/ እንደተገለጸው አንዳንድ ሰዎች ከፍተኛ የሆነ /የተለየ/ የ/Electro magentic wave/ ስለ ሚረጩ÷ ይህም በሌላው ሰው ላይ ያለውን ሥርጭት ስለሚረብሽ ለተለያዩ የአእምሮና የአካል ችግሮች ያጋልጣል:: ይህም ትንታኔ ቢሆን በንድፈ አሳብ ደረጃ ያለና በአገራችን ካለው የ«ቡድነት» ባሕል ጋር ያለው ተያያዥነት ገናሊጤን የሚገባው ነው::

በአጠቃላይ በአርአያ ሥላሴ የተገኘ አዳማዊ ሰው በሥነ ተፈጥሮው አልያም በዘር ውርስ ማለሉ የኾነውን ሌላውን ሰው የሚወጋ /«የሚበላ»/ሆኖ አይደለም:: በዚህም መሠረት «ቡድነት÷ቡዳ መባል ÷ቡዳ መሆን» የግድ ከባለ እጆች /ከተግባረ እድ/ ባለሞያዎች ጋር ብቻ ተያይዞ የሚታይበት ሁኔታ ሊኖር አይችልም÷አይገባም:: በአንድ አገር ይኖር የነበረ ሰው ወደ ሚኀራበተው ሌላ አገር ሲጓዝ ከመንገድ ላይ ሳለ ይመሽበታል:: ከዱር እንዳይተኛ በአውሬ እንዳይበላ ስጋት ገባው:: ወደ ሰፈርተኞቹ ቤት እንዳይገባ ነዋሪዎቹ «ቡዶች» ናቸው ስለሚባል ፈራ:: እያመነታ መንገዱን ቀጥሎ እግሩ ወዳደረሰው መንደር በድፍረት ይገባና ያገኘውን ሰው «አንተ÷ የቡዶቹ ሰፈር የትኛው ነው?» ብሎ ይጠይቀዋል:: «እዚያ ማዶ ነው፤ ነገር ግን እነርሱም እኛን ቡዶች ይሉናል» አለና መለሰለት ይባላል::

ስለሆነም ጠያቂዎቻችን እንደ ተናገሩት ይህ አስተሳሰብ ለልማታችንና ለዕድገታችን ሁነኛ መሠረት ሊኾን የሚችለውን የአገር በቀል ቴክኖሎጂ ባለቤቶችን፣ ሥርዓተ ማኅበራችንንና አጠቃላይ የሥራ ባሕላችንን በእጅጉ የጎዳ በመሆኑ ፈጽሞ ሊታረም የሚገባው ነው::

በመሠረቱ «ቡድነት» ርኩሳን መናፍስትና በጭንቀት የታወከ አእምሮ የሚፈጥሩት÷ ይህንንም በእምነት የተቀበሉ ወገኖች የሚያስፋፉት ችግር መሆኑን ከተቀበልን መፍትሔውም ከዚያው ጋር በተገናኘ የሚቀመጥ እንጂ ከተግባረ እድ ባለሞያዎች /ባለ እጆች/ ጋር መያያዝ አይኖርበትም::

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንም ከረጅም ጊዜ ጀምሮ አጋንንት ያደሩበትን በሽተኛ ወደ ቤተ ክርስቲያን አምጥተው ለካህናት ያስታውቃሉ:: ካህኑም በሽተኛውን አስቀርበው ቅዱስ ወንጌልንና ድርሳነ ሚካኤልን ደግመው÷ ጸሎት አድርሰውለት በፈለቀውና በቅዱሳን ስም በተሰየመው ጠበል ወይም በዕቃ ውኃ ሞልተውና ባርከው ያጠምቁታል፤ በመስቀልም ያሹታል፤ በሽተኛውም ይጮኻል፤ ያደረበት ጋኔን /ርኩስ መንፈስ/ ለቅቄአለሁ ይላል:: ካህኑም ጌታችን እንደ ተናገረ መልሶ እንዳይነካው ያምሉታል:: በሽተኛውም ይድናል:: ሰብአዊ ፍጡር ሆኖ በዐይኖቹ እየወጋ ሰውን ይበላ ዘንድ የተፈጠረም ሆነ የሚፈጠር ሰው የለም:: አጋንንት ግን ዓላማቸው ሰውን ከሰው ማጣላትና ሰላምን ማደፍረስ ስለሆነ በሰው አድረው ጤናውን በመንሳት «እገሌ በላኝ» ብሎ እንዲለፈልፍ በማድረግ ሰውን «ሰው በላ» ያሰኙታል:: «ሰው በላ-ቡዳ» ሆኖ የተፈጠረ ሰብአዊ ፍጡር አለ ብሎ ማመን ፍጥረታትን ሁሉ መልካም አድርጎ የፈጠረውን እግዚአብሔርን መቃወም ነው፤ በመልኩና በምሳሌው የፈጠረውን ሰውን ይበላ ዘንድ «ቡዳ» የሚባል ሰው ፈጠረ ማለት ክህደት ነውና:: ስለሆነም በልማዳዊ አስተሳሰብና በኀጢ አሠራር ተተብትባ ራስንና አገርን ከመጉዳት ይልቅ «ቡድነትን» እና ከእርሱ ጋር የተያያዘውን ችግርና መፍትሔውን ሁሉ በዚህ ደረጃ ብቻ መመልከቱ ይበጃል እንላለን::

*ወስብሐት ለእግዚአብሔር*



www.eotcmk.org

# የደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤል ቤተ ክርስቲያን

ዲ/ን ፋሲል አስረስ

የአዲስ አበባ ከተማን ሙሉ ገጽታ ለመመልከት ዘመን ባፈራው አውሮፕላን ተሳፍሮ ወደ ታች በማየት ካልሆነ በስተቀር በየጊዜው ወደ ጎን እየሰፋ ከመጣው የከተማዋ ዕድገት አንጻር አስቸጋሪ ነው:: እንጦጦ ተራራ ላይ ግን የከተማዋን ከፊል ገጽታ መመልከት ይቻላል::


የ108 ዓመት ዕድሜ ያላትና ፈጣን ዕድገት በማሳየት ላይ የምትገኘው አዲስ አበባ በውስጧ ከ84 አብያተ ክርስቲያን በላይ የያዘች ስትሆን ለዚህች ከተማ ጥንተ መሠረቷ ግን የእንጦጦ ተራራ ነው::

ምሽት ላይ እንጦጦ ተራራ ላይ ሁኖ ለሚመለከታት የአዲስ አበባ ከተማ የተለያዩ ኅብር ባላቸው መብራቶች ያጌጠች ናት:: ቁጥራቸው ትንሽም ቢሆን የዘመኑ ጥበብ ያረፈባቸውን ሰማይ ጠቀስ ፎቆች ሲመለከቱ ከሚወዱት ሰው የመለየት ያህል ከእንጦጦ ተራራ ለመውረድ አስቸጋሪ ነው::

የእንጦጦ ተራራ የቀድሞ ስም «ኢንዶጥናህ» ይባል እንደ ነበር በቦታው የሚገኙ አባቶች ያስረዳሉ:: በ1262 ዓ.ም ዋና ከተማቸውን ቤተ አምሐራ መካነ ሥላሴ /ወሎ/ በማድረግ የነገሡት ዐፄ ይኩኖ አምላክ ሁለተኛ ከተማቸውን የዛሬዋ እንጦጦን የቀድሞዋን ኢንዶጥናህን አድርገው በማዕከልነት ሲጠቀሙበት እንደ ቆዩ ይነገራል::

በ1375 ዓ.ም እንደ ነገሡና ወሎ÷ ግሸን ደብረ ከርቤ የሚገኘውን የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ግማደ መስቀል ወደ ሀገራችን እንዲመጣ ማድረጋቸው የሚነገርላቸው ዐፄ ዳዊት ቤተ መንግሥታቸውን በእንጦጦ ተራራ ላይ አሠርተው የኖሩ ሲሆን በእንጦጦ ደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤል ቤተ ክርስቲያን ቅጽር ግቢ ውስጥ ያስፈለፈሉት ዋሻ አሁን ድረስ የቱሪስት መስሕብ ሁኖ ከተለያዩ ዓለማት የሚመጡ የውጭ ሀገር ሰዎችንና የሀገር ውስጥ ጐብኝዎችን ትኩረት በመሳብ የሚጐበኝ ነው::

የእንጦጦ ተራራ የቀደሙትን ነገሥታት ትኩረት የሳበች ለብዙዎቹም በመዲናነት ያገለገለች እንደ መሆኗ በ1508 ዓ.ም የነገሡት ዐፄ ልብነ ድንግል በኢንዶጥናህ /እንጦጦ/ ተራራ ላይ ያሳነፁት ቤተ መንግሥት ነበራቸው፤ ቤተ መንግሥቱ በውስጡ የተለያዩ የሥዕል ጥበባት የነበሩበት ሲሆን በዘመኑ ተነሥቶ የነበረው የግራኝ መሐመድ ወራሪ ጦር ንብረቶቹን በመዝረፍ፤ ቤተ መንግሥቱንና በውስጡ የነበሩትን ሥዕላት አቃጥሏል:: ዐፄ ልብነ



ድንግልም የረር÷ ባዱቄ በሚገኘው ቤተ መንግሥታቸው ሁነው ቃጠሎውን ሲመለከቱ ከፍተኛ ኀዘን ተሰምቷቸው መኳንንቶቻቸውን በመጥራት እንዳስረዱ በታሪክ ተዘግቧል::

ዐፄ ምኒልክ ደብረ ሊባኖስ ገዳም ሰንብተው ሲመለሱ ሱል ልታ ላይ ሰፍረው ነበር ይባላል:: ከዚያም እንዳሉ የዐፄ ዳዊት ቤተ መንግሥት ፍርስራሹ የተገኘ ለመሆኑ ስለ ተነገራቸው ምኒልክ እንጦጦ ላይ በዚያው በዐፄ ዳዊት ከተማ ቤተ መንግሥታቸውን እንደ ቆረቆሩ ታሪክ ያስረዳል:: ያኔ ነው ለዛሬዋ አዲስ አበባ መመሥረት ምክንያት የሆነው መሠረት የተጣለው::

ዐፄ ምኒልክ በ1574 ዓ.ም በእንጦጦ አፋፍ ላይ ከተማ ከቆረቆሩ ከሁለት ዓመታት በኋላ በ1876 ዓ.ም ባለቤታቸው ወ/ሮ ጣይቱ ብጡል የእመቤታችንን ቤተ ክርስቲያን እንዲሠሩ ዳግማዊ ምኒልክን ጠየቁ:: ንጉሡም በዘመኑ በነበረው ችግር የተነሣ «አናጢ ማግኘት አይቻልምና ቤተ ክርስቲያን ለመሥራት ያዳግታል» በማለት መልስ ሰጡ:: ወ/ሮ ጣይቱም «ከርስዎ ፈቃድ ላገኝ እንጅ ያንን የሚያስፈጽመው እግዚአብሔር ስለሆነ ይፍቀዱልኝ» በማለታቸውና አጥብቀውም በማጠናከር ስለማለዷቸው ከሆነ ልሽ ሥሪ ብለው ፈቀዱላቸው::

በዚያን ጊዜ ቤተ መንግሥቱን ለመሥራት ዘጠኝ አናጢዎች ከጐንደር መጡ:: ጣይቱም እነዚህን አናጢዎች ይፈቅ ዱላቸው ዘንድ ዐፄ ምኒልክን ጠየቁ:: ዐፄ ምኒልክም «የተጀመረው ቤተ መንግ ሥት ሲፈጸም እሰጥሻለሁ» ሲሉ ተስፋ ሰጧቸው::

ምኒልክም ከዚህ በኋላ ወደ ወሎ ሔደው ስለ ነበር ከዚያ ሲመለሱ በ1876 ዓ.ም ቤተ ክርስቲያኑ የሚሠራበት ቦታ ተከልሎ፣ መሬቱ ተባርኮ መሠረትም ተጣለ:: ዳግማዊ ምኒልክ ዳግም በጥር 30 ቀን 1977 ዓ.ም የቅዱስ ራጉኤል ቤተ ክርስቲያንን ለመሥራት በዘመኑ በነበሩት ግብፃዊው ሊቀ ጳጳስ አቡነ ማቴዎስ አማካይነት፤ ሊቀ ጳጳሱ እያጠኑ፣ ዐፄ ምኒልክም በሥርዓተ መንግሥት ቁመው ከዳዊት መዝሙረ ተዘክሮን እየደገሙ፣ ካህናቱም ልብሰ ተክህኖ ለብሰው፣ 150 መዝሙረ ዳዊት ውዳሴ ማርያምና ወንጌል ደግመው፤ በየማዕዘኑ አራት መቶ እግዚኦታ እያደረሱ ግብፃዊው ጳጳስ ጸሎት ካደረሱ በኋላ አራት ድንጋዮች ባርከው ለዳግማዊ ዐፄ ምኒልክ ሰጧቸው:: ንጉሠ ነገሥቱም የመሠረት ድንጋዮችን ከጳጳሱ እጅ በታላቅ ትሕትና ተቀብለው የመሠረት ድንጋዩን አኖሩ::

ሥራው ስድስት ዓመት ቆይቶ በ1882 ዓ.ም ጥቅምት 26 ቀን ተፈጸመ:: ዐፄ ምኒልክና እቴጌ ጣይቱ ከታላላቅ መኳንንትና መሣፍንት ጋር ተገኝተው ምእመናን በተገኙበት በዓሉ ተከብሮ ዑደት ከተደረገ በኋላ ታቦተ ሕጉ ወደ መንበረ ክብሩ ገብቷል::

/ወደ ገጽ ፴፫ ዞሯል/



www.eotcmk.org

# ቅድስት ማርያም ግብፃዊት

/ወልደ ሚካኤል/

በዐቢይ ጾም (ጾመ ኢየሱስ) መጀመሪያ ላይ በዮርዳኖስ ወንዝ አጠገብ በሚገኝ ገዳም ያሉ መነኰሳት÷ መዝሙር እየዘመሩ÷ ዮርዳኖስን አቋርጠው÷በዮርዳኖስ በረሃ÷ አንዱ ሌላውን በማያየው አቅጣጫ በርቀት ተበታትነው÷ መላ ጾሙን ፈጣሪያቸውን ብቻ እያዘከሩ ያሳልፉ ዘንድ ከገዳማቸው ይወጣሉ:: በበረሃው ከቆዩ በኋላ በሆሣዕና ዕለት ወደ ገዳማቸው ይመለሳሉ::

ከዚያ ገዳም መነኰሳት አንዱ የሆነው ቅዱስ ዞሲማስ:- ከእኔ የበለጠ የብሕትውና ሕይወት ያለውና እኔ ያልደረስኩበትን የብሕትውና ሕይወት የሚያሳየኝ አገኝ ይሆንን? የሚል የትዕቢት አሳብ እየተመላለሰበት ወደ በረሃው ውስጥ ርቆ ሔደ:: ድንገት የእግዚአብሔር መልአክ ተገልጦለት ራሱን ታናሽ አድርጎ የሚያይበትን ሁኔታ ወደሚያይበት ቦታ ወሰደው:: በጉዞው በሃያኛው ቀን ሲጸልይ ሳለ የሰው የመሰለ ረጅም ግራጫ ፀጉር ዓይነት ነገር ተመለከተ፤ ቅዠት ወይስ መንፈስ ወይስ የሰይጣን ምትሃት ነው? እያለ አሰበ:: ከዚያም ራቁት የሆነ የሰውነቱ ቆዳ እንደ ተቃጠለ ያህል በፀሐይ ሐሩር የጠቆረ የሰው አካል መሆኑን ተረዳ::

በበረሃ ከሚኖሩ ቅዱሳን ባሕታውያን አንዱን ለማግኘት ልቡ ደስ አለው፤ ወደዚያ ሰው ሲሮጥ ያ አካል ግን ከርሱ ይሸሻል፤ በተጠጋ ጊዜ "የእግዚአብሔር አገልጋይ ሆይ ከእኔ ለምን ትሸሻለህ? እባክህ ስለ እግዚአብሔር ብለህ ቆየኝ፤ እንደ እኔ ካለ ሽማግሌ ለምን ትሸሻለህ?" አለ:: ይህንን ባለ ጊዜ ያ ሰው በበረሃው ዓለቶች ውስጥ ካለ ጉድጓድ ነገር እንደገባ ሆኖ አየ፤ ዞሲማስም ተንበርክኮ እንደ ሕፃን አለቀሰ:: "ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ስትል አባት ዞሲማስ ሆይ ኮ ይቅር በለኝ፤ እኔ ሴት ስለ ሆንኩና ራቁቴን ስለ ሆንኩ ወደ አንተ ልመጣ አልችልም፤ ካባህን ወርውርልኝና በእርሱ ሰውነቴን ሸፍኜ እመጣ ዘንድ" አለችው:: እርሱም ስላወቀችውና በስሙ ስለ ጠራችው አደነቀ፤ ካባውን ወረወረላትና ያን ከለበሰች በኋላ ወደ ዞሲማስ ዞራ "ኃጥእ ሴት የምሆን እኔን ለማየት ለምን ትፈልጋለህ? ከእኔ ምን ለመስማትና ለመማር ትፈልጋለህ? አባት ዞሲማስ" አለችው:: ዞሲማስምኮ መሬት ላይ ወድቆ ትባርከው ዘንድ ለመናት:: እርሷ ግን ከፊቱ አጐንብሳ "አባት ዞሲማስ ካህን ስለ ሆንክና ብዙ ጊዜ ቅዱስ ቁርባን ስታደርግ የኖርክ ስለሆነ መባረክ የሚገባህ አንተ ነህ" አለችው:: እርሱ ግን በእንባ ሆኖ "የከበርሽ ቅድስት ሆይኮ አንቺ ለዓለም የሞትሽ እንደ ሆንሽ አያለሁ ከዚህ በፊት ሳታውቂኝና ሳታይኝ በስሜ ጠርተሽኛል፤ ካህን መሆኔንም አውቀሻልና እግዚአብሔር የሚያስደንቅ ጸጋ ሰጥቶሻል፤ ስለ እግዚአብሔር ብለሽ ቡራኬሽን ትሰጭኝ ዘንድ ጸሎትሽን እፈልጋለሁና" አላት:: እንዲህ እያለ በልመና በተናገረ ጊዜ "ለሰዎች ሕይወትና ለነፍሳቸው ድኅነት የሚያስብና የሚጠነቀቅ እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን" አለች፤ እርሱም "አሜን" አለ::

እርሷም "እንዲህ የተራቆተችና ከምግባር ድሃ የሆነች ሴትን ለማየት ለምን መጣህ?" አለችው:: ከዚያም ስለ ሕዝበ ክርስቲያን፣ ስለ ቤተ ክርስቲያን ጠባቂዎችኮ ስለ ነገሥታቱ ጠየቀችውኮ ቅዱስ ዞሲማስም "ቅድስት እናት ሆይኮ በአንቺ ጸሎት ክርስቶስ ለሁሉም ሰላም ሰጥቶአል፤ እኔም አንቺ ስለ ዓለም ሁሉ ትጸልዪ ዘንድ ስለ እኔ ስለ ኃጥኡም ትጸልዪ ዘንድ እማልድሻለሁ" አላት:: እርሷም "ካህን የሆንከው አንተ ለእኔና ለሁሉም ጸልይ፤ ሆኖም ታዛዥ መሆን ስለሚያስፈልግ ያዘዝከኝን በደስታ እፈጽማለሁ" አለች:: ከዚያም ፊቷን ወደ ምሥራቅ አዞራ፤ ዐይኖቿን ወደ ሰማይ አቅንታ፤ እጆቿን ዘርግታኮ ለረጅም ጊዜ መጸለይ ጀመረች::

ቅዱስ ዞሲማስም ለረጅም ጊዜ ስትጸልይ ተመልክቶ ከመሬት ላይ ወድቆ አለቀሰ:: ደጋግሞ "ፈጣሪዬ ሆይኮ ማረኝ" አለ:: አንድ ክንድ ያህል ከመሬት ከፍ ብላ ዐያት:: ቅዱስ ዞሲማስም ምናልባት መንፈስ እንዳትሆን ብሎ ተጠራጠረ:: በዚህ ጊዜ ወደርሱ መጥታ አነሣችውና "አባት ዞሲማስ ሆይ÷ እግዚአብሔር ከሰይጣንና ከወጥመዱ ይጠብቀን፤ እርሱ ከእኛ ጋር ያለው ጦርነት ጽኑዕ ነውና" ብላ አማተበች:: ይህን ዐይቶና ሰምቶ እንዴት ወደ በረሃው እንደ መጣች ታሪኳን እንድትነግረው ለመናት÷ "ስለ ክርስቶስ ብለሽ አትደብቂኝ÷ ይህን መናገርሽ ለውዳሴ ከንቱ ብለሽ አይደለምና÷ ነገር ግን ለእኔ ለኃጥኡና ለማይገባኝ እውነቱን ለመንገር እንጂ:: የእግዚአብሔር ድንቅ ሥራ ይገለጥ ዘንድ ነው እንጂ:: ወደዚህ በረሃ የመራኝ የምታገለግይው እግዚአብሔር የአንቺን ሕይወት ሊያሳየኝ ነውና ስለዚህ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ትቃወሚ ዘንድ አይገባምና" አላት::

እርሷም "አባቴ ሆይ÷ አስጸያፊ ሕይወቴን እነግርህ ዘንድ በጣም ያሳፍረኛል፤ አንተ እንደምታስበው አይደለም፤ ነገር ግን ታሪኬን ስትሰማ ሰው ከክፉ አውሬ እንደሚሸሽ ከእኔ ትሸሻለህ፤ በደሌንም መስማት አትችልም:: ሆኖም ሳታቋርጥ ስለ እኔ ትጸልይልኝ ዘንድ ሁሉንም ነገር እነግርሃለሁ" አለች:: ከዚያም እንባዋ በፊቷ እየወረደ ታሪኳን መናገር ጀመረች::

"የትውልድ ሀገሬ ግብፅ ነው:: ገና በዐሥራ ሁለት ዓመቴ ቤተሰቦቼን ትቼ ወደ እስክንድርያ በመሔድ ራሴን ከክብር አሳንስኩኮ ድንግልናዬን አጣሁኮ ከዚያም የዝሙት ፍቅር አደረብኝ፤ ለኃጢአት የነበረኝን ፍቅር ታውቅ ዘንድ ትንሽ በዝርዝር ልንገርህ:- ዐሥራ ሰባት ዓመት ሲሆነኝ ሰዎችን የሚያቃጥል የኃጢአት እሳት ሆኜ ኖርኩኮ ብዙ-ችን አሳትኩ፤ ገንዘብ እንኳ እንስጥሽ ሲሉኝ ገንዘቡን አልቀበልም ነበር፤ በእግዚአብሔርም አላምንም ነበር፤ ነገር ግን እንደ ፈለግኹ አደርጋለሁ፤ ማንም አይከለክለኝም እል ነበር::

ከዕለታት በአንድ ወቅትኮ ሊቢያውያንና ግብፃውያን ወደ ባሕር እየተቻኰሉ ሲሔዱ አይቼኮ ወዴት ሊሔዱ እንደ ሆነ ስጠይቃቸውኮ የክቡር መስቀልን በዓል በኢየሩሳሌም ሊያከብሩ መሆኑን እና ቀኑም መዳረሱን ነገሩኝ:: በዚህ ጊዜ እኔም ብዙ ወዳጆችን አገኝ ዘንድ አብሬያቸው ልሔድ ወሰንኩኝ:: የምከፍለው ለጉዞውም ሆነ ለምግብ ገንዘብ አልነበረኝም:: ነገር ግን ሰውነቴ አሳስቷቸው በዚያም ብዙችን አጠመድሁ፤ የሰይጣን መረብ ነበርኩ:: በዚህም እኔ በሰውነቴ ብዙችን ማሳት እንደምችል እየተኩራራሁ እናገር ነበር::

### በቤተ ክርስቲያኑ በር አጠገብ

በመጨረሻም በጣም ብዙ ተሳላሚዎች በጌታችን መቃብር ላይ ወደ ተሠራችው ቤተ ክርስቲያን ሲሔዱ ዐየሁ:: ሔደውም ምን እንደሚያደርጉ ላይ ወደድኩ:: በበሩ እየተጨናነቁ ሊያልፉ ከሚሞክሩት ብዙ ሰዎች ጋር አብሬ ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ልገባ ሞከርሁ:: ነገር ግን በድንገት ከበሩ ወደ ኋላ የሆነ ኃይል ሲገፋኝ ታወቀኝ:: ሌሎች ሰዎች ሁሉ በቀላሉ ይገባሉ፤ እኔ ግን አልቻልኩም፤ የሆነ ኃይል እንድመለስ ወደ ኋላ እየገፋኝ እንደ ሆነ ተሰማኝ::





www.eotcmk.org

በመጀመሪያ በውስጤ ሳቅሁ። ይህም ስለ ደከመኝ ወይም ሴት በመሆኔ ደካማ ስለ ሆንኩ ይሆናል ብዬ አሰብኩ። የምችለውን ያህል ለመግባት ሁለተኛ ሞከርኩ። ሆኖም ስላልቻልኩ በሩ ላይ ቆምኩ። ሦስትና አራት ጊዜ ከሞከርኩ በኋላ ግን ኃይሌ አለቀ።

እልፍ ብዬ ሔጄ በበሩ አጠገብ ቆምኩ። ደረቴን እየደቃሁ አለቀስኩ። ከልቤ ማዘን ጀመርኩ። ለምን አልገባም? እንዳልገባ የከለከለኝ የኃጢአቴ ብዛት ነውን? አልኩ። ያን ጊዜ የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያምን ሥዕል ከበሩ ላይ ዐየሁ። የእርሷን ገጸ ሥዕል ግርማና ውበት ባየሁ ጊዜ ያለፈ ኃጢአቴ ከፊቴ ቁልጭ ብሎ ታየኝ፤ በራሴ አፈርኩኝ፤ በደሌም አሰቃየኝ። ከዚያም ከእመቤታችን ሥዕል ሥር ወድቄ ጌታዬንና መድኃኒቴን ለመከተልና ለማገልገል ሌላ ዕድል አገኝ ዘንድ ተማፀንኩ። መድኃኔዓለም ኢየሱስ ክርስቶስን እንዲያድነኝና በመንገዱ እንዲመራኝ ለመንኩት። ቅዱስ መስቀሉን ካየሁ በኋላ ወዲያውኑ ዓለምንና ደስታዋን በሙሉ እንደምክድና እርሱ በሚመራኝ ለመሔድ ቃል ገባሁ። ከጸለይኩ በኋላ የመተማመን መንፈስ ተሰማኝ። ከቆምኩበትና ከጸለይኩበት ቦታ ተነሥቼ ከሚሔደው ተሳላሚ ጋር ተቀላቀልኩ። ከዚያም በፊት አልደርስበት ካልኩት ቦታ መድረስ ቻልኩ። ያለ ችግር ገብቼ ከተቀደሰው ቦታ ደረስኩ። መሬት ላይ ወድቄ ቅዱስ መስቀሉን በመንቀጥቀጥና በእንባ ሳምኩ፤ እስከ እኩለ ቀን ድረስ ራሴን ረሳሁ። መጨረሻም ከቤተ ክርስቲያኑ ወጥቼ ቃል ከገባሁባት ከዚያች የእመቤታችን ሥዕል ሥር ሆኜ የኃጥአንን ንስሐ የሚቀበል እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን፤ የከበርሽ እመቤት ሆይ ኃጥእት እኔ ሌላ ምን ማለት እችላለሁ፡ሕ አሁን ከበደሌ እርቅ ዘንድ ጊዜው ነው፤ በንስሓ መንገድ ምሪኝ አልኩ። ያን ጊዜ «ዮርዳኖስን ብትሻገሪ ዕረፍትን ታገኛለሽ» የሚል ድምፅ ሰማሁ። ይህን ሰምቼ እመቤታችን ሆይ አትተዪኝ ብዬ አለቀስኩ። ከዚያ በኋላ ቶሎ ቶሎ እያልኩ ተጓዝኩ፤ ከተጓዦች አንዱ ትንሽ ገንዘብ ሰጠኝና በዚያ ትንሽ ዳቦ ለመንገዴ ገዛሁ፤ እያለቀስኩ የከተማውን በር አለፍኩ፤ በማታ ከዮሐንስ መጥምቅ ቤተ ክርስቲያን ደርሼ ሌሊቱን ሁሉ በዚያ እያለቀስኩ አደርኩ። በጧት ካስቀደስኩ በኋላ የዮርዳኖስን ወንዝ ተሻግሬ ወደዚህ በረሃ ደረስኩ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ከሰው ተለይቼ ወደርሱ የሚመለሱትን በሚቀበል ከፈጣሪዬ ጋር እኖራለሁ።

ቅዱስ ዞሲማስ «እመቤት ሆይ በዚህ በረሃ መኖር ከጀመርሽ ስንት ዓመት ሆነሽ?» አላት። እርሷም «፵፯ ዓመት» አለችው። ከዚያም «በሕይወትሽ ከሆነው ለውጥ የተነሣ ይህን ሁሉ ዓመት ያለ መከራ ኖረሻልን?» አላት። እርሷም «አባት ዞሲማስ ሆይ ልናገረው ስለምፈራው ነገር ጠየቅኸኝ፤ በፈጣሪዬ ቸርነት ያለፍኩትን ፈተናና መከራ ባስታውሰው እንደገና የሚመጣብኝና የሚያሸንፈኝ እየመሰለኝ እፈራለሁና» አለችው። እርሱም «የተቀደስሽ እመቤት ሆይ ምንም አትደብቂኝ» አላት። «አባት ዞሲማስ ሆይ ዐሥራ ሰባት ዓመት ከአራዊት ጋር ስታገል ኖርኩ፤ በመጀመሪያ በዚህ በረሃ ሕይወት በጣም ከባድ ነበር፤ ያለፈ ሕይወቴንና ያሳለፍኩትን ደስታ እያሰብኩ እፈተን ነበር፤ በዚህ በምድረ በዳ የሚጠጣ የውኃ ጠብታ እንኳን ለማግኘት አስቸጋሪ ነበር፤ ከረሃብና ከውኃ ጥም እንዲሁም ከፀሐይ ሐሩር የተነሣ በጣም ተሰቃይቻለሁ፤ ብዙ ጊዜ እታመምና ለሞት የተቃረብኩ እሆን ነበር፤ ያለፈ ሕይወቴ ትዝታ ደጋግሞ ባሰቃየኝ ጊዜ መሬት ላይ ወድቄ እያለቀስኩ ጌታዬ እንዲረዳኝ እለምነው ነበር፤ እያስጨነቁኝ የነበሩትን ነገሮች እንዴት ልገልጽልህ እችላለሁ? በመጨረሻም ፍጹም ሰላም በልቤ ተሰማኝ፤ ፈተናውን ሁሉ አለፍኩ፤ ፈጣሪዬ የፈለግኹትን ሰጠኝ፤ ስላለፈ የተጎሳቆለ ሕይወቴና በደሌ አብዝቼ አልቅሻለሁ፤ በመጨረሻም እግዚአብሔር አጽናናኝ» አለችው። አባት ዞሲማስ ከቅዱሳት መጻሕፍት ስትናገር ሰምቶ «ቅዱሳት መጻሕፍትን ተምረሻልን?» አላት። እርሷም «የዮርዳኖስን ወንዝ ከተሻገርኩ ጀምሮ ዛሬ የአንተን ገጽ ከማይ በስተቀር ሰው አይቼ አላውቅም፤ መጻሕፍትንም አልተማርኩም፤ ነገር ግን ሕያው የሆነ የእግዚአብሔር ቃል ዕውቀትን ሰጠኝ፤ እናም የእኔ ታሪክ ይህ ነው» አለችው። «ከመጀመሪያ እንደ ነገርኩህ እኔ ኃጥእት ነኝና ጸልይልኝ» አለችው። ይህን ብላ በተመስጦ ራሷን ጐንበስ ካደረገች በኋላ ወደ ቅዱስ ዞሲማስ ተመልሳ «ወደ ፈጣሪዬ እስክሔድ ድረስ የነገርኩህን ለማንም አትናገር። አሁን በሰላም ሒድ» አለችው። «በሚቀጥለው ዓመት በጾመ ኢየሱስ እንደ ገዳሙ ልማድ ዮርዳኖስን አትሻገር። በዚያው በገዳሙ ቆይ። ልሒድም ብትል አይሆንልህም። በጸሎተ ሐሙስ በዮርዳኖስ ወንዝ ዳር ቅዱስ ቁርባንን ይዘህ ጠብቀኝ» ብላው በበረሃው ውስጥ ተሠወረችው። ቅዱስ ዞሲማስም በጉልበቱ ተንበርክኮ ቆማበት በነበረው ቦታ ላይ ሰግዶ ይህን ሁሉ ላሳየውና ላደረገለት ለፈጣሪው ምስጋና አቀረበ። ወዲያውም በረሃውን ተጉዞ መነኰሳቱ ወደ ገዳማቸው በሚመለሱበት ዕለት እርሱም በዚያ ቀን ከገዳሙ ደረሰ።

ለአንድ ዓመት ያህል ያየውን ለማንም አልተናገረም። እርሷንም በድጋሚ ያሳየው ዘንድ እግዚአብሔርን በጸሎት ይለምን ነበር። ያ ዓመት ለቅዱስ ዞሲማስ በጣም ረዘመበት፤ ዓመቱ ቢቻል ኖሮ ወደ አንድ ቀን ቢያጥር ናፈቀ። ዐቢይ ጾም ሲገባ በጣም ታመመና ተኛ፤ እርሷ እንደ ነገረችው ከገዳሙ ቀረ። በጸሎተ ሐሙስ የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም ይዞ እንዲሁም ትንሽ ቴምርና የተቀቀለ ምስር ይዞ በነገረችው ቦታ በዮርዳኖስ ወንዝ ዳርቻ ጠበቃት። ለብዙ ጊዜ ከጠበቃት በኋላ ምናልባት የእርሱ ለዚህ ጸጋ አለመብቃት አስቀርቷት ወይም መጥታ አጥታው እንዳይሆን አሰበ።

ከዚያም የዚህችን ባሕታዊት ገጽ በእርሱ ፈቃድ ያሳየው ዘንድ ወደ እግዚአብሔር ጸለየ። ከጸለየ በኋላ በዮርዳኖስ ወንዝ በውኃው ላይ ወደ እርሱ ስትመጣ አያት፤ እርሱም በፊቷ ሊሰግድላት ባለ ጊዜ በውኃው ላይ እየተራመደች እያለች «አባት ዞሲማስ ምን እያደረግህ ነው? አንተ የክርስቶስን ቅዱስ ምሥጢር ይዘሃል!» አለችው። ከዚያም በሰላምና በደስታ ሆና እንዲባርካት ጠየቀችውና ከቅዱስ ምሥጢር ተቀበለች። እጆቿን ወደ ሰማይ አንሥታ የእፎይታ መግለጫ በሆነ እንባ ሆና «ጌታዬ ሆይ እነሆ ባሪያህን እንደ ቃልህ አሰናብታትኮ ዐይኖቼ ማዳንህን አይተዋልና» አለች። ወደ ቅዱስ ዞሲማስም ተመልክታ «አባቴ ሆይ ከይቅርታ ጋር ሌላም ነገር ላስቸግርህ ነው፤ አሁን ወደ ገዳምህ በሰላም ተመለስ፤ የእግዚአብሔር ቸርነትም ይጠብቅህ በሚመጣው ዓመት መጀመሪያ ወዳገኘኸኝ ቦታ ተመልሰህና በዚያ እንደ ገና ታየኛለህ፤ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነውና» አለችው። እርሱም «እኔ የአንቺን እርአያነት ተከትዬ ወደ በረሃው ለመግባት እናፍቃለሁ» አላት። ከዚያም ያመጣላትን ትንሽ የሚቀመስ ነገር እንድትቀ ምስ ጠየቃት፤ እርሷም ምስሩን በጣቶቿ ጫፍ ነካችና ሦስት ፍሬዎችን ወስዳ በአፏ አደረገችና «የእግዚአብሔር ጸጋ ነፍስን በንጽሕና ለመጠበቅ በቂ ነው» አለች። እንዲጸልይላትም ጠየቀችው።

ከዚያም የዮርዳኖስን ወንዝ በውኃው ላይ እየተራመደች ተሻገረች። በበረሃውም ተሠወረች። እርሱም በመለየቱ እያዘነ ሔደ። በሁለተኛውም ዓመት ወደዚያው በረሃ ሔደ፤ ነገር ግን ያረፈ ሰውነቷን በአሸዋው ላይ ወድቆ ዐየ። ቅዱስ ዞሲማስ በጣም አዘነና በጉኗ ተንበርክኮ ለረጅም ጊዜ እያለቀሰ ለዚህ ጊዜ የሚገባ ጸሎት ጸለየ። ከዚያም የት እንደሚቀብራት ሲያወጣና ሲያወርድ ሳለ ከራሷ አ



www.eotcmk.org

ጠገብ በአሸዋው ላይ "አባት ዞሲማስ በጸሎተ ሐሙስ ማታ ወደ አምላክ ሔጃለሁ፤ የደካማዪቱ የማርያምን ሥጋ በዚህ ቦታ ቅበረው፣ አፈር ወደ አፈር ይመለስ ዘንድ፣ ስለ እኔም ጸልይልኝ" የሚል ተጽፎ ተመለከተ:: ቅዱስ ዞሲማስ ባለ ፊው ዓመት ከቅዱስ ቁርባን ምሥጢር ከተካፈለች በኋላ እንዴት በዚያው ቀንና ሰዓት እዚህ ቦታ እንደ ደረሰችና እንዳረፈችኮ ሥጋዋም ዓመቱን ሙሉ ምንም ሳይለወጥ በመ ቆየቱ ተገረመ:: በዚህ ጊዜ ከጫካው አንበሳ መጣና እግሮቿን ከላሰ በኋላ ለመቅበር የሚበቃ ጉድጓድ ቆፈረ:: አባት ዞሲማስ ለሁሉም ትጸልይ ዘንድ እየተማፀነ እግሮቿን በእንባው አጠበ፤ ከዚያም ሥጋዋን በአፈር ሸፈነ:: የቅድስት ማርያም ግብፃዊት ልመናዋ ይደረግልን፣ ረድኤትዋ አይለየን፣ በረከትዋ ይደርብን::

ምንጭ፡-በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክሰ/ት/ቤት ማ/መምሪያማኅበረ ቅዱሳን፥ ነገረ ቅዱሳን- ፤ የግቢ ጉባኤያት መማሪያ መጽሐፍ፥1997 ዓ.ም፥ ገጽ 210-215::

## ፕሮፌሰር ኤፍሬም ይስሐቅ ከአ.አ.ዩ የክብር ዶክትሬት ዲግሪ በተቀበሉበት ወቅት በግእዝ ቋንቋ ያደረጉት ንግግር

ክቡር ማእምር ወሰባዊ ፕረዚዳንት ግርማ ወልደ
ጊዮርጊስ ርእሰ ብሔር ዘኢትዮጵያ
ክቡር ፕሮፌሰር አንድርያስ እሸቴ ፕረዚዳንት
ዘአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ
ወኩልክሙ መምህራን ወሊቃውንት ዕድ ወአንስት ሰላም
ለክሙ
እስመ ቀዳሚ አዌድሰክሙ በዐቢይ ቃል
አንትሙ ዘኃረይክሙኒ ለዝንቱ ክብር
ዘተረከብኩ በማእከሌክሙ ለዝንቱ መዓርግ
ሰብአ አፍአሂ አልአሉኒ ወብዙኃን ዘብሔረ አሜሪካ
ኃረዩኒ ወአክበሩኒ ዳግመ በቤተ ሀርቫርድ
አርድዕት አሰይትባደሩ በድርሳነ ዜናሃ ለአፍሪካ
ይረውጹ ለምስጋና በአንተ ለምዩ::
ምንትኑ አንከ ዘዮም ክብር ተፈልጦቱ ወተሌልዮቱ::
ሰማእክሙ ከመ ተብህለ በምሳሌ ዘእስራኤላውያን
«ኢይከብር ነቢይ በሀገሩ ወበቤቱ» በአንተዝ እብለክሙ
ጸባብ አንቀጽ ወጽዕቅት ፍኖት አንተ ትወስድ ለክብረ
ሰብእ
በቤተ አቡሁ ወሀገሩ እፎኬ ፈድፈደ ክብር ዘብሔርዩ
ወአልቦ ዘይኄይሰኒ አንበለ ክብር ዘሕዝብዩ
በኩለ መዋዕለ ሕይወትዩ::
ተዐገሡ ኅዳጠ ወአርምሙ ከመ አንግርክሙ
ወአይድዕምሙ ለውሉደ ኢትዮጵያ ወደቀመዛሙርት
ለዝንቱ ቤት
በዝ መዋዕል ተሰምዓ ዜናሃ ለሃገሪትነ እምጽንፍ እስከ
አጽናፍ
ወበአምሳለ ኢትዮጵያ ዘናፈቅራ እኩይ ራዕይ በመስኮተ
ዝንቱ ዓለም
በከመ አሕዛብ ዘአደግደገ ሥጋሆሙ እምደዌ ወረኀብ
እስመ ሐሰተ ይትናገሩ አሐዱ ምስለ ካልኡ
ወይጽሕፉ ኩሎ እኩየ ላዕለ ኢትዮጵያ
ኢትዮጵያሰ ሀገረ ብርሃን ዘባረካ እግዚአብሔር
ምድር ሠናይት ዘብዙኃ አትክልት ወአዝርእት
ወልምላሜ ወማዕድናት
እስመ ይእቲ ብሔረ ፍስሓ ወፍግዕ ወተድላ
ወአፍላጋቲሃኒ ይውሕዙ ወይሰግሩ ላዕለ ወታሕተ
በድምፅ ዓቢይ ወይሜግቡ ምድረ ግብፅ::
አንተ ጥንታዊት ኢትዮጵያ እምፍጥረተ ዓለም ሥረዊሃ
ሀገር ብዕልት በጥበብ ወበሥነ ጽሑፍ በአጽንኦ ሃይ
ማኖት
ወበፊደላት ቀዳሚያት
በከመ ጸሐፈ ደምያኖ ዳጉኤስ ዘብሔረ ብርቱካን
ሕዝበ ኢትዮጵያሰ ርኅሩኃን አክባሬ ኩሉ ሃይማኖት
ወመፍቀሬ ኩሉ ሰብእ ወይነብሩ በኅብረት በተፋቅሮ
ወበሰላም ለብዙኃት ዓመታት::
ፍቁራንየ ድኅረ ሠላሰ ዓመታት ይመጽእ ዓመተ ምሕ
ረት ሐዲሷ
ንቁም ወንትቀበሎ ውእተ ዘመነ ሶቤሃ ይኩን ለነ
ዘመነ ተሐድሶ ወሐመልማል ዘኢትዮጵያ
ወዘመነ ፍትሕ ወርትዕ::
መንግሥት ባሕቲቱ ኢይክል ገቢረ ኩሎ
ወተግባሩ ዐቢይ ለመንግሥት ዓቂበ ሀገር ከመ ይብዛኅ
ሰላም ወሠናይ ወፍትሕ በአፍአ ወበውስጥ
ወተፋቅሮ ምስለ ኩሉ ሰብአ ዓለም::
ባሕቱ አብዕሎተ ሀገር ተግባረ ኩሉነ::
ንሕንጻ ለኢትዮጵያ በኩሉ ጥበብ
ዞቦቱ ኪን በወርቅ ወበብሩር
ኩሎሙ ሕዝበ ኢትዮጵያ ጽሙዓን ለትምህርት /መጽሐ
ፈ ብርሃን/
አዌስክ ዳግመ ለግብር::
ሑሩ ወመሀሩ ወሥርዑ ወሕንፁ ሀገሪትነ ኢትዮጵያ
በሐዲስ ዓመት ዘይመጽእ::
ተንሥኡ ወፈጽሙ ዘንተ ዐቢየ ግብረ::

ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር
ወስብሐት ለእግዚአብሔር በኩሉ ጊዜ

## የ 1996 ዓ.ም. የአራት ግቢ ጉባኤያት የአብነት ትምህርት አቅዋም

| ተ.ቁ | የግቢ ጉባኤው ስም | የአብነት ትምህርት የተጀመረበት ዓመት | የሚሰጡት ትምህርቶች በቅደም ተከተል | የተማሪዎች ብዛት | | መዓርገ ዲቁና የተቀበሉ | ማስታወሻ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ጎንደር ሕክምና ሳይንስ ኮሌጅ | ነሐሴ ወር 1995 ዓ.ም | •ጸሎተ ዘዘወትር<br>•ውዳሴ ማርያም<br>•አንቀጸ ብርሃን<br>•ይዌድስዋ መላእክት<br>•መልክአ ማርያም<br>•መልክአ ኢየሱስ መዝሙረ<br>•ዳዊት ቀጥርና ንባብ /የቅዳሴ ተሰጥዎ በተጓዳኝ ይሰጣል/ | 20 | 4 | ለመቀበል ተመርጠው የተዘጋጁ አሉ | ●ከ1995 ዓ.ም ቀደም ብሎ በራሳቸው ተነሣሽነት በየአጥቢያው ተምረው ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሱ አምስት ያህል ተማሪዎች አሉ::<br>●በአሁኑ ወቅትም ከመደበኛው የአብነት ትምህርት ውጭ የግስ አገሳሰስንና የግስ እርባታን፣ አገባብንና የንባብን ስልትን የሚማሩ 40 ያህል ተማሪዎች አሉ:: ከእኒህም ሦስቱ ሴቶች ናቸው:: |
| 2 | ጅማ ዩኒቨርስቲ | ነሐሴ ወር 1991 ዓ.ም | ከላይ የተገለጹትን ጨምሮ፡- የዜማ ቃል ትምህርት /የውዳሴ ማርያም ዜማ ከሰላም ለኪ ጀምሮ፥ መስተጋብእ፣ አርባዕት፣ አርያም፣ ሠለስት፣ ክሥተት፣ መወድስ፣ ስብሐተ ነግህ፣ ጾመ ድጓ /ቅኔ /የግስ አገሳስ፣ የግስ እርባታ፣ ጉባኤ ቃና፣ ዘአምላኪየ | 200 ያህል ተማሪዎች ያሉ ሲሆን ከእኒህም 1/3ኛዎቹ ሴቶች ናቸው:: | | 14 | ●ተማሪዎች ዲቁና ከተቀበሉ በኋላ ግብረ ዲቁናን በተጓዳኝ እንዲማሩ ይደረጋል::<br>●ለወደፊቱ የመጽሐፍ ትርጓሜን ትምህርት ለመጀመር ይታሰባል::<br>●ዲቁና በዓመት ሁለት ጊዜ በአማካይ ለዐሥር ያህል ተማሪዎች ይሰጣል:: |
| 3 | ዓለማያ ዩኒቨርስቲ | 1992 ዓ.ም | •ጸሎተ ዘዘወትር<br>•ውዳሴ ማርያም<br>•አንቀጸ ብርሃን<br>•ይዌድስዋ መላእክት<br>•መልክአ ማርያም<br>•መልክአ ኢየሱስ ቀጥርና ንባብ | 67 | 30 | አምስት | |
| 4 | አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ስድስት ኪሎ ግቢ ጉባኤ | መስከረም ወር 1995 ዓ.ም | ከላይ በዓለማያ ግቢ ጉባኤ የተጠቀሱትን ትምህርቶች ቀጥርና ንባብ ጨምሮ የዜማ ቃል ትምህርት፣ ሙሉ የፍሬ ቅዳሴ ትምህርት በደብረ ዐባይ ዜማ ይሰጣል:: | 40 | 24 | 13 | -በማኅደረ ስብሐት ቅድስት ልደታ ለማርያም ቤተ ክርስቲያን በሳምንት ሁለት ቀን የሚማሩ 35 ያህል የቅድስት ማርያም ኮሌጅ ግቢ ጉባኤ ተማሪዎችም አሉ::<br>- በቀጣይነት በዓመት እስከ ኀምሳ ተማሪዎችን ሁለት ጊዜ ዲቁና የማስጠት ዕቅድ አለ:: |

ምንጭ:- ከየግቢ ጉባኤዎቹ የአመራር አባላት፣የአብነት መምህራንና ተማሪዎች ጋር የተካሔደ ቃለ ምልልስ



www.eotcmk.org

# የአብነት ትምህርት በግቢ ጉባኤያት

/አሉላ ጥላሁን/

በዚህ ጽሑፍ የአብነት ትምህርት ቤቶች የምንላቸው በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ግቢ ጉባኤያት ሰበካ በሚገኙ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ቅጽር ውስጥ ያሉ የቤት ታዛዎች፣ የዋርካ ጥላዎች፣ የመምህራን መኖሪያ ቤቶች፣ የስብከተ ወንጌል አዳራሾችና የመሳሰሉት ናቸው:: የመማር ማስተማር ሒደቱም በአንድ ወይም በተቀራረበ ደረጃ ያሉ ጀማሪ ወጣቶች የሚማሩባቸውን መጻሕፍት ይዘው እንደ መጡበት ጊዜ/እንደ አደራረሳቸው/ በቡድን በቡድን በመሆን የተመሳለሰ የቃል ጥናት በንባብ ያካሒዳሉ:: ይኸውም ከዘወትር ጸሎት ጀምረው ውዳሴ ማርያምን፣ አንቀጸ ብርሃንን፣ ይዌድስዋ መላእክትን፣ መልክአ ማርያምንና መልክአ ኢየሱስን እንዲሁም መዝሙረ ዳዊትን እስከ ሁለት ጊዜ በመድገም የቃል ጸሎት ትምህርት ያከናውናሉ፥ አራቱን የንባብ ሕጎች /ተነሽ፣ ተጣይ፣ ሰያፍ፣ ወዳቂ/ ለይተው ያውቃሉ:: በዚህም ከንባብ ቤት ወደ ዜማ ቤት ይዛወራሉ፤ በዜማ ቤትም ቀደም ሲል በንባብ የተማሯቸውን መጻሕፍት በዜማ ያጠኗቸዋል:: በይዘቱም ከውዳሴ ማርያም አንሥቶ ምዕራፉን፣ ጾመ ድጓንና ቅዳሴን ያካትታል:: ከዚህ በኋላ ወደ ቅኔ ቤት ተሸጋግረው የግስና ነባር ጥናት፣ በመጠኑ አካሒደው እስከ ዘአምላኪየ የደረሱ አሉ:: አካዳሚያዊ ትምህርታቸውን አጠናቅቀው ከሚማሩበት ተቋም ተመርቀው ከወጡም በኋላ ሁለት ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ በዚያው ሳሉ የወጠኑትን የመጽሐፍ ቤት ትምህርት አጠናክረው በመቀጠል አስተካክለው ለማንበብ፥ ለመተርጐምና ምሥጢር ለማደላደል ምንም ያህል ያልቀራቸው ጥቂት የማይባሉ ወጣት ሊቃውንት አሉን::

በርግጥ የአብነት ትምህርት ስንል የአሥራው፣ የአባትነት፣ የመምህርነት፣ የምስክርነት ትምህርት ማለታችን ሲሆን የአብነት /የምስክር/ ትምህርት ቤት ስንል ደግሞ የዜማውን ይትበሃል ዘልቀው፣ በቅኔው መንገድና ድርሰት ተራቅቀው፣ በመጻሕፍት የምሥጢር ባሕር ጠልቀው ገብተው ዋኝተው የሚወጡባቸውን ቤተ ጉባኤያት ማመልከታችን ነው:: ከዚህ አኳያ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በግቢ ጉባኤያት የሚሰጠው ትምህርት:-

- በአጀማመሩ የፊደላትን ስም ከመልካቸው፣ ከቁጥራቸው እንዲሁም ከግእዝ አቆጣጠር ጋር አያካትትም፤
- በፊደለ ሐዋርያ ደረጃ የ«መልእክተ ዮሐንስ»ን ግእዝ በማጋዝ፣ ውርድ /ንዑስ/ ንባብና ቁም/ዐቢይ/ ንባብ የሚካሔድበት የዘር መለያ፥ የንባብ መማሪያ የሚከናወንበት ሁኔታ የለም፤
- በግብረ /ገቢታ/ ሐዋርያ ደረጃ ሳይቆጥሩና ሳያግዙ ተነሺውንና ተጣዩን፥ ሰያፉንና ወዳቂውን፥ ሩቁንና ቅርቡን፥ ወንዱንና ሴቱን፥ ነጠላውንና ብዙውን ለይቶ ዘርፉንና ባለቤቱን አገናኝቶ ያለ ምልክት አቃንቶ ለንባብ አስቸጋሪ መስለው የተገመቱትን የንባብ መለያ መጻሕፍት /መጽሐፈ ግንዘት፣ አርጋኖን፣ መቅድምና ተአምረ ማርያም፣ ተአምረ ኢየሱስ፣ ውዳሴ አምላክና መጽሐፈ አርድእት፣ ሃይማኖተ አበው፣ ስንክሳር/ በአትሮንስ ላይ ዘርግቶ ማንበቡ አይታይም፤ ተማሪዎች ፊደል የሚገድፉ ጸሐፊያን ሆነው እንዳይገኙ የፊደልን ዓይነት፥ ቅርጽና አገባብ እንዲሁም የሥርዓተ ነጥቦችን አቀማመጥ ጠንቅቀው የሚማሩበት የጽሕፈት ትምህርት አይታይም፤
- የግብረ ገብነትና የእምነት አናቅጽ ያሉባቸውን መጻሕፍተ ሰሎሞንን፣ መጽሐፈ ሢራክን፣ መጽሐፈ ዲድስቅልያን መማርንና ማስተማርን አይጨምርም፤
- መዝሙረ ዳዊቱን ከመድገም ጋር አብረው የተጠረዙትን መኃልየ ነቢያትንና የሰሎሞንን መኃልየ መኃልይ አይመለከቱም:: በመሠረቱ ግን የፊደል ሥርዓተ ትምህርት፣ ፊደለ ሐዋርያና ግብረ /ገቢታ/ ሐዋርያ ለንባብ ቤት መነሻና መሠረት መሆናቸው ይታወቃል::

ከዚህም ከፍ ሲል ግቢ ጉባኤያቱ የቤተ ክርስቲያናችንን ጥንታዊና ትውፊታዊ የትምህርት ተቋማት፥ «የአብነት ትምህርት ቤት»፥ የሚያሰኙት:- ድጓ በጉንፎቹ፥ ድጓ ውኃው የዜማ ሊቃውንት፣ ዘራፊና ምስክር የኾኑ ባለ ቅኔዎች፣ አቋቋም ዐዋቂ ኾነው የማኅሌቱን የመቆም ሥነ ሥርዓት፥ የዜማውን ስልትና ዐቅድ በአጠቃላይ የአገልግሎቱን ልክና መልክ የጠነቀቁ ምሁራን፣ አራት ዐይና፥ ምሥጢር ተመራማሪ፥ ኃይለ ቃሉን አነጻጻሪ፥ በላኤ መጻሕፍት የተባሉ መተርጉማን የማይገኙባቸው፤ ለተማሪዎቹም የብቃት ማረጋገጫ ማኅተም የማይሰጥባቸው ናቸው::

ይሁንና የቱንም ያህል የተጠቀሱት ጉድለቶች ቢኖሩ፥ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች ስለ ሃይማኖትና ሃይማኖተኝነት፤ ስለ ቤተ ክርስቲያን ትምህርትና አገልግሎትዋ ከዐሥርተ ዓመት በፊት ከነበሩበት የእምነት፣ የአመለካከትና የሥነ ምግባር ችግር አኳያ ቀደም ሲል እንደ ተገለጸው በአሁኑ ወቅት በአብነት ትምህርቱ የተኬደበት ርቀት መሠረታዊና አበረታች ለውጥ ነው ሊባል ይችላል::

***ዛሬ የግቢ ጉባኤያት ተማሪዎች በአብነት ትምህርቱ የመማር ማስተማር ሒደት ተሳታፊዎች በመኾናቸው:-***

- ጥንታዊው ሥርዓተ ትምህርት ትውፊታዊ አቋሙን ጠብቆ በዘመናዊ መልክ የሚቀርብበት መሠረት በመጣል ላይ ይገኛል::
- በገንዘቡ፣ በዕውቀቱና በጉልበቱ ለቤተ ክርስቲያን የሚሠራው ምሁሩ ወጣት በአመዛኙ በአፍኣ /በዐውደ ምሕረት፣ በቢሮና በመስክ/ ተወስኖ የነበረው ትጋቱ በሥልጣነ ክህነት፣ በቅኔ ማኅሌትና በመቅደስ ውስጥ አገልግሎት ጥልቀት የሚያገኝበት ሁኔታ ተመቻችቷል::
- የቤተ ክርስቲያን ዋነኛ ተልእኮ የኾነው የመቀደስና የማወደስ አገልግሎት በቀሳውስት፣ በዲያቆናትና በደባትር እጥረት ተገትቶ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት እስከ መዘጋት የሚደርሱበት ችግር ከመሠረቱ ሊፈታ ተስፋ መሰነቅ ጀምረናል::
- በሁለት ዓይነት ትውልድ፣ በሁለት ዓይነት ትምህርት ቤት፣ በሁለት ዓይነት ሥርዓተ ትምህርት በማለፋቸው የተራራቁት ዘመናዊውና የቆሎ ተማሪው የማይተዋወቁበት ዘመን አልፎ፤ ዘመናዊው /የቀለሙ/ ተማሪ ቢጋች የኾነውን የቆሎ ተማሪ፥ የዕለት ተዕለት መከራና ጥንካሬ በቅርበት ተረድቶ በቁጭት የሚነሣሣበት፤ በአንጻሩም በማኅበራዊውና በተፈጥሮው ሳይንስ ልዩ ልዩ መስኮች ምሁርነቱ ከፍ ያለ አስተያየት የሚደረግለት የቀለሙ /ዘመናዊው/ ተማሪ የጥንታዊውና ትውፊታዊው ተቋም ሥርዓተ ትምህርት ተሳታፊ ሆኗል:: ስለዚህም የአበውን ትምህርት፣ ሥርዓት፣ ሥነ ምግባር፣ ክርስቲያናዊ ኑሮና ታሪክ ለዚህ ትውልድ እንዲደርስ ታላቅ አስተዋፅዖ አድርገው ሳለ ዘመኑ ሲገፋ እነርሱ ግን በነበሩበት በመቅረታቸው ብሶት የሚሰማቸውን የአብነት መምህራንንና ተማሪዎችን ልብና መንፈስ ለዘመናዊው ትምህርት እንዲነሣሣ፣ ያላቸውንም እንዲያከብሩትና እንዲጠብቁት አግዟቸዋል::
- ምሁሩ ወጣት ለሚፈለግበት የሞያ ሥነ ምግባርና ጠንካራ ስብእና ዓይነተኛ መሠረት የኾኑትን ጽኑ እምነት፣ ቅን መንፈስ፣ ትዕግሥትና ትሕትና በአብነት ትምህርቱ የመማር ማስተማር ሒደት ሊያገኛቸውና ሊላበሳቸው ችሏል:: ይህም ቤተ ክርስቲያን ለሥራ ባሕል መዳበርና ለአገር ዕድገት እንቅፋት ሳትሆን የሥልጣኔ በር ከፋችና ፍኖተ አእምሮ አደራጅ ለመሆንዋ የተግባር ማረጋገጫ ሆኗል::
- ምሁሩ ወጣት ከሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያንና ከአበው ካህናት ጋር በአሳብና በቋንቋ እንዲግባባ፤ በውስጥ በአፍኣ አገልግሎቱ የታመነ እንዲሆንና ተቀባይነቱ እንዲጐላ ረድቶታል::
- የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በቀለሙ ትምህርት፥ የግቢ ጉባኤያት በአብነት ትምህርት አንፀውና ቀርጸው የሚያወጧቸው ወጣቶች የነገ የቤተ ክርስቲያን አባቶችና የአገር መሪዎች ሲሆኑ በተሞላ ስብእናቸው ለሕዝባቸው ኩራትና ክብር እንደሚሆኑ የኮፕት ቤተ ክርስቲያንን ጳጳሳት፥ መነኮሳትንና ካህናትን እንደ አብነት በመጥቀስ ተስፋ የሚያደርጉ ወጣቶች አያሌ ናቸው::
- በአጠቃላይ በሥርዓተ ትምህርት ያለ መጣጣም ችግሮች ሳቢያ በመንፈሳዊው ተማሪና በቀለሙ ተማሪ መካከል የነበሩት የኑሮ፥ የአመለካከትና የባሕል ጽንፈኛ አቅጣጫዎች ለተፈጠረው የትውልድ ክፍተት ጥንተ ምክንያት በመኾን አንደኛው ሌላውን ባለማወቁ አንዱ ከሌላው የሚያገኘውን ጥቅም አስቀርቶት ነበር:: ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በግቢ ጉባኤያት በሚሰጠው የአብነት ትምህርት ግን ክፍተቱ በመሞላት ላይ ይገኛል:: ይህም እንግዲህ ዓላማው ሩቅ ግቡ ጥብቅ እንደ መኾኑ መጠን ያለ አንዳች ችግር የተገኘ ውጤትና ተስፋ አይደለም::

## በመማር ማስተማሩ ሒደት ካጋጠሙት ችግሮች መካከልም:-

- የግቢ ጉባኤያት ተማሪዎች /በተለይ ደግሞ እኅቶች/ የአቻዎቻቸውንና የሌሎች ሰዎችን አሉታዊ አመለካከት፣ አካዳሚያዊ ጫናና ተያያዥ ውጥረቶች ተቋቁመው





www.eotcmk.org

# የአብነት ትምህርት በግቢ ጉባኤያት

/አለሳ ጥላሁን/

በዚህ ጽሑፍ የአብነት ትምህርት ቤቶች የምንላቸው በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ግቢ ጉባኤያት ሰበካ በሚገኙ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ቅጽር ውስጥ ያሉ የቤት ታዛዎች፣ የዋርካ ጥላዎች፣ የመምህራን መኖሪያ ቤቶች፣ የስብከተ ወንጌል አዳራሾችና የመሳሰሉት ናቸው:: የመማር ማስተማር ሒደቱም በአንድ ወይም በተቀራረበ ደረጃ ያሉ ጀማሪ ወጣቶች የሚማሩባቸውን መጻሕፍት ይዘው እንደ መጡበት ጊዜ/እንደ አደራረሳቸው/ በቡድን በቡድን በመሆን የተመሳለሰ የቃል ጥናት በንባብ ያካሒዳሉ:: ይኸውም ከዘወትር ጸሎት ጀምረው ውዳሴ ማርያምን፣ አንቀጸ ብርሃንን፣ ይዌድስዋ መላእክትን፣ መልክአ ማርያምንና መልክአ ኢየሱስን እንዲሁም መዝሙረ ዳዊትን እስከ ሁለት ጊዜ በመድገም የቃል ጸሎት ትምህርት ያከናውናሉ፤ አራቱን የንባብ ሕጎች /ተነሽ፣ ተጣይ፣ ሰያፍ፣ ወዳቂ/ ለይተው ያውቃሉ:: በዚህም ከንባብ ቤት ወደ ዜማ ቤት ይዛወራሉ፡ በዜማ ቤትም ቀደም ሲል በንባብ የተማሯቸውን መጻሕፍት በዜማ ያጠኗቸዋል:: በይዘቱም ከውዳሴ ማርያም አንሥቶ ምዕራፍን፣ ጾመ ድጓንና ቅዳሴን ያካትታል:: ከዚህ በኋላ ወደ ቅኔ ቤት ተሸጋግረው የግስና ነባር ጥናት፣ በመጠኑ አካሒደው እስከ ዘአምላኪየ የደረሱ አሉ:: አካዳሚያዊ ትምህርታቸውን አጠናቅቀው ከሚማሩበት ተቋም ተመርቀው ከወጡም በኋላ ሁለት ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ በዚያው ሳሉ የወጠኑትን የመጽሐፍ ቤት ትምህርት አጠናክረው በመቀጠል አስተካክለው ለማንበብ፥ ለመተርጐምና ምሥጢር ለማደላደል ምንም ያህል ያልቀራቸው ጥቂት የማይባሉ ወጣት ሊቃውንት አሉን::

በርግጥ የአብነት ትምህርት ስንል የአሥራው፣ የአባትነት፣ የመምህርነት፣ የምስክርነት ትምህርት ማለታችን ሲሆን የአብነት /የምስክር/ ትምህርት ቤት ስንል ደግሞ የዜማውን ይትበሃል ዘልቀው፣ በቅኔው መንገድና ድርሰት ተራቅቀው፣ በመጻሕፍት የምሥጢር ባሕር ጠልቀው ገብተው ዋኝተው የሚወጡባቸውን ቤተ ጉባኤያት ማመልከታችን ነው:: ከዚህ አኳያ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በግቢ ጉባኤያት የሚሰጠው ትምህርት:-

- ☞ በአጀማመሩ የፊደላትን ስም ከመልካቸው፣ ከቁጥራቸው እንዲሁም ከግእዝ አቆጣጠር ጋር አያካትትም፤
- ☞ በፊደለ ሐዋርያ ደረጃ የ«መልእክተ ዮሐንስ»ን ግእዝ በማጋዝ፣ ውርድ /ንዑስ/ ንባብና ቁም/ዐቢይ/ ንባብ የሚካሔድበት የዘር መለያ፥ የንባብ መማሪያ የሚከናወንበት ሁኔታ የለም፤
- ☞ በግብረ /ገበታ/ ሐዋርያ ደረጃ ሳይቆጥሩና ሳያግዙ ተነሺውንና ተጣዩን፥ ሰያፉንና ወዳቂውን፥ ሩቁንና ቅርቡን፥ ወንዱንና ሴቱን፥ ነጠላውንና ብዙውን ለይቶ ዘርፉንና ባለቤቱን አገናኝቶ ያለ ምልክት አቃንቶ ለንባብ አስቸጋሪ መስለው የተገመቱትን የንባብ መለያ መጻሕፍት /መጽሐፈ ግንዘት፣ አርጋኖን፣ መቅድምና ተአምረ ማርያም፣ ተአምረ ኢየሱስ፣ ውዳሴ አምላክና መጽሐፈ አርድእት፣ ሃይማኖተ አበው፣ ስንክሳር/ በአትሮንስ ላይ ዘርግቶ ማንበቡ አይታይም፤ ተማሪዎች ፊደል የሚገድፉ ጸሐፊያን ሆነው እንዳይገኙ የፊደልን ዓይነት፥ ቅርጽና አገባብ እንዲሁም የሥርዓተ ነጥቦችን አቀማመጥ ጠንቅቀው የሚማሩበት የጽሕፈት ትምህርት አይታይም፤
- ☞ የግብረ ገብነትና የእምነት አናቅጽ ያሉባቸውን መጻሕፍተ ሰሎሞንን፣ መጽሐፈ ሲራክን፣ መጽሐፈ ዲድስቅልያን መማርንና ማስተማርን አይጨምርም፤
- ☞ መዝሙረ ዳዊቱን ከመድገም ጋር አብረው የተጠረዙትን መኃልየ ነቢያትንና የሰሎሞንን መኃልየ መኃልይ አይመለከቱም:: በመሠረቱ ግን የፊደል ሥርዓተ ትምህርት፣ ፊደለ ሐዋርያና ግብረ /ገበታ/ ሐዋርያ ለንባብ ቤት መነሻና መሠረት መሆናቸው ይታወቃል::

ከዚህም ከፍ ሲል ግቢ ጉባኤያቱ የቤተ ክርስቲያናችንን ጥንታዊና ትውፊታዊ የትምህርት ተቋማት፥ «የአብነት ትምህርት ቤት»፥ የሚያሰኙት:- ድጓ በጉንፎ፥ ድጓ ውኃው የዜማ ሊቃውንት፣ ዘራፊና ምስክር የኾኑ ባለ ቅኔዎች፣ አቋቋም ዐዋቂ ኾነው የማኅሌቱን የመቆም ሥነ ሥርዓት፥ የዜማውን ስልትና ዐቅድ በአጠቃላይ የአገልግሎቱን ልክና መልክ የጠነቀቁ ምሁራን፣ አራት ዐይና፥ ምሥጢር ተመራማሪ፥ ኃይለ ቃሉን አነጻጻሪ፥ በላኤ መጻሕፍት የተባሉ መተርጕማን የማይገኙባቸው፤ ለተማሪዎቹም የብቃት ማረጋገጫ ማኅተም የማይሰጥባቸው ናቸው::

ይሁንና የቱንም ያህል የተጠቀሱት ጉድለቶች ቢኖሩ፥ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች ስለ ሃይማኖትና ሃይማኖተኛነት፤ ስለ ቤተ ክርስቲያን ትምህርትና አገልግሎትዋ ከዐሥርተ ዓመት በፊት ከነበሩበት የእምነት፣ የአመለካከትና የሥነ ምግባር ችግር አኳያ ቀደም ሲል እንደ ተገለጸው በአሁኑ ወቅት በአብነት ትምህርቱ የተኬደበት ርቀት መሠረታዊና አበረታች ለውጥ ነው ሊባል ይችላል::

*ዛሬ የግቢ ጉባኤያት ተማሪዎች በአብነት ትምህርቱ የመማር ማስተማር ሒደት ተሳታፊዎች በመኾናቸው:-*

- ➢ ጥንታዊው ሥርዓተ ትምህርት ትውፊታዊ አቋሙን ጠብቆ በዘመናዊ መልክ የሚቀርብበት መሠረት በመጣል ላይ ይገኛል::
- ➢ በገንዘቡ፣ በዕውቀቱና በጉልበቱ ለቤተ ክርስቲያን የሚሠራው ምሁሩ ወጣት በአመዛኙ በአፍዓ /በዐውደ ምሕረት፣ በቢሮና በመስክ/ ተወስኖ የነበረው ትጋቱ በሥልጣነ ክህነት፣ በቅኔ ማኅሌትና በመቅደስ ውስጥ አገልግሎት ጥልቀት የሚያገኝበት ሁኔታ ተመቻችቷል::
- ➢ የቤተ ክርስቲያን ዋነኛ ተልእኮ የኾነው የመቀደስና የማወደስ አገልግሎት በቀሳውስት፣ በዲያቆናትና በደባትር እጥረት ተገትቶ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት እስከ መዘጋት የሚደርሱበት ችግር ከመሠረቱ ሊፈታ ተስፋ መሰነቅ ጀምረናል::
- ➢ በሁለት ዓይነት ትውልድ፣ በሁለት ዓይነት ትምህርት ቤት፣ በሁለት ዓይነት ሥርዓተ ትምህርት በማለፋቸው የተራራቁት ዘመናዊውና የቆሎ ተማሪው የማይተዋወቁበት ዘመን አልፎ፤ ዘመናዊው /የቀለሙ/ ተማሪ ቢጋች የኾነውን የቆሎ ተማሪ፥ የዕለት ተዕለት መከራና ጥንካሬ በቅርበት ተረድቶ በቁጭት የሚነሣሣበት፤ በአንጻሩም በማኅበራዊውና በተፈጥሮው ሳይንስ ልዩ ልዩ መስኮች ምሁርነቱ ከፍ ያለ አስተያየት የሚደረግለት የቀለሙ /ዘመናዊው/ ተማሪ የጥንታዊውና ትውፊታዊው ተቋም ሥርዓተ ትምህርት ተሳታፊ ሆኗል:: ስለዚህም የአበውን ትምህርት፣ ሥርዓት፣ ሥነ ምግባር፣ ክርስቲያናዊ ኑሮና ታሪክ ለዚህ ትውልድ እንዲደርስ ታላቅ አስተዋፅዖ አድርገው ሳለ ዘመኑ ሲገፋ እነርሱ ግን በነበሩበት በመቅረታቸው ብሶት የሚሰማቸውን የአብነት መምህራንንና ተማሪዎችን ልብና መንፈስ ለዘመናዊው ትምህርት እንዲነሣሣ፣ ያላቸውንም እንዲያከብሩትና እንዲጠብቁት አግዟቸዋል::
- ➢ ምሁሩ ወጣት ለሚፈልግበት የሞያ ሥነ ምግባርና ጠንካራ ስብእና ዓይነተኛ መሠረት የኾኑትን ጽኑ እምነት፣ ቅን መንፈስ፣ ትዕግሥትና ትሕትና በአብነት ትምህርቱ የመማር ማስተማር ሒደት ሊያገኛቸውና ሊላበሳቸው ችሏል:: ይህም ቤተ ክርስቲያን ለሥራ ባሕል መዳበርና ለአገር ዕድገት እንቅፋት ሳትሆን የሥልጣኔ በር ከፋችና ፍኖተ አእምሮ አደራጅ ለመሆንዋ የተግባር ማረጋገጫ ሆኗል::
- ➢ ምሁሩ ወጣት ከሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያንና ከአበው ካህናት ጋር በአሳብና በቋንቋ እንዲግባባ፤ በውስጥ በአፍዓ አገልግሎቱ የታመነ እንዲሆንና ተቀባይነቱ እንዲጐላ ረድቶታል::
- ➢ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በቀለሙ ትምህርት፥ የግቢ ጉባኤያት በአብነት ትምህርት አንፀውና ቀርጸው የሚያወጧቸው ወጣቶች የነገ የቤተ ክርስቲያን አባቶችና የአገር መሪዎች ሲሆኑ በተሞላ ስብእናቸው ለሕዝባቸው ኩራትና ክብር እንደሚሆኑ የኮፕት ቤተ ክርስቲያንን ጳጳሳት፥ መነኮሳትንና ካህናትን እንደ አብነት በመጥቀስ ተስፋ የሚያደርጉ ወጣቶች አያሌ ናቸው::
- ➢ በአጠቃላይ በሥርዓተ ትምህርት ያለ መጣጣም ችግሮች ሳቢያ በመንፈሳዊው ተማሪና በቀለሙ ተማሪ መካከል የነበሩት የኑሮ፥ የአመለካከትና የባሕል ጽንፈኛ አቅጣጫዎች ለተፈጠረው የትውልድ ክፍተት ጥንተ ምክንያት በመኾን አንደኛው ሌላውን ባለማወቁ አንዱ ከሌላው የሚያገኘውን ጥቅም አስቀርቶት ነበር:: ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በግቢ ጉባኤያት በሚሰጠው የአብነት ትምህርት ግን ክፍተቱ በመሞላት ላይ ይገኛል:: ይህም እንግዲህ ዓላማው ሩቅ ግቡ ጥብቅ እንደ መኾኑ መጠን ያለ አንዳች ችግር የተገኘ ውጤትና ተስፋ አይደለም::

## በመማር ማስተማሩ ሒደት ካጋጠሙት ችግሮች መካከልም:-

- ☞ የግቢ ጉባኤያት ተማሪዎች /በተለይ ደግሞ እኅቶች/ የአቻዎቻቸውንና የሌሎች ሰዎችን አሉታዊ አመለካከት፣ አካዳሚያዊ ጫናና ተያያዥ ውጥረቶች ተቋቁመው





www.eotcmk.org

ጊዜያቸውን መሥዋዕት ማድረግ ነበረባቸው፤

- ከፍ ላለው የዜማ ትምህርት /ምዕራፍ፣ ጾመ ድጓ/ ከፍተኛ የመጻሕፍት እጥረት አለ፤ በዚህም ሳቢያ ተማሪዎች ያለፈውን ሳይረሱ ከልሰው፤ ተከታዩን የትምህርት ክፍልም ቀድመው አጥንተው እንዳ ይመጡና የመማር ማስተማሩ ሒደት እንዲጓተት ምክንያት ሆኗል።
- በግቢ ጉባኤያት ባሉ አስፈጻሚ የአገልግሎት ክፍሎች መርሐ ግብሮች መደራረብ ሳቢያ የአባላት ከአብነት ትምህርት መስተጓጎል፤
- በመምህራን እጥረትና በቦታ ጥበት /አመቺ አለመሆን/ ምክንያት የጉባኤያት መታጠፍ፤
- የአብነት ትምህርቱ በንባብ /በመቁጠርና በማጋዝ የቃል ጸሎት/ እና በዜማ ጨኸት ስለሚጀምር አንዳንድ ተማሪዎች የግእዝን ቋንቋ በመጠኑ የሚረዱበት ዕድል ባለመኖሩ በንባብና በቃል ጸሎት ትምህርቱ በመዳከም የተማሩትን ያለመከለስና የመርሳት ለቀጣዩም ትምህርት ቀድሞ ያለመዘጋጀት በመጨረሻም ወደ ኋላ የመመለስ ሁኔታ ይታይባቸዋል፤

## የተጠቀሱትን ችግሮች ለመቅረፍና እጥረቶቹን ለማቃለል እንደ ግቢ ጉባኤ መጠን የተወሰዱ የመፍትሔ ርምጃዎች አሉ፡-

- የአብነት ትምህርቱን መርሐ ግብር የተማሪዎችን መደበኛ የትምህርት ክፍለ ጊዜ በማይጋፋ መልኩ ከሳምንቱ በተወሰኑ ዕለታት፣ በሠርክና በምሽት ሰዓታት እንዲሁም በሰንበታት በጥቂት በጥቂቱ፤ በተማሪዎች የመንፈቅ ዓመቱ የዕረፍት ጊዜያትና የትምህርቱ ይዞታ ቀለል በሚልባቸው ሳምንታት ደግሞ ሰፋ ተደርጎ እንዲሰጥ በመደረግ ላይ ይገኛል።
- የአብነት ትምህርቱን መርሐ ግብር የሚሳተፉ ተማሪዎች በአካዳሚያዊ ትምህርት ተሳትፏቸውና ውጤታቸው ደክመው እነርሱን አርአያ የሚያደርጓቸውን አቻዎቻቸውን ወደ ኋላ እንዳይመልሱ የእርስ በርስ ውይይት ይደረጋል፤ ከፍተኛ ምክርም ይሰጣል። ስለዚህም የአብነት ትምህርቱን ከሚሳተፉ ተማሪዎች አብዛኞቹ በቀለሙ ትምህርታቸው ውጤታማ በመሆን ለሌሎች አርአያ ሆነዋል፤ በአንዳንድ የተማሪው ስብሰባዎች ላይም ለአስተያየታቸው፣ ለትችታቸውና ለፍርዳቸው ቅድሚያ የሚሰጥበት፤ በክርክሮችም ወቅት «እስኪ የአብነት ተማሪዎች ይናገሩ» የሚባልበት ሁኔታ እንዳለ ለማስተዋል ተችሏል።
- የመምህራንንና ለመማር ማስተማር አስፈላጊ የኾኑ መጻሕፍትን እጥረት ለማቃለል ተማሪዎች በእጅ ጽሕፈት የሚገለብጡበት፤ እነርሱን ለማገዝ ከሚመደቡላቸው አስቀጻይ ተማሪዎች /የተማሪ ዲያቆናትና መሪጌቶች/ በመቀጸል፣ በሬድዮ ካሴት ቀርጸው ባመቻቸው ጊዜ አጥንተው ራሳቸውን በራሳቸው በማስተማር በመጨረሻም ብቃታቸውን ለማረጋገጥ ከመምህራቸው ዘንድ ቀርበው የሚፈተኑበት ሁኔታ ነው ያለው። ጅምሩ የሚበረታታ ቢሆንም አስቀጻይ ተማሪዎች በሚገባ ይዘው እያስቀጸሉ ጉድለቱን ካላስተካከሉ በቀር ተማሪዎች በእጅ ጽሕፈት ገልብጠው የሚያጠኑበት አኳኋን፣ ሊኖር ከሚችለው ግድፈተ ጸሐፊ አኳያ ስጋት ማሳደሩ አልቀረም።
- በመርሐ ግብሮች መደራረብና በቦታ ጥበት /አመቺ አለመሆን/ ሳቢያ የሚፈጠረውን የጉባኤ መታጠፍና የተማሪዎችን ከትምህርቱ መስተጓጎል ለማስቀረት የሚወጡ ፕሮግራሞች የአብነት ትምህርቱን ክፍለ ጊዜና የተሳታፊዎችን ሁኔታ ግምት ውስጥ እንዲያስገባ፣ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰበካ መንፈሳውያን ጉባኤያት አስተዳደር፣ በግቢ ጉባኤያት አመራርና በአስፈጻሚ የአገልግሎት ክፍሎች ሙከራዎች ተደርገዋል። ይሁንና በተለይም በመርሐ ግብሩ ሰዓት ተማሪዎችን ከሌሎች ኃላፊነቶች ነጻ ከማድረግ አኳያ በግቢ ጉባኤያት አስፈጻሚ የአገልግሎት ክፍሎች በኩል በቂ ጥረት እንዳልተደረገ ነው ተሳታፊ ተማሪዎች የሚናገሩት። በቅስናም በምርግትናም የሚያገለግሉ መምህራንን ለአብነት ትምህርትና ለተማሪዎቹ አስፈላጊና አመቺ ኾኖ በተገኘበት ጊዜ ሁሉ ከመፍቀድ አንጻር በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰበካ ጉባኤያት አስተዳደር የታየው በጎ ፈቃድና ትብብር የሚበረታታ ነው።
- የአብነት ትምህርቱን የጀመሩ ተማሪዎች የግእዙን ቋንቋ ባለመረዳትም ይሁን ትጋትን በሚጠይቀው የቃል ጸሎትና ዜማ ትምህርት ወደ ኋላ እንዳይመለሱ ስለ አብነት ትምህርት ዐውደ ጥናቶች የሚካሔዱበት በዚያም ላይ በመመሥረት ከተለያዩ አጥቢያዎች የመጡ የአብነት መምህራን ልምዳቸውን፣ ገጠመኞቻቸውን፣ ትምህርታቸውንና ምክራቸውን የሚያካፍሉበትን መድረክ የማዘጋጀት ተሞክሮዎች አሉ። በግቢ ጉባኤያት ደረጃ በሚዘጋጁ ዐውደ ርእዮችም አብነት ትምህርትን የተመለከቱ ትዕይንቶች ራሳቸውን ችለው በሰፊው የሚዳሰሱበት ተማሪዎችም ሰፊ ግንዛቤ የሚያገኙበት ሁኔታ አለ። የግእዝ ቋንቋን ያለ መረዳት ችግርን ከመቅረፍም አንጻር የጎንደር ሕክምና ሳይንስ ኮሌጅ ግቢ ጉባኤ ተሞክሮ እዚህ ላይ ሊጠቀስ ይገባል። ከተቋሙ በ1994 ዓ.ም የተመረቀውና እስከ መጽሐፍ /ትርጓሜ/ ቤት የዘለቀው ዲያቆን ዶክተር ሲሳይ ደመቀ ወልደ ተክሌ 40 ያህል /ሦስቱ ሴቶች ናቸው/ የግቢ ጉባኤውን ተማሪዎች ሰብስቦ ግእዝን በመደበኛ መርሐ ግብር በማስተማር ላይ ይገኛል። ሲያስተምርም ግስ አገሳሰስንና ግስ ርባታን ለብቻ፣ አገባብን ለብቻ፣ የንባብ ስልትን ለብቻ አድርጎ በሦስት ከፍሎ ነው። የልጆቹም የትምህርት አቀባበል የሚያመረቃ ከመሆኑም በላይ ግስ እስከ መግሰስ የደረሱ ተማሪዎች አሉ። እርሱም ለስኬታማነቱ እንደ ሠርቶ ማሳያ ነው የሚመለከታቸው። በሠርቶ ማሳያነታቸውም ብዙም ባልተለመደ ሁኔታ የአንደኛ ዓመት ተማሪዎችን ሳይቀር የግእዝ ትምህርት ለመማር ያነሣሣ ሆኗል። ለግቢ ጉባኤያቱ የሚመደቡ መምህራንም የተማሪውን የመረዳት ችሎታ አጢነው ትምህርቱን በአጭር ጊዜና በቀላሉ ሊረዳ የሚችልበትን ስልት መቀየስ፣ የተማሪውን የተጣበበ ጊዜና ሥነ ልቡና አገናዝበው አስፈላጊውን ትብብር ሁሉ እንዲያደርጉ በግልጽ የማነጋገሩ ሁኔታ አለ።

## ከወደፊት ዕቅድ አኳያ፡-

በአብዛኞቹ ግቢ ጉባኤያት በንባብ ቤትና በዜማ ቤት ጥቂት ትምህርቶች ተወስኖ ያለውን የአብነት ትምህርት ወደ ቅኔ፣ አቋቋምና ትርጓሜ መጻሕፍት ደረጃ የማሳደግ አሳቦች አሉ። ለዚህም ባሉት ከመጠቀም ጀምሮ ተጨማሪ መምህራንን በሚቻለው መንገድ ሁሉ ለማግኘት ጥረቶች ይደረጋሉ። በማኅበረ ቅዱሳን የዋናው ማዕከል ትምህርት ክፍልም ሆነ በየደረጃው የሚገኙ የቤተ ክርስቲያናችን አካላትና አባላት በዚህ ረገድ አስፈላጊውን ድጋፍ እንዲሰጧቸው ያነጋገርኳቸው ተማሪዎችና የግቢ ጉባኤያቱ አመራር አባላት ጠይቀዋል። በተጓዳኝም ደረጃ በደረጃ ነባሩን ሥርዓተ ትምህርት በማኅልበት ከግቢ ጉባኤያት ተማሪዎች ዕድሜ፣ ኑሮና ሥነ ልቡና ጋር በሚጣጣም መልኩ የማስተማርያና የመማሪያ መርጃ መሣሪያዎች በጽሑፍ፣ በድምፅና በምስል ወድምፅ እየተዘጋጁ መምህራን እንዲመሩባቸው፣ ተማሪዎች እንዲማሩባቸው ለተተኪው ትውልድ ሊተላለፉ በሚችሉበት ሁኔታ እንዲሠራጩና በየቤተ መጻሕፍቱ እንዲቀመጡ ቢደረግ የሚሉ ጥቆማዎችም አሉ። እንደ ዓለማያ ዩኒቨርስቲ ግቢ ጉባኤ ደግሞ **«የአብነት ትምህርት ቤት ቀን»** በሚል መርህ መርሐ ግብር አዘጋጅቶ ግንዛቤ ለማስጨበጥና የተማሪውን ተሳትፎ ለመጨመር ታቅዷል።

እንግዲህ ከብዙው በጥቂቱ እንደ ማሳያ በወሰድናቸው አራት ግቢ ጉባኤያት /በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የስድስት ኪሎ ግቢ ጉባኤ፣ የጅማ ዩኒቨርስቲ ግቢ ጉባኤ፣ የዓለማያ ዩኒቨርስቲ ግቢ ጉባኤ፣ የጎንደር ሕክምና ሳይንስ ኮሌጅ ግቢ ጉባኤ/ የአብነት ትምህርት ይዞታ ምን ያህል ተስፋ ሰጪ ጅምሮች እንዳሉት ተመልክተናል። ጅምሮቹን ለማጠናከር መምህራኑን በልዩ ልዩ ዕለታዊ ወጪዎቻቸው የምንደጉምበት፣ ለተማሪዎቹ አስፈላጊውን እገዛ ሁሉ የምናደርግበት ዘላቂ የጋራ ጥረትና ትብብር ቢኖረን ደግሞ ጥንታዊው ሥርዓተ ትምህርታችን በአቋሙ ዘመናዊነትን፣ በመሠረታዊ ጠባዩ ትውፊታዊነቱን ሊጠብቅና ሊጎናጸፍ ይችላል። ትውልዱም ከአባቶቹ እቅፍ ወጥቶ በዘመኑ ፍልስፍናና ጥበብ /ተጥባበ ሥጋ/ ብቻ ተውጦ ከትምህርተ አበው፣ ከሥነ ምግባርና ከመንፈሳዊ በረከት ውጭ እንዳይሆን ይረዳል።

እኔ ካነጋገርኳቸው ተማሪዎች በመነሣት ያልኩትን ብዬአለሁ፤ እነርሱስ ስለ አጀማመራቸው፣ ስለ መማር ማስተማሩ ሒደትና ስለ ነበራቸው ገጠመኝና ስለ ወደፊት ዕቅዳቸው ምን ይላሉ? አለፍ አለፍ እያልኩ በየርእሱ የማቀርበውን ምላሻቸውን እንድትመለከቱ በመጋበዝ እኔ ከወዲሁ ልሰናበት።

<u>ስም</u>፡- ዲያቆን ዶክተር ሲሳይ ደመቀ ወልደ ተክሌ
<u>ዕድሜ</u>፡- 29
<u>ተቋም</u>፡- ጎንደር ሕክምና ሳይንስ ኮሌጅ
<u>ትምህርት/ሞያ</u>፡- የሕክምና ዶክተር
<u>ዲቁና የተቀበለው</u>፡- በ1978 ዓ.ም ከብፁዕ አቡነ ሰላማ በወቅቱ የባሌ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ የነበሩ

## «እየታረምኩ ባስተካከልኩት የበለጠ ተምሬያለሁ»

ግእዙ ለአብነት ትምህርቱ መማሪያ ቋንቋ (medium of instruction) ነው፤



www.eotcmk.org

ስለዚህ ልዩ ትኩረት አድርጌበት በሥርዓት አጥንቼዋለሁ:: በቤተ ክርስቲያንም በአገልግሎት ወቅት /በተለይ ጠዋት ጠዋት በኪዳን ወቅት ተሳትፎ ስለነበረኝ/ ድርሳናቱን፣ ገድላቱን፣ ተአምራቱን ሳነብ ታላላቅ አባቶች አብረውኝ ስላሉ ጆሮዬን ሰጥቼ በሚገባ ነው የምሰማቸው፤ እነርሱ እየተከታተሉ «እንዲህ በለው» እያሉ እየመለሱ ያርሙኛል:: ራሴ አንብቤ ካገኘሁት በላይ የጠቀመኝ እነርሱ እያረሙ ያስተካከሉኝ ነው:: ስለዚህ ግእዙን በይበልጥ የምታውቀውና የምትለምደው በራስህ ብቻ ሳይሆን በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ላይ በመትጋት ነው:: ...

በአፍዓ ላለው አገልግሎቴም በእጅጉ ነው የሚያግዘኝ፥ እኔ በማስተምርበት ወቅት የማስበውን በግእዝ ጠቅሼ ማስተማር እችላለሁ፤ ትርጓሜውንም ምሥጢሩንም:: ባለፈው ጊዜ ወደ ሁመራ ሔደን ሳለ ኅብረተሰቡ አማርኛ አያውቅም፥ ትግርኛ ነው የሚናገረው:: ስለዚህ ግእዝን እያገናዘብን፣ እየተረጎምን አብረን ስንነግረው እንዴት ደስ አለው መሰለህ:: ለስብከተ ወንጌል ከሚሰማሩት ወንድሞች ብዙዎቹ ግእዙን የመጥቀስ ሁኔታ አለ:: ነገር ግን አስተካክሎ መናገሩ ስለማይኖር በሚያውቁት ዘንድ ነዘንም ትዝብትም ያሳድራል:: በተለይ በተማሪውም በሊቃውንቱም ዘንድ «እንዲህ ቢላት ኖሮ» እያሉ ሲቆጩም ትሰማለህ:: የሚንቁም አሉ:: እንዲያውም አንዳንዶቹ ታዛቢዎች ጠዋት በጉባኤ ላይ ተገኝተው እንደ ኾነ ከሰዓት በኋላ አይደግሙም:: ለምንድን ነው ብለን ምክንያቱን ብንጠይቅ «አይ፥ እኒህማ አማርኛ፣ አማርኛን እንጂ መች ሌላ ይናገራሉ?» ይሉሃል:: እና ግእዙን ጠንቅቆ ዐውቆ መገኘት በሊቃውንቱ፣ በካህናቱ፣ በምእመናኑም ዘንድ ሙሉ ሰው ያደርግሃል፤ ያስከብርሃል::

## «ቤተ ክርስቲያናችን ለጥያቄዎች ሁሉ የተዘጋጀ መልስ እንዳላት ተረድቼበታለሁ»

የቤተ ክርስቲያንን ትምህርት እየገፋህበት ስትሔድ ይመስጥሃል፤ ለሥርዓቱ ትቆረቆራለህ:: ለማታውቀው ነገርኮ አትቆረቆርም:: አሁን እኔ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ሲጣስ በጣም ነው የሚሰማኝ፤ በተለይ ፍትሐ ነገሥትን ከተማርኩ በኋላ:: በሌላ በኩል ባሕረ ሓሳብን /አቡ ሻህርን/ በጉባኤ ላይ ለማስተማር በጣም ነበር የሚከብደኝ:: አሁን ግን ራሳችን ተምረን ስናሰላው ስናስተምረው እንዴት ያረካል መሰለህ:: በቃ የኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ሃይማኖት አባልና ቤተሰብ በመሆኔ እኮራለሁ፤ እርስዋን የመሰለ ለጥያቄዎች ሁሉ የተዘጋጀ መልስ ያላት እናት ቤተ ክርስቲያን ከቶ የት ትገኛለች? እላለሁ፤ የመጻሕፍቱን ትርጓሜ ስትመለከተውማ ሌላ ነገር ነው፤ የመጻሕፍቱን ምሥጢር አንብቤ ለመረዳት ችያለሁ:: በበኩሌም የሌሉኝን መጻሕፍት ወደ መግዛት ነው ዘመቻ ያደረግሁት:: ቤቴ ከገባሁ በቃ ንግግሬ ከመጻሕፍት ጋር ነው::

## «ጥሩ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ የመኾን ዕቅድ አለኝ»

የአብነት ትምህርቱን በዚህን ያህል መጠን በመከታተሌ ለውስጥ አገልግሎቴ በእጅጉ ነው የረዳኝ:: ለምሳሌ:- ባሳለፍነው ዐቢይ ጾም ውስጥ ዳዊት ማስተዛዘል ነበርና አብሬ አስተዛዝል ነበር:: በአብዛኛው ምዕራፍ ነው የሚቆመው፤ ምዕራፍ እየተማርኩ ስለሆነ አብሬ እቆም ነበር:: ጾመ ድጓም መጽሐፉ ስላለኝ ከመምህሬ ጋር አብሬ እቆማለሁ፤ ከእርሳቸው ጋር አብሬ የሚባለውን እላለሁ:: መልክአ መልክእ ዜማዎችን መማር ለማኅሌቱ ይጠቅምሃል:: መልክኡ ሲባል አብሬ እላለሁ:: ሌሊቱን በሙሉ እየተመላለሰ ይባላል:: የሚያስቸግርህ ራስህን ችለህ ለመቆም ነው እንጂ ከሌላው ጋር ከኾነ አያዳግትህም:: አሁን አቋቋም ትንሽ ከያዝክ ከሌሎች ጋር አብረህ ስለምትቆም አትቸገርም:: አብነት ኾነህ ለመቆም ግን የግዴታ ጥሩ አድርገህ መማር ይገባሃል::

እኔ እንዲያውም ወደፊት ያለኝ ዕቅድ ጾመ ድጓውንና ምዕራፉን ከጨረስኩ በኋላ መዝገብ ቅዳሴውን መማር ነው:: ዜማውን አሁን ስለምለየው ስድስት ወይም ሰባት ወር ቢፈጅብኝ ነው፥ አያቆየኝም:: የመጻሕፍቱን ትርጓሜ በሙሉ እንዲሁ አድርሼ ጥሩ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ የመኾን ዕቅድ ነው ያለኝ::

ቀድሞም ቢሆን ከጎንደር ሕክምና ሳይንስ ኮሌጅ በ1994 ዓ.ም እንደ ተመረቅሁ የተመደብኩት ትግራይ ነበር:: ከጓደኞቼ ጋር ተነጋግሬ የተቀያየርነውና ወደ ጎንደር የመጣሁት ለአብነት ትምህርቱ ስል ነው:: «ከልብ ካለቀሱ እንባ አይገድም» እንደሚባለው በዚህ ዓመት የሚመረቁ ወንድሞቼና እኅቶቼ በሚሔዱበት ሥፍራ ሁሉ ሊኖሩ የሚችሉ መምህራንን በግል በመቅረብ፣ በድምፅ፣ በምስል ወድምፅ፣ በመጽሐፍ ራሳቸውን ለማስተማር መሞከር አለባቸው:: ቤተ ክርስቲያናችን በማዕከል ያቋቋመቻቸውን ማሠልጠኛዎች ከማጠናከር ጋር እንዳስፈላጊነቱ በዳር አገር ላሉትም መታሰብ ይኖርበታል::

ስም:- ሲስተር ማርታ አሰፋ  
ተቋም:- ጅማ ዩኒቨርስቲ  
ትምህርት/ሞያ:- ፖስት ቤዚክ ነርሲንግ

## «...መጽሐፍ ባለመያዝህ ጸሎትህን አታስታጉልም»

የአብነት ትምህርቱ በሁሉም መስክ ጥቅም አለው፤ ለምሳሌ የትም ቦታ ኾነህ ውዳሴ ማርያምን ልትጸልይ ትችላለህ:: መጽሐፍ አልያዝኩም ብለህ ጸሎትህን አታስታጉልም:: ይህም ማለት በቃላችን አጥንተነዋል፤ ግእዙ ለቃል ጥናትም ይሁን ለጸሎት ይመቻል:: ምናልባት በአማርኛ ቢሆን ያን ያህል አንይዝም ነበር:: በቤተክርስቲያን የሚነበቡ መጻሕፍት አሉ፤ በሚነበቡበት ወቅት የምታውቃቸው ግእዝ ቃላት ስለሚኖሩ ደስተኛ ኾነህ ትሰማዋለህ፤ ቃል በቃልም ባይኾን መንፈሱን ትረዳዋለህ:: በቅዳሴውም፣ በማኅሌቱም ጊዜ እንደዚሁ በደስታ ትከታተላለህ ትሳተፋለህ::

መጻሕፍትን በማንበብ በኩል ጠብቀው፣ ሳልተው የሚነገሩ ፊደላት አሉ፤ የተለያየ ትርጉም ሊሰጡ የሚችሉ:: እንዲያውም መምህራን ልዩነቱን ሲነግሩን በድ ፍረት የሚካሔደው ንባብ ያስፈራሃል:: ይህም ክብደት እንድትሰጠው ያደርግሃል፤ ምሥጢር እንዳታፋልስ:: በሌላም በኩል አባቶቻችን ይህን የመሰለ ትምህርት ይዘው ለማቆየት በብዙ መድከማቸውን ስለ ሚያስገነዝበኝ አባቶቻችንን በቅርስነት እንድመለከታቸው፣ የበለጠ እንዳከብራቸው አድርጎኛል፤ ተተኪዎቻቸው እንድንሆንም ኀሊናችንን ያስገድደናል::

## «የማኅበሩን ዓላማ ለማሳካት ይረዳል»

በአሁኑ ወቅት የቤተ ክርስቲያን ችግር የሚባለው ገንዘብ ወይም በጉልበት የሚሠራ ነገር ብቻ አይደለም:: በዝግ ያሉ፣ የሚከፍታቸው አገልጋይ ያጡ ብዙ አብያተ ክርስቲያናት አሉ፤ በግቢ ጉባኤ ያት የሚሰጠው የአብነት ትምህርት በዚህ ረገድ ያለውን ክፍተት ይሞላል:: ከግእዙ ይልቅ አማርኛ ብቻ እየተመረጠ ያለበት ሁኔታም አለ፤ ግእዙን ተምረን እንወቅ የሚል ትውልድ መነሣት ይኖርበታል:: ይህን ትውልድ ለማምጣት በግቢ ጉባኤያት የሚሰጠው የአብነት ትምህርት አመቺ ነው፤ ለግእዙ እንዲቆረቆር ያደርገዋል::

ይህ ትውልድ ደሞዝ ከፈሉኝ ሳይል ቤተ ክርስቲያንን በገንዘቡ፣ በዕውቀቱ ፣ በጉልበቱ የሚያገለግል ነው:: በዚህ ደግሞ ከሞያው ባሻገር የአብነት ትምህርትን በመቅሰሙ፥ በውስጥ አገልግሎቱ ብቁ ሆኖ መገኘቱ ቤተ ክርስቲያንን በእጅጉ ይጠቅማታል:: በዚያውም ላይ ከእርሱ የሚያንሱትን፥ እርሱን የሚከተሉትን ማስቀጸሉ መምህራኑን ማገዝ፥ መርዳት ነው:: ስለዚህ በግቢ ጉባኤያት የአብነት ትምህርት መስጠቱ የማኅበራችንን ዓላማ በሚገባ ያሳካል፤ ወጣቱንም ሙሉ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ እንዲሆን ያደርገዋል::

## «ቅኔ አእምሮን ክፍት ያደርጋል»

በግቢ ጉባኤያት የሚሰጠው የአብነት ትምህርት የትውልዱን አስተሳሰብ በመለወጥ ረገድ ቀላል የማይባል ሚና አለው፤ በአንድ ወቅት «ዕድሜ» የሚባል መጽሔት ሳነብ «የቅኔ ትምህርት የተማሩ ሰዎች ለብዙ ነገር አእምሯቸው ክፍት ነው፤ ከቅኔ የረቀቀ ነገር የለምና::» ይላል:: ለምሳሌ በእኛ ግቢ ቅኔ የጀመሩ ተማሪዎች በቀለሙ ትምህርታቸው በአብዛኛው ከፍተኛ ውጤት ያመጣሉ:: የአብነት ትምህርት በይዘቱ መንፈሳዊ ነውና ለራሳቸው፣ ለጓደኞቻቸውና ለቤተሰቦቻቸው ጥሩ ሰብእና እንዲኖራቸው ያደርጋል:: ወደ ቤተ ክርስቲያን መሔድ ኋላ ቀርነት እንዳልኾነ፣ የቤተ ክርስቲያንን ትምህርት ከዘመኑ ዕውቀት ጋር አያይዞ መሔድ እንደሚቻልና ይህንንም በተግባር የሚያሳይ ትውልድ እንዲወጣ ይረዳል:: የሕክምና ዶክተር ወይም የዩኒቨርስቲ መምህር ሆኖ ቀዳሽ ወዳሽ መሆን፥ ስለ ተማሩ ብቻ ከቤተ ክርስቲያን መራቅን የሥልጣኔ ምልክት አድርገው ለሚወስዱት ጥሩ የእርምት ትምህርት ያስተላልፋል:: የቤተ ክርስቲያንን ትምህርት መማር ከማይጠቅም ነገር ያርቃል፤ መልካም መልካሙ እንደ ማይቀርብን እንዲያውም አትርፎ እንደሚያሰጥ ያስረዳቸዋል:: ቅኔ የሚማሩት ብቻ ሳይሆኑ እንደ አጠቃላይ በሚሰጠው የአብነት ትምህርት የሚሳተፉት ብዙዎቹ ለማለት ይቻላል በቀለሙ ትምህርት በጣም ጥሩ ውጤት ነው ያላቸው:: በዚህ ጉዳይ ላይም መዘናጋት እንዳይኖር በግልጽ ነው የምንነጋገረው:: ለተመልካቾቻችን የውድቀት ምክንያት እንዳንሆን ጥንቃቄ እናደርጋለን:: ይህን በተመለከተም በልዩ መርሐ ግብርም ሆነ በዘወትር መርሐ ግብር ላይ ምክር ይሰጣል:: ...

ስም:- ዲ.ን ዶክተር ሲሳይ  
ተቋም:- ጅማ ዩኒቨርስቲ  
ትምህርት/ሞያ:- የሕክምና ዶክተር  
መዓርገ ዲቁና:- ሐምሌ 1993 ዓ.ም ከብፁዕ አቡነ ሳሙኤል በወቅቱ የጅማ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ የነበሩ



www.eotcmk.org

## «መታመንን ለማግኘትና አገልግሎትን ለማቀላጠፍ ረድቶናል»

የአብነት ትምህርት በግቢ ጉባኤያት መስጠቱ ማኅበራችን ወደ ቤተ ክርስቲያን ገብቶ፣ የአባቶችን ሁኔታ ተረድቶ ከእነርሱ ጋር ተግባብቶ መሥራት ስላለበት በተለይም ደግሞ የጅማ ንዑስ ማዕከል ሥራ በአብዛኛው በጅማ ግቢ ጉባኤ ስለሚሠራ ለዚህ ተግባር በእጅጉ ይረዳናል:: እንዲያውም አንዳንድ ነገሮችን ማስፈቀድ ስንፈልግ ከመግባባታችን የተነሣ ደብዳቤ መጻፍ እንኳ አያስፈልገንም:: መታመኑ ስላለ እናንተ ካላችሁ ብለው ነው ብዙ ነገር የሚለቁልን:: ይህ ደግሞ ለአገልግሎታችን ቅልጥፍናን አስገኝቶልናል:: ከግቢ ጉባኤያችን ለአገልግሎት ሁል ጊዜ ግንባር ቀደም የሚኾኑት በአብነት ትምህርት የሚሳተፉቱ ናቸው:: አገልግሎትን በማስተባበርና በማቀናጀት፣ በማስተማሩም፣ በማኅሌቱም በቅዳሴውም በመሳተፍ ጉልህ ሚና አላቸው:: ተመርቀው ከሔዱትም እንደ ምንሰማው በውስጥ አገልግሎት /በማኅሌት/ ከአባቶች ጋር ስለሚሳተፉ ይህ አቀራረባቸው ለስብከተ ወንጌሉ በጣም እየረዳቸው ነው::

ይኼ ለትውልዱ አዲስ ነገር ነው፤ ከዘመናዊው ትምህርት ጋር ትውፊታዊውን የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ተምሮ ማገልገል ይቻላል:: ቤተ ክርስቲያን የሥልጣኔ ባላንጣ አይደለችም:: እንዲያውም ለዕድገት መሠረት ለትውልዱ የምትስማማ መሆኗን የሚናገር ይመስለኛል:: ይህም ለቤተ ክርስቲያን ያለንን ክብር ይጨምርልናል::

ማኅበረ ቅዱሳን÷ የአብነት ትምህርት በስሩ ባቀፋቸው ግቢ ጉባኤያት ሁሉ እንዲስፋፋ፣ እንዲጠናከር ማድረግ አለበት፤ ወደፊት አገሪቱን የሚረከብ ትውልድ ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ነው የሚወጣው:: ይህ ትውልድ ጥሩ አመለካከት ኖሮት፣ ቤተ ክርስቲያን ምን እንደ ሆነች ተረድቶ መሠማራት ይኖርበታል:: ለቤተ ክርስቲያንም እንደ ግብፃውያን መነኮሳትና ካህናት ታላላቅ ቦታ ለመድረስ የሚችሉ አባቶችን ልናገኝ እንችላለን::

በበኩሌ ለወደፊቱ ስነሣ የነበረኝን ዓላማ ይገፔ ለመጓዝ ነው:: እዚህ ጋር እቆማለሁ የምለው ነገር የለም:: በተቻለኝ መጠን አቅሜ እስከ ፈቀደ መቀጠል እፈልጋለሁ:: የቤተ ክርስቲያን አባቶች የትም ቦታ ስላሉ ባለኝ ላይ የመጨመር ፍላጐት ነው ያለኝ:: በይበልጥም ደግሞ በዜማው በኩል ለመድከም እፈልጋለሁ:: አርአያ የኾኑኝና ያተጉኝ ደግሞ መምህሬ ሊቀ ማእምራን ተመስገን ጌታሁን ናቸው::

## «ከመ ቀለመ ጸሐፊ 'ዘበጠበጠ' ይጽሕፍ»

ብዙዎቹ ገጠመኞች እንኳን÷ መምህራችን በየመካከሉ የሚነግሩን ነው እንጂ እኛ ከቆይታችን አንጻር ያለን ብዙ አይደለም:: ሁሉንም ነገር በተደላደለ ሁኔታ ነው የተማርነው:: ይሁንና ብዙዎቹ ገጠመኞቼ አባባል /ንባብ/ ላይ የሚያተኩሩ ስለሆነ የሚያስቁ ናቸው፤ በአንድ ወቅት ዳዊት በምንቆጥርበት ሰዓት «ከመ ቀለመ ጸሐፊ ዘጠበጠበ ይጽሕፍ» የሚል ነበር፤ እና ይህንን አንድ ጓደኛችን ሲቆጥር «ከመ ቀለመ ጸሐፊ ዘበጠበጠ...» ብሎ የተናገረው ያስቀኛል፤ ያው ቀለም ስለሆነ «ዘበጠበጠ» ብለው ያስኬዳል ብሎ ነው መሰለኝ::

<u>ስም</u>:- ዲ.ን ያሬድ ታደሰ<br>
<u>ዕድሜ</u>:- 23<br>
<u>ተቋም</u>:- አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ<br>
<u>ሞያ/ትምህርት</u>:- ሥራ አመራር/ ማኔጅመንት/<br>
<u>መዓርገ ዲቁና</u>:- መጋቢት 23 ቀን 1996 ዓ.ም ከብፁዕ አቡነ መልከ ጼዴቅ የከንባታ ሃዲያ ጉራጌና ስልጤ ሀገረ ስብከት ጳጳስና የጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ

## «ኮቸሮአቸውን የቀመስኩባትን ቀን...»

የማልረሳው ነገር አገር ቤት በአቅራቢያዬ ወደሚገኘው አቋቋም ት/ቤት ሔጄ «ልማር መጣሁ» ስላቸው÷ «አልጋችንን እንልቀቅልህ» ያሉኝ፤ ከሚበሉት ከሚጠጡት ተጨንቀው አዘጋጅተው ያስተናግዱኝን አልረሳውም:: እንደ ድሮው እኔነቴ ቢሆን «ቆጡ ተባይ ይኖረዋል÷ እህሉ ውጥንቅጥና በርበሬ የበዛበት ስለሆነ ጨጓራዬን ያመኛል፣ ኮቸሮው ሆዴን ይቆርጠኛል» ብዬ እንቅ÷ እጸየፍ ነበር:: አሁን ግን ምንም እንኳን የቀለም ተማሪ ብሆንም የእነርሱ ቤተሰብና አባል ለመሆን በመቻሌ ደስተኛ ነኝ:: በተለይ በ1994 ዓ.ም ሐምሌ 7 ቀን ለመጀመሪያዬ ጊዜ የእነርሱን ኮቸሮ የቀመስኩበት ቀን በጣም የተደ ሰትኩበት ነበር:: ሰው በተለያየ ምክንያት የሚፈራቸውን የአብነት ተማሪዎች እኔ ቀርቤ ይህን ያህል ከእነርሱ ጋር ለመሳተፍ በመብቃቴ ደስተኛ ነኝ:: ብዙ ጊዜ ደረቁ እንጀራ በበርበሬ በተበጠበጠ ውኃ ውስጥ ይነከርና ያ ይበላል:: እኛ ይብዛም ይነስም ድሎት ያለን እንኳ የነርሱን ወዝ ያህል ሊኖረን አይችልም፤ በቃ÷ በምግብ እጥረት የተጎዱ አይመስልህም÷ በሚታመሙበት ወቅት ሰው እነርሱን ስለማያቀርባቸው በሕክምና ሥፍራዎች ወረፋ እንኳን ከእርሱ ጋር አያስልፏቸውም:: ይናቃሉ:: ታድያ የተቋም ተማሪዎች የኾንነው እነርሱን ደግፈን ወስደን ስናሳክማቸው ሁሉም ይረባረብላቸዋል፤ ለእኛ ብሎ ሪፈራል ሁሉ ወደ ደብረ ማርቆስ ይጻፍላቸዋል:: ይህን ጊዜ እኔ የሚሰማኝን መግለጽ ያዳግተኛል:: እኛ የተቀበልናቸውን ሰው ይቀበላቸዋል፤ አለ አንዳች ነገር እንዲህ እንደ ማንከባከባቸው ይረዳል::

## «ያሬድ ከመጣ አቦዝናችሁ እንዳታስቀምጡት»

በአገር ቤት ከአቋቋም ተማሪዎች ዘንድ ስማር የአቋቋም መምህሩ ዐሥራ አራት ልጆችን ብቻ መርጠው ነው የሚያስተምሩት:: ሰባቱ በአንድ ፈረቃ፣ ሰባቱ በሌላ ፈረቃ ነው የሚማሩት:: ሰባቱ ሲማሩ ሰባቱ ደግሞ ወንበር ዘርግተው ያስተምራሉ:: ትምህርቱ ቀን ከ4:00-8:00 ማታ ደግሞ 1:00-4:00 ነው:: ስለዚህ ባስፈለገኝና በሔድኩ ጊዜ ሁሉ የሚያስ ተምረኝ አላጣም፤ ስሳሳትም ደግሞ ወዲያው ያርሙኛል:: ይህ በተለይ ለእኔ ጠቅሞኛል÷ ከበደኝ ብዬ እንዳላስብ አድርጎኛል:: የተወለድኩበት ኅብረተሰብ የዩኒቨርስቲ ተማሪ ሲባል ትልቅ ቦታ ይሰጣል፤ በርግጥ በአንድ በኩል ለእኛ ካለው በበለጠ እነርሱ /የአብነት ተማሪዎቹ/ አላቸው፤ ይህ ክብርና ክብካቤ ተገብቶን አይደለም:: በሌላ በኩል ደግሞ የዕረፍት ጊዜዬ አጭር እንደ ኾነና ወደ ተቋም እንደምመለስ ያውቃሉ:: ስለዚህ ባለኝ ጊዜ ቶሎ ቶሎ አስተምረውኝ እኔም ጥሩ ነገር ይገፔ እንዲያዩኝ ይፈልጋሉ:: አንድ ዜማ በፍ ጥንት ይገፔው ሲያዩኝ በቃ÷ ደስ ብሏቸው «ይበል ይበል÷ ዕፁብ ዕፁብ» ይላሉ:: «አገ ርን ሊለውጥ÷ ቤተ ክርስቲያንን ሊያገ ለግል የሚችለው የተማረው ሰው ነው:: ስለዚህ አንተ በሚገባ ተምረህ ከሔድህ በዩኒቨርስቲ ያሉ ጓደኞችህን ደግሞ ታስ ተምራለህ» ይሉኛል:: በተለይ በየአገሩ እንደ እኔ በመንፈሳዊ ት/ቤት የሚማሩ የተቋም ጓደኞች አሉኝ ስላቸው÷ «በቃ÷ አንተ ደግሞ ከእነርሱ በበለጠ ተምረህ ሔደህ ማስተማር አለብህ» እያሉ በጉጉት ያስተምሩኛል፤ መምህሩም «ያሬድ ከመጣ አቦዝናችሁ እንዳታስቀምጡት» ብለው ተማሪዎቻቸውን ያስጠነቅቃሉ::

<u>ስም</u>:- ዲ.ን ዘላለም ታደሰ<br>
<u>ዕድሜ</u>:- 25<br>
<u>ተቋም</u>:- አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ<br>
<u>ሞያ/ትምህርት</u>:- ቢዝነስ ኤጁኬሽን<br>
<u>መዓርገ ዲቁና</u>:- መጋቢት 23 ቀን 1996 ዓ.ም ከብፁዕ አቡነ መልከ ጸዴቅ የከንባታ ሃዲያ ጉራጌና ስልጤ ሀገረ ስብከት ጳጳስና የጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ

## «ደጀ ሰላም አያዋጣህም...»

በግቢያችን የአብነት ትምህርትን እንደ ምንማር የሚያውቁቱ መጀመሪያ ላይ «ቄሱ»÷ «ዕጨጌው» እያለ ይተርቡን ነበር:: ይህን የሚሉን «ከአሁን በኋላ ደግሞ የት ልትደርስ ነው?» እያሉ የሚያሾፉብን የኛም ልጆች ጭምር ናቸው:: «አንተ ደጀ ሰላም ገብተህ አያዋጥህም ዐርፈህ ትምህርትህን ተማር ይሉኛል::» በግቢ ውስጥ ያሉት ተማሪ ዲያቆናት ራሱ ማገልገል አይፈልጉም ነበር:: በኋላ የቀለሙንም መንፈሳዊውንም ትምህርት አጣጥመን ማስኬዳችንን ሲረዱ ግን ትርፍ ጊዜያቸውን ሰጥተው እኛን ማበረታታት፣ ማስተማር ያዙ:: አብዛኛው ሰውም ለእኛ አክብሮት አለው:: ከዚህ አኳያ ጉባኤው እየሰፋ መጥቶ ተማሪው በዝቶ ነበር:: ስለዚህ አንድ ተማሪ «የአብነት ትምህርት ይማራልኮ» ከተባለ አስተያየት እንዲሰጥ፣ እንዲተች፣ እንዲፈርድ የሚጠየቀው እርሱ ነው:: ይህ እንግዲህ በግቢ ጉባኤው ነው:: በአገር ቤትም በፊት ወደ ሰንበት ት/ቤትና ወደ ቆሎ ት/ቤት ብሔድ ደስ ደስ የማይለው አባቴ እኔን መደገፍ ያዘ:: እንዲያውም ስቀር «ዛሬ ምን ኾነሃል? አትሔድም እንዴ?» ይለኛል::...

ባለፈው ብፁዕ አቡነ መልከ ጼዴቅ የተናገሩት አለ፤ «የቤተ ክርስቲያንን ችግር የውጭ ሰው ኾኖ ከማየት የውስጥ ሰው የበለጠ ይረዳል» ነበር ያሉት:: ብፁዕ አቡነ መልከ ጼዴቅ ሢመተ ዲቁናውን ሲሰጡንም «ቤተ ክርስቲያን በእናንተ ደስ ይላታል፤ ስለ እናንተ አስምታ ትዘምራለች» ብለውናል:: ከላይ ጀምሮ እንዲህ የሚያበረታቱን አባቶች እንዲበዙልን እሻለሁ:: በውጭ ኾነን በዕውቀታችን፤ በገንዘባችን፣ በጉልበታችን ልንረዳ እንችላለን:: ይሁንና ይህ ሊቀጥል የሚችለው የውስጡ ጥሩ እስከ ኾነ ድረስ ነው:: በውስጥ አገልግሎቱ በአሁኑ ወቅት በየሥፍራው ክፍተት አለ÷ የአብነት መምህሩና ተማሪው ብዙ ችግሮች ተጋርጠውባቸዋል:: ለእነዚህ ችግሮች ግን የበይ ተመልካች ወይም ተቺ ከመሆን የተቋም ተማሪው እየተማረ ይተካል ማለት ነው፤ በበጎ ፈቃዱ የሚያበረክተውን አገልግሎቱን አጠናክሮ ለመቀጠል ያበቃዋል::



www.eotcmk.org

## «አንዱ ለሌላው ባይተዋር እንዳይሆን»

የአብነት ትምህርቱ በሁሉም ዘርፍ /ከንባብ ቤት እስከ መጽሐፍ ቤት/ ተስፋፍቶ መሰጠት አለበት። ተማሪዎች ወደ ተቋም እንደ ገቡ ጀምሮ ግንዛቤው ተፈጥሮ እንዲማሩ ቢደረግ፤ በተለይም በመጨዎቹ ዓመታት በዲግሪው መርሐ ግብር ተማሪዎች ሦስት ዓመት ብቻ ስለሚቆዩ አሁን ባለው ሁኔታ ሁለተኛ ዓመት ላይ የሚጀመር ከኾነ ቀሪው ጊዜ ብዙውን ነገር ለመማር አነስተኛ ነው የሚኾነው። ስለዚህ ተማሪዎች ወደ ተቋም እንደ ገቡ ቢያንስ በመጀመሪያው ዓመት ሁለተኛ መንፈቅ ዓመት ላይ ቢጀምሩ ተመርቀው በሚወጡበት ጊዜ ከፍ ያለ ደረጃ ላይ ደርሰው በሥጋዊውም ኾነ በመንፈሳዊው ዕውቀት ተስለው ይመረቃሉ። …ለምሳሌ የእኔ አባት ካህንም በሥራ አመራር ሞያ ደግሞ የመንግሥት ሠራተኛም ነበርና በአጋዴን አካባቢ ሲሠራ በነበረበት ወቅት መደበኛ ሥራውን እየሠራ በቤተ ክርስቲያንም ይቀድስ ያወድስ ነበር። በአካባቢው ካህናት እንዳልነበሩም ነው የነገረኝ። ስለዚህ ለወደፊቱ ካህናቱና ዲያቆናቱ አነስተኛ የሆኑበት ወይም ጨርሶ አብያተ ክርስቲያናት በተዘጉበት ቦታ ባለኝ ጊዜ ለማገልገል እሻለሁ።

ዛሬ የአብነት ትምህርት ተምረው ዘመናዊውን ዕውቀት ይዘው የሚወጡት ነገ አገርን የሚመሩ ባለ ሥልጣናት፣ ቤተ ክርስቲያንን በከፍተኛ ደረጃ የሚያገለግሉ አባቶች ሊሆኑ ይችላሉ። ያን ጊዜ በሞያቸውም ሆነ በመንፈሳዊ ሕይወታቸውና ዕውቀታቸው የተመሰገነ ሰብእና ይኖራቸዋል። የትውልዱን አመለካከት ከፍ በማድረግ ቤተ ክርስቲያንን በዓለም መድረክ የሚያስመሰግኑ ይሆናሉ። በአንጻሩም ካህናት ለትውልዱ ያላቸው አመለካከትና ቀረቤታ የተሻለ ይሆናል። በአጠቃላይ አንዱ ለሌላው ባይተዋር እንዳይሆን ይረዳል።

በተለይ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች ከመላው የአገሪቱ ክፍል ስለሚመጡ በሁሉም የአገራችን ክፍሎች ባላገር የኾኑ ካህናትንና የአብነት መምህራንን ለማፍራት የሚያስችልበት ምቹ ሁኔታ በግቢ ጉባኤያት ይፈጠራል የሚል እምነት አለኝ። ለምሳሌ፦ እኔ ባለሁበት አካባቢ አገልጋይ ካህናት ከመሐል ወይም ከሰሜን የአገሪቱ ክፍል ብቻ ስለሚመጡ እነርሱ በዕድሜ መግፋት ሳቢያ ሲደክሙ፣ በሞት ሲለዩ ወይም በተለያየ ምክንያት አካባቢውን ሲለቁ ተተኪዎችን ማፍራት ላይ ከፍተኛ ችግር አለ። የአገልግሎቱ ቀጣይነትም አስተማማኝ አይሆንም።

**ስም**:- ደብሪቱ አቤ
**ዕድሜ**:- 22
**ተቋም**:- ዓለማያ ዩኒቨርስቲ
**ሞያ/ትምህርት**:- ዕፀዋት ሳይንስ

## «የኢሉባቦር ጫካዎቿ ሶስና…»

የአብነት ትምህርቱን የሁለተኛ ዓመት ተማሪ ሳለሁ ነው የጀመርኩት። በቤተ ክርስቲያናችን አገልግሎቱ /ቅዳሴው÷ ማኅሌቱ/ በአብዛኛው በግእዝ ነው። በመሆኑም ትምህርቱንም ይሁን ቋንቋውን ማወቅ አለብኝ በማለት፤ በሌላ በኩልም ቆየት ባለው የሐመር መጽሔት እትም-ኪነ ጥበብ ዓምድ «በኢሉባቦር ጫካዎች ውስጥ» በሚል ርእስ በተከታታይ በቀረበው ልቦለድ ውስጥ ሶስና የቦሩን ጌታንና ጋሻ ጃግሬዎቹን እንደዚያ ድል ልታደርግ የቻለችው ውዳሴ ማርያምን በቃሏ አጥንታ ለመጸለይ በመቻሏ ነው። እኔም የኾነ ችግር በሔድኩበት ቢገጥመኝ እንደ እርስዋ እጠቀምበታለሁ የሚለው ነው ያነሣሣኝ። በርግጥ ቀደም ሲል ተመርቀው የሔዱ እኅቶችም አርአያ ሆነውኛል። ትምህርቱን ከመጀመሬ በፊት ለመማር ሳስብ ወደፊት ላልቀጥልበት እችላለሁ የሚል ስጋት ነበረኝ። በተለይ በጀመርንበት አካባቢ የግእዙ ቃላት ይከብደኝ ነበር። በኋላ ላይ እየለመድኩት ስሔድ ግን ማቋረጥ እንደ ሌለብኝ ወሰንኩ። ከጸታ አንጻር እዚህ በግቢ ጉባኤው እንኳ ምንም አይሉንም፤ እቤት ግን አባቴ ካህን ስለሆነ አስተምረኝ ስለው «ምን ያደርግልሻል÷ መቅደስ ግብተሽ አትቀድሽ» ይለኝ ነበር። አሁን አሁን እንኳ አያያዜን በመመልከት ያበረታታኛል።

## «የሚባለው ስለማይገባኝ እንቅልፌ ይመጣ ነበር»

… በፊት ማኅሌት ሔጄ ስቆም የሚባለው ስለ ማይገባኝ÷ ወይ እንቅልፌ ይመጣል፤ አልያም በቆምኩበት አሳቤ ይበታተናል። እንዲህ ከሚሆን ለምን አልቀርም እያልኩ እቀር ነበር። አሁን ግን መጽሐፍ ይዤ ከዲያቆናት ጠይቄም ቢሆን የሚባለውን ለመረዳት ጥረት አደርጋለሁ። በዚህ የተነሣ ከማኅሌት መቅረት ደስ አይለኝም።

ወደ ተቋም ከመግባቴ በፊት ትውልድና ዕድገቴ ባሕር ዳር አካባቢ በመሆኑ መምህራኑን በተለይም ደግሞ ተማሪዎቹን ከምእመናኑ ሲዘከሩ ማየትም ኾነ ሲማሩ የመስማት ዕድሉም አጋጥሞኛል።

ከነበርኩበት ቦታ አኳያ እዚህ ያለውን ሁኔታ ሳነጻጽረው በጣም ነው ያሳዘነኝ። ይሁንና በግቢ ጉባኤው የሚማሩ ወንድሞችን ስመለከት ወደፊት የቤተ ክርስቲያናችን ችግር ሊቃለል እንደሚችል ተስፋ አድርጌአለሁ።…

የመምህር እጥረት አለ፤ አንድ መሪጌታ ብቻ ነው ያሉን። እና ሁላችንም አጥንተን÷ ተዘጋጅተን መጥተን በአንድ ቀን የተማርነውን ተፈትነን መሔድ አንችልም። ሳንፈተን የምንቀርበት ጊዜ አለ። የመማሪያ መጻሕፍት እጥረት አለ። በተለይ ዜማ የሚያጠኑ ልጆች በቂ መጽሐፍ የላቸውም። በስብከተ ወንጌል አዳራሹ ውስጥ ብንማርም የቦታ ጥበት ችግር አለ፤ በተለይ ተደራራቢ መርሐ ግብሮች አሉ።

ችግሩን ለመፍታት አስፈላጊ መጻሕፍት በተወሰነ መጠን ተገዝተዋል፤ በተመሳሳይ ሁኔታ መርሐ ግብሮቹን ከማጣጣም አንጻር ጥረት መደረግ ያለበት ይመስለኛል።

**ስም**:- ዲያቆን ኢያሱ መከተ
**ዕድሜ**:- 23
**ተቋም**:- ዓለማያ ዩኒቨርስቲ
**ሞያ/ትምህርት**:- ኬሚስትሪ
**መዓርገ ዲቁና**:- ኅዳር 27 ቀን 1996 ዓ.ም ከብፁዕ አቡነ ድሜጥሮስ የምሥራቅ ሐረርጌ ሊቀ ጳጳስ የምሥራቅ ሐረርጌ ሀገረ ስብከት ጳጳስ

## «ዲያቆናት ውዳሴ ማርያምን ሲያድሉ…»

በቤተ ክርስቲያን የሚሰጠው ትምህርት በተለይ የውስጥ አገልግሎቱ ብዙ ጊዜ ከግእዝ ጋር የተያያዘ ነው። በመሆኑም የአብነት ትምህርቱን መጀመሬ ቋንቋውን ለማወቅ ጥረት ከማድረግ አንጻር ነው። በሌላ በኩል በግቢያችን ውስጥ የሚማሩ ወንድሞችና እኅቶች አሉ። እነርሱ ሲማሩ ዐይቼ ፈለጋቸውን በመከተል ነው። በዚህ ላይ በተለይ ዲያቆናት ውዳሴ ማርያምን ሲያድሉ ስመለከት ያስደስተኛል፤ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የኾነ ቦታ መያዝ መቻል ነውና። እኔም እግዚአብሔር ለዚህ ነገር ቢያበቃኝ እያልኩ እመኝ ነበር። በርግጥ ከውጭ ሲታይ ወይም ሲጀመር ቢከብድም ወደ ውስጥ ስትገባ ግን ይቀልሃል።

## «ሁለት ዲግሪ ይዞ መውጣት ነው»

ብዙዎች ለቀለሙ ትምህርት ፍላጎት አጥተን በአብነት ትምህርቱ ብቻ የተሳብንና ጊዜ የምናጠፋ ይመስላቸዋል። ይሁንና በእግዚአብሔር ረድኤት በራሳችንም ጥረት በቀለሙ ትምህርት ውጤታችን የተሻለን ኾነን እንገኛለን። እኔ እንዲያውም ጊዜያችንን ቀንሰን በመስጠታችን በመጨረሻ ላይ ሁለት ዲግሪ ይዞ የመውጣት ያህል አድርጌ ነው የማየው። …

በግቢ ጉባኤያችን የአብነት ትምህርት መሰጠቱ በአጥቢያውም ኾነ በአካባቢው ያለውን የአገልጋዮች እጥረት ከማቃለል አኳያ ትልቅ አስተዋፅዖ ነው ያለው። በተለይም በግብርናው ሞያ ያሉ ወንድሞች በአመዛኙ ወደ ገጠር ስለሚሠማሩ የሚቀርፏቸው ችግሮች ብዙ ናቸው። አሁን እንኳን በተጨባጭ እዚህ በኀደለው ገብቶ ለማገልገል እየተቻለ ነው። ይህ ደግሞ በአጥቢያችን በባቴ ደብረ ማኅቶት ቅዱስ ዐማኑኤል ቤተ ክርስቲያን ብቻ ሳይሆን በተለያዩ አጋጣሚዎች ለዓመታዊ ክብረ በዓላት ራቅ ብለን ለምንሔድባቸው የገጠር አብያተ ክርስቲያናትም ጭምር ነው። በተጨማሪም ተማሪዎች በግቢ ውስጥ ሳሉ በውስጥ አገልግሎቱ በቅተው ነቅተው ይወጡበታል፤ ሥርዓቱን ይጠነቅቁበታል።

በግሌ በግቢ ጉባኤው ውስጥ የማገለግለው በመዝሙርና ሥነ ጥበብ ክፍል ነው። ብዙም ነው ባልልም የክፍሉ አባላት የግእዝ መዝሙራትን ለማስጠናት ሲዘጋጁ አንዳንድ ቃላት እንዴት እንደሚነበቡ ይጠይቁኛል። እኔም የምችለውን ያህል ተነሽ ተጣይውን፣ ሰያፍ ወዳቂውን ለማስረዳት እሞክራለሁ። …

ትምህርቱን መማር መጀመራችን በተወሰነ መልኩም ቢሆን ዲቁና ከተቀበልን በኋላ ሌሊት ገሥግሰን ለኪዳኑ፣ ለቅዳሴው እንድንመጣ ትጋታችንን ጨምሮልናል። የሚታዘዙትን ጸሎታት አብረን እንካፈላለን። ይህ ትጋት በተዘዋዋሪ የቀለሙ ትምህርት ለሚሻው የጊዜ አጠቃቀምና ትኩረት ራሳችንን እንድናስገዛ /የእንቅልፍ ሰዓታችንን ቀንሰን/ ረድቶናል።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር



www.eotcmk.org

# ፈተና የሚመጣው ከየት ነው?

## በፈተና የሚጸና ሰው የተባረከ ነው።" /ያዕ. 1÷12/

መምህር ደጀኔ ሽፈራው

*ባለፈው እትም እንደ ተመለከትነው ፈተናን እንደ ወጥመድ፥ እንደ መረብ፥ እንደ መሰናክል የሚያመጣው ጥንተ ጠላታችን ሰይጣን ነው። ምክንያቱም ጥንት አዳምንና ሔዋንን በምኞት ፈትኖ የጣላቸው እርሱ ነውና። ዘፍ.3÷1 ፤ራእ.12÷7-9። በአዲስ ኪዳንም ጌታችንና አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክር ስቶስ በገዳመ ቆሮንቶስ በፈቃዱ በተፈተነው ፈተና ስስትን በትዕግሥት፥ ፍቅረ ንዋይን በጸሊአ ንዋይ፥ ትዕቢትን በትሕትና ድል በማድረግ ፈተና ከሰይጣን መሆኑን አሳይቶናል። ይኸውም ለእኛ አብነት ሲሆነን ነው። ማቴ.4÷1-11። ቅዱስ ማቴዎስ በዚህ ምዕራፍ ላይ ሰይጣንን ፈታኝ ብሎታል።*

*ሰይጣን ሰውን ለመፈተን የሚገባበት በር፥የሚሾልክበት ቀዳዳ አለው። ይህም የእያንዳንዱ ሰው ድካም ነው። ስለሆነም የፈተና መምጫውን መንገድ ዐውቀን ለሕይወታችን እንድንጠነቀቅ "ፈተና ከየት ይመጣል?" የሚለውን ከዚህ እንደ ሚከተለው በዝርዝር እንመለከታለን።*

1ኛ፦ ከራስ

ፈተና ከራስ ይመጣል፤ ይኸውም ሰውነትን ካለመቆጣጠር ማለትም ፈቃደ ሥጋን ለፈቃደ ነፍስ ካለማስገዛት የሚመጣ ነው። የሰው ልጅ ወደ መንፈሳዊ ሕይወት ካላዘነበለ ፈቃደ ሥጋው እንደ ከብት ይነዳዋል፥ እንደ በግ ይጐትተዋል፥ እንደ መጠጥ ያስከረዋል። በዚህን ጊዜ ሰይጣን፥ የሥጋ ፍላጐቱንና የዐይን አምሮቱን ምክንያት አድርጐ ይፈትነዋል። በኃጢአት የሚቆሽሽበትን፥ በበደል የሚረክስበትን ክፉ ምግባር ያሠራዋል። ይህም ፈጥነው ንስሐ ካልገቡበት ሞተ ነፍስን /ከእግዚአብሔር መለየትን፣ በገሃነመ እሳት መውደቅን፣ በእሳት ባሕር መጣልን/ የሚያመጣ ነው። "ዳሩ ግን የሚፈሩና የማያምኑ፣ የርኵሳንም፣ የነፍስ ገዳዮችም፣ የሴሰኞዎችም፣ የአስማተኞችም፣ ጣዖትንም የሚያመልኩ የሐሰተኞዎች ሁሉ ዕድላቸው በዲንና በእሳት በሚቃጠል ባሕር ነው፤ ይኸውም ሁለተኛው ሞት ነው።" እንዲል። ራእ.21÷8። ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብም "ነገር ግን እያንዳንዱ በራሱ ምኞት ሲሳብና ሲታለል ይፈተናል። ከዚህ በኋላ ምኞት ጸንሳ ኃጢአትን ትወልዳለች፤ ኃጢአትም ካደገች በኋላ ሞትን ትወልዳለች።" ብሏል። ያዕ.1÷14-15።

ምኞትን በተመለከተ ከቅዱስ መጽሐፍ የአንዳንድ ሰዎችን ታሪክ እንመለከታለን። ምክንያቱም በቅዱስ መጽሐፍ መጻፉ እኛ እንድንማርበት፥ እንድንገሠጽበት፥ ልባችንን እንድናቀናበትና እንድንመከርበት ነውና። 2ኛጢሞ.3÷16-17። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በሮሜ መልእክቱ ላይ "በመጽናትና መጻሕፍት በሚሰጡት መጽናናት ተስፋ ይሆንልን ዘንድ አስቀድሞ የተጻፈው ሁሉ ለትምህርታችን ተጽፎአልና።" በማለት ይኸንኑ የመሰለ ነገር ደግሞ ተናግሯል። ሮሜ.15÷4። አምኖን ወልደ ዳዊት በእኅቱ በትዕማር የተፈተነው ፈተና የመነጨው ውስጡን ባሸነፈው ፍትወተ ሥጋ ነው። ከዚህም የተነሣ ከትካዜ ባሕር እስከ መውደቅ፥ በደዌ ዳኛ በአልጋ ቁራኛ እንደ ተያዘም ሰው እስከ መታመም ደርሷል። ይህን ነገር እንዲያስብ የገፋፋው የውስጥ ምኞቱ ነው። ጌታችን በወንጌል፦ "ከልብ፦ ክፉ አሳብ፥ መግደል፥ ምን ዝርነት፥ ዝሙት፥ መስረቅ፥ በውሸት መመስከር፥ ስድብ ይወጣልና።" በማለት የተናገረው ይኼንን ነው። ማቴ.15÷19። ይኼም ለሕይወት ከባድ ፈተና ነው። ምክንያቱም ከበጐ ሥራ ሁሉ ይለያልና ነው። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ "እኔ ግን ከኃጢአት በታች ልሆን የተሸጥሁ የሥጋ ነኝ /ሥጋዊ ደማዊ የምኾን እኔ ለኃጢአት ተሸጬ እኖራለሁ። በሥጋዊ በደማዊ ግብር ተስቤ በኃጢአት እመላ ለሳለሁ/።.... በውስጡ ሰውነቴ በእግዚአብሔር ሕግ ደስ ይለኛልና፤ /ሕገ እግዚአብሔር ለልቡናዬ የተስማማ ነው፥ አንድም በልቡናዬ አድሮ ያለ ሕገ እግዚአብሔር ያማረ ነው/፥ ነገር ግን በብ ልቶቼ /በሰውነቴ/ ከአእምሮዬ ሕግ ጋር /በውስጤ ካለ ከእግዚአብሔር ሕግ ጋር/ የሚዋጋውን /ባለመስማማት የሚጣላውን/ እና በብልቶቼ ባለ በኃጢአት ሕግ የሚማርከኝን /የሚያሸንፈኝን/ ሌላ ሕግ አያለሁ። /ፈቃደ ሥጋዬ አይሎ ወደርሱ ማረከኝ/። እኔ ምንኛ ጐስቋላ ሰው ነኝ! ለዚህ ሞት ከተሰጠ ሰውነት ማን ያድነኛል? /ፈራሽ በስባሽ ከሚሆን ከዚህ ሰውነቴ ፈቃድ ማን ባዳነኝ?/ እያለ በእኑሩ ሕይወት ተገብቶ ለቆሮንቶስ ሰዎች የጻፈላቸው ለዚህ ነው። ሮሜ.7÷14፣22-24።

አምኖን ክፉውን ከደጉ የሚለይበት ኀሊና እያለው በውስጡ ተጸንሶ ባደገ ምኞት ተከቦ ለጊዜያዊ ደስታ በኃጢአት ወደቀ። ምክንያቱም መጀመሪያ ከወደዳት ውድ ይልቅ ኋላ የጠላት ጥላቻ በልጧልና። በዚህም የእኅቱ ልብ በሐዘን እንዲሰበር አድርጓል። ይኸውም ከክብር ስላሳነሳት ደናግል ብቻ ይለብሱት የነበረውን ልብሷን እስክትቀድ፥ በራሷም ላይ ትቢያ እስክትነሰንስ፥ እንባዋንም እንደ ክረምት ጐርፍ እስክታፈስ ድረስ ነው። የአምኖንም መጨረሻ አላማረም። ወንድማቸው አቤሴሎም ለእናቱ ልጅ ለትዕማር ይበቀልላት ዘንድ አምኖንን በጦር አስወግቶ ከሚወዳት ዓለም ሳይወድ አሰናብቶታል። 2ኛሳሙ.13÷1-33።

2ኛ፦ ከባልንጀራ፦

ሰው የሚመስለው ባልንጀራውን ነው። ለዚህም ነው ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት "ከቸር ሰው ጋር ቸር ሆነህ ትገኛለህ /ንጽሕ ሥጋን ከያዘ ሰው ጋር ንጽሕ ሥጋን ትይዛለህ፥ ከወጣኒ ጋር ወጣኒ ሆነህ ትገኛለህ፥ ሠላሳ ከሚያፈሩ ጋር ሠላሳ ታፈራለህ/፥ ከንጹሕ ጋር ንጹሕ ሆነህ ትገኛለህ /ንጽሐ ነፍስን ከያዘ ጋር ንጽሐ ነፍስን ትይዛለህ፥ ከማዕከላዊ ጋር ማዕከላዊ ትሆናለህ፥ ስድሣ ከሚያፈሩ ጋር ስድሣ ታፈራለህ/፥ከቅን ሰው ጋር ቅን ሆነህ ትገኛለህ /ንጽሐ ልቡናን ከያዘ ሰው ጋር ንጽሐ ልቡናን ትይዛለህ፥ ከፍጹም ጋር ፍጹም ትሆናለህ፥ መቶ ከሚያፈሩ ጋር መቶ ታፈራለህ/፥ ከጠማማም ጋር ጠማማ ሆነህ ትገኛለህ፤" ያለው። መዝ.17÷25። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም፦ "አትሳቱ፥ ክፉ ባልንጀርነት መልካሙን አመል ያጠፋል።" ብሏል። 1ኛቆሮ. 15÷33።

በዚህ ዓለም በበጎዎች ተስበው ወደ በጎ ሕይወት ከመጡት ይልቅ በክፉዎች ተስበው ወደ ክፉ ሕይወት የገቡ ሰዎች ይበዛሉ። ይኸውም ክፉውን በጐ አስመስለው በማሳየት ስለሚያበረታቷቸው ነው። አዳምንና ሔዋንን ከእግዚአብሔር አንድነት የለያቸው የእባብ ጓደኝነት ነው። ዘፍ.3÷4-8። የያዕቆብን ልጅ ዲናን ከክብር እንድታንስ ያደረጋት የአሕዛብ ሴቶች ልጆች ጓደኛነት ነው። ዘፍ.34÷1-31። ከላይ እንደ ተመለከትነው አምኖን በውስጡ በተጸነሰው ክፉ አሳብ እንዲገፋበት ያደረገው የኢዮናዳብ ጓደኝነት ነው። 1ኛሳሙ.13÷5። ሐማ መርዶክዮስን ለመስቀል ግንድ ያዘጋጀው እበላ ባይ ጓደኞቹ መክረውት ነው። አስ.5÷14። ሮብዓም የተከበሩ የእስራኤል ሽማግሌዎችን ያሳዘነው በጓደኞቹ ምክር እንደ ከብት ተነድቶ ነው። 1ኛነገ.12÷11። እነዚህ ሁሉ መጨረሻቸው አላማረም። አዳምና ሔዋን መንጸፈ ደይን ወድቀው፥ በእግረ አጋንንት ተጠቅጥቀው ለአምስት ሺህ አምስት መቶ ዓመት በፍዳ በመርገም ኖሩ። ዲናም ንጽሕናዋን አጐደፈች፥ ክብሯን አዋረደች፥ በእርሷ የተነሣም ብዙ ሕይወት ጠፋ። አምኖንም ሕይወቱን አጣ። ሐማም "ሥራ ለሠሪው፥ እሾኽ ለአጣሪው" እንዲል ለመርዶክዮስ ካዘጋጀው ግንድ ላይ ተሰቀለ። ሮብዓም የተመካበትን ሥልጣን አጥቶ፥ ከቤተ መንግሥት ወጥቶ ተሰደደ።

በባልንጀራ በኩል የሚመጣ ፈተና ድምፅ የሌለው መሣሪያ ነው። ሲመዘዝ አይታይም፥ ሲተኰስም አይሰማም። መትቶ ከጣለ በኋላ ነው የሚታወቀው። ይህም የሚሆነው በማወቅም ይሁን ባለማወቅ የጠቀሙ መስለው ስለ ሚጐዱ ነው። በዓለም ላይ በባልንጀሮቻቸው ክፉ ምክር እንደ ጋሪ ፈረስ በአንድ አቅጣጫ ብቻ የሚነዱ አሉ። መጨረሻቸውም "ለሰው ቅን የምትመስል መንገድ አለች፥ ፍጻሜዋ ግን የሞት ነው።" እንደ ተባለው ይሆናል። ምሳ. 14÷12። ማንኛችንም ብንሆን መለስ ብለን





www.eotcmk.org

ከልጅነት እስከ ዕውቀት ያለ ውን ሕይወታችንን ብንመረምር ከባልንጀሮቻችን የተማርነውና የፈጸምነው በደል ብዙ ነው:: በተለይም በተለያዩ ሱሶች ተጠምደን መላቀቅ ያቃተን ሰዎች የሲጋራውን አጫጫስ፥ የጫቱን አቃቃም፥ የመጠጡን አጠጣጥ፥ የዝሙቱን አፈጸጸም፥ የጉቦውን አቀባበል፥ የሐሰትን አነጋገር፥ የገንዘብን አሰራረቅ በአጠቃላይ የድፍረትን ኃጢአት የተማርነው ከባልንጀሮቻችን ነው:: ስለዚህ ባልንጀራችን ማን እንደ ሆነ አስቀድመን መመርመር አለብን::

3ኛ ከሥልጣን:-

ጌታችንና አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በወንጌል እንደ ተጻፈ:- ሕሙማንን በመፈወሱ፥ ሙታንን በማስነሣቱ፥ ኅብስት አበርክቶ በማብላቱ ሊያነግሡት ፈለጉ:: ይኸውም "ብንታመም ይፈውሰናል፥ ብንሞት ያስነሣናል፥ ብንራብ ይመግበናል፤ ስለዚህ በዚህ ዓለም ውጣ ውረድ ምን አደከመን? እርሱን አንግሠን እንቀመጥ ነዋ! " ብለው ነው:: እነዚህም "መጨረሻቸው ጥፋት ነው፥ ሆዳቸው አምላካቸው ነው፥ ክብራቸው በነውራቸው ነው፥ አሳባቸው ምድራዊ ነው" እንደ ተባለባቸው ሰዎች ዓይነት ናቸው:: ፊል.3፥19:: በተጨማሪም "እንዲህ ያሉት ለገዛ ሆዳቸው እንጂ ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ አይገዙምና፤" ይላል:: ሮሜ. 16፥18::

ጌታችን፥ እነዚህ:- የበረከተውን ኅብስት በልተው የጠገቡ ሰዎች ያነግሡት ዘንድ ሊመጡና ሊነጥቁት እንዳላቸው ዐውቆ ደግሞ ወደ ተራራው ብቻውን ፈቀቅ አለ:: ከፊታቸው ዘወር አለ:: በኋላም በብዙ ፍለጋ አግኝተውት: - "መምህር ሆይ፥ ወደ ዚህ መቼ መጣህ?" አሉት:: እርሱ ግን "እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ የምትፈልጉኝ እንጀራን ስለ በላችሁና ስለ ጠገባችሁ ነው እንጂ ምልክቶችን ስላያችሁ አይደለም:: ለሚጠፋ መብል አትሥሩ፤ ነገር ግን ለዘላለም ሕይወት ለሚኖር መብል የሰው ልጅ /ወልደ ዕጓለ መሕያው ክርስቶስ/ ለሚሰጣችሁ ሥሩ፤" አላቸው::

ጌታችን ሊያነግሡት ባሉ ጊዜ ከፊታቸው ዘወር ያለው ስለ ሁለት ነገር ነው:: አንደኛው "እኔ ማንም የማያነግሠኝ የባሕርይ ንጉሥ ነኝ፤" ሲላቸው ነው:: "እግዚአብሔርሰ ንጉሥ ውእቱ እምቅድመ ዓለም፤ እግዚአብሔር ግን ከዓለም አስቀድሞ ንጉሥ ነው:: /ቅድመ ዓለም ንጉሥ፥ ማዕከለ ዓለም ንጉሥ፥ ድኅረ ዓለም ንጉሥ ነው፤/" እንዲል:: መዝ.73፥15:: "የነገሥታት ንጉሥና የጌታዎች ጌታ የሚል ስም አለው::" የሚልም አለ:: ራእ. 19፥16:: ሁለተኛው ለእኛ አብነት ሲሆነን ነው:: ይኸውም "ዓለም ልሹማችሁ ስትል ከሥልጣን ፊት ዘወር በሉ፥ ሥልጣንን ሽሹ፤" ሲለን ነው:: ዮሐ.6፥15-27:: 1ዮሐ. 2፥16:: ምክንያቱም ይህች ዓለም ብዙ ሰዎች በፍቅረ ሢመት /በሥልጣን ፍቅር/ የሚቸገሩባት ዓለም ናትና::

በዚህ ዓለም እንደ ምንመለከተው በሁሉም የሥራ መስክ ቅንነት ከነበራቸው ሰዎች ብዙዎቹ ሥልጣን ከጨበጡ በኋላ የቀደመ መልካም ሥራቸውን ይተዋሉ:: ፍርድ ያጓድላሉ፥ ደኻ ይበድላሉ፥ ጉቦ ይበላሉ፥ ለዘመድ አዝማድ ያደላሉ፥ ሰው ይንቃሉ:: ሰውን ማፈር፥ እግዚአብሔርን መፍራት ይተዋሉ:: በውስጣቸው ሆኖ ከሚወቅሳቸው የገዛ ኅሊናቸው ጋር ይጣላሉ:: ይሉኝታ ያጣሉ:: ከዚህም የተነሣ ሕይወታቸው ፈተና ውስጥ ይወድቅና ለሥልጣናቸው ሲሉ የማይፈጽሙት ወንጀል የለም:: በሥልጣናቸው ተመክተው ሌላውን ይገፋሉ::

ንጉሡ አክዓብ የደሀውን የናቡቴን ርስት ለመንጠቅ የተነሣው፥ በኋላም በሚስቱ በኤልዛቤል አማካይነት "ንጉሡንና እግዚአብሔርን ሰድቧል፤" በሚል ቃል በሐሰት አስመስክሮ ናቡቴን በማስገደል ርስቱን የነጠቀው በሥልጣኑ ተመክቶ ነው:: ከዚህም የተነሣ ወደ ነቢዩ ወደ ኤልያስ "ተነሥተህ በሰማርያ የሚኖረውን የእስራኤልን ንጉሥ አክዓብን ትገናኝ ዘንድ ውረድ፤ እነሆ፥ ይወርሰው ዘንድ በወረደበት በናቡቴ የወይን ቦታ ውስጥ አለ:: አንተም:- እግዚአብሔር እንዲህ ይላል:- ውሾች የናቡቴን ደም በላሱበት ሥፍራ የአንተን ደም ደግሞ ውሾች ይልሱታል ብለህ ንገረው::" የሚል የእግዚአብሔር ቃል መጣ:: ምዕ.20፥1-19::

የዚህ ዓለም ሰዎች አልሆንላቸው ብሎ ነው እንጂ በሥልጣናቸው የሚጋፉት ሰውን ብቻ ሳይሆን በልዕልና ያለ እግዚአብሔርንም ለመጋፋት ይፈልጋሉ:: ለዚህም ነው ፈርዖን..." ቃሉን እሰማ ዘንድ፥ እስራኤልን እለቅቅ ዘንድ እግዚአብሔር ማነው? እግዚአብሔርን አላውቅም፥ እስራኤልንም ደግሞ አልለቅም፤" ያለው:: ዘጸ. 5፥2:: ይህ ንጉሥ እግዚአብሔር በሙሴና በአሮን እጅ በፊቱ ብዙ ተአምራትን ቢያደርግም እግዚአብሔርን ወደ ማወቅ አልተመለሰም:: ፍጻሜውም ከነሠራዊቱ በባሕረ ኤርትራ ሰጥሞ መቅረት ሆነ:: ዘጸ.14፥26-31::

የአሦር ንጉሥ ሰናክሬምም መልእክተኛ ልኮ:- "ሕዝቅያስ፥ እግዚአብሔር ያድነናል ብሎ እንዳያታልላችሁ ተጠንቀቁ :: በውኑ የአሕዛብ አማልክት አገሮቻቸውን ከአሦር ንጉሥ እጅ አድነዋቸዋልን? የሐማትና የአርፋድ አማልክት ወዴት አሉ? ሰማርያን ከእጄ አድነዋታልን? እግዚአብሔር ኢየሩሳሌምን ከእጄ ያድን ዘንድ ከእነዚህ አገሮች አማልክት ሁሉ አገሩን ከእጄ ያዳነ ማነው?" እስከ ማለት የደረሰው ሥልጣን ባመጣበት ትዕቢት ምክንያት ነው:: በመጨረሻ ግን ከእግዚአብሔር የታዘዘ መልአክ ሠራዊቱን በሰይፍ ስለ መታበት ሁሉም በድን ሆነው አድረዋል:: ቁጥራቸውም አንድ መቶ ሰማኒያ አምስት ሺህ ነው:: እርሱም ወደ ሰናክሬም ሸሽቶ በሚያመልከው ጣዖት ፊት ሲሰግድ የገዛ ልጆቹ አድራሜሌክና ሳራሳር በሰይፍ መትተው ገድለውታል:: ይኸንንም ያደረጉት "ሕዝቡ ካለቀ ነገ እኛ በማን ላይ ልንነግሥ ነው፤" በማለት ለሥልጣን ብለው ነው:: ኢሳ. 36፥18-20፤ 37፥36-38:: በሥልጣን ጉዳይ ልጆች እንኳ ለወላጆቻቸው አይራሩም:: ለዚህም ነው የዳዊት ልጅ አቤሴሎምም በጥበብ የሕዝቡን ልብ ከሰረቀ በኋላ በአባቱ መንግሥት ላይ ዓምፆ እንዲሰደድ ያደረገው:: 2ኛ ሳሙ.15፥1-37:: በመጨረሻም ከአባቱ ሠራዊት ጋር ጦርነት ገጥሞ፥ በጦር ተወግቶ፥ በሰደፍ ተመቶ ይህቺን ዓለም ተሰናብቷል:: 2ኛሳሙ. 18፥14:: የሥልጣን ነገር ወንድማማቾችንም እርስ በርስ ያጨካክናቸ ዋል:: ለዚህም ነው አቤሜሌክ ሰብዓ ወንድሞቹ ን ያሳረዳቸው:: መሳ.9፥5:: ችግሩ አንዱ ከሌላው፥ የሚመጣው ካለፈው አይማ ርም:: ንጉሡ ናቡከደነፆር "መኖሪያህም ከምድር አራዊት ጋር ይሆናል፤ እንደ በሬም ሣር ትበላ ዘንድ ትገደዳለህ፥ ሰባት ዘመናትም ያልፉብሃል::" የሚል ፍርድ ተፈርዶበት ተፈጽሞበታል:: ጠጉሩ እንደ ንስር፥ ጥፍሮቹም እንደ ወፍ ጥፍር ረዘሙ፥ የገዛ ውሾቹም እየጮኹ ከቤተ መንግሥቱ ወጥቶ ተሰደደ:: ለሰባት ዓመት እንደ ከብት ሣር በላ:: ከዚህ በኋላ ልቡን ወደ እግዚአብሔር መለሰ:: ዳን. 4፥28-33:: ነገር ግን ዓለም ከናቡከደነፆር አልተማረም::

ሌላው ቀርቶ ልጁ ብልጣሶር እንኳ ከአባቱ ስሕተት መማር አልቻለም:: እርሱም እንደ አባቱ እየግዚአብሔርን በመድፈር ከንዋያተ ቅድሳቱ ከመኳንንቱ ጋር በላባት፤ ጠጣበት:: እግዚአብሔርም ገሥጾት ዕለቱኑ ሞቷል:: የተመካበትንም ሥልጣን ሜዶናዊው ዳርዮስ ወስዶታል:: ዳን.5፥1-31::

በአዲስ ኪዳንም በወንጌል እንደ ተጻፈው:- ንጉሡ ሄሮድስ ሕፃኑን ኢየሱስ ክርስቶስን ከእናቱ ከድንግል ማርያም ጋር ያሳደደው፥ በእርሱም ምክንያት በቤተ ልሔምና በአውራጃዋ የነበሩትን፥ ሁለት ዓመት የሆናቸውን ከዚያም የሚያንሱትን ሕፃናት ሁሉ ያስገደለው ለሥልጣን ብሎ ነው:: ይኸውም የተወለደው ሕፃን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ምድራውያን ነገሥታት እንደ ዳዊትና ሰሎሞን በይሁዳ ነግሦ የእርሱን ሥልጣን የሚያስቀር መስሎት ነው:: እርሱም ዕድሜ አላገኘም:: ማቴ.2፥1-20:: ሄሮድ ስም በሥልጣኑ ተመክቶ የሚያስር የሚገድል ሰው ነበር:: በዚህም መሠረት ሐዋርያውን ቅዱስ ያዕቆብን በሰ ይፍ ገድሎታል:: ቅዱስ ጴጥሮስን ደግሞ በሁለት ሰንሰለት አሳስሮ ወደ ወኅኒ ቤት ወርውሮታል:: የሐዋ.12፥1-4:: ይኸንን ያደርግ የነበረው እርሱ ራሱ ለመመለክ ስለ ፈለገ ነው:: ይህም የጢሮስና የሲዶና ሰዎች በቢትወደዱ አማላጅነት የንጉሡን እሺታ አግኝተው ለመታረቅ በቀረቡ ጊዜ ገሃድ ወጥቷል:: በዚህ ቀን ንጉሡ በወርቅ የተንቆጠቆጠ ልብሰ መንግሥቱን ለብሶ በሚያስፈራና በሚያንቀጠቅጥ ኹኔታ በዙፋን ተቀምጦ ሕዝቡን ተናገራቸው:: ሕዝቡም "ይህ ድምፅ የእግዚአብሔር ድምፅ ነው፥ የሰው አይደለም፤" ብለው በመጮኽ አምልኮታቸውን ገለጡለት:: እርሱም አይገባኝም ሳይል በደስታ ተቀበለ:: በዚህ ምክንያት ማለትም እግዚአብሔር ክብር ስላልሰጠ የጌታ መልአክ በሰይፍ መታው፥ በትልም ተበልቶ ሞተ:: የሐዋ.12፥20-23:: ዓለም እስከ ዛሬ ድረስ እነዚህን የመሳሰሉ የሥልጣን ሰዎችን አስተናግዳለች፥ ፍጻሜያቸው አላማረም እንጂ:: ለአብነት ያህል የታላላቁን ነገሥታት ታሪክ አነሣን እንጂ ይህ ችግር ከታች ከአጥቢያ ዳኛ፥ ከጭቃ ሹምና ከምስለኔ (ከታች እስከ ላይ ባሉ የአገልግሎትና የአስተዳደር መዋቅሮች የተሠየሙት) ጀምሮ ያለ ችግር ነው:: ይነ ስም ይብዛም፥ ሥጋዊም ይሁን መንፈሳዊ ሁሉም በሥልጣኑ ተፈትኖ ፈተናውን ወድቋል::

*ይቆየን::*





www.eotcmk.org

# ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ምንድን ነው?

ቀሲስ ስንታየሁ አባተ

ከአንዳንድ ምእመናን በስልክ፣በደብዳቤ፣በኢሜይል ከሚደርሱን ጥያቄዎች መካከል አብዛኛዎቹ በሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ዙሪያ የሚያተኩሩ ናቸው፡፡ «ባለንበት አገር በምትገኘው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሚያገለግሉ አንዳንድ ሰዎች ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን መጽሐፍ ቅዱሳዊ እንዳልሆነ፣ይልቁንም ኦሪታዊና ያለፈበት ነው ይላሉ፡፡ በመሆኑም እነዚህ ሰዎች ጫማ እንዳደረጉ ፣ሴቶች በወር አበባ ላይ እንዳሉ ወደ ቤተ ክርስቲያን ቢገቡ ችግር እንደ ሌለው፣ በሌላ በኩልም ሥጋ ወደሙን ለመቀበል ዐሥራ ስምንት ሰዓት መጾም እንደማይገባ፣የሚቀደሱትን ቅዳሴያትና ጊዜያታቸውን እንደ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ሳይሆን እንደ ዘመኑ ሥልጣኔ መምራት፣በመዝሙር በኩል በያሬዳዊ ዜማና ቤተ ክርስቲያናችን ካጸደቀቻቸው የመዝሙር መሣሪያዎች በተገኘው ዜማና መሣሪያ ብንዘምር ችግር የለውም» እያሉ ግራ እያጋቧቸው መሆኑን ገልጠው ጠይቀውናል፡፡

በመሠረቱ የእነኚህ የጥርጥር አሳቦች ዋነኛ አቀንቃኞች ችግር የሥርዓተ እምነት ብቻ ሳይሆን የሃይማኖትም መሆኑ መስተዋል ይኖርበታል፡፡ ቀድሞም የበግ ለምድ ለብሰው ሲያራምዱት የነበረውን የተሳሳተ እምነት አሁን በሚሰማውና በሚታየው መንገድ እያረጋገጡ የሚገኙት ደግሞ ወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስ እንደ ጻፈው «ከእኛ ዘንድ የወጡ ናቸው ግን ከእኛ ወገን ያልነበሩ÷ከእኛ ወገን እንዳልሆኑ ይገለጡ ዘንድ» ነው፡፡ 1ዮሐ.2÷18–19፡፡ ከዚህ አንጻር መዓርገ ክህነታችንን ሥያሜቸው፣ልብሰ ተክህኖአችንን መሸፈኛቸው ያደረጉ፣ለመንጋው የማይራሩ ጨካኞች ተኩላዎችም ይሁኑ ቤተ ክርስቲያናችን በየጊዜው አውግዛ የለየቻቸው የተሐድሶ መናፍቃን ጆሌዎች÷ሰው ሰውኛውን ቀላል በሚመስሉ ነገሮች ተሸጋግረው መጨረሻ ወደ ሌላው አዘቅት ሊጨምሩን የአጽራረ ቤተ ክርስቲያንን ተልእኮ ተሸክመው የሚንቀሳቀሱ በመሆናቸው ማንነታቸው ሊያደናግረን ድርጊታቸው ሊያሸብረን አይገባም፡፡

ስለ ግለሰቦቹ ወትሮም የነበረን አቋም አንድና ያው ቢሆንም በተለይ ማኅበራዊና መንፈሳዊ ችግሮች የተከበበው ምእመን የዘወትር ጥያቄ ግን ያሳስበናል፡፡

በመሆኑም የዝግጅት ክፍላችን በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ ላሉትና ተመሳሳይ ጥያቄ ለሚያነሡ ወገኖች መልስ ይሆን ዘንድ በሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ዙሪያ ቤተ ክርስቲያናችን የምታስተምረውን ትምህርት እንደ ሚከተለው አቅርቧል፡፡

## ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ምንድን ነው?

ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን የሁለት ቃላት ጥምር ነው፡፡ ሥርዓት ሠርዐ ከሚለው የግእዝ ግስ የተገኘ የምዕላድነት ዘር ያለው ስም ነው፡፡ ትርጉሙም ሕግ፣ደንብ፣ አሠራር... ማለት ነው፡፡ /ሊቀ ካህናት ክንፈ ገብርኤል አልታዬ÷ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ÷1992 ዓ.ም. ÷ገጽ 4/፡፡ ሥርዓት አንድ ድርጊት የሚፈጸምበት መመሪያ ደንብ ማለት ነው፡፡ ቤተ ክርስቲያን የሚለውም ሐረግ እንደ የአገባቡ የእግዚአብሔር የስሙ ማደሪያ የክብሩ መገለጫ የሆነው ቤት፣ በክቡር ደሙ የተዋጀውን የምእመናንን ሰውነት እንዲሁም በእግዚአብሔር ስም የተሰበሰቡ የምእመናንን አንድነት ያመለክታል፡፡ ማቴ.21÷13፤ 18÷17፡፡ በአጠቃላይ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ሲል የቤተ ክርስቲያን ሕግ÷ ቀኖና÷ አሠራር ማለት ነው፡፡ በዚህም ጽሑፍ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ስንልም ቅድስት ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በእምነትና በጥምቀት ወልዳ አካሎቿ ያደረገቻቸው ምእመናን የሚመሩበትን ሕግና ትእዛዝ የሚያመለክት ነው፡፡

## የሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን አመሠራረት፡—

የሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን አመሠራረት ከመዘርዘር በፊት የቤተ ክርስቲያንን የጉዞ ሒደት በጥቂቱ መመልከት ይገባል፡፡ የቤተ ክርስቲያንን የጉዞ ሒደት በሦስት ደረጃ /phase/ መክፈል ይቻላል፡፡ እነዚህም ሰው ከመፈጠሩ በፊት በዓለመ መላ እክት የነበረችው የቅዱሳን መላእክት አንድነት፣ከአዳም ጀምሮ እስከ ዘመነ ሐዲስ መግቢያ የነበሩ የደጋግ ሰዎች አንድነት፣በክርስቶስ ደም የተመሠረተችው የክርስቲያኖች አንድነት ናቸው፡፡ በሦስቱም ደረጃዎች የነበሩት አንድነቶች ቤተ ክርስቲያን ለመባል የበቁት በአንድነቱ ውስጥ ያሉት ግእዛን /ለባዊነት፣ ነባቢነት፣ሕያውነት/ ያላቸው ፍጥረታት ልዑል እግዚአብሔርን በማምለክ፣ መሥዋዕት በማቅረብ፣በሕጉ በመጽናት አንድነት ስላላቸው ነው፡፡

በሦስቱም ደረጃዎች የተጠቀሱት አንድነቶች ከእግዚአብሔር ጋር የነበራቸው ግንኙነት በሥርዓት ላይ የተመሠረተ ነበር፡፡ ቅዱሳን መላእክት በጥንተ ተፈጥሮ ህልውናቸውን ካገኙበት ዕለት ጀምሮ የአሠፋፈር፣የአመሰጋገን፣የመላላክ... ሥርዓት አላቸው፡፡ ቅዱሳን መላእክት እግዚአብሔርን ሲያመሰግኑ በክንፎቻቸው መላ አካላቸውን ይሸፍናሉ፡፡ ኢሳ.6÷3፤ራእ.4÷8፡፡ ሲያመሰግኑም ነጭ ልብስ ለብሰው፣የወርቅ አክሊል በራሳቸው ደፍተው የወርቅ ጽንሐሕ ይዘው በጽንሐሕአቸውም መልካም መዓዛ ያለው የዕጣን መሥዋዕት እያሳረጉ ነው፡፡ ራእ. 4÷4–5 8÷1–5፡፡ የተቀሩትም በሚያመሰግኑት በእግዚአብሔር ፊት መለከት ይነፋሉ፡፡ በፊቱም አክሊላቸውን ያኖራሉ፡፡ ራእ.4÷11፤፣8÷6፡፡ ይህ ሥርዓት ነው፤ የሥርዓቱም ባለቤት እግዚአብሔር ነው፡፡

ከአዳም ጀምሮ እስከ ክርስቶስ ድረስ የነበሩ ደጋግ ሰዎችም በእምነት ጸንተው እግዚአብሔርን ያገለገሉባቸው፣ እርሱንም ደስ ያሰኙባቸው፣ ታላቅ ዋጋን ያገኙባቸውና ቃል ኪዳን የተቀበሉባቸው ሥርዓቶች ነበሯቸው፡፡ እነዚህ ሥርዓቶችም እስከ ሙሴ ድረስ በሕገ ልቡና ብቻ የሚታወቁ ሲሆኑ ከሙሴ በኋላ ግን ከሕግ መሰጠት ጋር አብረው የተሰጡ ናቸው፡፡ ከእነዚህ ሥርዓቶችም መካከል በደብረ ሲና የተነገረውን ብቻ ማየት ይበቃል፡፡

ደብረ ሲና አስቀድሞ እግዚአብሔር ለሙሴ በአምሳለ ነበልባል ወሐመልማል የተገለጠባት ቦታ ናት፡፡ ሙሴ እግዚአብሔር የገለጠለትን ምሥጢር ለማየት በቀረበ ጊዜ ጫማውን ከእግሩ እንዲያወልቅ ታዘዘ፡፡ ለምን? እግዚአብሔር በዚያች ቦታ ምሥጢሩን ከመግለጡ የተነሣ ቦታዋ ተቀድሳለችና እግዚአብሔር የቀደሰውን ቦታ ማክበር የሚገባ በመሆኑ ጫማውን እንዲያወልቅ ተነገረው፡፡ ይህ ሥርዓት ነው፡፡ ዘጸ.3÷1፡፡ ከዚህም በኋላ ደብረ ሲና እግዚአብሔር በሙሴ በኩል ሕግጋቱንና ትእዛዛቱን ለሕዝቡ የሰጠባት፣ሥርዓት የተሠራባት ናት፡፡ ሙሴ ለሁለተኛ ጊዜ በእግ ዚአብሔር ተጠርቶ ወደ ደብረ ሲና ከመውጣቱ በፊት ለእርሱና ለሕዝቡ የተነገረው ሥርዓት ነበር፡፡

- ሕዝቡ ወደ እግረ ደብረ ሲና ከመውጣታቸው ከሦስት ቀናት በፊት ጀምረው ራሳቸውን እንዲቀድሱ፣መኝታ እንዲለዩ፣ ልብሳቸውን እንዲያጥቡ፤ 1ኛ



www.eotcmk.org

ሳሙ.21፥1-6።

- ወደ ተራራው ከወጡ በኋላ ደግሞ ከሕዝቡ ወገን የሆኑት ፈጽመው ተራራውን እንዳይነኩት ታዝዘዋል። /ዘጸ.19፥9-25/።

ሙሴና ወንድሙ አሮን ወደ ደብረ ሲና ከወጡ በኋላ ሙሴ ከአሮን ተለይቶ እግዚአብሔርን ያነጋገረበት የጨለማ ቦታ አለ። ይህም ደብረ ሲና በአቋቋም ከሦስት ክፍል እንደ ተከፈለች ያሳያል። ሕዝቡ የነበሩበት የተራራ ሥር /እግረ ደብር/፣አሮን ብቻውን የነበረበትና ሙሴ ከእግዚአብሔር ጋር ሲነጋገርበት የነበረው የጨለማው ክፍል /ርእሰ ደብር/ ናቸው። ዘጸ.19፥16-25፤ 20፥1-21። ቅዱስ ዳዊት «ጌታ በመቅደሱ በሲና በመካከላቸው ነው» በማለት የተናገረው ከላይ በተገለጠው መሠረት ደብረ ሲና በቤተ መቅደስ አምሳል ከሦስት ተከፍላ በአንደኛው ክፍሏ እግዚአብሔርና ሙሴ የተነጋገሩባት ስለሆነ ነው። መዝ.67፥17።

በደብረ ሲና እግዚአብሔር ሙሴንና ሕዝቡን ያዘዛቸው ነገር እግዚአብሔርን የሚያመልክ ሕዝብ በሥርዓት መኖር የሚገባው መሆኑን ያሳያል። ባልና ሚስት መኝታ በመለየት ራሳቸውን ይቀድሱ አለ። ለምን? በባልና በሚስት መካከል ያለው ተራክቦ ኃጢአት ነውን? ልብሳቸውን ይጠቡ አለ። ለእግዚአብሔር የሚያስፈልገው የልብ ወይስ የልብስ ንጽሕና? በባልና በሚስት መካከል በሕግ የሆነ ተራክቦ ኃጢአት ባይሆንም እግዚአብሔር በክብር ወደ ሚገለጥበት ወደ መቅደሱ ተራራ የሚወጡ ሁሉ ለሦስት ቀናት ያህል እንዲጠበቁ፣ልብሳቸውን እንዲያጥቡ እግዚአብሔር ወደደ፤ አዘዘ፤ ሥርዓት ሠራ። ከዚህም በተጨማሪ በዘመነ ኦሪት በነበረው ደብተራ ኦሪትም ሆነ መቅደሰ ኦሪት በርካታ ሥርዓቶች ተሠርተዋል። እግዚአብሔር ጽድቃቸውን የመሰከረላቸው እነ ዳዊት፣ ዘካርያስና ኤልሳቤጥ በእግዚአብሔር አምላክ ፈቃዱን ለመፈጸም የበቁት የተሠራላቸውን ሥርዓት ፈጽመው ነው። ምክንያቱም ሥርዓት በልቡና ያመኑትን እምነት በተግባር የሚታመኑበት /የሚፈጽሙበት/ የአሠራር መመሪያ ነው።

ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሚያስተምርበት ዘመን የእግዚአብሔርን ሥርዓት ችላ ብለው የራሳቸውን ሥጋዊ ወግ ብቻ ይዘው ይጓዙ የነበሩ ፈሪሳውያንን ነቅፏቸዋል። ማቴ.15፥6። እርሱ ግን እንደ ሰውነቱ በቤተ መቅደስ እየተገኘ በሙሴ በኩል ለሕዝብ ሰጥቶት የነበረውን ሥርዓት ሲፈጽም እንደ ነበር በመጽሐፍ ተጽፏል። ሉቃ.2፥21-24፤ 41-43። በሚያስተምርበት ዘመንም ደቀ መዛሙርቱ ይከተለው የነበረውን ሕዝብ በሥርዓት እንዲያስተናብሩ አዝዟል። ከቤተ ሳይዳ አጠገብ በምትገኝ ምድረ በዳ አምስት እንጀራና ሁለት ዓሣ ይከተሉት ለነበሩት አምስት ሺህ ሰዎች አበርክቶ ከመመ ገቡ በፊት ደቀ መዛሙርቱን « በየክፍሉ አምሳ አምሳውን አስቀምጡአቸው» አላቸው። ሉቃ.9፥14። በየክፍልና አምሳ አምሳ ማለት ለምን አስፈለገ? የእግዚአብሔርን በረከት ለመቀበል በሥርዓት ሆኖ በመገኘት መጠባበቅ የሚገባ በመሆኑ አይደለምን?

በክርስቶስ ደም በተመሠረተችው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አገልጋዮች ይሆኑ ዘንድ የተሾሙ ቅዱሳን ሐዋርያት ማንኛውንም ሐዋርያዊ ተልእኮ ይፈጽሙ የነበረው በሥርዓት ነው። ቅዱስ ጴጥሮስና ቅዱስ ዮሐንስ ከቀኑ በዘጠኝ ሰዓት ሊጸልዩ ወደ ቤተ መቅደስ እንደ ወጡ በሐዋ.3፥1 ላይ ተጠቅሷል። እግዚአብሔር በሌላ ሰዓት አይሰማም ወይ? ለምንድን ነው በዘጠኝ ሰዓት የተባለው? ካልጠፋስ ቦታ ለምን በቤተ መቅደስ አለ? ቤተ ክርስቲያን «በቀን ሰባት ጊዜ አመሰግንሃለሁ» ያለውን የዳዊትን ቃል መሠረት በማድረግ «ሰባቱ የጸሎት ጊዜያት» በማለት ሥርዓት አድርጋ ከወሰነቻቸው ሰዓቶች አንዱ ዘጠኝ ሰዓት ስለሆነ አይደለምን? ሊጸልዩ ወደ ቤተ መቅደስ የሔዱትስ ጌታችን በቤቱ የማይገባ ድርጊት ይፈጽሙበት የነበሩትን አውጥቶና አጽድቶ የጸሎት ቤት ትሆን ዘንድ ባርኮ ስለ ሰጠ አይደለምን? ማቴ.12፥12-16።

ቅዱሳን ሐዋርያትና በትምህርታቸው አምነው ተጠምቀው ከቤተ ክርስቲያን አንድነት አባል የሆኑ ሁሉ በግልም ይሁን በአንድነት ወደ ቤተ መቅደስ እንዳ ይገቡ ከተከለከለ በኋላም ቢሆን ቤተ ክርስቲያን ያለ ሥርዓት የኖረችበት ጊዜ የለም። ይልቁንም ቅዱሳን ሐዋርያት የሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን አስፈላጊነት በሚገባ አብራርተው አስረድተዋል። ደንግገዋልም። «ወንድሞች ሆይ፥ በእኛ እንደ ተቀበለው ወግ ሳይሆን ያለ ሥርዓት ከሚሔድ ወንድም ሁሉ ትለዩ ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እናዛችኋለን»፤ «ወንድሞች ሆይ፥ ያለ ሥርዓት የሚሔዱትን ገሥጹአቸው» እንዲል። 2ተሰ.3፥6፤1ተሰ.5፥14።

ከቅዱሳን ሐዋርያት በኋላ የተነሡ ቅዱሳን አበው ቤተ ክርስቲያን ተልእኮዋን ለመፈጸም የምትችልበትን ሥርዓት በተሰጣቸው ሥልጣን መሠረት ሠርተዋል። «...የቀረውን እንድታደራጅ፣ በየከተማውም እኔ አንተን እንዳዘዝሁ፣ ቀሳውስትን እንድትሾም በቀርጤስ ተውሁህ» ቲቶ.1፥5። ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን በአንድ ጊዜ አልተደነገገም። በመሆኑም ነው ቅዱስ ጳውሎስ የቀርጤስን ሰዎች ካሳመነና መምህር የሚሆናቸው ቲቶን መድቦ ቤተ ክርስቲያኒቱ የምትመራበትን ሥርዓት እንዲያደራጅ በመልእክቱ የሚያሳስበው። በዚሁ መሠረት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በጥምቀት የወለደቻቸውን ምእመናንን የምትመራበት ሥርዓት ሥልጣኑን በመንፈስ ቅዱስ ባገኙት አበው ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት አንድነት /ሲኖዶስ/ አማካይነት ትደነግጋለች። ቤተ ክርስቲያናችን በዓለም ዐቀፍ ደረጃ /ከቅዱሳን ሐዋርያት ሲኖዶስ አንሥቶ በኒቂያ፣በቁስጥንጥንያና በኤፌሶን/ በተደረጉ ጉባኤያት የተደነገጉ ሥርዓቶችን የምትቀበለው ከላይ በተገለጠው እውነታ መሠረት ነው። በሀገር ዐቀፍ ደረጃም ቢሆን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የበላይ መሪ የሆነው ቅዱስ ሲኖዶስ መክሮና ዘክሮ ከአሥራው መጻሕፍት፣ቤተ ክርስቲያኒቱ ከተቀበለቻቸው መጻሕፍተ ሊቃውንትና አዋልድ መጻሕፍት እንዲሁም በዓለም አቀፍ ደረጃ ከተደረጉ ዐበይት ጉባኤያት ውሳኔዎች አንጻር የሚወስነውና የሚደነግገው ሥርዓት ተፈጻሚ ይሆናል።

በአጠቃላይ እምነት ባለበት ሥርዓት አለ። ያለ ሥርዓት የሚፈጸም ነገረ ሃይማኖት የለም። የሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንም አመሠራረት ከክርስትና መገለጥ ጋር አብሮ የተገኘ ነው። በዓለመ መላእክት ያሉ ቅዱሳን መላእክት፣በዘመነ ብሉይ የነበሩ ደጋግ አበው፣ በክርስቶስ ደም የተመሠረተችው ቤተ ክርስቲያን ሁሉ ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸው አንድነት የሚጸናበት፣እምነታቸው በተግባር ላይ የሚውልበት በሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን አማካይነት ነው። ቅዱስ ጳውሎስ አስቀድሞ ባስተማራቸው ወግ /ሥርዓት/ ጸንተው የተገኙትን አመስግኖ በቀጣዩ ደግሞ በሃይማኖት ሲኖሩ ሊፈጽሙት የሚገባቸውን ሥርዓት ለቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን በዝርዝር የጻፈላቸው ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን፥ እምነት ባለው ክርስቲያን ሕይወት ውስጥ የግድ መፈጸምና መጠበቅ የሚገባው ስለሆነ ነው። 1ቆሮ.11፥2-16። ሐዋርያው የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ልትመራበት የሚገባትን ሥርዓት ካስረዳ በኋላ «ዳሩ ግን ማንም ቢፈቅድ እኛ ወይም የእግዚአብሔር አብያተ ክርስቲያናት እንዲህ ያለ ልማድ /ከሥርዓት ውጪ መሆን/ የለንም» ብሏል። ይህም ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ከዘመንና ጊዜ በኋላ የተደነገገ ሳይሆን በፊት በአበው ቀደምትና በደጋግ ነቢያት በኋላም በቅዱሳን ከሐዋርያት ዘመን ጀምሮ የተመሠረተ መሆኑን ያሳያል። 1ቆሮ.11፥16።

## የሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ምንጭ

ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን በዘፈቀደ ሰዎች ከልቡናቸው አንቅተው የመሠረቱትና የሚመሠርቱት አይደለም። የትመጣነቱን ሊያስረዳ የማይችል «ሥርዓት»ም ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ተብሎ አይነገርም፤ አይቆጠርም። ከዚህ እውነታ ተነሥተን የቅድስት ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችንን ሥርዓቶች ምንጮች ስንመረምር መጽሐፋዊ ሆነው እናገኛቸዋለን። እነዚህ መጻሕፍትም በቤተ ክርስቲያናችን እውቅናን /ተቀባ





www.eotcmk.org

ይነትን/ ያገኙ ናቸው:: የሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ምንጮች የሚባሉትም:–

1. መጻሕፍተ ብሉያት
2. መጻሕፍተ ሐዲሳት
3. የሐዋርያት ሲኖዶስ
4. ሥርዓተ ጽዮን
5. አብጥሊስ
6. ትእዛዝ
7. ዲድስቅልያ
8. ፍትሐ መንፈሳዊ
9. የሦስቱ ጉባኤያት /ኒቂያ፣ ቁስጥንጥንያ፣ ኤፌሶን/ ውሳኔዎች
10. በየዘመኑ የተነሡ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት የጻፏቸው የሥርዓት መጻሕፍት ናቸው::

ከላይ በተዘረዘሩት መጻሕፍት ምንጭነት ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ሲደነገግ በአንድና በሁለት ሰዎች መስማማት ብቻ የሚከናወን ሳይሆን በቅዱስ ሲኖዶስ ተመክሮበት ነው:: ቅዱስ ሲኖዶስም ለቤተ ክርስቲያን ሥርዓት መሠረት የሆኑትን ሥርዓተ ደብተራ ኦሪትን፣ሥርዓተ መቅደስ ኦሪትን፣ሥርዓተ ካህናተ ኦሪትን አስተውሎ ለሐዲስ ኪዳን ቤተ መቅደስ በሚስማማው መልኩ ይደነግጋል:: ምክንያቱም በብሉይ ኪዳን የነበረችው ቤተ መቅደስ በሰማይ ያለችው የአማናዊቷ ቤተ መቅደስ ምሳሌ ነበረች:: ዕብ.8÷5–6:: ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ደግሞ ሰማያውያንና ምድራውያን አንድ የሚሆኑባት፣ በሰማያዊቱ ቤተ መቅደስ ያለው ሥርዓት የሚፈጸምባት የእግዚአብሔር የምሕረት አደባባይ ናት::

ምድራዊቷ ቤተ መቅደስ ምሳሌዋ ከሆነችው ከሰማያዊቷ ቤተ መቅደስ በምንጭነት የተወሰዱ ሥርዓቶች አሏት:: የመሠዊያ /የታቦት/ መኖር፣ የሚለበሰው ነጭ ልብስ፣በመሠዊያው ፊት የሚያገለግሉ ካህናት፣ የሚቀዳጁት አክሊል፣ የሚያበሩት መብራት፣የሚያሰሙት የምስጋና ድምፅ፣ የሚይዙት ጽንሐሕ፣ የሚያሳርጉት ዕጣን፣ የሚያወጁት የመጽሐፍ ቃል ...በተለያዩ የራእየ ዮሐንስ ምዕራፎች ተገልጧል::

## የሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን አስፈላጊነት

አንዳንድ ሰዎች ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን እንደ አላስፈላጊና በምእመናን ላይ ቀንበር እንደ መጫን አድርገው ይመለከታሉ:: በመሆኑም ከሥርዓት የተለየ ሕይወት ይመራሉ:: በርግጥ የሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን አስፈላጊነትና ጥቅም ያልተረዳ ሰው ያላመነበትን ሥርዓት መፈጸሙ ለእርሱ እንደ ሸክም ሊመስለው ይችላል:: የአምልኮት መልክ ያላቸው ነገር ግን መንፈሳዊነት የጎደላቸው÷መንፈሳውያን መሆን ያልቻሉ፣ ለሥጋ ድካማቸውና ጥቅማቸው መሸፈኛ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን ያቃልላሉ:: ለመንፈሳዊ ሰው የሚከብደው ግን ኃጢአትን መሥራት÷በደልን መፈጸም ብቻ ነው::

ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን በማወቅና በመረዳት የምንፈጽመው ከሆነ በእምነት አድርገን የቅድስናን ሕይወት እናገኝበታለን:: ቀንበሩ ልዝብ ሸክሙ ቀሊል ነው:: ባለመረዳትና በተለምዶ ብቻ የምንፈጽመው ከሆነ ግን መሰላቸትን፣ መተቸትንና ኑፋቄን ያመጣል:: ለመንፈሳዊ ሕይወታችን እንቅፋት ይሆንብናል:: ተምሮ ተረድቶ አምኖ መቀበሉ ለሌለው ሰው ጫማውን አውልቆ ወደ ቤተ ክርስቲያን መግባት፣በቅዱሳት ሥዕላት ፊት ቆሞ መጸለይ፣ሥጋ ወደሙን ለመቀበል የሚደረጉ ቅድመ ዝግጅቶችና ከተቀበሉም በኋላ የሚፈጸሙ ሥርዓቶች ተረት ይመ ስለዋል:: በሒደትም ሥርዓተ ቤተ ክር ስቲያንን በመተቸት የተጀመረ ዝለት ነገረ ሃይማኖትን ሁሉ እስከ መካድ ያደርሳል:: ለመካድ ያበቃል::

ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ቀንበር ሆኖ የሚጫን ሕግ ሳይሆን ለልቡና የሚረዳ፣ አእምሮን ወደ ረቀቀው ሰማያዊ ምሥጢር የሚያሸጋግር የቤተ ክርስቲያን አካልና በዘመናት ቅብብሎሽ የተረከብነው ሐዋርያዊ ቅርስ ነው:: ወደ ቤተ ክርስቲያን ለመግባት ጫማችንን ከእግራችን እናወልቃለን:: ድርጊቱን በመረዳት የምንፈጽመው ከሆነ ጫማችንን ከእግራችን እንዳወለቅነው ሁሉ ወደ ቤቱ ገብተን የለመነው እግዚአብሔር በምሕረቱ ብዛት በእግረ ልቡናችን ተገዝተን ሽተን የፈጸምነውን ኃጢአት ከልቡናችን አውልቆ እንደ ሚጥልልን እንረዳለን:: በሥርዓተ ቅዳሴያችን ምንበቂ የሆነ ብርሃን ቢኖር እንኳን ሻማ ወይም ጧፍ አብርተን ነው የምንቀድሰው:: ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን የሚነቅፍ ሰው ምናልባት ይህ መብራት እያለ ጧፍ ወይም ሻማ ማብራታችን ብክነት መስሎ ሊታየው ይችላል:: በእምነት ለምንፈጽመው ግን በቅዳሴያችን የምናመሰግነውና የምንለምነው እግዚአብሔር ብርሃን መሆኑን፣ ብርሃን መጎናጸፉን በእርሱም ጋር በእምነት በጥምቀት በመልካም ሕይወት አንድነት ያላቸው ብርሃናውያን መሆናችንን የምንገልጥበት ሥርዓት ነው:: አንድም ጧፍ፣ ሻማ መሥዋዕተ እግዚአብሔር ናቸው በሌላም በኩል ጧፉ፣ሻማ እየቀለጠ፣እየነደደ ለሌላው ብርሃን እንደሚሰጥ ሁሉ ጌታችን እርሱ ሞቶ ለእኛ ሕይወት እንደሆነን፤ ቅዱሳንም እርሱን አብነት አድርገው በትምህርታቸው በቱሩፋታቸው ለዓለም ብርሃን መሆናቸውን ያመለክታል:: /ማቴ.5÷14–16፤ ፊልጵ. 2÷15–16፣ዮሐ.1÷4–9፤9÷52/:: በዚህ መሠረት ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን እንደ ነፍስና እንደ ሥጋ የሆኑ ሁለት ክፍሎች አሉት:: በአፍአዊ ድርጊት የምንፈጽመው እንደ ሥጋ ያለ ሲሆን ከድርጊቱ በስተ ጀርባ ያለው ረቂቅ መንፈሳዊ ምሥጢር ደግሞ እንደ ነፍስ የሆነው ክፍል ነው:: ሥጋው ከላይ የምናየው መመሪያው ሲሆን ነፍሱ ደግሞ ከውስጥ የምናገኘው መንፈሳዊ ትርጓሜው ነው:: መመሪያውን ብቻ የሚቀበል ሥጋን /በድን/ ብቻ እንደ ተቀበለ ነው:: መንፈሳዊውን ትርጓሜ ብቻ የወሰደም ነፍስን /የማይጨበጠውን/ ብቻ እንደ ተቀበለ ይሆናል:: ሁለቱን ማዋሐድ ይገባል::

ልዑል እግዚአብሔር የሥርዓት ባለቤት ነው:: በሕግ በአምልኮ ወደ እርሱ ሊቀርቡ የሚሹ ሁሉ መንፈሳዊ አካሔዳቸው ሥርዓትን የተከተለ እንዲሆን ይወድዳል:: ምክንያቱም «እግዚአብሔር የሁከት አምላክ አይደለም::» 1ቆሮ.14÷33:: የሁከት አምላክ ባለመሆኑም በምእመናን መካከል ልዩነት ተፈጥሮ ሁከት እንዳይሆን በአንድ መመሪያ፣ በአንድ ልቡና . እንዲያመልኩት ሥርዓትን ሠርቷል:: ሐዋርያው «ሁሉ በአግባብና በሥርዓት ይሁን» በማለት በሰጠው ትምህርት መሠረት ቤተ ክርስቲያን ከእግዚአብሔር የተቀበለችውን የመሰብሰብ፣ የመጠበቅና የመመገብ ተልእኮዋን ለልጆቿ የምትፈጽመው በሥርዓቷ አማካይነት ነው:: ይህም ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን የክርስትና እምነት መገለጫና መጠበቂያ፣ የመጨረሻው ግብ ሳይሆን ግባቸውን ለማሳካት የሚረዳቸው፣ ለእግዚአብሔር መገዛታቸውን የሚገልጡበት፣ ያለመለያየት ሥርዓተ አምልኮአቸውን ለመፈጸም የሚግባቡት ቋንቋቸው ነው::

## በአጠቃላይ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን

1. አስተማሪ ነው:: ቤተ ክርስቲያን በሥርዓቷ አማካይነት መሠረተ እምነቷን /ዶግማዋን/ ታስተምርበታለች:: ለምሳሌ:– በትእምርተ መስቀል በማማተብ ሥርዓት ብቻ ሕፃናት ምሥጢረ ሥላሴን፣ ነገረ መስቀሉንና ነገረ ድኅነትን ይማራሉ::

2. ነፍስና ሥጋ ባለመለያየት የሰማያዊ ምሥጢር ተካፋይ እንዲሆኑ ያደርጋል:: ምሳሌ:– የምንለብሰው ነጭ ልብስ፣ በእግዚአብሔር ፊት የምንሰግደው ስግደት፣ በተመስጦ ሆነን እጆችንን ዘርግተን የምንጸልየው ጸሎት፤

3.ፍጥረታት ለእግዚአብሔር ምስጋና ድርሻ እንዲኖራቸው ያደርጋል::

ምሳሌ :– ከበሮው መዝሙሩን ያጅባል፤ ዕጣኑ የቀረበው ጸሎት ያርግበታል:: ራእ.8.4:: ስንዴው፣ ወይኑ፣ የወይራ ዘይቱ ከምስጋናም አልፎ ጸጋን ያሰጣል::

ለመሥዋዕተ ወንጌል ማዘጋጃነት የሚያገለግለው ስንዴው፣ ወይኑ ዘላለማዊ ሕይወትን ለማግኘት ያስችላል::

4.የመጽሐፍ÷ ቅዱስን መንፈሳዊ ትርጉም በጉልህ በውል ለመረዳት ያስችላል::

ለምሳሌ:– ምሥጢረ ተክሊል፤ በዚህ ሥርዓት አማካይነት በሙሽራውና በሙሽሪት መካከል ያለው አንድነት /መዋሐድ/ በክርስቶስና በቤተ ክርስቲያን መካከል ያለውን አንድነት አጉልቶ ያስረዳል:: ኤፌ.5÷21–33::

/ይቆየን/

ወስብሐት ለእግዚአብሔር



www.eotcmk.org

# ዝክረ ቴዎፍሎስ፡ጴጥሮስ ወሚካኤል

**ባለፈው እትማችን ከ43 ዓመታት በፊት በፋሺስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል የሰማዕትነት አክሊል የተቀዳጁትን የሰማዕቱ ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ ቀዳማዊንና የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ 2ኛ የኢትዮጵያ ዜና ሕይወትና የሰማዕትነት ታሪክ አቅርበናል። አሁን ደግሞ ብፁዕ አቡነ ሚካኤል ቀዳማዊ «ጳጳስ ዘአዜብ ኢትዮጵያ ተላዌ አሠሩ ለአቡነ ዜና ማርቆስ» /? – 1929 ዓ.ም/ አቅርበናል። መልካም ንባብ።**

መዓርገ ጵጵስናን ከመቀበላቸው በፊት አባ ኃይለ ሚካኤል ይባሉ የነበሩት ብፁዕ አቡነ ሚካኤል በቀድሞው ቤጌምድር ጠቅላይ ግዛት አፈረ ዋናት ልጫ መስቀለ ክርስቶስ በተባለ ቦታ ተወለዱ። በዚያው በተወለዱበትም አካባቢ ግንድ አጠመም ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን በጥምቅት እንደ ገና ሲወለዱ ስመ ጥምቀታቸው ኃይለ ሚካኤል ተባለ።

ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ በዚያው በትውልድ አገራቸው መሪ ጌታ ዋሴ ከተባሉ አስተማሪ የመጀመሪያ ደረጃ የቤተ ክህነት ትምህርታቸውን አጠናቀቁ። ከዚያ በኋላ ከግብፃዊው አቡነ ጴጥሮስ ማዓርግ ዲቁና ተቀብለው በዚያው በትውልድ አገራቸው ዘገቦ ጽዮን በተባለ ቤተ መቅደስ በዲቁና አገለገሉ።

ብፁዕነታቸው ትምህርታቸውን በመቀጠል በጎንደር መካነ ሰማዕት ቅዱስ ገላውዴዎስ ቤተ ክርስቲያን ጉባኤ ዘርግተው ያስተምሩ ወደ ነበሩት መሪ ጌታ ተድላ ዘንድ ሔደው ጸዋትወ ዜማን፣ ማኅደረ ማርያም ከነበሩት መ/ር ወልደ ሩፋኤልም መዝገብ ድጓን በሚገባ ተማሩ።

የዜማ ትምህርታቸውን በተገለጠው ሁኔታ ያጠናቀቁት ብፁዕ አቡነ ሚካኤል መጻሕፍትን ለመማር በነበራቸው ፍላጐት የተነሣ ወደ ጎንደር ከተማ በመሔድ ከመ/ር ተስፋዬ ዘንድ የብሉያትንና የሐዲሳትን ትርጓሜ በሚገባ አጠኑ። በጎንደር የጀመሩትን የመጻሕፍት ትርጓሜ ትምህርት የበለጠ ለመማር በወቅቱ ስመ ጥር ወደ ነበሩት የብፁዕ አባቶች መምህር ወደ ነበሩት መምህር አካለ ወልድ ዘንድ ተሻገሩ። በዚያም ሐዲሳቱን በሚገባ በማስፋፋትና ቅኔን ከነምሥጢሩና አገባቡ ጠንቅቀው ለቅኔ መምህርነት የሚያበቃ ምስክርነት ያዙ።

መንፈሳዊውን ትምህርት ከዳር ለማድረስ ቆርጠው የተነሡት ብፁዕ አቡነ ሚካኤል ከቦሩ ሥላሴ ወደ አዲስ አበባ መጥተው በገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ደብር ሰፊ ጉባኤ ዘርግተው ያስተምሩ ከነበሩት መ/ር ወልደ ጊዮርጊስ ዘንድ የዓሥራ አራቱን ቅዳሴያት ዜማ በጥንቃቄ ተማሩ። በዚህ ጊዜ በወቅቱ የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ከነበሩት ግብፃዊው አቡነ ማቴዎስ መዓርገ ቅስናን ተቀበሉ።

በዚህ ሁሉ ሒደታቸው፣ ትምህርታቸውና ግብረ ገብነታቸው ለሰዎች ዘንድ ስለ ተመሰከረ ይህም በቤተ መንግሥቱ በመሰማቱ ወደ መኳንንቱና መሳፍንቱ ቀርበው የወ/ሮ ወለተ ዮሐንስ አበ ነፍስ ለመሆን በቁ። ሞያቸውና ግብረ ገብነታቸው የበለጠ ከዕለት ወደ ዕለት እየተጠናከረና እየተመሰከረ በመሔዱም ከአበ ነፍስነት አገልግሎት አልፎ ወደ ቤተ መንግሥቱ በመግባት የምክር ድጋፍ እንዲያደርጉ ተሾሙ።

ከንጉሡ ቤተ መንግሥት በሚወጣው ሕግና መመሪያ በቀጥታ ተሳታፊ በመሆን በማገልገል ላይ የነበሩት ብፁዕነታቸው ከዚያ ከፍ ላለውና ለትምህርታቸውና ለማንነታቸው ተስማሚ የሆነ ቦታ ተመርጠላቸው የዜና ማርቆስና የገዳማት አስተዳዳሪ ሆነው ተሾሙ። የተሰጣቸውን ሐላፊነት በብቃት እየተወጡ ጥቂት ዓመታት ከቆዩ በኋላ እንደ ገና በአዲስ አበባው ደብረ ጽጌ ቅዱስ ዑራኤል፣ ቀይቶም በማኅበረ ማርያም በእልቅና ተሹመው ለሕዝበ ምእመናኑ ትምህርት በመስጠት፣ ካህናትን በማትጋት ሲያገለግሉ ቆዩ።

በኮፕትና በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መካከል ለረጅም ዘመናት ዘልቆ የነበረው የጵጵስና ሹመት ክርክር ተፈጽሞ ኢትዮጵያውያን ወደ ጵጵስና ሹመት መድረክ እንዲቀርቡ በተደረገ ጊዜ ለታላቁ ሹመት ከተመረጡት አባቶች ብፁዕ አቡነ ሚካኤል አንዱ ሆኑ። ከሌሎች አባቶች ጋር ወደ ካይሮ በመሔድም ግንቦት 18 ቀን 1921 ዓ.ም. መዓርገ ጵጵስናን ተቀበሉ።

አቡነ ሚካኤል ተብለው ወደ ሀገራቸው የተመለሱት ብፁዕነታቸው ከዓመት በኋላ «አባ ሚካኤል ጳጳስ ዘአዜብ ኢትዮጵያ ተላዌ አሠሩ ለአቡነ ዜና ማርቆስ» ተብለው በኢሊባቦርና በከፋ ጠቅላይ ግዛቶች ተሾሙ።

ዕድሜያቸውን በሙሉ በትምህርትና በትኅርምት ያሳለፉት ብፁዕነታቸው የዘወትር ዓላማቸው ምእመናንን ማስተማር ነበረና በተሰጣቸው ሀገረ ስብከት የሚገኙ የመንፈስ ቅዱስ ልጆቻቸውን በመንፈሳዊ ትምህርት እና ምክር ያጠናክሩ፣ ተወዳጅ የነበረውንም ሐዋርያዊ ተልእኮአቸውን ያፋጥኑ ጀመር። በዚህ ተግባራቸው እርሳቸውም እየተደሰቱና እግዚአብሔርን እያመሰገኑ፣ ምእመናንም በብፁዕነታቸው ትምህርተ ወንጌል እየጠገቡና ቅድስት ቤተ ክርስቲያ ናቸውን እያወቁ ለሰባት ዓመታት ቆዩ።

ምንም እንኳን በቂ ናቸው ባይባልም ያሉት አራት አባቶች ኢትዮጵያን ተከፋፍለው ለረጅም ዘመናት በቋንቋው የሚናገር ብፁዓን አበው አጥቶ የቆየውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ከካህናቱና ሊቃውንቱ ጋር በመተባበር እውነተኛውን የወንጌል ትምህርት እያስተማሩ ከቤተ ክርስቲያኑ ጋር በማስተዋወቅ ላይ ሳሉ በ1928 ዓ.ም. ግፈኛው የኢጣልያ ፋሽስት ጦር ኢትዮጵያን ወረረ። ወረራውም ከሰሜኑና መካከለኛው የሀገሪቱ ክፍል አልፎ እሳቸው ሀገረ ስብከት ደርሶ መንበረ ጵጵስናቸው የነበረበት የጎሬ ከተማ ኮሎኔል ማልታ በተባለ የጦር አዛዥ በሚመራ የጦር ኃይል እጅ ወደቀ። በዚህ ጊዜ ብፁዕነታቸው መንበረ

**ከዚያም ከኮሎኔል ማልታ ፊት ቀርበው ሕዝብን ከማነሣሣት ሥራቸው ተቆጥበው የማረጋጋት ሥራ ለምን እንደማይሠሩ ተጠየቁ። ቆራጡ ብፁዕ አቡነ ሚካኤልም በጠላት እጅ መውደቃቸው ምንም ሳያስፈራቸው የፋሽስትን በኢትዮጵያ የበላይነት ወይም አስተዳዳሪነት መንበር መቀመጥ በፍጹም ዕውቅና የማይሰጡትና የማይቀበሉት መሆኑን፣ ኢትዮጵያ የኢትዮጵያውያን ብቻ መሆን ዋን፣ ይህንንም ሐቅ አለመመስከር፣ ሕዝቡንም ለትግል አለማስተባበር ፍጹም ኃጢአት መሆኑን በድፍረት ዘርዝረው አስረዱ።**



www.eotcmk.org

ጽጽስናቸውን ለቀው ሰምቢ ወደ ተባለች የገጠር ቀበሌ በመሔድ በፍጹም አባትነት፣ ስሜትና ወኔ «ኢትዮጵያ የኢትዮጵያውያን ብቻ እንጂ የሌላ አይደለችም» በማለት የአገሬ ስብከታቸው ሕዝብ ባሕር አቋርጦ ሊወረው በመጣው ጠላቱ ላይ እንዲነሣ ማስረባበር ጀመሩ።

ይህ የብፁዕነታቸው ስብከት ለወራሪው ኃይል ትልቅ እሳት ሆነ። ይህንንም በተረዳ ነገር ያወቀው ፋሺስት ፈቃደኛ ከሆኑ ሕዝቡ «መንግሥቴ የጣልያኑ ፋሺስት መንግሥት ነው» ብለ ይቀበል ዘንድ እንዲሰብኩ፣ ካልፈቀዱ ግን መስበካቸውን እንዲያቆሙ በደብዳቤ ጠየቃቸው። ሰውም ልኮ አስጠየቃቸው። ብፁዕነታቸው ግን በዓላማ መጽናትን ያውቁበታልና ከእውነተኛው የአገር ፍቅር ዓላማቸው እንደ ማያፈገፍጉ፣ እስከ መጨረሻውም ደማቸውን አፍስሰው ለውድ አገራቸው ቤዛ ለመሆን የማይቀዘቅዝ ስሜት እንዳላቸው በሙሉ ልብ አረጋግጠው ላኩበት።

ይህንን የብፁዕ አቡነ ሚካኤልን ጽናት የተረዳው ፋሺስትም ያሰበውን ለመተግበር የብፁዕነታቸውን ዐቋም በማረጋገጥ በሌሎች ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን ላይ እንደ ፈጸመው ሁሉ በእርሳቸውም ላይ የግድያ ርምጃ ለመፈጸም ወሰነ። ብፁዕነታቸውም ለጠላት በአንደበታቸው ባረጋገጡለት መሠረት በአገሬ ስብከታቸው ከአውራጃ ወደ ወረዳ እየተዘዋወሩ ሕዝቡ የተባበረ ክንዱን በጠላት ላይ እንዲያነሣ ከውግዘት ጋር መስበካቸውን ቀጠሉ። በስብከት ጉዞ ላይ እንዳሉ እዚያው ሰምቢ ቀበሌ አጠገብ ከሚገኝ ጫካ ውስጥ በጠላት ጦር ተከብበው በቆራጥነትና በአርበኝነት ሲዋጉ አንድ ሌሊት ካደሩ በኋላ በመጨረሻ ከሌሎች ሁለት አርበኞች ጋር በጠላት እጅ ወደቁ።

ከዚያም ከኮሎኔል ማልታ ፊት ቀርበው ሕዝብን ከማነሣሣት ሥራቸው ተቆጥበው የማረጋጋት ሥራ ለምን እንደ ማይሠሩ ተጠየቁ። ቆራጡ ብፁዕ አቡነ ሚካኤልም በጠላት እጅ መውደቃቸው ምንም ሳያስፈራቸው የፋሽስትን በኢትዮጵያ የበላይነት ወይም አስተዳዳሪነት መንበር መቀመጥ በፍጹም ዕውቅና የማይሰጡትና የማይቀበሉት መሆኑን፣ ኢትዮጵያ የኢትዮጵያውያን ብቻ መሆንዋን፣ ይህንንም ሐቅ አለመመስከር፣ ሕዝቡንም ለትግል አለማስተባበር ፍጹም ኃጢአት መሆኑን በድፍረት ዘርዝረው አስረዱ።

ይህንን ቆራጥነታቸውን ከአንደበታቸው የተረዳው ፋሺስትም በሰጡትቁርጠኛ መልስ ተናዶ እርሳቸውንና አብረዋቸው የተያዙትን ቀኝ አዝማች ይነሡንና ግራ አዝማች ተክለ ሃይማኖት ይባሉ የነበሩ አርበኞችን ለስምንት ቀናት ያህል ሌሊት በውርጭ ቀን በፀሐይ ሲያሰቃያቸው ሰነበተ። በመጨረሻም ኅዳር 21 ቀን 1929 ዓ.ም. ከተያዙት ሁለት አርበኞች ጋር በጥይት ተደብድበው እንዲሞቱ ፍርድ አስተላለፈ። ኅዳር 24 ቀን 1929 ዓ.ም. ፍርዱ ተግባራዊ ሆኖ ብፁዕነታቸው በሰማዕትነት ዐረፉ። ነጻነቷ ተመልሶ ንጉሡ ከስደት የተመለሱ በኋላ በ1934 ዓ.ም መታሰቢያ ይሆናቸው ዘንድ በሰማዕትነት ባለፉበት ጎሬ ከተማ አንድ ት/ቤት እንዲቆም አደረጉላቸው። የብፁዕ አቡነ ሚካኤል ረድኤት አይለየን። አሜን።


## በቃል ያለው እንዳይረሳ
# ከሰይጣን ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ

ሐመርና ስምዐ ጽድቅ በልዩ ልዩ ጊዜ ለምእመናን ካቀረቧቸው ሥራዎች መካከል የተውጣጡትን የተለያዩ መጣጥፎች፣ ግጥሞች፣ አባባሎች፣ ምሳሌዎች፣ ወ.ዘ.ተ. በተለያዩ እትሞች ተበታትነው ቀርበው ከነበሩት መካከል የተወሰኑት በዚህ መጽሐፍ ተሰባስበው ቀርበዋል። በተመሳሳይ ከዚህ በፊት ምሥጢሬን ላካፍላችሁ አንደኛና ሁለተኛ መጽሐፍ እንዲሁም ቬነሲያን የመሳሰሉ ተመሳሳይ ዝግጅቶችን ማቅረባችን ይታወሳል።

**በሁሉም የሐመር መጽሔት እና የስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ**
**ማከፋፈያዎቻችን ውስጥ ያገኟቸዋል !!**
**ስልክ ቁጥር 23-45-29/23-45-30/22-86-01**

**DAANDII AMANTII**
**/ፍኖተ ሰሚን/**
**የሚል አዲስ የኦሮምኛ ቁጥር ፩ መጽሐፍ በሥርጭት ላይ ውሏል !!**
**ቁጥር ፪ በቅርብ ቀን ተዘጋጅቶ ይቀርባል !!**
**አሳታሚና አከፋፋይ:- ማኅበረ ቅዱሳን**




## ደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤል

/ከገጽ ፲፯ ዞሯል/

የተባሉ መነኩሴ የቀረጹት ለመሆናቸው ይነገራል። ይህ ግን የተጨበጠ ማስረጃ አልተገኘለትም። እንዲሁም ዐፄ ምኒልክ ከኢየሩሳሌም እንዳስመጡት ይነገራል። ከዐፄ ዮሐንስ ለዐፄ ምኒልክ እንደ ተሰጠም የሚናገሩ አሉ።

ቤተ መቅደሱ እንዴት እንደ ተሠራ ድምፀ ተዋሕዶ ጋዜጣ በ1980 ዓ.ም ጸሐፊ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ የጻፉት መጽሐፍ ጠቅሰው እንደ ዘገበው:- አንድ መነኩሴ ዝዋይ ከደሴቱ ውስጥ ገብቶ ብዙ መጻሕፍትን አገኘ። ከዚያም ትልልቅ መጻሕፍት አግኝቶ ከመጻሕፍቱ ክብደት የተነሣ ለማውጣት ባለመቻሉ የዐፄ ልብነ ድንግልን ታሪክ የያዘች፣ ራጉኤል መልአክ ለዐፄ ልብነ ድንግል የነገራቸው ራእይ ያለበትን አንድ ትንሽ ክብረ ነገሥት ይዞ ወጣ። ይህንንም መጽሐፍ ንጉሡ ተቀብለው በማንበብ ከዐፄ ዮሐንስ ጋር ተስማምተው መግዛታቸውን፥ እንጦጦ ከተማ ሆነው የእመቤታችን የእግዝእትነ ማርያምንና የቅዱስ ራጉኤልን ቤተ ክርስቲያን ተክለው በማቋቋም አገራቸውን ሁሉ ማቅ ናታቸውን ራጉኤል መልአክ ለዐፄ ልብነ ድንግል በራእይ ከነገራቸው ታሪክ ውስጥ ተመዝግቦ አገኙት ይላል።

ለዚህ ነበር ዐፄ ምኒልክ የቀድሞው ዐፄ ዳዊት ከተማ ያስከተሙበት ቦታ በውል ተመርምሮ እስኪገኝ በወጨጫ ላይ ቤት ለማሠራት የጀመሩት።

የእንጦጦ ደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤል ቤተ ክርስቲያን በነበረው ሥርዓት መሠረት ዐፄ ምኒልክ ለቤተ ክርስቲያኑና ለካህናቱ መገልገያ የሆነ ሁለት መቶ ጋሻ መሬት ተክለው ደብሩን ደብረው፣ በየዓመቱ ከመንበረ ክብሩ ወጥቶ ዑደት ተፈጽሞ እስኪመለስ ከንጋቱ ጀምሮ ነጋሪት እየተጐሰመ፣ መድፍ እየተተኮሰ በታላቅ ሥነ ሥርዓት ሲከበር የኖረ ታላቅና ታሪካዊ ቤተ መቅደስ ነው።

በወቅቱ በተለያየ ምክንያት ነፍስ የገደለ፥ ቤት ያቃጠለ፥ ቋንጃ የቆረጠ ወንጀለኛ በዚህ ደብር ገብቶ በመማፀን እጁን ከሰጠ ሙሉ ምሕረት የሚደረግለት መሆኑን ዐፄ ምኒልክ ቃል የገቡለት እጅግ የከበረ ታላቅ ደብር ነበር።

ታቦተ ሕጉ ወደ መሐል ከተማ እንዲዛወር ንግሥት እቴጌ መነን በመጠየቃቸው ቤተ ክህነትም ፈቅዶ የቀድሞው ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ /የአሁኑ መርካቶ/ ቦታ ግንቦት 1 ቀን 1945 ዓ.ም በወቅቱ የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳት፣ ቆይቶም ፓትርያርክ የነበሩት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ፓትርያርክ ቡራኬ ሰጥተው የመሠረት ድንጋይ አኖሩ። ሥራው ሁለት ዓመት ፈጅቶ በ1947 ዓ.ም ተጠናቅቆ ጳጉሜን 6 ቀን ታቦተ ሕጉ ከእንጦጦ ወደ መሐል ከተማ ካመራ በኋላ ለማረፊያ ወደ ተተከለው

/ወደ ገጽ ፵ ዞሯል/





www.eotcmk.org

# «ግእዝ ፈጽሞ አይሞትም፤ ማንም ሊገድለውም አይችልም።»

*ፕሮፌሰር ኤፍሬም ይስሐቅ /Ph.D.,D.H.L. (hon.)/*

የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በመጀመሪያ ዲግሪና በድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር ያሠለጠናቸውን 3,558 ተማሪዎች ሐምሌ 18 ቀን 1996 ዓ.ም ባስመረቀበት ወቅት ባከናወኑት ምርምርና ጥናት እንዲሁም በሕይወት ዘመናቸው ለኢትዮጵያ ብሎም ለአፍሪካ ባበረከቱት ከፍተኛ አስተዋፅዖ አምስት ታላላቅ ምሁራንን መርጦ የክብር ዶክትሬት ዲግሪ ሰጥቷል። ከእኒህም መካከል ባለፈው የሐመር መጽሔት እትም እንግዳችን የነበሩት ፕሮፌሰር ኤፍሬም ይስሐቅ ይገኙበታል። በወሊጋ በምትገኘው ነጆ ወረዳ የተወለዱት ፕሮፌሰር ኤፍሬም ይስሐቅ ሚኒስትሮች፣ ከፍተኛ ባለሥልጣናት፣ አምባሳደሮች፣ ታዋቂ ሰዎችና የተመራቂዎች ቤተሰቦች በታደሙበት ሥነ ሥርዓት ላይ ንግግር ያደረጉት በግእዝ ቋንቋ ነበር። በንግግራቸውም ኢትዮጵያ የ ራስዋ ባሕል፣ ቋንቋዎችና እምነት ያላት የብሔር ብሔረሰቦች መገኛ ጥንታዊት አገር መሆኗን ጠቁመው፤ ይህችን እያላት ያጣች አገር ለማሳደግ ሁሉም በያለበት ተግቶ መንቀሳቀስ እንደ ሚገባው አስገንዝበዋል። አገሪቱ ከሌላው ዓለም የምትፈልገው የቴክኖሎጂ ሽግግር ብቻ መሆኑን አመልክተው መጪውን ብሩህ ዘመን የልማት፣ የዕድገትና የብልጽግና ለማድረግ ከተኛንበት መንቃት ይጠበቅብናል ብለዋል። ሁሉም በየሚሔዱበት ሁሉ በኢትዮጵያ ብሩህ ቀን መፈንጠቁን ማብሠርና ለተግባራዊነቱ ም ያለ ምንም ቀስቃሽ መሥራት እንዳለበት ጠቁመዋል። ፕሮፌሰር ኤፍሬም ይስሐቅ በሀርቫርድ ዩኒቨርስቲ የአፍሪካ-አሜሪካ ጥናት ትምህርት ክፍል የግእዝ ቋንቋ ትምህርት እንዲጀመር፣ የኢትዮጵያን ጥንታዊ ሥልጣኔ ከሥር ጀምሮ ለማጥናት ከፍተኛ ጥረት ያደረጉ፣ ማይምነትን ከኢትዮጵያ ለማጥፋት በግንባር ቀደምነት የተሳተፉ፣ በመምህርነት ሞያ ያገለገሉና በማገልገል ላይ የሚገኙ፣ 17 ቋንቋዎችን ያህል መናገር የሚችሉ፣ ለሰላም ግንባታ አስተዋፅዖ ያደረጉ መሆናቸውን ባለፈው እትማችን መግለጻችን ይታወሳል። ከነዚህም ጋር አትዮጵያዊ አለባበስን፣ ሐበሻና ኢትዮጵያዊነትን፣ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ለአንድነትና ሰላም ያላትን አስተዋፅዖ፣ የግእዝና የዕብራይስጥን ቋንቋ ዝምድናና የግእዝን ቀዳሚነት የተመለከቱ ማብራሪያዎቻቸውን አቅርበናል። በአሁኑ ዝግጅታችን አሉላ ጥላሁንና ተስፋዬ ሽብሩ ከምሁሩ ጋር ያደረጉትን ቆይታ የመጨረሻ ክፍል እናስነብባለን። በዚህ አጋጣሚ የዝግጅት ክፍላችን የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለፕሮፌሰር አፍሬም ይስሐቅ በሰጣቸው የክብር ዶክትሬት ዲግሪ የተሰማውን ከፍተኛ ደስታ ለመግለጽ ይወዳል።

## የግእዝ ቋንቋና መጻሕፍት /መጽሐፈ ሔኖክ፥ መጽሐፈ ኩፋሌ/ ታላቅነት

ብዙ ጊዜ በየአጋጣሚው የምመክረው ነገር አለ። በዓለም ላይ የመጽሐፍ ቅዱስን የጥንት ታሪክ የሚመራመሩ ሰዎች ቢያንስ ሰባት ቋንቋዎችን ማወቅ አለባቸው። ዕብራይስጥን፣ ግሪክን፣ ሱርስትን /የሶርያን/፣ የኮፕትን፣ የላቲንንና የግእዝን ቋንቋዎች ማወቅ አለባቸው። መጽሐፍ ቅዱስ አስቀድሞ ከተተረጎመባቸው ሰባት ቋንቋዎች የመጀመሪያው የግእዝ ቋንቋ ነው። ከዚያም ውጭ ብዙ መጻሕፍተ አይሁድ አሉ። ብዙዎቹ ወደ ግሪክ፣ ላቲንና ሶርያ ተተርጉመዋል። በወቅቱ መጻሕፍትን የማቃጠል ነገር ስለ ነበር ተቃጥለው የጠፉ አንዳንዶች አሉ። በአገራችን ግን መጻሕፍትን ማቃጠል ክልክል ነው። ዐይታችሁ እንደ ሆነ ብዙ መጻሕፍት ላይ «ዘፋሀቆ /ዘዐውአዮ/ ዝንቱ መጽሐፍ ውጉዝ ውእቱ፤ ይህን መጽሐፍ የፋቀው ወይም ያቃጠለው የተወገዘ ይሁን» ይላል። በዚህና በመሳሰሉት ምክንያቶች ከሌላው ዓለም ጠፍተው በአገራችን ተጠብቀው የሚገኙ እንደ መጽሐፈ ሔኖክና መጽሐፈ ኩፋሌ የመሳሰሉ መጻሕፍት ይገኛሉ። ሊቃውንት እንደ ሚሉት አሁን ያለው የይሁዲ እምነት ተጠብቆ የክርስትና ሃይማኖትም የተስፋፋበት መሠረተ ቃል በመጽሐፈ ሔኖክ ላይ ተገልጿል።

ምክንያቱም በወንጌላት ላይ የሚጠቀሱት ቃላት ከመጽሐፈ ሔኖክ



ፕሮፌሰር አፍሬም ይስሐቅ የክብር ዶክትሬት ዲግሪ በተቀበሉበት ወቅት



የመጡ ናቸው። ለምሳሌ፦ ወልደ ዕጓለ መሕያው /የሰው ልጅ/ ይላል፤ ስለ መጨረሻው ዘመን ስንናገር ስምንተኛው ሺ እንላለን፤ ይህ ትልቅ ነገር ነው። በሌላው አይታወቅም፤ በኢትዮጵያ በሚገኘው የግእዝ መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ



www.eotcmk.org

ነው ይኼ የሚታወቀው:: ባዘጋጀሁት መጽሐፍ ላይ ይህንን ገልጫለሁ፤ መጽሐፈ ሔኖክ ብቻ ሳይሆን መጽሐፈ ኩፋሌም ለጥንቱ የእሥራኤል ታሪክ ጥናት ጠቃሚ ነው ተብሎ ማናቸውም ተመራማሪ ይጠቀምበታል::

ኢትዮጵያ በጥንታዊው የሥነ ጽሑፍ ታሪክ በዓለም የመጀመሪያውን ረድፍ የምትይዝ አገር ናት:: በእንግሊዝ፣ በፈረንሳይ፣ በጀርመን ዛሬ የሚጻፉት ሁሉ ከኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ በኋላ የመጡ ናቸው:: ከኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ ጋር የሚወዳደሩት ትልልቆቹ የግሪክ፣ የአራማይክ፣ የላቲን የመሳሰሉቱ ናቸው:: ኢትዮጵያን ታላቅ ከሚያደርጓት ሀብቶቿ አንዱ ይኸው የግእዝ ሥነ ጽሑፍ ነው:: የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንት መጽሐፉ እንዴት ኾኖ በግእዝ እንደ ተተረጐመ ማጥናት ይኖርባቸዋል:: ይኸ ደግሞ ከሰባቱ የመጽሐፍ ቅዱስ መሠረታዊ ቋንቋዎች እኩል በመኾኑ እንጂ በሌላ አይደለም:: ዛሬ መጽሐፍ ቅዱስ በ3000 ያህል ቋንቋዎች ተተርጉሟል:: በተጨማሪም በሌላ ዓለም የጠፉት መጽሐፈ ሔኖክና መጽሐፈ ኩፋሌ በግእዙ ብቻ ነው የሚገኙት:: አንዳንዶቹ ቋንቋውን ስለ ማይችሉ በግእዙ ብቻ ያጠኑታል:: አሁን በስፓኒሽ፣ በፈረንሳይኛ፣ በጀርመንኛ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተሠሩ ሥራዎችን ብታዩ መጽሐፈ ሔኖክን አስመልክቶ የማይጽፍ ሊቅ የለም:: እኛ ከግእዙ ወደ እንግሊዝኛ ቋንቋ ከተረጎምናቸው ደግሞ ሁሉም ያነቡታል:: ዋናውን መሠረት ማየት አለብን የሚሉ ደግሞ ግእዙን ለመማር ይሞክራሉ::

## በቤትዎ ያሉና ያነበቧቸው መጻሕፍት
## «ሕይወቴን በሙሉ ስለ ኢትዮጵያ አንብቤያለሁ»

ያነበብኳቸው መጻሕፍትና ጽሑፎች ብዙ ናቸው:: ምናልባትም ሕይወቴን በሙሉ ስለ ኢትዮጵያ አንብቤያለሁ ማለት ይቻላል:: ብዙ ቋንቋ ስለ ማውቅ ስለ አገራችን የተጻፈ ካጋጠመኝ አላልፈውም::

በቤቴም ከመላው ዓለም በአያሌ ቋንቋዎች የተሰባሰቡ መጻሕፍት አሉኝ:: ወደ አገራችን ስንመለስ በግእዝ የተጻፉ 200 መጻሕፍት አሉኝ:: በልዩ ልዩ ጆርናሎች ላይ ስለ አገራችን የተጻፉትን መጣጥፎች አሰባስቤ አስቀምጫለሁ:: እነዚህም በጀርመንኛ፣ በጣሊያንኛ፣ በፈረንሳይኛ የተጻፉ ናቸው:: አንድ ሁለቱን ልጥቀስላችሁ:: 'ሬስኛ ዶ ስቱድ ኢትዮፒ'፣ 'ሪንዲኮንቲ ዘ ሪያል አካዳሚ ደሊቼ'- በኢትዮጵያ ቋንቋ፣ ወግ፣ ባሕልና ሥነ ጽሑፍ ላይ ያተኩራሉ:: በአጠቃላይ ሰብስቤ ሰባት ቅጽ መጻሕፍት ወጥቶአቸዋል:: በመጽሐፍ ደረጃ የታተሙትን ማግኘት ቀላል ነው:: በየመደብሩ ላገኛቸው እችላለሁ:: በአርቲክል መልክ የተጻፉትን መሰብሰብ ግን ከባድና አስቸጋሪም ነው:: ለማሳተም አስቤም ወደ ግማሽ ሚሊዮን ብር እንደ ሚያስፈልገኝ ነው የተነገረኝ::

## የግእዝ ሥነ ጽሑፍ ይዘትና ጥልቀት?
## «አገራችን በሥነ ጽሑፍ በኩል ያላት ሀብት ሰፊና ጥልቅ÷ በጣም ጥልቅ ነው::»

ከዓመታት በፊት በአገራችን በሚገኙት የግእዝ መጻሕፍት ዙሪያ ጥናት አድርጌ ነበር:: ከዚያ መነሻ አድርገህ ገምት ብባል ቢያንስ አሁን ኢትዮጵያ ውስጥ 30 ሺ አብያተ ክርስቲያን ይገኛሉ:: በእያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን ሦስትም፣ አራትም መጻሕፍት ይኖራሉ ብዬ እገምታለሁ:: በየገዳማቱ 10 ሊኖር ይችላል:: ያኔ እኔ ባጠናሁት ጊዜ ከሁለት እስከ ሦስት መቶ መጻሕፍት ያላቸውም አጋጥመውኛል:: ትግራይ፣ ጐንደርና ላሊበላ ደርሼ በኤርትራ የሚገኘውን ደብረ ቢዘንንም ጐብኝቻለሁ:: ሀርቫርድ ውስጥ አማርኛን የሚያስተምሩ የእኔ ረዳት ነበሩ:: ኢትዮጵያዊ ናቸው:: በአንድ ገዳም ውስጥ ካህን ነበሩና መጽሐፍ እንዲያሳዩኝ ጠየቅኋቸው:: የእኛ ካህናት እንደ ሚታቀው እያለም የለምን ያዘወትራሉ:: ይጠራጠራሉም:: አልሚ ልሁንም አጥፊ ያውቁኛል:: ስለዚህ «ድሮ ነበር÷ አሁንማ ምን አለ?» አሉኝ:: ያለውን ያሳዩኝ አልኳቸው:: አንድ ክፍል ወስደው ጥቂቱን አሳዩኝ፤ 50 መጻሕፍት ገደማ ይሆናሉ:: ተደሰትኩኝ:: አንደኛው ካህን ደግሞ ስላልተጠራጠሩ ይመስላል ለአበ ምኔቱ «ሌላውንም እናሳያቸው?!» ይሏቸዋል:: አምነውኝ አንዱን ክፍል ይከፍቱታል:: ግድግዳው ሁሉ በመጻሕፍት የተሞላ ነበር:: በወቅቱ እንደ ገመትኩት 2000 የሚሆኑ መጻሕፍት ነበሩ:: በደስታ ሰከርኩ:: የ13ኛው፣ የ14ኛው ክፍለ ዘመን ታሪካችን ተመዝግቧል:: አንዱ መጽሐፍ በተለይ ሦስት ሺ ገጽ ነበረው:: መጽሐፍ ቅዱስ ነው:: እያንዳንዱ ገጽ በአንድ ፍየል ቆዳ ላይ እንደ ተጻፈ ነገሩኝ:: ሰው ያልደረሰባቸው የጥንት ገዳማት ለወደ ፊቱ ታላላቅ ነገር እንደ ሚገኝባቸው አምናለሁ፤ ይኸውም ደግሞ ልክ በቁምራን ዋሻ በ1940ዎቹ እንደ ተገኙት የሙት ባሕር ጥቅልሎች (The Dead Sea Scrolls) ማለት ነው:: አንዳንዶቹ እንዲያውም ጽሕፈታቸው ከእኛ መጻሕፍት ጋር የተያያዙ ሳይሆኑ አይቀሩም:: ወደ እንግሊዘኛ ተርጉሜ ሳበቃ ተንትኜ ያሳተምኩት የአባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ ድርሰት የኾነ መጽሐፈ ምሥጢር የተሰኘውን መጽሐፍ ነበር:: እዚያ ላይ ለምሳሌ «Liturgy»/ሥርዓተ ቅዳሴ/ አለ:: ያ ቅዳሴ በሙት ባሕር ከተገኘው ጋር ይገጣጠማል:: በመሆኑም ሥነ ጽሑፎቻችን በዚህ መልኩ ብዙ ምርመራ ያሻቸዋል:: የኾነው ኾኖ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መጻሕፍት /ሥነ ጽሑፎችን/ የሚወዳደረው ከትንንሾቹ ጋር ሳይሆን የግሪክን፣ የላቲንን፣ የአራማይክን፣ የዕብራይስጥን ከመሳሰሉት ከታላላቆቹ ጋር ነው:: በአጠቃላይ በአገራችን ያለው ሀብት በተለይም በሥነ ጽሑፍ በኩል እንዲህ እንደ ዋዛ የሚያነሡት አይደለም:: ሰፊና ጥልቅ፣ በጣም ጥልቅ ነው::

በተቃራኒው ደግሞ እንደ ምታውቁት ብዙዎቻችን ራሳችንን አናከብርም:: በ1960ዎቹ ብቅ ያለው ትውልድ አባላት ስለ ማኦ፣ ስለ ሌኒን ሲያነብና ሲጽፍ ዐየሁና «ለምን የራሳችንን ሊቃውንት መርምረን ለሕዝባችን አናስተዋውቃቸውም?» አልኩ:: ይህን ጊዜ አንድ ወንድሜ «ኢትዮጵያ ትልቅ አገር ናት ትላለህ፤ ሼክስፒር የት አለ? ሞልዬር የት አለ?» አለኝ:: ምጭጭ..... ያሳዝናል! ይህ የኾነበት ምክንያቱ÷ ወጣቶቻችንን ስለ ኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ ስላላስተማርናቸው ነው:: ታድያ መልሼ ምን አልኩት÷ አንተ ወንድሜ ሆይ÷ ክብረ ነገሥትን፣ ገድለ ተክለ ሃይማኖትን፣ ገድለ ገብረ መንፈስ ቅዱስን፣ ገድለ ክርስቶስ ሠምራን፣ ገድለ ኢየሱስ ሞዐን፣ ገድለ ወለተ ጴጥሮስን... የመሳሰሉ መጻሕፍት አሉን:: አንብበሃቸው ታውቃለህን? አልኩት:: እንኳን ሊያነብ ቃላቱንም እንደ ማያውቅ ነገረኝ:: በእውነቱ እናንተም ተደንቃችሁ አታባሩም:: ሌላው ሁሉ ቢቀር እንኳን ዘመኑን አስተሳሰቡን ለቃኘ አንባቢ ጥሩ የኪነ ጥበብ ዘዴና ዕውቀት ይቀስምባቸዋል:: እነ ሼክስፒር ትላንት የመጡ ናቸው:: ከእነርሱ በፊት ቀደም ብሎ ብዙ የሚነገርላቸው ሥነ ጽሑፋዊ ሀብቶቻችን አሉ:: ሰሞኑን አንድ መምህር እኔ ዘንድ መጥተው ነበር:: «ስለ ገድለ ክርስቶስ ሠምራ ያውቃሉ ወይ?» ብለው ጠየቁኝ:: እኔ «በፈረንሳይኛ ቋንቋ ተተርጉሞ አንቤበዋለሁ» አልኳቸው:: በጽሑፎቻችን ውስጥ ያሉት ገጸ ባሕርያት ሰላም የሚወዱ፣ ዕርቅ አድርጉ የሚሉ ናቸው:: እንዲያውም «ሰይጣንን ለምን ከእግዚአብሔር ጋር አትታረቅም?» ያሉ ናቸው:: ዳሩ ግን ኢትዮጵያውያን ወጣቶች ስለነዚህ ታላላቅ ሰዎች እንዲማሩ የሚያስችላቸው ነገር አልነበረም:: ከአሁን በኋላ እንግዲህ በኢትዮጵያ ትምህርት ቤቶች ግእዝ መሠረታዊ /required/ የኾነ ቋንቋ መኾን አለበት:: መሠረታዊ /required/ ማለቴ ማናቸውም ኢትዮጵያዊ የግድ ለአንድ ዓመት እንዲማረው ያስፈልጋል ማለቴ ነው:: ከዚያ ቀጥሎ ደግሞ ክርስቲያኑም፣ እስላሙም ኾነ ይሁዲው ኢትዮጵያዊ ሁሉ አንዳንድ የኢትዮጵያ መጻሕፍትን ማንበብ ይገባዋል:: ...እንዴ...



www.eotcmk.org

እኒህ የጥንት መጻሕፍት ናቸው'ኮ::

በበኩሌ በ1969 እ.ኤ.አ የአፍሪካ-አሜሪካውያን ትምህርት ክፍል ሲከፈት መጀመሪያ የተቀጠርኩት አፍሪካዊ ፕሮፌሰር /ከነጮቹም በፊት/ እኔ ነኝ:: በወቅቱ <The Ethiopian Church> /የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን/ ብዬ ያስተማርኩት ኮርስ አለ:: <The Ethiopian Literature> /የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ/ ብዬም የኢትዮጵያን ሥነ ጽሑፍ አስተምሬአለሁ:: የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ ሰፊ ነው:: የዶክትሬት ዲግሪዬንም የተቀበልኩት በግእዝ ሥነ ጽሑፍ ነው::

«መጽሐፈ ብርሃን»ን፣ «መጽሐፈ ሔኖክ»ን፣ «ዜና ዮሴፍ»ን ከግእዝ ምንጭ በመቅዳት ነው ጥናቴን የሠራሁት:: «መጽሐፈ ብርሃን»ን፣ «መጽሐፈ ሔኖክ»ን ሌሎችንም ወደ እንግሊዘኛ ተርጉሜያለሁ:: በተለይ መጽሐፈ ሔኖክ የተከበረ መጽሐፍ ነው:: በእንግሊዝም ሆነ በአሜሪካን ሀገር ጥናቶቼ ለኅትመት በቅተዋል:: በኅትመት ሒደት ላይ ያሉም አሉ:: በሀርቫርድ ዩኒቨርስቲ በፕሪስተን 400 የሚሆኑ የግእዝ መጻሕፍት አሉ:: እነዚህንም በቅደም ተከተል ካታሎግ እንዲኖራቸው አድርጌያለሁ:: በእየሩሳሌምም እንደዚሁ 600 የሚሆኑ የግእዝ መጻሕፍት አሉ:: አቡነ ማቴዎስ ከሚባሉ /በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ገዳማት ሊቀ ጳጳስ የነበሩ/ አባት ጋር በመተባበር ዝርዝሩን አውጥተናል:: ይህ ዓይነቱ የግለሰብ ጥረት ቢኖርም በጋራ ራሳችንን ለማስከበር ጥረት አላደረግንም:: እኔም በግእዝ ትምህርት ላይ ብቀጥልበትም አብዛኛው የእኔ ምርምር በዕብራይስጥ፣ «ከሙት ባሕር ጥቅልሎች» በ«ሰከንድ ቴምፕል» ታሪኮች ላይ ያተኮረ ነው:: እነዚህን በዚህ ወቅት ስለ ሚፈልጓቸው ነው:: የእኛም ቢፈለግ የሠራነው አለ:: በሒደትም እንቀጥልበታለን:: ለምሳሌ ድሮ ወጣት እያለሁ አንድ የጻፍኳት «የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን» (The Church of Ethiopia) የምትል መጽሐፍ ነበረች:: ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ጥልቅ ፍቅርና አክብሮት አለኝ:: ስለዚህ ታሪኳን አጠናለሁ:: በዚያም ፍቅር ነው ስለ ቤተ ክርስቲያኒቱ አጥንቼ መጽሐፍ ያሳተምኩት:: መጽሐፏ ታትማ በወቅቱ እናራምደው ለነበረው የፊደል ሠራዊት ገቢ አስገኝታለች:: በአገራችንም በ1966 ዓ.ም ለተከሰተው ድርቅ ገቢ አስገኝታለች:: አሁን መጽሐፏ ብዙ አዳዲስ ጥናቶች ተካተውባት እንደ ገና ተዘጋጅታለች:: በመጪው ዓመት ለኅትመት ትበቃለች:: እንደ ቀድሞው «የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን» (The Church of Ethiopia) በሚል ርእስ ነው የተዘጋጀችው::

## የግእዝ ሥነ ጽሑፍ ጥናት ወቅታዊ ሁኔታ

## «'የኢትዮጵያስ የት አለ?' የሚል አዲስ ትውልድ እየመጣ ነው::»

በአሁኑ ወቅት የሚያሳዝነው ሁኔታ ቀደም ብዬ እንደ ተናገርኩት የእኔ ትውልድ /በዕድሜ የእሳቸው ጓደኞች የሆኑትን ማለታቸው ነው/ «ሼክስፒር፣ ሞሊዬር» እያሉ የምዕራባውያንን መጻሕፍት እያነበቡ፣ «የኢትዮጵያስ የት አለ?» የሚሉበት ወቅት ነው:: ይህ ደግሞ ግእዙን ባለመማራቸው ነው:: ለምሳሌ:- በቤልጅየም የሚተረጎሙ የግእዝ መጻሕፍት አሉ፤ ብዙ ናቸው:: <Corpus Scriptorum Christianorum Orientalum> የሚባል ተከታታይ እትም <series> አለ:: ከዚህ እትም አንዱ <Scriptorus Ethiopice> ይባላል - የኢትዮጵያ መጻሕፍት - ማለት ነው:: እዚያ ውስጥ በርካታ ገድሎች አሉ:: እኒህን መጻሕፍት ለመግዛት 400 ብር ነው የፈጀብኝ:: በቁጥር ወደ 50 የግእዝ መጻሕፍት ይሆናሉ:: አብዛኞቹ በላቲን፣ በፈረንሳይኛና በጣልያንኛ ነው የተተረጎሙት፤ በእንግሊዘኛ የተተረጎሙት በጣም ጥቂት ናቸው:: ዛሬ የተማረው ኢትዮጵያዊ ጥሩ አድርጎ የሚያውቀው እንግሊዝኛውን ነው:: አንዳንዶቹን እኛ መተርጎም ጀምረናል:: እኔ ለምሳሌ መጽሐፈ ሔኖክን፣ መጽሐፈ ብርሃንን ተረጎምኩኝ:: ጊዜ ቢኖረኝ ሌላም እሠራ ነበር:: ይኼን ሁሉ የምልበት ምክንያት የዛሬ ትውልድ የምዕራብን ትምህርት ተምሮ እርሱን እያጋነነ የቆየ ነው:: «በጣም ደስ የሚያሰኘው ምንድን ነው?» ብትሉኝ:- «ኢትዮጵያ ምንድን ናት?» የሚል አዲስ ትውልድ እየመጣ ነው... በተለይ አሜሪካን አገር <World Wide Union of Ethiopian Students > /ዓለም ዐቀፍ የኢትዮጵያውያን ተማሪዎች ኅብረት/ የሚባል አለ:: እዚያው የተወለዱ ወይም ያደጉ ናቸው:: ስለ አገራቸው ለመማር በጣም ነው የሚጓጉት:: በየሁለት ሳምንቱ ቅዳሜ ቅዳሜ እየተሰበሰቡ የኢትዮጵያን መጻሕፍት ለማንበብ ይፈልጋሉ:: እኔንም እየደወሉ ይጠይቁኛል:: ስለ ኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የጻፍኩትን መጽሐፍ ሰጥቻቸው እያነበቡት ነው:: የእኔ ትውልድ ዋና ዝንባሌ ግን ፖለቲካ ነው:: የፖለቲካ ባክቴሪያ አንጎሉን መርዞት ተበጥብጧል:: ይህ አዲሱ ትውልድ ግን በኢንጂነሪንግ፣ በሕክምና፣ በኮምፒዩተር ሳይንስ ሞያዎች እየተካነ፣ በኢንተርኔት መጻሕፍትን በማንበብና በመመራመር ነው ደስታው የሚፈጸመው:: በዚሁ እንደ ሚቀጥል ተስፋ አለኝ:: እናንተም በእውነት በርቱበት፤ እንግሊዘኛን ጨምሮ በሚያስፈልገው የአገር ቤት ቋንቋ ሁሉ መተርጎሙ ይጠቅማል እንጂ አይከፋም::

## የግእዝ ፊደላትን ስለ ሚቀንሱቱ

## «አንድን ነገር በማያስፈልግና በማይጠቅም ሁኔታ እናሻሽላለን ማለት ማበላሸት ነው::»

እኔ በክብር የምለው «የግእዝ ፊደላት መቀነስ አለባቸው» የሚሉ አስተማሪዎችን አንጎል እንቀይር ነው:: /ረጅም ሳቅ/:: እውነት ነው÷ ሀሌታው «ሀ»፤ ሐመሩ «ሐ»፤ ብዙኀኑ «ኀ» ልዩነት አላቸው:: እኒህ ደግሞ በትግርኛው ቋንቋ ይበልጥ ይለያሉ:: በሌሎችም ቢሆን የሚለዩበት ሁኔታ አለ:: ስለዚህ የቋንቋዎችን ሁሉ ንጉግር ለማዳመጥ እነዚህን ፊደላት መጠበቅ አለብን:: ስለዚህ ፊደላቱን መቀነስና አንዱን ለሁሉ መጠቀም የትርጉም ፍልሰትን ያመጣል:: ለምሳሌ በዕብራይስጡ «አሌፍ»ን እንደ «ኸ» ቢያደርጉት ትርጉሙ ሌላ ነው የሚኾነው:: በአዲስ ዓመት በእሥራኤል አገር ጸሎት ሲደረግ «ሃየዮም»ን በሚገባ የማይችሉ «ኸራስ አለም» ብለው የሚያነቡ ሰዎች አሉ፤ ትርጉሙ ግን «ዛሬ እግዚአብሔር ዓለምን አጠፋት» ማለት ነው:: የቀናው ትርጉሙ ግን «ሃዮም ኸራስ አለም»- ዛሬ እግዚአብሔር ዓለምን ፈጠራት - /ሳቅ/... ስለዚህ ፊደላትን ብንለውጥ የዚህን ያህል ትርጉሙን ይለውጥብናል:: በመሆኑም በአማርኛም የነበረው የግእዝ ፊደል ቢቆይልን ክፉ አይደለም:: እውነት ነው÷ «አ» እና «ዐ»፣ «ሀ»÷ «ሐ» እና «ኀ»፣ «ሠ» እና «ሰ»፤ «ጸ» እና «ፀ» በአማርኛ ንግግር ውስጥ ላይለዩ ይችላሉ:: ግን ምንድን ነው ችግሩ÷ ችግር የለበትም:: እንዲያውም እኒህን አቆይተን መጨመር ያለብን ሌሎች ፊደላት አሉ:: በኦሮምኛ "Dhaaba" /ዳባ/ ስንል በግእዝ ፊደላት ውስጥ አናገኛቸውም:: አናሲሞስ ነሲብ የሚባሉ መጽሐፍ ቅዱስን ወደ ኦሮምኛ ሲተረጉሙ ጨምረውበታል:: በፊደል ገበታችን ውስጥ ደግሞ የአማርኛ የኾኑ ስድስት ፊደላት ያህል ቢኖሩ /ኘ፣ጨ፣ሸ፣ቸ፣ዠ፣ጀ/ እንጂ ፊደሎቻችን ግእዝ ፊደላት ናቸው:: ግእዝ ፊደላት ነው የሚባሉት:: በዚህ መልኩ በኦሮምኛው ቋንቋ ውስጥም ካሉ ድምፆች አንድ ሁለት ፊደላት ሊጨመሩ ይችላሉ፤ በሌሎቹ ቋንቋዎችም ሲነገሩ እንዲሁ:: አልያ ፊደላትን የምንቀንስ ከኾነ ከዚህ በፊት የተጻፉ መጻሕፍትን ማንበብ አይቻልም:: ስለዚህ ሁል ጊዜ አንድን ነገር በማይጠቅምና በማያስፈልግ ሁኔታ እናሻሽላለን ማለት ማበላሸት ነው:: ሌሎች ብዙ ማሻሻል የሚገባንና የምንችላቸው ነገሮች አሉ:: ጉልበታችንን በዚያ ላይ ብናውል ይመረጣል::



www.eotcmk.org

### የግእዝ ቋንቋ ሞቷል ስለሚሉቱ

### «ግእዝ ፈጽሞ ሊሞት አይችልም፤ ማንም ሊገድለውም አይችልም»

«ግእዝ ሞቷል» የሚሉቱ ራሳቸው የሞቱ ሰዎች ይሆናሉ:: /ረጅም ሳቅ/:: እንዲያውም እውነቱን ልንገራችሁ ከአማርኛም ከትግርኛም ከሌሎቹ ሁሉ ቅድም እንደ ነገርኳችሁ በየገዳማቱ በየአድባራቱ በግእዝ ያሉት በሺ የሚቆጠሩ መጻሕፍት ገና ለትውልደ ትውልድ የሚነበቡ ናቸው፤ ግእዝ ፈጽሞ ሊሞት አይችልም:: ይኼ እኮ ነው የጽሕፈት ዋና ነገሩ:: አንድ ነገር ከተጻፈ ከትውልድ ወደ ትውልድ ይተላለፋል:: ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ይዘዋወራል:: እውነት ነው÷ የግእዝ ቋንቋን ብዙ ሰዎች አልተማሩም፣ ግን እነዚህ መጻሕፍት በመኖራቸው ግእዝን ማንም ሊገድለው አይችልም:: ከአማርኛ መቶ ጊዜ እጥፍ ግእዝ ሕይወት አለው፤ ሕያው ነው:: ተጽፎበታል፤ ጽሕፈት ነው ሕይወት የሚሰጠው::

### የኢትዮጵያ ሚልኒየም /2000 ዓ.ም/ ለኢትዮጵያ ዳግም ትንሣኤ

### «መጥፎ ገጽታዎቻችንን ለውጠን የለማች÷ ያደገች አገር ለማምጣት ትንሽ መሥዋዕትነት እንክፈል::»

ኢትዮጵያውያንን በአያሌ ስብሰባዎች ላይ አገኛቸዋለሁ:: ሁለት ምስሎች አነሣና አሳያቸዋለሁ:: አንደኛው የመራባችንን፣ የጦርነታችንን፣ የድህነታችንንና የማይምነታችንን ምስል ነው:: ይህንን አልወደውም ብዬ ፊታቸው ላይ በጫጭቄ እጥለዋለሁ:: ሁለተኛውን ደግሞ እዩልኝ በጥንታዊነቷ፣ በታሪኳ፣ በባሕሏ ለመላው ጥቁር ሕዝብ የነጻነት ምሳሌ የሆነች አገር አለችን:: አሜሪካን አገር በሔድንበት ቦታ ሁሉ አገራችን የረኀብ፣ የበሽታ፣ የጦርነት አገር እንደ ሆነች አድርገው ነው የሚወስዷት:: ባለፈው ሳምንት ወደ ኢትዮጵያ እሔዳለሁ ብዬ ብናገር:- "Oh! Is it safe?" /አያሰጋም ወይ?/ አሉኝ:: ሳቅሁባቸው:: አገራችን ግን ከችግሯ ሁሉ ጋር የሰላም ሀገር ናት:: ይሁንና መልኳ በዓለም ዘንድ የተበላሸ ሆኗል:: ያንን መጥፎ ገጽ ታችንን ለውጠን የለማችና ያደገች አገር ለማምጣት ትንሽ መሥዋዕትነት እንክፈል እላቸዋለሁ::

በዚህ ምክንያት ነው ባለፈው ዓመት መስከረም አንድ ቀን ጥቂቶቻችን ተሰብስበን "International Committee of Solidarity for Ethiopian Renaissance" ብለን አንድ ተቋም የመሠረትነው:: ተቋሙ ለኢትዮጵያ ዳግም ትንሣኤ /ተሐድሶ/ ነው የሚሠራው:: በአሜሪካ፣ አውሮፓና ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ወገኖች ሁሉ በዚህ ኮሚቴ ውስጥ ይሠራሉ:: የኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠር ከፈረንጆቹ ይለያል፤ 2000 ዓ.ም እንኳ ገና አልሞላም:: በፈረንጆቹ ዘንድ ከአራት ዓመት በፊት «ሚልኒየም» ብለው በመላው ዓለም አክብረውታል:: ይህ ደግሞ የአውሮፓውያኑ ኾኖ ሳለ ሙስሊሞቹ፣ ዐረቦቹ፣ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ሳይቀር አክብሮታል:: እኛም ኢትዮጵውያን የየትኛውም እምነት ተከታይ እንሁን የራሳችንን ሚልኒየም ማክበር አለብን:: ስለዚህ «የኢትዮጵያ ሚልኒየም» ብለን ኮሚቴ አቁመናል:: መንግሥት ከእኛ ጋር እንዲተባበር አደራ ብለናል:: እንግዲህ ይህ የዘመን አቆጣጠር ከቤተ ክርስቲያን ጋር የተገናኘ ነው:: ብቻ ያሰብነውን ሁሉ ለማድረግ ጊዜው አጥሯል:: በአውሮፓም፣ በአፍሪካም በሌሎችም ክፍላተ ዓለማት ያሉት ያንን ዓመት "Ethiopian Year" ብለው እንዲሠይሙት እንጠይቃቸዋለን:: ያ ከመድረሱ በፊት በአገራችን በሰላሟ፣ በልማቷና በዕድገቷ ላይ የምንሠራቸው ሥራዎች አሉን:: ይህንን በልዩ ልዩ መንገድ ከማንጸባርቅ ጀምሮ በቤተ ክርስቲያን አንድ ነገር እንዲደረግ ያስፈልጋል:: በመንግሥት በኩል የታሰበ ነገር ያለ ይመስለኛል፤ ይህ ነገር ለኢትዮጵያ ሀብትን ይጨምራል፤ ቱሪዝምን ይጨምራል:: ኢትዮጵያ ምን እንደ ኾነች ለማስረዳትም ያግዛል:: እንግዲህ "Ethiopian Mellinium" የዳግም ትንሣኤ ጥረታችንን ወደ ፊት ለመግፋት ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል ብለን እናስባለን:: እናንተም በፈቃደኝነት በዚህ ጉዳይ ላይ ልትረዱን ትችላላችሁ:: በእኛ በኩል አንድ ሰው ቀጥረናል፤ ኢትዮጵያውያን ባሉበት ሁሉ ተንቀሳ ቅሰን እንመዘግባለን:: በእውነቱ የእኛ የመተባበርና የፈቃደኝነት ማጣት እንጂ ዐቅም አያንሰንም:: በትብብራችን ግን የአገራችንን ዳግም ትንሣኤ ለማየት እንችላለን::

*ይቀጥላል::*

# ትንሣኤ ሙታን ...

*/ከገጽ ፳፱ የዞረ/*

የውኃ ጠብታ የሚሰጠው ግን አይገኝም፤ እንግዲህ ይህን ከመሳሰለውም ቅጣት ለመዳን በዚህ ዓለም እያሉ መልካም ሥራ በመሥራት ጸንቶ መገኘት ይገባል::

## ሕይወት ዘለዓለም

በዳግም ምጽአት ጻድቃን ወደ ዘለዓለም ሕይወት ይሔዳሉ:: ይህም ዐይን ያላየው÷ ጆሮም ያልሰማው÷ በሰውም ልብ ያልታሰበ እግዚአብሔር ለሚወዱትና ለሚወዳቸው ያዘጋጀው÷ ዓለም ሳይፈጠር ለቅዱሳኑ የሰጠው ነው:: ጻድቃን በወዲያኛው ዓለም መከራ የለባቸውም:: "ለሁሉም እንደ ሥራው መጠን እስኪከፍለው ድረስ የጻድቃን ነፍሳት ከዚያ /ገነት/ ይኖራሉ፤ በዚያም ይጠበቃሉ::" እንዲል ቅዳሴ ዘሠለስቱ ምእት:: "ንዜንወክሙ ፍሥሓ ዘይከውነክሙ" እንዲል የዚህ ዓለም መከራ ችግር ውጣ ውረድ አልፎ በመንግሥተ ሰማይ ተድላና ደስታ ይሆናል:: በዚያ መራብ÷ መጠማት÷ ፍርሃት÷ ጨለማ÷ ሥቃይ የለም:: ክቡር ዳዊት "ጥቀ ፍቁር አብያቲከ እግዚኦ እግዚአ ኃያላን፤ የሠራዊት አምላክ እግዚአብሔር ሆይ÷ ማደሪያዎችህ እንደምን የተወደዱ ናቸው::» መዝ.83÷1:: በማለት መንግሥተ ሰማያት የምትወደድ አብዝተው ሊሿትና ሊጋደሉላት የምትገባ መካነ ቅዱሳን መሆኗን ተናገረ:: ሰው ያላየው÷ ያልሰማውና እንዲህ ነው ብሎ ሊናገረው የማይቻለው ደስታ በዚያ አለ:: ቅዱስ ጳውሎስ እስከ ሦስተኛው ሰማይ ድረስ ተነጠቀ፤ በዚያም ያየውን «ሊነገር የማይችል» ብሎ ገልጾታል:: /1ቆሮ.12÷3/::

የመንግሥተ ሰማይ መዓዛና ውበት እንዲህ ነው ተብሎ አይነገርም:: በዚያ አግኝቶ ማጣት የለም፤ ጠብ÷ ክርክር÷ ቅንዓት የለም፤ ለነፍስ ጭንቀት የለባትም፤ ሌሊትና ቀን÷ በጋና ክረምት÷ ሐሩርና ቁር የሉም:: ሁልጊዜ ያማረ ታይቶ የማይሰለች የማይጠገብ ነው እንጂ:: "ለዓለመ ዓለም ይሴብሑከ፤" የተባሉ መዘምራን፣ ማኅሌትና ቅዱሳን መላእክት በአንድነት (በምታስደንቅ ኅብረት) «ቅዱስ÷ ቅዱስ÷ ቅዱስ» እያሉ በማያርፍ ቃል ሲያመሰግኑ ማየትና መስማት እጅግ ውብ ያማረም ነው:: አባ ዮሳማስ ማርያም ግብፃዊትን "በበረሃ በምድረ በዳ ይህን ያህል ረዥም ዓመታትን እንደምን አሳለፍሽ" ቢላት "በመንግሥተ ሰማይ ተስፋ" በማለት መለሰችለት:: እንግዲህ እኛም ሕይወት ዘለዓለምን ለመውረስ መንግሥተ ሰማይን ተስፋ በማድረግ ልንተጋ ይገባናል:: እግዚአብሔር በቸርነቱ የሚሰጠን እያንዳንዷ ዕለት የጽድቅ ሥራ ሠርተን፣ ርስት መንግሥተ ሰማያትን ለመውረስ በመሆኑ እምነትን ከበጎ ምግባር አዋሕደን በመያዝ የቸርነቱን ሥራ እንዲሠራልን በመለመን መመላለስ ይኖርብናል:: ልንመለከት የሚገባንም ያሸነፉትን እንጂ በልዩ ልዩ ምክንያት ተሰበው ከመንገድ የቀሩትን መሆን የለበትም:: ዕለተ ሞትን በማሰብ ምሬረ ገሃነመ እሳትን (የገሃነመ እሳትን መከራና ሥቃይ) በማወቅና በመልካም አነዋወር በመኖር የተሰጠችንን ጊዜ በአግባቡ ለመጠቀም እንድን ችል የእግዚአብሔር ቸርነት÷ የድንግል ማርያም የእናትነት ፍቅርና ርኅራኄ÷ የቅዱሳን ሁሉ ተራዳኢነት አይለየን:: አሜን::





www.eotcmk.org

*ዲ.ደሳለኝ ቀለብ*

*ውድ አንባብያን፣ ዲ/ን ደሳለኝ ባለፈው ትምህርቱ ተውሳከ ግሥ ማለት ምን ማለት እንደሆነ፣ዓይነቶቹንና አገልግሎቶቹን በምሳሌዎች እያስደገፈ አስነብቦናል:: በዚህኛው ደግሞ ካቆመበት ጀምሮ ትምህርቱን ካጠናቀቀ በኋላ መልመጀዎችን ያቀርብልናል:: እንደተለመደው ጥያቄዎቹን በመመለስ ተሳተፉ::*

*ሐ. ምክንያትን የሚገልፅ* ***/Adverb of reasons/-*** *አስረጅ:- ይህ ደግሞ "ና" የሚለውን ፊደል የሚወልድ ነገሩ ወይም ሁኔታው ለምን እንደ ተፈጸመ የሚያመለክት የተውሳከ ግስ ዓይነት ነው::*

እስመ = ና /Since, Because, For/ ፣ ስለ ...
አምጣነ = ና /Since, Because, For/
አኮኑ = ና /Since, Because, For/

ሖረ - ሔደ /ሔዷል / - /Went – Pas tense/
አነ - እኔ I / እስመ ሖርኩ - ሔድኩና /ሔጃለሁና – Because I went
አንተ - አንተ You እስመ ሖርከ - ሔደሃልና – Because you went
አንቲ - አንቺ You እስመ ሖርኪ - ሔደሻልና – Because you went
አንትሙ /እናንተ/ You እስመ ሖርክሙ - ሔዳችኋልና –Because you went
አንትን እናንተ / You ለሴቶች እስመ ሖርክን - ሔደችኋልና – Because you went
ንሕነ /እኛ / We እስመ ሖርነ - ሔደናልና – Because we went
ውእቱ /እሱ/ Heእስመ ሖረ - ሔዷልና – Because he went
ይእቲ /እሷ/She እስመ ሖረት - ሔዳለችና –Because she went
ወእቶሙ /እነሱ/ They እስመ ሖሩ - ሔደዋልና – Because They went
ወእቶን /እነሱ/ They እስመ ሖራ - ሔደዋልና – Because They went

ተወልደ - ተወለደ /ተወልዷል/ He was born
አምጣነ ተወለድኩ - ተወልጃለሁና
" ተወለድከ - ተወልደሃልና
" ተወለድኪ - ተወልደሻልና
" ተወለድክሙ - ተወልዳችኋልና
" ተወለድክን - ተወልዳችኋልና
" ተወለድነ - ተወልደናልና
" ተወልደ - ተወልዷልና
" ተወልደት - ተወልዳለችና
አምጣነ ተወልዱ - ተወልደዋልና

ተጠምቀ - ተጠምቋል፣ ተጠመቀ / Was baptized/
አኮኑ ተጠመቁ - ተጠምቄአለሁና - Because / since / was baptized
" ተጠመቀ - ተጠምቀሀልና - Because / since/ you were baptized
" ተጠመቂ - ተጠምቀሻልና - Because / since / you were baptized
" ተጠመቅክሙ - ተጠምቃችኋል- Because / since / you were baptized
" ተጠመክን -ተጠምቃችኋልና- Because / since / you were baptized
" ተጠመቅነ -ተጠምቀናልና- Because /since/ we were baptized
" ተጠምቀ - ተጠምቋልና- Because / since he were baptized
" ተጠምቀት- ተጠምቃለችና- Because / since she were baptized
" ተጠምቁ -ተጠምቀዋልና- Because / since/ they were baptized
" ተጠምቃ-ተጠምቀዋልና-/ለሴቶች/-Because / since/ they were baptized

አነ ተጠመቁ፣እንጂ ተጠመቅኩ፣ አንተ ተጠመቀ እንጂ፣ ተጠመቅከ አንቲ፣ ተጠመቂ እንጂ፣ ተጠመቅኪ አይልም፣ የግሶች የመጨረሻ ፊደል ገ፣ ቀ፣ ከ፣ ነ፣ ከሆነ ለሦስቱ መራሕያን አነ፣ አንተ፣ አንቲ ከዚያም ላይ ማጥበቅ እንጂ ተጨማሪ ፊደል የለም የግሱ የመጨረሻ ፊደል ነ ከሆነ ንሕነ ለሚለው መራሒም እንዲሁ፣ ምሳሌ ኮነ= ሆነ= ኮነ= ሆነ ይህ ሁሉ ግን ለቀዳማይ /ለኃላፊ/ አንቀጽ ነው:: አኮኑ በግስ ይወሰናል አኮኑ አልቦ አይባልም አኮ ለብቻው = አይደለም የሚል ትርጉም አለው

**መ. ሁኔታን የሚገልጽ /Adverb of condition**
እመ /ለእመ/ - ምንም እንኳን /Although/
ለእመ /እመ/... ኢ - ካለ ... /If... not/
ባሕቱ፣ አላ= ነገር ግን፣ ይሁን እንጂ /Neverthelese, But, However

<u>ምሳሌ</u>

ለእመ መጽአ= ቢመጣም እንኳ /Although he came/
ለእመ ኢሖረ - ካልሔደ- /If he did not go/
ለእመ ቅዱስ አንተ - ቅዱስ ብትሆን
አላ መሐረነ - ማረን እንጂ - But forgive us

**ሠ. ውጤትን አመልካች /Adverb of result/**
በእንተዝ - ስለዚህ /Therefore, Hence, As a result/
በእንተ ዝንቱ -/Therefore, Hence, As a result/
በእንተ ውእቱ -Therefore, so that Hence, As a result/
ወበ እንተዝ - ስለዚህ /ም/

<u>ምሳሌ</u>

- አነ ሖርኩ ኀበ ቤተ እግዚአብሔር፣ በእንተዝ ረከብኩ በረከተ ቅዱሳን= እኔ ወደ ቤተ እግዚአብሔር ሔድኩ፣ ስለዚህም የቅዱሳንን በረከት አገኘሁ::
- ዮም ተወልደ መድኃኔዓለም በእንተ ዝንቱ ተፈሥሐ ኵሉ ዓለም ዛሬ የዓለም መድኃኒት ተወለደ፣
ስለዚህ ዓለም ሁሉ ደስ አለው::
- በእንተ ውእቱ ብእሲ ተሰቅለ ዐማኑኤል /Emanuel was crucified be cause of that man/.
- አ ማርያም በእንተዝ ናፈቅረኪ እስመ ወለድኪ ለነ መብልዐ ጽድቅ፣ ማርያም ሆይ÷ስለዚህ እንወድሻለን:: የእውነት መብልን ወልደሻልና::
በእንተ ዛቲ - ስለዚህች /Because of this/
በእንተ ይእቲ - ስለ እርሷ /Because of that /
በእንተ ኵሉ - ስለ ሁሉ /For all /

**ረ. ቦታን ገላጭ /Adverb of Place/**
ይህ ተውሳከ ግሥ ነገሩ የት፣ ወዴት እንደ ተፈጸመ የሚያመለክት የተውሳከ ግሥ ዓይነት ነው::
ህየ /ከሃ/ - እዚያ /there/
ዝየ - እዚህ /here/
ውእቱ ነበረ ህየ - እሱ እዚህ ተቀመጠ /He sat there/
አነ ነበርኩ ዝየ - እኔ እዚህ ተቀመጥኩ /I sat here/
ንሕነ ሖርነ ኀበ ገዳመ ሲና :: ወበህየ ረከብነ ሰላመ ቅዱሳን:: እኛ ወደ ሲና በረሃ /ገዳም/ ሔድን፣ በዚያም የቅዱሳንን ሰላም አገኘን::
- ለእመ ሀሎከ ዝየ እምኢሞተ አልዓዛር እኁየ፣ ከዚህስ ኖረህ ቢሆን ወንድሜ አልዓዛር ባልሞተ ነበር
here and there - ከዚህም ከዚያም /ከየአቅጣጫው/
ላዕሉ ወታህቱ - ላይና ታቹ - up and down

**የጊዜ፣ የሁኔታ፣ የከፍታ ተውሳከ ግሦች አጠቃላይ ለውጥ በአጠቃቀም/ ሒደት በግእዝ**

በእነዚህ የተውሳከ ግሥ ዓይነቶች አጠቃላይ ሒደት ስንል በግእዝ ታላቅ ትኩረት የሚሰጠውና የአንድን ቃል የመጨረሻ ፊደል ወደ ግእዝ በመለወጥ ከቃሉ፣ ወደ፣ ከ፣ በ... የሚሉትን ፊደላት ለትርጉም በሚመች መልኩ ለማውጣት የሚያስችል ነው:: ምሳሌ:-
ቅድመ - ፊት - ቅድመ - በፊት፣ ወደ ፊት፣ በፊት
ግብት - ድንገት - ግብተ - በድንገት፣
ምድር - ምድር - ምድረ - በምድር፣ ከምድር ወደ ምድር፣ ሰማይ - ሰማይ - ሰማየ በሰማይ- ከሰማይ ወደ ሰማይ
ሀገር-ሀገር - ሀገረ - በሀገር - ከሀገር፣ ወደ ሀገር
ጸሎት - ጸሎት - ጸሎተ - በጸሎት፣ ወደ ጸሎት
ድኩም - ደካማ - ድኩመ - በደከመ ሁኔታ
ጌሰም - ነገ - ጌሰመ - በነገው፣ ወደ ነገ
ፍጡን - ፈጣን - ፍጡነ - በፍጥነት
ገዳም - ገዳም - ገዳመ - ወደ ገዳም፣ በገዳም፣
ርኁቅ - ሩቅ - ርኁቀ - በራቀ /በሩቅ/
ወትረ - ዘወትር ወትረ - ዘወትር ፣ በዘወትር

<u>ምሳሌ</u> :- አንዱን ቃል ለመለወጥ ስንፈልግ

1. አነ ወረድኩ ገዳመ - እኔ ወደ ገዳም ሔድኩ
- I went to a monastery

ወደ የሚለው ቃል የወጣው ገዳመ ከሚለው ቃል ነው::
ወሞተ ዝንቱ ግብተ - He died accidentally – በድንገት ሞተ
አነ መጻእኩ ፍጡነ - እኔ በፍጥነት መጣሁ
- I came quickly

ምሳሌ:- ሁለት ቃላትን ለመለወጥ ስንፈልግ
አነ ወረድኩ ገዳመ ርኁቀ - እኔ ወደ ሩቅ ገዳም ሔድኩ
- I went to the far monastery
- አንትሙ ጸለይክሙ መዓልተ ወሌሊተ
እናንተ ቀንም ሌሊትም /በቀንም በሌሊትም /ጸለያችሁ/

<u>ሲጠቃለል</u>

| ቅጽል /Adjective/ | ተውሳከ ግሥ /Adverb/ |
|---|---|
| ፍጡን-ፈጣን /Quick, fast/ | ፍጡነ-በፍጥነት /Quicly, Fast/ |
| ግብት - ድንገት /Accident/ | ግብተ - በድንገት /Accidentally/ |
| ፍጹም - ፍጹም /Perfect/ | ፍጹመ - በፍጹም /Perfectly/ |

**<u>የተውሳከ ዝርዝር</u>**

በቅድም /ቅድም/ - ፊት በፊት ቅድመ - በፊት /began /
/በ/ ቅድሜየ - በፊቴ In front of me Before me
ቅድሜከ - በፊትህ
ቅድሜኪ - በፊትሽ
ቅደሜክሙ - በፊታችሁ

/ወደ ገጽ ፴ ዞሯል/



www.eotcmk.org

# የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሰሜንና ደቡብ አሜሪካ

## *መቋቋም *መስፋፋት *ወቅታዊ ችግር

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ዓለም ዐቀፋዊት ናት ሲባል፡ በሐዋርያዊ እግሮቿ ተጉዛ ያልደረሰችበት የዓለም ክፍል የለም ለማለት ነው:: ቤተ ክርስቲያ ቀደም ሲል ደርሳ በዚያ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንንም ሆነ ሌሎች ምእመናን እያገለገለችባቸው ካሉ የዓለም ክፍሎች አንዱ ሰሜን አሜሪካ ነው::

የታሪክ መዛግበት እንደ ሚያስረዱት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሰሜን አሜሪካ እንድትቋቋም ምክንያት የሆነው የፋሺስት ኢጣሊያ ወረራ ነው:: እንደ ሚታወቀው ሀገራችን ውቅያኖስ አቋርጦ በመጣ ወራሪ ኃይል በግፍ በተወረረችበት ጊዜ ኢትዮጵያውያን የግል ጥቅሙን ለማስጠበቅ በመጣ ወራሪ አንገዛም በማለት በሚችሉት ሁሉ ሀገራቸውን ነጻ ለማውጣት ስፊ ትግል አድርገዋል:: ሀብት ንብረታቸውን ትተው ጫካ በመግባት በአጥንታቸውና በደማቸው አገራቸውን ሊታደጉ በአርበኘነት የተሰማሩ ቆራጥ ኢትዮጵያውያን የመኖራቸውን ያህል በቻሉት መንገድ ከሀገር ወጥተው የኢትዮጵያን በግፍ መወረር ለዓለም የሚያሰሙ ንቁ ኢትዮጵያውያን ነበሩ::

አገራችን የተፈጸመባትን በደል ለዓለም በተለይ በሰሜንና በደቡብ አሜሪካ በማሰማት የሚታወቁት ዶክተር መልአኩ በያን የተባሉት ኢትዮጵያዊ ነበሩ:: እኒህ ሰው ኢትዮጵያ በፋሺስት ኢጣሊያ በተወረረችበት ዘመን በ1929 ዓ.ም የኢትዮጵያ ዓለም ዐቀፍ ፌደሬሽን /Ethiopian World Federation/ የተባለ ድርጅት አቋቋሙ:: የዚህ ድርጅት ተቀዳሚ ዓላማ በምዕራቡ ክፍለ ዓለም ላሉት ጥቁሮች ኢትዮጵያን ጨምሮ የአፍሪካን ሕዝብ ታሪክ ለማስተማርና የጥቁሮችን አንድነትና ኅብረት ለማጠናከር የነበረ ቢሆንም ይህንን ዓቢይ ዓላማውን ለማስፈጸም በወቅቱ የኢትዮጵያን በግፍ መወረር ለዓለም ያሰማ ነበር::

በሀገሪቱ ታሪክ እንደ ሚታወቀው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ለሚታለም ማንኛውም ለውጥ በሐዋርያነት ቀዳሚ ሥፍራ ነበራት:: በዚህ የተነሣ በአሜሪካ የተቋቋመው ድርጅት የያዘውን ዓላማ ከግብ ለማድረስ የቤተ ክርስቲያኗ ሚና ከባድ ሊሆን እንደ ሚችል በመገንዘቡ፡ በአካባቢው ተቋቁማ አገልግሎቷን እንድትጀምር በወቅቱ ቤተ ክርስቲያኗን ሲመሩ የነበሩትን አባቶች በደብዳቤ ጠየቀ::

ግብዣውን የሰሙት አባቶችም በግልም ሆነ በጉባኤ ጉዳዩን ሲያብላሉት ከቆዩ በኋላ እ.ኤ.አ በ1952 /1944 ዓ.ም/ ቤተ ክርስቲያን በአካባቢው የምትቋቋምበትን ሁኔታ አጥንተው ይመለሱ ዘንድ አባ ገብረ ኢየሱስ መሸሻን /በኋላ አቡነ አትናቴዎስ ተብለው በምዕራቡ ክፍለ ዓለም የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ጳጳስ የሆኑ/ እና አቶ አበራ ጀምበሬን መልዕክተኞች አድርገው ላኩ:: ልዑካኑም ወደ ዚያው ሔደው ጋባዡን ድርጅትና በአካባቢው የሚኖሩ ምእመናንን ካነጋገሩ . በኋላ ከሕዝቡ ፍላጎት አንጻር የቤተ ክርስቲያኗን መቋቋም ጉዳይ ጊዜ የማይሰጠው መሆኑን በማመን ከማዕከላዊ የቤተ ክርስቲያኗ አስተዳደር በመነጋገር የመጀመሪያውን ቤተ ክርስቲያን በትሪኒዳድና ቶቤጎ አቋቁመው ወደ ኢትዮጵያ ተመለሱ::

የልዑኩ ሪፖርት ከተሰማ በኋላ ይዋል ይደር ሳይባል የሕዝቡ ጥያቄ ተቀባይነት እንዳገኘ በመግለጽ ሕዝቡን አጽናንቶና መክሮ የሚመለስ ሌላ አንድ ልዑክ ወደ ቦታው እንዲሔድ ተወሰነ:: በዚህም መሠረት በወቅቱ የሐረር ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስና የፓትርያርኩ የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ረዳት በነበሩት ብፁዕ አቡነ ቴዎፍሎስ /በኋላ 2ኛው የኢትዮጵያ ፓትርያርክ/ እ.ኤ.አ በ1954 /1946 ዓ.ም/ የሚመራ ልዑክ ወደ አሜሪካ ተጓዘ::

ልዑኩም የቤተ ክርስቲያኗ ቅዱስ ሲኖዶስ በሰጠው አደራና ተልዕኮ መሠረት አሜሪካ ከገባበት ጊዜ ጀምሮ ከቦታ ቦታ በመዘዋወር የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ተከታይ መሆን ለሚፈልጉ ምእመናን ቤተ ክርስቲያኗ ጥያቄያቸውን ሙሉ በሙሉ እንደ ተቀበለች፣ ዕቅዱንም በሥራ ለመተርጐም በትጋት እንደ ምትንቀሳቀስ፣ በዚህም ሌሎች አብያተ ክርስቲያናትን ለማቋቋም ራሳቸው ብፁዕ አቡነ ቴዎፍሎስ ተመልሰው እንደ ሚመጡ አስረድተውና ቃል ገብተው ወደ አገራቸው ተመለሱ::

ይህንን የብፁዕነታቸውን የተሥፋ ቃል የሰነቁት ምእመናኑም ለዘመናት ሲመኙት የነበረው ነገር እውን ሊሆን ጊዜው መድረሱን በማየት እየተደሰቱ፡ ዐቅሙ ያላቸው ደግሞ ቤተ ክርስቲያን የሚሆናቸውን ሕንፃ በመግዛት ዝግጅት ሲያደርጉ ቆዩ:: በዚህ ረገድ ኒው ዮርክ አካባቢ የሚገኙ ምእመናን ብሩክሊን ኒውዮርክ ውስጥ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ስም ሕንፃ ገዝተው እንደ ነበረና ታክስ ስላልተከፈለበት ከጥቂት ጊዜ በኋላ የኒውዮርክ ማዘጋጃ ቤት እንደ ወረሰባቸው ይነገራል::

ብፁዕ አቡነ ቴዎፍሎስ በገቡት ቃል መሠረት እ.ኤ.አ. ኦክቶበር 25, ቀን 1959 /ጥቅምት 15 ቀን 1951 ዓ.ም/ወደ አሜሪካ ተመልሰው በኒው ዮርክ ከተማ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ስም የተሠየመውን ድርጅት ባርከውና መርቀው ከፈቱ::

ይህ በቤተ ክርስቲያን ዙሪያ የአሜሪካውያን ምእመናን ስብስብ እያደር እየሰፋና እየሞቀ ሔደ:: በመሆኑም እ.ኤ.አ. December 25,1969 /ታኅሣሥ 15 ቀን 1961 ዓ.ም/ ሃምሳ አምስት ሺ ዶላር ከባንክ ተበድረው ብሮንክስ ኒው ዮርክ አንድ ሌላ አሮጌ ሕንፃ በቤተ ክርስቲያ ስም ገዙ:: ይሁን እንጂ ወቅቱ በአሜሪካ ጥቁሮች የነበረባቸው ጫናና ሥራ አጥነትና ሙሉ በሙሉ ያልተገፈፈበት ስለነበር ጥቁሮቹ ከባንክ የተበደሩትን ገንዘብ መክፈል አልቻሉም:: በዚህ የተነሣ ቀደም ሲል የተጠቀሰው ሕንፃ ዕጣ ፈንታ በዚህም ሊደርስ ተቃረበ::

ምእመናኑ እንሰባሰብበታለንና እንጸልይበታለን ብለው በብድር የገዙት ሕንፃ ሊወረስባቸው በመሆኑ በጥልቅ ኃዘን ላይ ሆነው ሳለ እ.ኤ.አ. በጥቅምት ወር 1963 በሃያ አምስተኛው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት በዓል ላይ ለመገኘት ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ኒውዮርክ ተገኙ:: በዚህ የተደሰቱት ምእመናኑም ንጉሡ ዘንድ በመቅረብ ችግራቸውን በመግለጽ ርዳታ እንዲያደርጉላቸው ጠየቁ:: ንጉሠ ነገሥቱም የምእመናኑን ትጋት አድንቀው የሚቻለው ሁሉ እንደ ሚደረግላቸው ቃል ገብተውላቸው ወደ አገራቸው ተመለሱ::

ንጉሡ በጉባኤው ተሣትፈው ወደ ኢትዮጵያ እንደ ተመለሱም በብድር መልክ 32,000 ዶላር እንዲላክላቸው ሲሉ ለሚኒስትሮቻቸው ትእዛዝ አስተላለፉ:: በትእዛዙም መሠረት ኢትዮጵያ ኮንስትራክሽንና ቢዝነስ ባንክ ገንዘቡ ወጭ ሆኖ ተላከ:: ወደ ኒውዮርክ የተላከው ገንዘብ በአምስት ዓመት የሚከፈል ሆኖ ገንዘቡ ሙሉ በሙሉ እስከሚመለስ ድረስ የሚወልደውን ገንዘብ ንጉሡ እንደ ሚከፍሉ ስምምነት ላይ ተደርሶ ለምእመናኑም በተያዥነት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጠቅላይ ጽ/ቤት በዋስነት ፈርሞ ነበር:: በጠቅላይ ቤተ ክህነቱ በኩል የፈረሙት በዚያን ጊዜ የቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ የነበሩት ንቡረ ዕድ ኤርምያስ ከበደ ነበሩ::

በዚህ መሠረት ገንዘቡን ያገኙት በኒውዮርክ የሚገኙ ምእመናን ሕንፃውን ገዝተው የቅድስት ቤተ ክርስቲያንን አገልግሎት ማግኘት ጀመሩ:: ኒውዮርክ ላይ ያሉ ምእመናን ባገኙት የገንዘብ ብድር ገዝተው በመድኃኔ ዓለም ስም በሠየሙት ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን እየተሰባሰቡ ሲማማሩና ቤተ ክርስቲያናቸውን የበለጠ በማወቅ ላይ ሳሉ እ.ኤ.አ. በ1966 ዓ.ም ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ጃማይካን ጐበኙ:: በዚህ የተነሣ በሰሜኑ የአሜሪካ ክፍል እንደ ሚኖሩት ምእመናን ሁሉ በዚያ የሚገኙ ጥቁሮችም ከኢትዮጵያና ከኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ጋር ለመገናኘት ፍላጐት አደረባቸው:: ይህንንም ለንጉሡ ገለጡ::

ንጉሠ ነገሥቱ በኒው ዮርክ



www.eotcmk.org

እንዳደረጉት ሁሉ በዚያ የሚኖሩትን ጥቂቶች ሐሳብና ፍላጐት ተቀብለው ከመከሩና ካጽናኑ በኋላ በቅርብ ሆኖ የሚያስተምራቸውና የሚያገለግላቸው አባት እንደሚፈኩላቸው ቃል ገብተው ወደ ኢትዮጵያ ተመለሱ:: ይህ የንጉሡ ቃል ምንም እንኳን በፍጥነት ባይፈጸምም በ1973 ዓ.ም አካባቢ ቀደም ሲል ቤተ ክርስቲያንን በመወከል ከአቶ አበራ ጀምበሬ ጋር ወደ ኒውዮርክ ሔደው የነበሩት አባ ገ/ኢየሱስ መሸሻ /በኋላ ብፁዕ አቡነ አትናቴዎስ/ ከአባ ላእከ ማርያም ማንደፍሮ /በኋላ አቡነ ይስሐቅ ተብለው በብፁዕ አቡነ አትናቴዎስ ቦታ የተተኩት/ ጋር በመሆን ተላኩ:: እነዚህ አባቶች ወደ አካባቢው ከሔዱበት ጊዜ ጀምሮ ሰፋ ያለ አገልግሎት አበርክተዋል::

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከላይ በተገለጠው ዓይነት በሰሜንና ደቡብ አሜሪካ እንቅስቃሴዋን እንደ ጀመረች የዐፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት በደርግ ተተካ::

ምንም እንኳን የኮሙኒዝምን ርዕዮተ ዓለም በማንገብ ወደ ሥልጣን የወጣው መንግሥት በሀገር ቤት ላለችዋ ቤተ ክርስቲያን ሐዋርያዊ እንቅስቃሴ እንቅፋት ቢሆንም ለውጭው በተለይም በሰሜንና ደቡብ አሜሪካ ለነበራት እንቅስቃሴ ከፍተኛ አስተዋጽዖ አበርክቷል:: ምክንያቱም የመንግሥቱን ለውጥ ተከትሎ በርካታ ኢትዮጵያውያን በስደት ከኢትዮጵያ ወጥተው ወደ ተለያዩ የአሜሪካን ግዛቶች ገብተዋልና::

እንኳንስ ባልጠበቁት ሁናቴ ሲሰደዱ በሀገር ሰላም እንኳን አብዝተው መጸለይና መጾም የሚወዱት ኢትዮጵያውያን በስደት አገራቸው እየተሰባሰቡ ይጸልዩና እርስ በእርሳቸው ይጽናኑ ጀመር:: ስብሰባቸው እየዋለ እያደረ ሲሔድ ለምን ቤተ ክርስቲያን አንመሠርትም በሚል በያሉበት ግዛት በቅዱሳን ስም አብያተ ክርስቲያንን ይመሠርቱ ጀመር:: በመሠረቷቸው አብያተ ክርስቲያን አማካይነት አልፎ አልፎ ይታዩ ከነበሩ ፖለቲካዊ ልዩነቶች በስተቀር ያለምንም የዘረና የጐሳ ልዩነት ከአንዱ ቤተ ክርስቲያን ወደ ሌላው በመዘዋወር ኢትዮጵያዊ መልካቸውን ጠብቀው ቃለ እግዚአብሔርን እየተማማሩ መኖር ጀመሩ::

በ1960ዎቹ መጨረሻና በ1970ዎቹ በሰሜን አሜሪካ በነበሩ አብያተ ክርስቲያን ምእመናን መካከል የፖለቲካ ልዩነት ነበር ሲባል ያን ያህል የተጋነነና ምእመናኑን የሚያለያይ አልነበረም:: በጣም ያነሡ ልዩነቱን ሁሉም በየራሱ ይዞ በአካባቢው ለቤተ ክርስቲያኗ አን ድነትና መጠናከር ጥረት ያደርግ ነበር:: በተለይ በሰርግ፣ በክርስትና፣ በጸሎተ ፍትሐት፣ በዐበይት በዓላት ሁሉ እየተገናኘ አምልኮቱን ይፈጽም፣ የናፈቀውን ባሕሉንና ቋንቋውን ይጣገብ ነበር::

ይቆየን::

## ደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤል

/ከገጽ ፴፫ የዞረ/

ድንኳን አርፎ መስከረም 1 ቀን 1948 ዓ.ም ቅዳሴ ቤቱ ተከብሯል::

ረዥም ዕድሜን ባስቆጠረውና ጥንታዊው የእንጦጦ ደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤል ቤተ ክርስቲያን መስከረም 1 ቀን የቅዱስ ራጉኤል በዓለ ሢመት /በፀሐይና በጨረቃ ላይ የተሾመበት - መጋቤ ፀሐይ ወወርኃ/፣ እንዲሁም ግንቦት 1 ቀን እመቤታችን በተወለደችበት ዕለት በአድባረ ሊባኖስ ተገኝቶ ብርሃናት እንዲያጅቡ ያደረገበት መታሰቢያ እንዲሁም ታኅሣሥ 1 ቀን የቅዱስ ኤልያስ በዓል በታላቅ ድምቀት ሲከበር የኖረ ቢሆንም፣ ትኩረት ተነፍጐት ማዕጠንት እንኳን አጥቶ ቆይቷል:: በአሁኑ ሰዓት ስብሐተ እግዚአብሔር እንዳይቋረጥና የቀድሞው ክብሩ ተጠብቆ እንዲቆይ በደብሩ ከፍተኛ ጥረት እየተደረገ ሲሆን በ1896 ዓ.ም በጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ ተበርክቶ የነበረው ድርሳነ ራጉኤል ተሰርቆ ወደ ውጭ ሀገር ከሄደ በኋላ በ22 ዓመቱ በእግዚአብሔር ፈቃድ ወደ ነበረበት ተመ ልሷል::

የእንጦጦ ደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤል ቤተ ክርስቲያን ከጠቅላይ ቤተ ክህነት በ13.8 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ሲገኝ ጥቅጥቅ ያለውን ደን አቋርጦ ጠመዝማዛውን ዳገታማ አስፋልት አልፎ እንጦጦ ሲደርሱ ከፍተኛ የመንፈስ ርካታ የሚያስገኝ ከመሆኑም በተጨማሪ ከቦታው የሚገኘውን በረከት ተካፋይ ያደርጋል::

በአሁኑ ወቅት በእንጦጦ ደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤል ቤተ ክርስቲያን ሙዚየም ለመገንባት የልማት ኮሚቴ ተዋቅሮ እንቅስቃሴ እየተደረገ ሲሆን፣ ቅርሱ ተጠብቆ እንዲኖር ሕዝበ ክርስቲያኑ በሐሳብም ሆነ በማናቸውም ነገር ድጋፍ ማድረግ ይጠበቅበታል:: ድጋፍ ማድረግ ለሚፈልጉም በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አራት ኪሎ ቅር ንጫፍ በደብሩ ስም በተከፈተው የቁጠባ ሒሳብ ቁጥር 96542 ገቢ ማድረግ ይቻላል::

ከአዘጋጁ:-

*ጽሑፉን ለማዘጋጀት እንዲረዳን በርዕሰ ደብር ኀሊና ግርማ ተዘጋጅቶ የቀረበውን ጽሑፍ በመላክ ለተባበሩን ለደብሩ አስተዳዳሪ ለመልአከ ኃይል አባ ወ/ገብርኤል ወ/ሳሙኤል ከፍተኛ ምስጋና እናቀርባለን::*

*ረድኤተ እግዚአብሔር አይለየን*

/ከገጽ ፴፰ የዞረ/

ቅድሜክን - በፊታችሁ
ቅድሜነ - በፊታችን
ቅድሜሁ - በፊቱ
ቅድሜሃ - በፊቷ
ቅድሜሆሙ - በፊታቸው
ቅድሜሆን - በፊታቸው
የዝርዝር መንገዱን በበለጠ ለመረዳት ሐመር 11ኛ ዓመት ቁጥር 2ን ተመልከት

### ግብረ ቤት፣ ኀረይ

1. እኑየ መጽአ ______
   ሀ. ፍጡነ ለ. ፍጡን ሐ. ዮም
   መ. ጌሠም ሠ. ህወሐ ረ. ለወመ
2. ተፈሥሐ /ተደሰተ/ አበው ______ ተወልደት ማርያም መድኀኒቶሙ
   ሀ. በእንተ ዝንቱ ለ. አኮኑ
   ሐ. አምጣነ መ. እስመ
   ሠ. እንበለ ሀ/
3. ዮሐንስ ወጴጥሮስ ሰበኩ ______ መንግሥተ ሰማያት
   ሀ. ከመ ለ. በእንተ ሐ. እስመ መ. በእንተዝ
4. አንትሙ ሖርክሙ
   ሀ. ሀገር ርኁቅ ለ. ሀገረ ርኁቀ ሐ. ርኁቅ ሀገር መ. ለወሐ
5. አፍርንጅ ወሰዱ ብነ ታቦታተ /ንዋያተ/
   ሀ. ሀገርነ ለ. ሀገርየ ሐ. ሀገሮሙ መ. ሀገርከ ሠ. ሀገርኪ
6. አነ ሰገድኩ ቅድመ ቤተ መቅደስ ______ ባረከኒ አምላኪየ
   ሀ. በእንተ ለ. በእንተዝ
   ሐ. አምጣነ
   መ. ለወሐ ሠ. ሀወለ
7. አንትሙ ጸለይክሙ ______ ወ______
   ሀ. መዓልተ ወሌሊተ ለ. በመዓልት ወበሌሊት
   ሐ. መዓለት ወሌሊት መ. ሀወለ
8. ገበርኩ ግበረ ቤትየ ______ ተፈስሐት እምየ
   ሀ. አኮኑ ለ. እስመ
   ሐ. በእንተዝ መ. ቅድመ
9. እግዝእትየ ቀረብኩ ኀቤኪ ወሰገድኩ ______
   ሀ. ቅድሜየ ለ. ቅድሜኪ ሐ. ቅድሜሆሙ መ. ቅድሜከ
10. ኦኃውየ ተጋደሉ በእንተ ኢትዮጵያ ______ አልቦ ተስፋ ዘእንበለ ሀገር
    ሀ. እስመ ለ. አኮኑ ሐ. ቅድመ መ. በእንተዝ

### አስተዛምድ ቃላተ ሀ መስለ ቃላተ ለ

| | |
|---|---|
| 1- ሀገረ | ሀ. እዚህ |
| 2- ሀገር | ለ. እዚያ |
| 3- ህየ | ሐ. በየዓመቱ |
| 4- ዝየ | መ. ወደ ክ/ ሀገር |
| 5- በእንተ ኩሉ | ሠ. ሀገር |
| 6- በበዓመቱ | ረ. ስለ ሁሉ |
| 7- ዓመታት | ሰ. ዓመቶች |



www.eotcmk.org

# « በእግዚአብሔር እንድንወደድ መስቀሉን እንውደድ »

*ብፁዕ አቡነ መልከ ጼዴቅ የጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅና*
*የከንባታ ሀዲያ ጉራጌና ስልጤ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ*

ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ካልዕ የዛሬ 14 ዓመት፤ ሐምሌ 22 ቀን 1982 ዓ.ም ባጋጠማቸው ድንገተኛ የመኪና አደጋ ከዚህ ዓለም በሞት መለየታቸው ይታወቃል። ሰከንድ በደቂቃ፥ ደቂቃ በሰዓት፥ ሰዓት በቀን፥ ቀናት በሳምንታት፥ ሳምንታት በወራት፥ ወራት በዓመታት እየተተኩ ተፈጥሮአዊ ዑደታቸውን ሲያደርጉ ታላቁ አባት ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ካልዕ ካረፉ ዓሥራ አራት ዓመታት ተቆጠሩ።

ሐምሌ 22 ቀን 1996 ዓ.ም የብፁዕነታቸው ዓሥራ አራተኛ ዓመት በዓለ ዕረፍት በዝዋይ ሐመረ ብርሃን ቅዱስ ገብርኤል ገዳም ሲከበር፤ ከየአቅጣጫው ከእግራቸው ሥር ቁጭ ብለው የተማሩ፣ እሳቸው ጸጉራቸውን ላጭተው ያመነኮሱዋቸው አባቶች ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት፣ ቆሞሳት፣ መነኮሳትና የደብር አለቆች በበዓሉ ላይ ተገኝተው ነበር።

የብፁዕነታቸው የመጀመሪያ ፍሬ ብፁዕ አቡነ መልከ ጼዴቅ የአባታችንን በዓለ ዕረፍት ለማክበር በዕለቱ ከተገኙት አራት ሊቃነ ጳጳሳት አንዱ ነበሩ። የብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስን ማንነት እንዲያስተምሩ የምሥራቅ ሸዋ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስና የገዳሙ ኃላፊ በሆኑት በብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ተጋብዙ፣ እንባ እየተናነቃቸው ስለ አባታችን ከዚህ የሚከተለውን ትምህርት አስተላለፉ:-

"የተከበራችሁ የአባታችን ልጆች:- የእኛ አባት አቡነ ጎርጎርዮስ /የሁላችንም አባት/ ቅዱስ ጳውሎስን ይመስላሉ "ሊተሰ ፈቃደ ልብየኒ ወጸሎትየኒ ከመ ይሕየው ኩሉ እስራኤል፤ የእኔስ የልቤ ፈቃድና ጸሎት እስራኤል ሁሉ እንዲድኑ ነበር" የእሳቸው ፍቃድ ይህን ይመስል ነበር። አብረናቸው ኖረናል። የአቡነ ጎርጎርዮስ ጸሎታቸው፣ ምኞታቸው ዕቅዳቸው "ከመ ይሕየው ኩሎሙ ኢትዮጵያውያን" ፤ኢትዮጵያውን ሁሉ እንዲድኑ" ጸሎታቸው ነበር። "ኢተለወጡ ሶቤሃ ዘሥጋ ወደም፥ የሥጋዬን ፈቃድ አልተከተልኩም" እንዳለው ሁሉ የእኛ አባት አቡነ ጎርጎርዮስ በእውነት ለማድላት አይደለም፣ የእኛ አባት ስለሆኑም፥ ከሳቸው ስለተወለድንም አይደለም፤ ማንም ይመሰክርላቸዋል። ብፁዕ አባታችን መስቀሉን ከተሸከሙ በኋላ፣ ጥሪው ከደረሳቸው በኋላ ይህን ዓለም ያልተከተሉ፣ ለራሳቸው ያልኖሩ ለቤተ ክርስቲያን የኖሩ፣ የሃያኛው ክፍለ ዘመን ሐዋርያ አዎ! በእውነት "ዘፈለጠኒ ወአውጽአኒ እምከርሠ እምየ ፀውዓኒ በጸጋሁ" ብለው መናገር የሚችሉ አባት ነበሩ። በእውነት የተጠሩ ጥሪያቸውን ያከበሩ አባት፣ ጥሪያቸው የሠመረላቸው የተሳካላቸው አባት ነበሩ። ራሳቸውን የማይወዱ፤ የክርስቶስ መስቀል ፍቅር የገባቸው፤ መስቀሉን የተሸከሙ አባት ናቸው። ስለዚህ ነው ወደዚህ ምድረ በዳ የመጡት። አሁን ያሉት አባታችን አቡነ ጎርጎርዮስ እንደ ተናገሩት እዚህ ወደ ተናቀው ቦታ፣ ወደ ተረሳው ቦታ፣ የሚናከስ ቢንቢ ወዳለበት ኩርንችት ወዳለበት ወደ ተረሳው ሕዝብ "ሕዝብ ዘይነብር ውስተ ጽልመት ወጽላሎተ ሞት ርእየ ብርሃነ ዐቢየ፤ በጨለማ የሚኖር ሕዝብ ታላቅ ብርሃን አየ" እንደ ተባለው እዚህ አካባቢ የነበሩ አብያተ ክርስቲያን ተዘግተው ሳሉ ወደ ተዘጉት አብያተ ክርስቲያን የመጡት፣ የመስቀሉ ፍቅር ስለ ገባቸው ነው። ስለዚህ ነው ሥራቸው የሠመረላቸው ብዙ የወለዱት፣ ልጆቻቸው አዕላፍ የሆኑት። መስቀሉን የተሸከመ እንደዚህ ይሠምርለታል፤ እንደዚህ ይሳካላታል። እኛ ብዙ ጊዜ የማይሳካልን ለራሳችን ስለምናደላ ነው። ደፍረን መናገር እንችላለን። ገና ገና የመስቀሉ ፍቅር አልገባንም። "እስመ ዓዲ ኢመጽአ መንፈስ ቅዱስ፤ መንፈስ ቅዱስ ገና አልመጣም" እንደ ሚለው ነው። በእውነቱ እሳቸው ሞቱ እንዴ? ጎርጎርዮስ ሞቱ እንዴ? አልሞቱም የእግዚአብሔር ፍቅር ያለው ሰው አይሞትም፤ ሥራው አይሞትም፤ እና ድንቅ ነው! በጣም ድንቅ ነው! በጣም ደስ ይለናል። ቤተ ክርስቲያን እንዲህ ያለ ሐዋርያ ያስፈልጋታል። ቢንቢ ይበላኛል የማይል፣ ደጋ ቆላ የማይል ሐዋርያ አባት ያስፈልጋታል። ቤተ ክርስቲያን ዘረኛ ያልሆነ አባት፣ ብሔራዊ አባት፣ አብርሃማዊ የሆነ አባት ያስፈልጋታል። እግዚአብሔር አብርሃምን "ዘርህን እንደ ሰማይ ክዋክብት እንደ ምድር አሸዋ አበዛዋለሁ" ብሎ እንደ ባረከው የአቡነ ጎርጎርዮስ ልጆቻቸው ክዋክብት ናቸው። ዛሬ የእሳቸው ልጆች እዚህ የተሰበሰበነው ብቻ ነን? ብዙ ልጆች አሉዋቸው። እንዲሁ "እግዚአ ሕያዋን" እየደገሙ እየቀደሱ 14ኛዓመት በአሜሪካ፤ 14ኛ በዓለ ዕረፍት በአውሮፖ፤ አዎ እግዚአብሔርን የወደደ እንደዚሁ ነው። እንዲህ ያብባል፣ እንዲህ ይወደዳል። እንድንወደድ መስቀሉን እንውደድ፤ እግዚአብሔርን እንውደድ። እኛ አብረን ኖረናል፣ መቋሚያቸውን ይዘናል፤ ጫማቸውን ይዘናል፤ እናውቃቸዋለን። «በዘነአምር ንነገር ወበዘርኢነ ሰማዕተ ንከውን፥ የምናውቀውን እናገራለን የሰማነውን እንመሰክራለን» እንደ ተባለው በደንብ እናውቃቸዋለን። ስለምናውቃቸውም እንናገራለን። መንፈሳዊነት ያስፈልጋል። "መጥወተ ርእስ ኃዲገ ርእስ" ያስፈልጋል በምንኩስና። ቤተክርስቲያንን ለማገልገል የተሰለፍን፣ ሁሉ እንዲከተለን መጥወተ ÷ርእስ ያስፈልጋል። አሁን እንዳልኩት ዛሬ ራሱን የሚሰጥ ቢሞቀኝም ቢበርደኝም ዓለማዬ ነው የሚል ያስፈልጋል።

አሁን ይህ ገዳም ገጠር ይመስላል? በ70 ዓመተ ምሕረት አይተነዋል። ለዚህ ቦታ እንግዶች የሆናችሁ መጀመሪያ አባታችን እዚህ ሲመጡ ምድረ በዳ ነበር፤ የአውሬ መፈንጫ ነበር። አሁን ምድረ ገነት ሆኗል። "ሰብእ ይቄድሶ ለመካን፥ ቦታን ሰው ይቀድሰዋል"። ለዚህም በብፁዕ አባታችን አማካይነት ዝዋይ ተቀደሰች፤ እንዲህ ነው! አዎ ጥሩ ነው፤ ሁሉ ደስ የሚል ነው። ዛሬ የቅኔ መምህራኑ፣ የአቋቋም መምህራኑ፣ መነኮሳቱ፣ አስተዳዳሪዎቹ፣ ጳጳሳቱ ከዚህ ቦታ ወጥተዋል። ይሄ ነበር ምኞታቸው የአባታችን÷ ተሳካላቸው። ዛሬ በየተቋማቱ፣ በየኮሌጁ፣ በየዩኒቨርስቲው "ጎርጎርዮስ÷ ጎርጎርዮስ" ነው የሚባለው። እና ይሄ የሆነበት ምክንያት ዓላማቸውን ያወቁ አባት ስለ ነበሩ፣ ከራሳቸው ይልቅ ለቤተ ክርስቲያን የሚቆረቆሩ ስለ ነበሩ ነው። አባታችን አርቀው የሚያዩ፣ ዛሬ ያለውን ዓለም እንደ መነጽር ያዩት ነበር፤ ይተነብዩ፣ ይናገሩ ነበር። እና ሌሎች አባቶች ይናገራሉ። የብፁዕ አባታችን ልጆቻቸው ብዙ ናቸው። ልጆቻቸውን ሰብስበው «ከመ እንተ ታስተጋብእ ዶርሆ ዕጐሊሃ ታሀተ ክነፊሃ፤ ዶሮ ጫጭቶችዋ በክንፎችዋ ውስጥ እንደ ምትሰበስብ» እንደ ሚለው ምንም ከነበረው እንዳይጐድል ልጆቻቸው እንዳይበርዳቸው፣ ትምህርት ቤቱ እንዳይዘጋ ብዙዎቻችን ደክመናል። እሳቸው ግን እስከ አሁን ድረስ «ዕቀብ አባግዕየ÷ በጐቼን ጠብቅ፣ ጠቦቶቼን አሰማራ» እንዳለው በፊት በምግብና፣ አሁን በታላቅ ማዕረግ ምእመናንን በማስተባበር ልጆቻቸውን በሚገባ እየተከባከቡ ነው። ግቢውን ዛሬ ነው ያየሁት ወደዚህ ከመጣሁ ቆይቻለሁ። ሐዋርያት እየዞሩ እንደ ሚያገለግሉት በየቦታችን አልሰነፍንም። ሌሎች ዝዋዮች ብዙ ዝዋዮች እንዲኖር ነበር የአባታችን ሕልማቸው፤ ሐዋርያት በዓለም ሁሉ እንደዞሩ ሁሉ የአባታችን ልጆች በኢትዮጵያ በአውሮፓ፣ በአፍሪካ፣ በአሜሪካ ሁሉ ዝዋይ እየሆነ ነው። እኛ ሁላችን ዛሬ በስማቸው ማኅሌት ቆመን ቅዳሴ ቀድሰን በረከት አገኘን። ስለዚህ ሁላችን የብፁዕ አባታችንን ፈለግ ልንከተል ይገባል። እሳቸው መንገዱን አሳይተውናል። የወንጌልን ብርሃን በምእመናን ሕይወት አቀጣጥለዋል። እሳቸው በአጭር ጊዜ ያበሩትን የወንጌል ብርሃን በተጠናከረ መልኩ እንዲቀጥል ልጆቻቸው እግዚአብሔርን አጋዥ በማድረግ ቤተ ክርስቲያንን እናገልግል። ስናገለግል ብቻችንን አይደለንም። ቸሩ ፈጣሪያችን ከሁላችን ጋር ነው።

የብፁዕ አባታችን በረከታቸውና ጸሎታቸው ከሁላችን ጋር ይሁን።

## ኖኅተ ሰማይ

- የቤተ መቅደስ ትርጓሜና ምሳሌዎች
- ቤተ መቅደስ በመጽሐፍ ቅዱስ
- ሦስቱ የቤተ መቅደስ አሠራርና በዙሪያው ያሉ ንዋያት ምሳሌያዊ ትርጉም
- ወደ ቤተ መቅደስ ለመግባት መደረግ ያለባቸው ዝግጅቶች
- በቤተ መቅደስ ውስጥ የተከለከሉ ነገሮች
- የቤተ መቅደስ መገልገያ የሆኑ ንዋየተ ቅድሳት፣ ለመሥዋዕት የሚቀርቡ መባዎች /ዕጣን፣ዘቢብ.../፣ የማኅሌት ንዋያት /ከበሮ ጸናጽል/ ትርጉም
- እነዚህንና ሌሎች በቤተ መቅደስ ዙሪያ የሚነሡ ጥያቄዎች በስፋት የተመለሰበት መጽሐፍ ነው::

*አዘጋጅ:- ዲ/ን ያሬድ ገብረ መድኅን*
*አከፋፋይ:- ማኅበረ ቅዱሳን*

መጽሐፉን በሁሉም የሐመር መጽሔትና ስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ ማከፋፈያ ውስጥ ያገኙታል !!
ስልክ 22-86-01/23-45-29

## ምበበኛው ሕፃን

ልጆች ፍቅርን፣ ሰላምን፣ የሥራና የንባብ ባሕል እያዳበሩ፤ በሃይማኖታቸው የጸኑ በምግባራቸው የቀኑ ሆነው እንዲያድጉ መጻሕፍት ትልቅ ድርሻ አላቸው:: ስለሆነም ልጅዎ በመንፈሳዊ ዕውቀትና ሥነ ምግባር እንዲኃለብት ይህን መጽሐፍ እንዲያነብ ያበርክቱለት !!

*አዘጋጅ:-* የሰዋ ወርቅ ወ/ገብርኤል
*አሳታሚ:-* በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ማኅበረ ቅዱሳን

መጽሐፉን በሁሉም የሐመር መጽሔትና ስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ ማከፋፈያ ውስጥ ያገኙታል !!
ስልክ 22-86-01/23-45-29

**በሥርጭት ላይ ውለዋል !!**


# አቡነ ጎርጎርዮስ ዐጸደ ሕፃናት ወደ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት ተሸጋግሮ

## እስከ 2ኛ ክፍል ድረስ እየመዘገበ ነው !!


- የሥነ ምግባር ትምህርት በቂ ጊዜ ተመድቦለት እንደ አንድ የትምህርት ዓይነት ይሰጣል።
- የትምህርት አሰጣጡ ልጆችን በሚመጥን መልኩ በኮምፒዩተር ይታገዛል::
- ጥሩ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ክሂል እና በቂ ልምድ ያላቸው መምህራን ተዘጋጅተዋል::

*አድራሻ:- ከቅዱስ ዑራኤል ቤተ ክርስቲያን ወረድ ብሎ አዲስ አበባ ጤና ቢሮ አጠገብ*

ስልክ 51-06-59/51-37-42
**ማኅበረ ቅዱሳን**




በተለያየ መጠን ታትመው
በገበያ ላይ የዋሉ ፖስተሮች




ሁሉንም ኅትመቶች በሐመር መጽሔት እና በስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ ማከፋፈያዎች ውስጥ ያገኟቸዋል !!
ስልክ 22-86-01/23-45-29

**አዲሱ ማከፋፈያችን መርካቶ ራጉኤል ቤተ ክርስቲያን አካባቢ አገልግሎት መስጠት ጀምሯል:: ንዋያተ ቅድሳትንና የኅትመት ውጤቶቻችንን በጅምላ ለማሠራጨት የምትፈልጉ ሁሉ ልታገኙን ትችላላችሁ !!**

ስልክ 13-81-30
Website:- http://www.eotc-mkidusan.org E-mail:- lemat@eotc mkidusan.org

ሜጋ ማተሚያ ድርጅት

ዋጋ ብር 3.50

©

!" #$ %

& ' ( ) * $++